ቅይጣት

በአደባባይ የተፈሩ ሦስት ጥያቄዎች

ከፊሊፕ ያንሲ



ማውጫ

መቅድም .....

አንደኛ መጽሐፍ፡- እግዚአብሔር በጥላ ውስጥ .....

ክፍል አንድ፡- ዝምታውን ማድመጥ .....

1. ከፍተኛ ስሕተት 1
2. በጭስ ውስጥ 8
3. ሰው የማይደፍራቸው ጥያቄዎች.....16
4. . . . ቢሆን 23
5. ምንጩ.....30

ክፍል ሁለት፡- ተራከበ፡- አብ.....33

6. ኪሳራ.....33
7. ወላጅ 38
8. በቀጥታ የሚተላለፍ የፀሐይ ብርሃን.....44
9. አንድ አንጸባራቂ ወቅት.....51
10. እሳትና ቃሉ.....56
11. የቆሰለ አፍቃሪ.....61
12. እውነተኛነት እጅግ መልካም ነው 68

ክፍል ሦስት፡- ቅርበተ ወልድ.....72

13. ዝቅታ.....72
14. ታላላቅ ተስፋዎች.....76
15. መለኮታዊ ገለልተኛነት 82
16. የተላለፈ ተአምር 88
17. እድገት.....92

ክፍል አራት፡- መለወጥ፡- መንፈስ ቅዱስ.....99

18. ሽግግር 99
19. የነፍስ መለወጥ.....103

20. ፍጻሜ 110

ሁለተኛ መጽሐፍ፡- በድቅድቅ መመልከት 118

21. ጣልቃ 119

22. ብቸኛው ችግር 124

23. በአጽናፈ-ዓለሙ ውስጥ የምንጫወተው ሚና 129

24. እግዚአብሔር ፍትሕ-አልባ ነውን? 137

25. እግዚአብሔር ለምን ማብራሪያ አይሰጥም? 149

26. እግዚአብሔር ዝም ይላል? 163

27. እግዚአብሔር ለምን ጣልቃ አይገባም? 174

28. እግዚአብሔር ስውር ነውን? 189

29. ኢዮብ ለምን ደስተኛ ሆኖ ሞተ? 196

30. ውርርድ- ሁለት ምሳሌዎች 204

ምስጋና 213

ዋቢ መጻሕፍት (Bibliography) 214

ጥቂት ስለ ደራሲው 216

ቅይማት

በአደባባይ የተፈሩ ሦስቱ ጥያቄዎች

ከፊሊፕ ያንሲ

ትርጉም፡– ግርማዊ

እርማት፡– በመሐሪ ታደሠ፥
አክሊሉ አበበ ና
ስሜ ታደሠ

Copyright

©1999 by SIM -ETHIOPIA AREA, Addis Ababa, Ethiopia.
Originally published in the U.S.A under the title
DISAPPOINTMENT WITH GOD.
Copyright ©1988 by Philip Yancey, Grand Rapids, Michigan.
All rights reserved.

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

መቅድም

ይህን መጽሐፍ ማዘጋጀት ከጀመርሁ በኋላ ስለ ጉዳዩ ከሰሙት አንዳንድ የቤተ ክርስቲያናችን ምእመናን የስልክ ጥሪዎች ደርሰውኝ ነበር። «ከእግዚአብሔር ጋር ስለ መቀያየም መጽሐፍ እየጻፍህ ነው አሉ። እውነት ነው?» እያሉ ይጠይቁኛል። «እውነት ከሆነ የምለው አለኝ፤ ከዚህ በፊት ስለዚህ ጉዳይ ለማንም ባልተነፍስም የክርስትና ሕይወት ከፍተኛ የቅይማት ጊዜያትን ያካተተ ነው።» እኔም የስልክ ጥሪ ካደረጉልኝ ግለሰቦች መካከል ከአንዳንዶቹ ጋር ቃለ ምልልስ አድርጌአለሁ። እነዚህ ወገኖች ያጫወቱኝ ታሪኮች የዚህን መጽሐፍ አቅጣጫ ለመቀየስ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

ብዙ ሰዎች ከክርስትና እምነታቸው በሚጠብቁትና በትክክል በሚለማመዱት ሁኔታ መካከል ሰፊ ክፍተት እንዳለ አስተውያለሁ። የድልና የስኬት ተስፋ የሚፈነጥቁትን መጻሕፍት፥ ስብከቶችና ግላዊ ምስክርነቶች ከተጠቀሙ በኋላ እግዚአብሔር በሕይወታቸው ውስጥ በላቀ ሁኔታ የመሥራቱን መረጃ ለመረዳት ይጠባበቃሉ። እንዲህ ዓይነቱን መረጃ ካላገኙ ግን የቅይማት፥ የክህደትና የበደለኝነት ስሜት ይንጣቸዋል። አንዲት ሴት እንዲህ ብላለች፤ «ብዙ ጊዜ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ግላዊ ግንኙነት መመሥረት» የሚል ሐረግ ስሰማ ኖሬአለሁ። የሚያሳዝነው ግን ይህ ከየትኛውም ዓይነት ግላዊ ግንኙነት የተለየ መሆኑ ነው። «እግዚአብሔርን አላየሁትም፤ ድምፁን አልሰማሁም፤ ወይም ዳሰሳው አልተሰማኝም፤ ወይም የግንኙነቱን መሠረታዊ ክፍል አካላት ተለማምጄ አላውቅም። ከተነገረኝ መልእክት ወይም ከእኔ አንድ የተበላሸ ነገር አለ ማለት ነው።»

ቅይማት የሚከሰተው ልምምዳችን በተሰፋ ከምንጠባበቀው አሽቆልቁሎ ሲገኝ ነው። በዚህ ምክንያት የዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያው አጋማሽ ከእግዚአብሔር በትክክል ልንጠብቅ የምንችለውን ነገር ለማግኘት መጽሐፍ ቅዱስን ያስሳል። አንዳንድ ወገኖች በተለይም ቅይማት የዋጣቸው ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለመመርመር ብዙም ትዕግሥት እንደማይኖራቸው ስለማውቅ ከዚህ ላለመጀመር አመንትቼ ነበር። ይሁንና፥ እግዚአብሔር ራሱ እንዲናገር ለማድረግ የተሻለ ምን የጅማሬ ስፍራ ሊኖር ይችላል? ቀደም ሲል በአእምሮዬ ውስጥ ያለውን አሳብ አስወግጄ መጽሐፍ ቅዱስን የራሱ «መዋቅር» እንዳለው ታሪክ ለማንበብ ሞክሬአለሁ። በዚህ ጊዜ ያገኘሁት ነገር አስደንቆኛል። ያነበብሁት ታሪክ በሕይወቴ አብዛኛውን ጊዜ ከሰማሁት የተለየ ነበር።

በመሆኑም፥ ሁለት የተለያዩ ዓይነት መጻሕፍት ለማዘጋጀት ዐቅጄ «ይህንኑ አድርጌአለሁ። ሁለቱንም መጻሕፍት በአንድ ሽፋን ውስጥ አስቀምጫለሁ።» ሁለተኛው መጽሐፍ ይበልጥ ወደ ተግባራዊና ልምምዳዊ ጉዳዮች በመዝለቅ ለትክክለኛ ካዘጋጀኋቸው አሳቦች ጋር ይዛመዳል፤ እነዚህም ከእግዚአብሔር ጋር መቀያየምን የሚጨምሩ ዓይነት ናቸው። በመጨረሻም፥ ሁለቱም አቀራረቦች በአንድ መጽሐፍ ውስጥ እንደሚጠቃለሉና አንዱ ያለሌላው የተሟላ ሊሆን እንደማይችል ደምድሜአለሁ።

አንድ ጊዜ ለጓደኛዬ ስለዚሁ መጽሐፍ ሳብራራለት ራሱን በመነቅነቅ፥ «ከዚህ በፊት ለእግዚአብሔር ሥነ ልቦናዊ ምርምር እንዳላደረግሁለት እርግጠኛ ነኝ» ሲል ተናገረ። እኔም ለማድረግ የሞከርሁት ይህንኑ እንዳልሆነ ተስፋ አደርጋለሁ። ነገር ግን እግዚአብሔርን በይበልጥ ለማወቅ አፈልጋለሁ፤ አንዳንድ ጊዜ ለምን እንዲህ በምሥጢራዊ መንገዶች እንደሚሠራ ወይም ደግሞ ለምን ምንም የማይሠራ እንደሚመስል ለመረዳት እሻለሁ።

ይሁንና፥ ጥቂት የማስጠንቀቂያ ቃላት መሰንዘሩ አስፈላጊ ነው። ይህ እምነትን ለመከላከል የሚያገለግል መጽሐፍ ባለመሆኑ፥ ለእግዚአብሔር መኖር መረጃዎችን ለመዘርዘር አልሞክርም። ሌሎች ይህንን በአጥጋቢ ሁኔታ ያከናወኑት ከመሆኑም በላይ እኔ የማነሣው ጉዳይ ከምክንያታዊነቱ ይልቅ በስሜታዊ ጥርጣሬዎች ላይ ያተኮረ ነው። ቅይማት ተስፋ ተጥሎበት ሳይሳካ የቀረውን ግንኙነት የሚመለከት ነው። «እግዚአብሔር ከቶም ተአምራት ይሠራልን?» በሚለው ጥያቄ ዙሪያም ሙግት አልገጥምም። እርሱ ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል እንዳለውና ሲሠራበትም እንደኖረ አረዳለሁ። ይህንኑ በተደጋጋሚ የማያደርገው ለምንድን ነው? ምልክቱን አይተው ለማመን በሚፈልጉ እውነተኛ ተጠራጣሪዎች ፊት ለምን ራሱን ሽባ ያደርገዋል? በምድር ላይ ፍትሕ-አልበኝነትና ሥቃይ እንዲኖር ለምን ፈቀደ? የእግዚአብሔር ጣልቃ-ገብነት ከ«ተአምርነት» ይልቅ «ተራ» የማይሆነው ለምንድን ነው?

አንድ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ፤ በምንም ዓይነት የክርስትናን እምነት ሚዛናዊ አመለካከት አያቀረብሁ አይደለም። እኔ የምጽፈው በአንድ ወይም በሌላ ወቅት የእግዚአብሔርን ዝምታ ላደመጡ ሰዎች ነው። ለእምነት ምሳሌነት እንደ ኢዮብ ዓይነቱን ሰው ታሪክ ለመረዳት እንደ መሞከር ነው። በሌላ በኩል፥ ጦርነትን ገለል አድርገው ድልን ብቻ የሚያውጁ በርካታ ክርስቲያናዊ መጻሕፍት አሉ። ይህ ስለ እምንት የተጻፈ መጽሐፍ ነው። ነው። ይሁንና፥ እምነትን የሚያየው በተጠራጣሪዎች ዓይን ነው።

በመጨረሻም፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን እንዴት እንደተጠቀምሁ ማብራራት ይኖርብኛልና በግርጌ ማስታወሻ ወይም በምንባቡ ውስጥ በቅንፍ ለማስቀመጥ አልፈለግሁም። ይህ የተብታባ ሰው ንግግር እንደማዳመጥ ሁሉ በንባብ ሂደት ውስጥ እንቅፋት ይፈጥራል። በመሆኑም፥ ጥቅሶቹን ከምዕራፉ መጨረሻ ላይ ማስቀመጡን መርጫለሁ። እውነተኛ መርማሪዎች ትክክለኛውን ምንባብ መከትል ይኖርባቸዋል።

አቤቱ፥ ንቃ ለምንስ ትተኛለህ?
ተነሥ፥ ለዘወትርም አትጣለን።
ለምንስ ፊትህን ትሰውራለህ?

መዝሙር (44)፡23–24

አንደኛ መጽሐፍ

እግዚአብሔር በጥላ ውስጥ

«ከቤት ውጭ ጽልመት ባጠላበት ስፍራ መቀመጥ የለብህም።
ነገር ግን ከዋክብትን ለማየት ከፈለግህ፥
ጨለማ መኖር እንዳለበት ትገነዘባለህ።
ከዋክብት ጨለማውን እንደ አንድ መስፈርት አይፈልጉትም፤
አይጠይቁትምም።

(አኒ ዲላርድ)

ማውጫ

መቅድም .....

አንደኛ መጽሐፍ፡- እግዚአብሔር በጥላ ውስጥ .....

ክፍል አንድ፡- ዝምታውን ማድመጥ .....

1. ከፍተኛ ስሕተት 1
2. በጭስ ውስጥ 8
3. ሰው የማይደፍራቸው ጥያቄዎች.....16
4. . . . ቢሆን 23
5. ምንጩ.....30

ክፍል ሁለት፡- ተራከበ፡- አብ.....33

6. ኪሳራ.....33
7. ወላጅ 38
8. በቀጥታ የሚተላለፍ የፀሐይ ብርሃን.....44
9. አንድ አንጸባራቂ ወቅት.....51
10. እሳትና ቃሉ.....56
11. የቆሰለ አፍቃሪ.....61
12. እውነተኛነት እጅግ መልካም ነው 68

ክፍል ሦስት፡- ቅርበተ ወልድ.....72

13. ዝቅታ.....72
14. ታላላቅ ተስፋዎች.....76
15. መለኮታዊ ገለልተኛነት 82
16. የተላለፈ ተአምር 88
17. እድገት.....92

ክፍል አራት፡- መለወጥ፡- መንፈስ ቅዱስ.....99

18. ሽግግር 99
19. የነፍስ መለወጥ.....103

20. ፍጻሜ 110

ሁለተኛ መጽሐፍ፡- በድቅድቅ መመልከት 118

21. ጣልቃ 119

22. ብቸኛው ችግር 124

23. በአጽናፈ-ዓለሙ ውስጥ የምንጫወተው ሚና 129

24. እግዚአብሔር ፍትሕ-አልባ ነውን? 137

25. እግዚአብሔር ለምን ማብራሪያ አይሰጥም? 149

26. እግዚአብሔር ዝም ይላል? 163

27. እግዚአብሔር ለምን ጣልቃ አይገባም? 174

28. እግዚአብሔር ስውር ነውን? 189

29. ኢዮብ ለምን ደስተኛ ሆኖ ሞተ? 196

30. ውርርድ- ሁለት ምሳሌዎች 204

ምስጋና 213

ዋቢ መጻሕፍት (Bibliography) 214

ጥቂት ስለ ደራሲው 216

ቅይጣት

ክፍል አንድ
ዝምታውን ማድመጥ

ምዕራፍ አንድ

ከፍተኛ ስሕተት

"Where Is God When It Hurts?" ወይም «በምንጎዳበት ወቅት እግዚአብሔር ወዴት ነው?» የሚለውን መጽሐፍ ካሳተምሁበት ጊዜ አንሥቶ ከእግዚአብሔር ጋር ከተቀያየሙ ሰዎች ደብዳቤዎችን ላገኝ ቆይቻለሁ።

አንዲት ወጣት እናት የጀርባ ችግር ያለባት ልጅ በመውለዱ ምክንያት ደስታዋ ወደ ምሬት እንደገባ ገልጻ ጻፈችልኝ። የሕክምና ክትትሉ ምን ያህል የቤተሰቡን ጥሪት እንዳሟጠጠውና ባለቤቷ ለታማሚ ልጃቸው በተሰዋው ጊዜ በማዘኑ ትዳሯ መቀመቅ መውረዱን ተረከች። ሕይወቷ ሲፈራርስ በአንድ ወቅት ስለ አፍቃሪ አምላክ ታምን የነበረውን መጠራጠር ጀመረች። የምሰጣት አንዳች ምክር ይኖር ይሆን?

አንድ የግብረ ሰዶማዊነት ኃጢአት ቁራኛ የሆነ ግለሰብ በተከታታይ በጻፋቸው ደብዳቤዎች ቀስ በቀስ ታሪኩን አጫወተኝ። ከአሥር ለሚበልጡ ዓመታት ከዚህ ኃጢአት ለመገላገል መፍትሔ ሲሻ ቆይቷል። ለዚህም የካሪዝማቲኮችን የፈውስ አገልግሎቶች፤ ክርስቲያናዊ የርዳታ ቡድኖችንና የመድኃኒት ሕክምና ሳይቀር ሞክሯል። ከዚህም አልፎ የሥነ-ልቡና አዋቂዎች የሚሰጡትን ሕክምና በመከተል የኤሌክትሪክ ኃይል ከብልቱ ላይ እንዲያሳርፉ በማድረግ ጭምር ከችግሩ ለመላቀቅ ጥሯል። ይህ ሁሉ ግን ሊረዳው አልቻለም። የኋላ ኋላ በቡድን የግብረ ሰዶም ተግባር የሚፈጽሙ ወንዶች ቡድን አባል ሆነ። እግዚአብሔርን መከተል ቢሻም ከሚኖርበት የርግማን ሕይወት የተነሣ ለመንፈሳዊ ኑሮ ብቁ እንዳልሆነ ይሰማዋል።

አንዲት ወጣት ሴት በሕይወቷ በቀጣይነት ስለዘለቀው ጭንቀት እያፈረች ጻፈች። የሚያስጨንቅ ምንም ምክንያት እንደሌላት ትናገራለች። ጤነኛና ጥሩ ወርሐዊ ገቢ ያላት ስትሆን፥ የቤተሰብ ዳራዋ ርጋታን የተላበሰ ነበር። ነገር ግን ብዙውን ጊዜ ከመኝታዋ ስትነሣ ሕይወትን ለመቀጠል የሚያስችል አንድም ምክንያት አይታያትም። ስለ ሕይወትም ሆነ ስለ እግዚአብሔር ግድ የላትም። በምትጸልይበት ጊዜም የሚሰማት አምላክ ስለመኖሩ ትጠራጠራለች።

በዓመታት ውስጥ የደረሱኝ እነዚህና ሌሎችም ደብዳቤዎች በተለያዩ አገላለጾች ቢቀርቡም ወደ አንድ መሠረታዊ ጥያቄ ያመራሉ። ይህም፥ «መጽሐፍህ የሚናገረው ስለ አካላዊ ሥቃይ ነው። ይሁንና፥ የእኔ ዓይነቱን ሥቃይ እንዴት ታየዋለህ? ስሜታዊ ሥቃይ ሲደርስብኝ እግዚአብሔር ወዴት ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ ምን ይላል?» የሚል ዓይነት ነው። ለግለሰቦቹ ደብዳቤዎች የምችለውን ያህል ጥሩ ምላሽ ለመስጠት እጥራለሁ። ይህንንም የማደርገው በወረቀት ላይ የተጻፉትን ቃላት ብቃት-አልባነት በኃዘኔታ እየተገነዘብሁ ነው። ቃል፥ የትኛውም ቃል ቁስልን የማጠገግ ኃይል ይኖረው ይሆን? እኔም ራሴ እነዚህን አሰቃቂ ታሪኮች ካነበብሁ በኋላ የባለታሪኮቹን ጥያቄዎች ደግሜ እንደማነሣ መናዘዝ ይኖርብኛል። ስሜታዊ ሥቃይ ሲንጠን እግዚአብሔር ወዴት ነው? ብዙውን ጊዜ የሚያስቀይምን ለምንድን ነው?

♥

ከእግዚአብሔር ጋር የምንቀያየመው እጅግ በተለዩ ሁኔታዎች ውስጥ ብቻ አይደለም። ለእኔ ጉዳዩ ከተራ ዕለታዊ ሕይወትም ጋር የሚያያዝ ነው። በሺጋጎ ከተማ አንድ ሌሊት ያሳለፍሁት ቀዝቃዛ ወቀት አይረሳኝም። ውርጩ በጥቁር አብረቅራቂ በረዶዎች መንገዶችን እያለበሰ ያፉአሜል። በዚያን ሌሊት መኪናዬ ለአደጋ በሚያጋልጥ አካባቢ ቀጥ ብላ ቆመች። ኮፈኑን ከፍቼ ከሞተሩ ላይ ሳጎነብስ ከላይ የሚወርደው ዝናብ ጀርባዬን ያጠጣው ጀመር። «እባክህ፥ ይህ መኪና እንዲነሣልኝ እርዳኝ» እያለሁ ደጋግሜ ጸለይሁ።

ሽቦዎችንና ቱቦዎችን ወዲህም ሆነ ወዲያ ባደርግ መኪናው ሊነሣ አልቻለም። ስለሆነም፥ አንድ ሰዓት ሙሉ መኪናዬን የሚጎትት ሌላ መኪና እስኪመጣ ድረስ በፈራረሰ አሮጌ ምግብ ቤት ውስጥ ተቀምጬ ለመጠበቅ ተገደድሁ። የረጠበው ልብሴ ውኃ እያንጠባጠበ ከፕላስቲክ ወንበር ላይ ተቀምጬ እግዚአብሔር ስላለሁበት አስቸጋሪ ሁኔታ ምን እንደሚያስብ አሰላሰልሁ። በዚያን ምሽት ቀጠሮ የተያዘለት ስብሰባ የሚያመልጠኝ ሲሆን ምናልባትም ለሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ሁኔታዎችን ለማስተካከል በርካታ ሰዓታት ማባከን ይኖርብኝ ይሆናል። ይህም የቆሙትን መኪኖች ለማንሣት ከፍተኛ ገንዘብ ለሚጠይቁ ባለሙያዎች የሚከፈለውን ገንዘብ የሚያካትት ነበር። እግዚአብሔር ስለ እኔ ውጥረት ወይም የገንዘብና የጉልበት ብክነት ግድ ብሎት ይሆን?

ስለ ጭንቀቷ እንዳፈረችው ሴት ሁሉ፥ እኔም እንዲህ ዓይነቱን ያልተመለሰ ጸሎት በማንሣቴ ማፈሬ አልቀረም። አልነሣ ያለው መኪና እንዲንቀሳቀስ መጸለዩ አሳዛኝና ራስ ወዳድነት ብሎም ጅልነት ሊመስል ይችላል። ዳሩ ግን አሳዛኝ ቅይማቶች በእሳተ ገሞራዊ የጥርጣሬ ፍንዳታዎች እምነቴን እየተጫኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንደሚበራከቱ ተገንዝቤአለሁ። እግዚአብሔር ስለ ዕለታዊ ዝርዝሮች፥ ስለ እኔ ይገደው ይሆን? እያልሁ አስባለሁ፤ ጸሎት ነገሮችን አይለውጥም ብዬ ስለደመደምሁ፥ ብዙ ጊዜ ላለመጸለይ እፈተናለሁ። ወይስ ጸሎት ነገሮችን ይለውጥ ይሆን? ስሜቴና እምነቴ ይዋዥቃል። እነዚህ ጥላሬዎች በቀስታ ወደ ልቤ መፍሰስ ከጀመሩ ለዐበይት የስንክሳር ጊዜያት እንኳ የሚኖረኝ ዝግጁነት አነስተኛ ነው። ጎረቤቴ በካንሰር በሽታ ተይዛ ለመሞት ታጣጥራለች። እኔም ተግቼ ጸለይሁላት። ዳሩ ግን እየጸለይሁላት እያለሁ እንኳ እጠራጠራለሁ። እግዚአብሔር ሊታመን ይችላል? እጅግ ብዙ ትናንሽ ጸሎቶች የማይመለሱ ከሆነ ትልልቆቹስ ይመለሱ ይሆን?

አንድ ጠዋት ያረፍኩበትን የሆቴል ክፍል ቴሌቪዥን ስከፍት አንድ በጣም የታወቀ ወንጌላዊ አራት ማዕዘናዊ ፊት መስተዋቱን ሞልቶት አየሁ። ፊቱ የብስጭት እሳት እየተፋ፥ «በእግዚአብሔር ላይ ተቆጥቻለሁ!» ሲል ተናገረ። ሰውዬው በ «ዘር እምነት» እና እግዚአብሔር ለሰዎች ባለው ፍጹማዊ አሳቢነት ላይ ኑሮውን የመሠረተ በመሆኑ ኑዛዜው አስደነቀኝ። ነገር ግን እግዚአብሔር እንዳዋረደው በመግለጹ ማብራሪቱን ቀጠለ።

እርሱ እንደሚለው፥ እግዚአብሔር ከፍተኛ የአገልግሎት ፕሮጀክት እንዲያዋቅር ይነግረዋል። ነገር ግን ፕሮጀክቱ የገንዘብ ችግር አስከተለበት። ይህም ንብረቶቹን እንዲሸጥና ፕሮግራሞቹን እንዲያቅብ አስገደደው። እርሱ የራሱን ድርሻ እየተወጣ እያለ እግዚአብሔር ግን ቃሉን ሳይጠብቅ ቀረ።

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ይህንኑ ወንጌላዊ ቴሌቪዥን ላይ አየሁት። በዚህ ጊዜ እምነትንና ተስፈኛነትን እየሰበከ ነበር። ሰፊ ባለ አራት ማዕዘናዊ ፊቱን በፈገግታ አብርቶ ወደ ካሜራው በመጠጋት፥ በሚሊዮን በሚቆጠሩ ተመልካቾች ላይ ጣቱን ጠቆመ። «በዚህ ሳምንት አንድ መልካም ነገር ያጋጥማችኋል!» ሲል «መ-ል-ካም» የምትለውን ቃል ሦስት ቦታ ላይ ሰባብሮ በማግባባት ተናገረ። ደንበኞቹን ለማግባባት የሚችለውን ያህል ጥረት የሚያደርግ ነጋዴ ይመስላል። ከጥቂት ቀናት በኋላ ግን የዚህ ሰውዬ ልጅ ራሱን እንደገደለ ከዜና እወጃ ለመረዳት ችያለሁ። በዚያ አስከፊ ሳምንት

ወንጌላዊው ወደ እግዚአብሔር ምን ብሎ እንደጸለየ በማሰብ እገረማለሁ።

እንዲህ ዓይነቶቹ ትግሎች ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ግላዊ አሳቢነት ሲሰነዘሩ የምሰማቸውን መፈክሮች መሳለቂያ ያደርጓቸዋል። ይሁንና፥ ማንም ቢሆን ከቅይማት ሽለቆ ነፃ አይደለም። ይህ በአገልጋዮችም ሆነ በሚያገለግሉ ክርስቲያኖች ላይ የሚደርስ ነው። መጀመሪያ ቅይማት ይመጣል፤ ከዚያም የጥርጣሬ ዘር። በመቀጠልም የቁጣ ወይም የክህደት ምላሽ ይከተላል። እግዚአብሔር ሊታመን ስለመቻሉና ሕይወታችንን በእርሱ ላይ ልንጥል ስለ መቻላችን እንጠይቃለን።

♥

ለረዥም ጊዜ ስለዚሁ ከእግዚአብሔር ጋር ስለ መቀያየም እያሰብሁ ብቆይም ለሁለት ምክንያቶች ስል ለመጻፍ አልፈለግሁም ነበር። በመጀመሪያ፥ ቀላል ምላሽ የማይገኝላቸው ጥያቄዎችን እንደምጋፈጥ አውቅ ነበር። እንዲያውም ብዙዎች ጭራሽ ምላሽ የላቸውም። ሁለተኛ፥ በዕውቀት ላይ በማተኮር የሰውን እምነት ሊጎዳ የሚችል መጽሐፍ ለመጻፍ አልፈለግሁም ነበር።

አንዳንድ የማውቃቸው ክርስቲያኖች «ከእግዚአብሔር ጋር መቀያየም» የሚለውን ሐረግ እንደማይቀበሉ አውቃለሁ። እንዲህ ዓይነቱ ነገር ስሕተት እንደሆነ ይናገራሉ። ኢየሱስ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ተራሮችን እንደሚያንቀሳቅስ ተናግሮአል። ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ከተሰባሰቡ ሊሳካ የማይችል ጉዳይ አይኖርም። የክርስትና ሕይወት የድል ሕይወት ነው። እግዚአብሔር ደስተኞች፥ ጤነኞችና በብልጽግና የተደላደልን እንድንሆን ይሻል። ከዚህ የወጣው ነገር ሁሉ የእምነት ጉድለትን ያሳያል ይላሉ።

ይህንኑ አሳብ የሚያራምዱትን ሰዎች ስጎበኝ ነበር መጽሐፉን ለመጻፍ የወሰንሁት። ለአንድ የመጽሔት ላይ ጽሑፍ ስለ ሥጋዊ ፈውስ ሳጠና ነበርና ለዚሁ ስል በኢንዲያና ገጠራማ አካባቢ ወደሚገኝ ጥሩ ዝና ወዳለነበረው ቤተ ክርስቲያን አመራሁ። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ከሺካጎ ትሪቡን እና ከኤቢሲ «ናይትላይን» ልዩ ዘገባ መረጃ አግኝቼ ነበር።

የዚህ ቤተ ክርስቲያን አባላት እምነት የትኛውንም ዓይነት በሽታ እንደሚፈውስና ከየትኛውም ሌላ አቅጣጫ፥ ለምሳሌ ከሕክምና ፈውስ መፈለግ በእግዚአብሔር ላይ እምነት ማጣትን እንደሚያመለክት

ያምናሉ። በትሪቡን ላይ የወጡት ጽሑፎች የዚህ እምነት ተከታዮች የሆኑ ወላጆች ልጆቻቸው በቀላሉ በሕክምና ሊወገዱ ከሚችሉ እንደ መንጋጋ ቆልፍ፥ ብርድ ወይም ጉንፋንን ከመሳሰሉ በሽታዎች ጋር ሲታገሉ ዝም ብለው እንደሚታዘቡ ያስረዳሉ። የትሪቡን ሠዓሊ ለቤተ ክርስቲያናቸው ዶክትሪን ለመገዛት ሲሉ ሕክምናን አሻፈረኝ ብለው የሞቱትን ሰዎች ለማመልከት በአሜሪካ ካርታ ላይ ሐውልቶችን ሠርቷል። በጠቅላላው ጎምሳ ሁለት ሐውልቶች ነበሩ።

ከቀረቡት ዘገባዎች ለመረዳት እንደተቻለው፥ በዚያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነፍሰ ጡር ሴቶች ከብሔራዊው አማካይ ሰምንት እጥፍ በወሊድ እንደሚሞቱ ተመልክቷል። ትናንሽ ልጆች ደግሞ ከዚህ ሦስት እጥፍ የመሞት ዕድል ያጋጥማቸዋል። ይህም ሆኖ፥ ቤተ ክርስቲያኒቱ እየተስፋፋች በመሄድ በአሥራ ዘጠኝ የአሜሪካ ግዛቶችና በአምስት የውጭ አገሮች ቅርንጫፎችን ከፍታለች።

በኢንዲያና የምትገኘውን ቤተ ክርስቲያን ሙቀት በሚያይልበት የነሐሴ ወር ጎብኝቻለሁ። ሙቀቱ የአስፋልት መንገዶችን ያንጸባርቃቸዋል። የእህል ነዶዎችንም ጉልበት አሳጥቶ አስጎንብሶአቸዋል። በሰብሉ መስክ መሐል ሕንጻው ተጎብሮአል። ሕንጻው ግዙፍ ሲሆን፥ ለእህል መጠበቂያ እንደተሠራ ሁሉ በብቸኝነት ተሸብቦአል። ከመኪና ማቆሚያው ዘንድ መገናኛ መነጋገሪያ የያዙ ሁለት አስተናጋጆችን አነጋገርሁ። ቤተ ክርስቲያኒቱ የመረጃ ጉዳይ ያብከነከናታል። በተለይም ቀደምት አባሎቿ ከስ ስለመሠረቱባት ተበጥብጣ ነበር።

በአገልግሎቱ ወቅት የአከራሪነት ምልክት የጠበቅሁ ይመስለኛል። ስሜታዊነት ያየለበትና አድማጮቹን እንዳያስቡ የሚከላከል ስብከት ቀረበ።

ከዚህ በፊት እንዲህ ዓይነት ነገር አጋጥሞኝ አያውቅም። ለዘጠና ደቂቃዎች ሰባት መቶ ሰዎች ሆነን በግማሽ ክብ ሕንጻ ውስጥ ስንዘምርና መጽሐፍ ቅዱስ ስናጠና ቆየን።

ከአጠገቤ የሚገኙት «ተራ ሰዎች» ነበሩ። ሴቶች ቀሚስ ለብሰዋል። ሱሪ ያደረገች ሴት አትታይም። ብዙም ጌጣጌጥ አይጠቀሙም። ወንዶች ሸሚዝና ክራባት ለብሰው ከቤተሰቦቻቸው ጋር የተቀመጡ ልጆችን ፈር ለማሳያዝ አስተዋጽኦ አደረጉ።

ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በላይ በዚህ ቤተ ክርስቲያን ልጆች ጎልተው ይታያሉ። የማይደርሱባት ስፍራ የለም። ለዘጠና ደቂቃዎች በዝምታ መቀመጡ የሕፃናቱን ትዕግሥት ስለሚያሟጥጥ

ወላጆች ሁኔታውን ለማስተካከል ሲጥሩ አየሁ። በቀለም ያሸበረቁ ብዙ መጻሕፍት ነበሩ። እናቶች ከልጆቻቸው እጆች ጋር ይጫወታሉ። አንዳንዶች ቤተ ክርስቲያኒቱን በገንዘብ ለመደገፍ አሻንጉሊቶችን ይዘው መጥተዋል።

ስሜታዊነትን ብቻ ለማየት መጥቼ ብሆን ኖሮ አዝኜ እመለስ ነበር። ባሕላዊ የአሜሪካን ሕይወት የሚመሩ ቤተሰቦች እንዳሉ ጭምር ለመረዳት ችያለሁ። በዚያ የሚገኙ ወላጆች እንደ ማንኛውም ወላጅ ልጆቻቸውን ይወዳሉ።

ይህም ሆኖ፥ እነዚያ በካርታ ላይ የተሣሉ ትናንሽ ሐውልቶች ወደ አእምሮዬ ማቃጨላቸው አልቀረም። ከነዚህ ወላጆች አንዳንዶቹ ለሞት ከሚያጣጥሩ ልጆቻቸው አልጋ ጠርዝ ላይ ተቀምጠው ምንም ጥረት ያላደረጉ ናቸው። አንድ አባት የአሥራ አምስት ወራት ልጁ ለሁለት ሳምንታት ከትኩሳት ጋ ሲዋጋ እየተመለከተ በጸሎት ስላሳለፋቸው ጊዜያት ለትሪቡን አውግቷል። በሽታው መጀመሪያ ልጁን አደነቆረው። ከዚያም አሳወረው። በዚህ ጊዜ የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ አባቱ የበለጠ እምነት እንዲያዳብርና ሐኪም ከመጥራት እንዲታቀብ ገፋፋው። በቀጣዩ ዕለት ልጁ ሞተ። የአስከሬን ምርመራው ልጁ በቀላሉ ሊታከም በሚችል መንጋጋ ቆልፍ እንደ ሞተ አመልክቷል።

የኢንዲያና ቤተ ክርስቲያን አባላት በአብዛኛው ለችግሮቻቸው እግዚአብሔርን አይወቅሱትም። ቢያንስ ቢያንስ እግዚአብሔርን እንደሚወቅሱ አይናገሩም። ከዚህ ይልቅ ለደካማ እምነታቸው ራሳቸውን ጥፋተኛ ያደርጋሉ። በዚህ መሀል ሐውልቶች እየበዙ ይሄዳሉ።

ከዚያን ዕለቱ የሰንበት አምልኮ የወጣሁት እንደ ማናቸውም የሕይወት ዙሪያ ጉዳዮች ስለ እግዚአብሔር የምናስበውና የምናምነው ጉዳይ ከፍተኛ ለውጥ እንደሚያስከትል በጽኑ በማመን ነበር። እነዚህ ሰዎች ጭራቆች ወይም ልጆቻቸውን ለመግደል የሚሹ አልነበሩም። ነገር ግን ከሥነ-መለኮታዊ ስሕተታቸው የተነሣ በርካታ ልጆቻቸውን አጥተዋል። (እንደ እውነቱ ከሆነ የኢንዲያና ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ከብዙ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትና ሃይማኖታዊ የመገናኛ ብዙኃን ከምሰማው ብዙም የተለየ አልነበረም። የተጋነኑ የእምነት ተስፋዎችን ደጋግመው ያቀርባሉ።)

በኢንዲያና የሚገኙትን እውነተኛ ሰዎችና በደብዳቤ ጥያቄዎቻቸውን ያቀረቡልኝን ግለሰቦች በማሰብ ወደ ጎን ልለው የፈለግሁትን ጉዳይ ልጋፈጠው ወሰንሁ። እናም ይህ የሥነ-መለኮት መጽሐፍ በቀለ። ይህ በምንም ዓይነት ቴክኒካዊ መጽሐፍ አይደለም።

ይልቁንም፥ ስለ እግዚአብሔር ማንነትና አንዳንድ ጊዜ ለምን ግራ በሚያጋባ መንገድ እርምጃ እንደሚወስድ፥ በሌላ ጊዜ ደግሞ ለምን እርምጃ እንደማይወስድ የሚናገር መጽሐፍ ነው።

ሥነ-መለኮት በሰሚናሪ ውስጥ ፕሮፌሰሮችና ተማሪዎቻቸው የአእምሮ ጅምናስቲክ የሚያሠሩበት ብቻ ሊሆን አይችልም። ሁላችንንም ይነካናል። አንዳንድ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር በከፍተኛ ደረጃ ስለ ተቀያየሙ እምነታቸውን አጥተዋል። እግዚአብሔር በተወሰነ አቅጣጫ እርምጃ እንዲወስድ ይጠብቁና «ጉድ ይሠራቸዋል።» ሌሎች እምነታቸውን ላያጡ ይችላሉ። ይሁንና፥ እነርሱም ከእግዚአብሔር ጋር መቀያየማቸው አልቀረም። እግዚአብሔር ጣልቃ እንደሚገባ በማመን ለተአምራት ይጸልያሉ። ጸሎታቸው ግን ምላሽ አያገኝም። ይህ በኢንዲያና ቤተ ክርስቲያን ቢያንስ ሃምሳ ሁለት ጊዜ ተከስቷል።

ምዕራፍ 2

በጭስ ውስጥ

አንድ ከሰዓት በኋላ የስልክ ጥሪ ደረሰኝ። ደዋዩም በዊተን የድኅረ ምረቃ ኮሌጅ ውስጥ የሥነ-መለኮት ተማሪ እንደሆነ ገለጸልኝ። «ስሜ ሪቻርድ ይባላል። ከዚህ በፊት አንተዋወቅም። ነገር ግን አንዳንድ ጽሑፎችህን ስላነበብሁ ቅርበት ይሰማኛል። አንድ ደቂቃ ይኖርሃል?» አለኝ።

ሪቻርድ ስለ ራሱ መናገሩን ቀጠለ። ወደ ክርስትና የመጣው የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ሆኖ አንድ የኢንተርቫርሲቲ ሠራተኛ ባቀረበለት ምስክርነት መሆኑን ገለጸልኝ። ይህም ሆኖ፥ የሪቻርድ ንግግር አዲስ ክርስቲያን አያስመስለውም። ምንም እንኳ የትኞቹን ክርስቲያናዊ መጻሕፍት ማንበብ እንዳለበት እንድነግረው ቢጠይቀኝም፥ የምጠቅሳቸውን ሁሉ እንዳነበበ ተገነዘብሁ። ፈጣንና አስደሳች ጭውውት አድርገን ልናበቃ ስንል የደወለበትን እውነተኛ ምክንያት ተረዳሁ።

«በዚህ አንተን ላስቸግርህ አልፈልግም» አለ ሽብር እያተራመሰው። «ሥራ ሊበዛብህ እንደሚችል አውቃለሁ። ነገር ግን አንድ ውለታ እንድትውልልኝ እፈልጋለሁ። አየህ፥ በኢዮብ ላይ ጥናታዊ ጽሑፍ አዘጋጅቻለሁ። ፕሮፌሰሩ ጽሑፉን ወደ መጽሐፍነት እንድለውጠው ነግሮኛል። ጽሑፉን አይተህ አስተያየት ልትሰጥ የምትችልበት ዕድል ይኖር ይሆን?»

ፈቃደኛነቴን ገለጽሁለትና ጽሑፉ በጥቂት ቀናት ውስጥ ደረሰኝ። እንደ እውነቱ ከሆነ ብዙም ጥሩ ሥራ ይሆናል ብዬ አልጠበቅሁም ነበር። ብዙውን ጊዜ የድኅረ ምረቃ ጥናታዊ ጽሑፎች ኃይል ስለማይኖራቸው፥ ይህ በአንጻራዊ ሁኔታ የቅርብ ጊዜ አማኝ የነበረው ግለሰብ ተስፋ አስቆራጭ በሆነው የኢዮብ ታሪክ ላይ የሚያጓጓ ትኩስ አሳብ ይዞ ይመጣል የሚል እምነት አልነበረኝም። ነገር ግን ተሳስቻለሁ። ጽሑፉ ተስፋ የሚጣልበት ስለ ነበረ ለሚቀጥሉት ጥቂት ወራት ሪቻርድና እኔ በስልክና በደብዳቤ እየተገናኘን ወደ መጽሐፍነት ሊለወጥ በሚችልበት ሁኔታ ላይ ስንነጋገር ቆየን።

ከአንድ ዓመት በኋላ ሪቻርድ ለጎትመት የተዘጋጀ መጽሐፍና ከአሳታሚ ድርጅት ጋር የተደረገ ውል ከእጁ ካስገባ በኋላ መቅድሙን እጽፍለት ዘንድ ደውሎ ጠየቀኝ። እስካሁን ከሪቻርድ ጋር በአካል ተገናኝተን አናውቅም ነበር። ይሁንና፥ ጥረቱን ወድጄለታለሁ። እናም ለመጽሐፉ ድጋፍ መስጠት እችል ነበር።

ስድስት ወራት አለፉ። በዚህ ጊዜ ለመጽሐፉ የመጨረሻ እርማትና ከለሳ ተደረገለት። ከዚያም መጽሐፉ ሊታተም ሲል ሪቻርድ ስልክ ደወለልኝ። በዚህ ጊዜ ድምፁ ከቀድሞው የተለየ ውጥረት ይስተዋልበታል። የሚገርመው ታትሞ ሊወጣ ስለተቃረበው መጽሐፍ የማነሣቸውን ጥያቄዎች ሁሉ ወደ ጎን ይገፋቸው ጀመር።

«ፊሊፕ፥ መገናኘት አለብን። አንድ ልነግርህ የተገደድሁት ነገር ስላለ በአካል መገናኘት አለብን። በዚህ ሳምንት አንድ ከሰዓት በኋላ ብመጣስ?» ሲል ጠየቀኝ።

♥

ሙቀት ያረገቡ የፀሐይ ጨረሮች ከሦስተኛው ፎቅ ላይ በሚገኘው አፓርታማዬ ውስጥ ሠፍረዋል። መዝጊያው መጋረጃ ስላልነበረው ዝንቦች እንዳሻቸው መግባት መውጣት ይዘዋል። ሪቻርድ ነጭ የጠረጴዛ ቴኒስ ቁምጣና እጅጌ-ጉርድ ሸሚዝ ለብሶ ከአጠገቤ ተቀመጠ። ላብ ከግንባሩ ይፈልቃል። ለዚህ ስብሰባ ሲል በተጨናነቀው የሺካጎ ትራፊክ ውስጥ ለአንድ ሰዓት ያህል መኪናውን ሲነዳ የቆየ በመሆኑ፥ መጀመሪያ ሰውነቱን ለማቀዝቀዝ አንድ ብርጭቆ በረዶ የተቀላቀለበት ሻይ በፍጥነት ጠጣ።

ሪቻርድ ቀጠን ያለ ሸጋ አካላዊ ቁመና ያለው ወጣት ነበር። ከሲታ ፊቱና በአጭሩ የተከረከመው ፀጉሩ መንፈሳዊነትን የተላበሰ መነኩሴ አስመስለውታል።

አካላዊ ቋንቋ መልእክት የሚያስተላልፉ ከሆነ፥ የሪቻርድ አኳኋን ብዙ ይናገራል። እጆቹን ያጣምራቸዋል፤ መልሶ ደግሞ ይለያያቸዋል፤ እግሮቹንም እንደዚሁ። ፊቱ በውጥረት ተጠፍሮአል።

ትንሽ መናገር ጀመረ። «በእኔ ላይ ለመቆጣት በቂ ምክንያት አለህ» ሲል ጀመረ። «ግራ የመጋባት ስሜት ቢጫንህ አልፈርድብህም።»

ስለ ምን እንደሚያወራ የማውቀው አልነበረኝም፥ «ስለ ምን?» ስል ጠየቅሁት።

«ይኸውልህ፥ ነገሩ እንደዚህ ነው። በአንተ ርዳታ የተዘጋጀው መጽሐፍ በሚቀጥለው ወር መቅድምህን ይዞ ከገበያ ላይ ይውላል። እውነቱ ግን ከእንግዲህ ወዲህ በዚያ መጽሐፍ ውስጥ ባሰፈርሁት አሳብ የማላምን መሆኔ ነው። እናም ይህንኑ የማስረዳት ኃላፊነት ያለብኝ መስሎ ተሰምቶኛል።»

ለአፍታ ዝም አለ። ከመንጋጋው ላይ የውጥረት መንጋ ሲተራመስ ተመለከትሁ። «እግዚአብሔርን እጠላዋለሁ!» ሲል ድንገት ተናገረ። «የለም፥ እንደዚያ ማለቴ አይደለም። እንዲያውም በእግዚአብሔር አላምንም።»

የሰጠሁት ምላሽ አልነበረም። እንዲያውም፥ ሪቻርድ ከወላጆቹ መፋታት ጀምሮ ታሪኩን በተረከባቸው ቀጣይ ሦስት ሰዓታት ውስጥ የተናገርሁት ጥቂት ብቻ ነበር። «ፍችውን ለማስቀረት የምችለውን ሁሉ አደረግሁ። በዩኒቨርሲቲ ሳለሁ ገና ወደ ክርስቶስ መምጣቴ ስለነበር፥ እግዚአብሔር ስለ እኔ ይገደዋል ብዬ ተጃጃልሁ። ተስማምተው በትዳር ይዘልቁ ዘንድ ባለማቋረጥ ቀንና ሌሊት ጸለይሁ። እንዲያውም ለተወሰነ ጊዜ ትምህርቴን አቋርጬ ቤተሰቤን ለማስታረቅ ጣርሁ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ እያደረግሁ ያለሁ መስሎኝ ነበር፤ ነገር ግን ሁሉንም ነገረ ወደ ባሰ ደረጃ ያደረስሁ ይመስለኛል። ይህ ምላሽ ያላገኘ ጸሎት የመጀመሪያው ገጠመኝ ሆነ።

«ስለ እምነት የበለጠ ለመማር ወደ ዊተን ኮሌጅ ተሻገርሁ። አንድ የሆነ ነገር እያበላሸሁ እንዳለሁ ተረዳሁ። በዊተን «ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገርሁ»፥ «ጌታ ተናገረኝ» የሚሉ ዓይነት ሐረጎችን የሚጠቀሙ ሰዎች አጋጠሙኝ። እኔም አንዳንድ ጊዜ እንደዚያ ብዬ ነበር። ይሁንና፥ እንዲህ በምልበት ጊዜ ከበደለኛነት ስሜት ነፃ ሆኜ አላውቅም። እውነት እግዚአብሔር አንድ ነገር ተናግሮኝ ያውቃል? የሰማሁት ድምፅ ካለመኖሩም በላይ ላየው ወይም ልጨብጠው የምችለው የእግዚአብሔር ማረጋገጫ አልነበረኝም። ይሁንና፥ እንደዚያ ዓይነት ቅርበት ለማግኘት ስናፍቅ ኖርሁ።

«ከፍተኛ ውሳኔ የሚጠይቅ ጉዳይ በሚያጋጥመኝ ጊዜ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ አንብቤ የእግዚአብሔርን ምሪት በጸሎት እጠይቃለሁ። ስለ ውሳኔው ትክክለኛ ስሜት ሲሰማኝ እርምጃ እወስዳለሁ። ነገር ግን ሁልጊዜም ትክክል ካልሆነ ውሳኔ ላይ እደርሳለሁ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ በትክክል የተረዳሁ ሲመስለኝ የተገላቢጦሹ ይከሰታል።

ከመንገዱ የሚወነጨፉ ድምፆች ይሰሙኛል። ጎረቤቶቼ በፎቆቹ ላይ ይወጣሉ፤ ይወርዳሉ። እነዚህ ድምፆች ግን ሪቻርድን አላወኩትም። መናገሩን ቀጠለ። እኔም ምንም እንኳ አሁንም በእግዚአብሔር ላይ ይህን ያህል ጥላቻ ያሳየበትን ምክንያት ገና ባልረዳም አልፎ አልፎ በአዎንታ ራሴን እያወዛወዝሁ ስሰማው ቆየሁ። ብዙ ትዳሮች ይፈርሳሉ፤ ብዙ ጸሎቶች ሳይመለሱ ይቀራሉ። ይህን ያህል በቁጣ የጦፈበት እውነተኛው ምክንያት ምንድን ነው?

ቀጥሎም ስላመለጠው የሥራ ዕድል ገለጸልኝ። ድርጅቱ ለእርሱ የገባውን የተስፋ ቃል በማጠፉ ለስፍራው ያነሰ ብቃት ያለውን ሰው ቀጠረ። ይህም ሪቻርድ የትምህርት ቤት ዕዳዎቹን ለመክፈል እስከማይችል ድረስ ያለምንም የገቢ ምንጭ መና እንዲቀር አደረገው። በተመሳሳይ ጊዜ እጮኛው ተለየችው። በቅጽበት ለምን አሳዛን እንደ ቀየረች ሳትገልጽለት ከእርሱ ጋር የነበራትን ግንኙነት አቋረጠች። እጮኛው ሼረን በሪቻርድ መንፈሳዊ ዕድገት ላይ ቁልፍ ሚና ትጫወት ስለነበር፥ ስትለየው ከእምነቱ የተወሰነው ክፍልም አብሯት የተለየው መሰለው። ብዙውን ጊዜ ስለ ወደፊት ሕይወታቸው አብረው ይጸልዩ ነበር። አሁን ግን እነዚያ ጸሎቶች የጭካኔ ቀልድ ያህል አብከነከኑት።

በተጨማሪም፥ ሪቻርድ ተከታታይ አካላዊ ችግሮች ነበሩት። እነዚህም ከምስኪንነቱና ከጭንቀቱ ላይ ተጨማሪ ሸክሞች ሆኑበት። ወላጆቹ በተለያዩ ጊዜ ያሠቃዩት የመጣል ቁስሎች ዳግም የተቀሰቀሱ መሰሉ። እግዚአብሔር እንደ ሼረን «አለሁልህ» እያለ ሊያታልለው ቆይቶ ይሆን? ምክር ፍለጋ ወደ አንድ መጋቢ ዘንድ ሄደ። ከውኃው ውስጥ እየሰጠመ እንዳለ የተሰማው መሆኑን ይናገራል። በእግዚአብሔር ለመታመን ቢሻም፥ ጥረቱ ሁሉ አንድ እፍኝ አየር ዘግኖ ከመመለስ አልዘለለም። ስለ እርሱ ደኅንነት ግድ የሌለው የሚመስለውን አምላክ ለምን ያምልከው?

መጋቢው የሪቻርድን ሁኔታ በማጤን ብዙም አላዘነለትም። ይህም ሪቻርድ የእርሱ ችግሮች ከሰውዬው ተለምዶአዊ የጋብቻ ፍችዎች፥ የካንሰር በሽተኞች፥ የአልኮሆል ቁራኛዎችና የኮብላይ ልጆች ወላጆች ጉዳዮች ጋር እንደማይስተካከሉ በግልጽ ተገነዘበ። «የእጮኛህ ጉዳይ ሊቃለል ከእግዚአብሔር ጋር ያለህ ችግር ይቃለላል» ሲል ከለበጣ ፈገግታ ጋር አሰናበተው።

ለሪቻርድ ችግሮቹ ቀላሎች ሆነው ሳለ አፍቃሪው ሰማያዊው አባት ለምን በእንዲህ ዓይነት ቅይማት እንዲሠቃይ እንዳደረገው ሊገባው አልቻለም። ልጁን እንዲህ የሚያሠቃይ ምድራዊ አባት ሊኖር አይችልም። ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄዱን ባያቋርጥም፥ በልቡ ውስጥ የጥርጣሬ ካንሰር ይፋፋ ጀመር። በትምህርት ቤት የተማረውና በመጽሐፍ ውስጥ የጻፈው ሥነ-መለኮት ሊሠራለት አልቻለም።

«ነገሩ ግራ ነው» ሲል ገለጸልኝ። «ይሁንና፥ በእግዚአብሔር የበለጠ በተቆጣሁ መጠን የበለጠ ኃይል የማገኝ ይመስለኛል። ላለፉት አያሌ ዓመታት ከውስጤ እንደተቦረቦርሁ አውቃለሁ። አሁን መጠራጠር ስጀምርና ትምህርት ቤቱንና በአካባቢዬ የሚገኙትን ሌሎች

ክርስቲያኖች ከምጠላበት ደረጃ ላይ ስደርስ፥ ወደ ሕይወት ተመልሼ እንደመጣሁ ያህል ይሰማኛል።»

የሆነ ነገር ቀስቅሶት ሪቻርድ አንድ የእሑድ ምሽት የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም ተካፈለ። በወቅቱ የተለመዱ ምስክርነቶችና ምስጋናዎች ቢቀርቡም፥ በተለይ አንድ ሪፖርት የሪቻርድን ስሜት አስቆጣው። በሳምንቱ የመጀመሪያ አካባቢ አንድ አውሮፕላን በአላስካ ተከስክሶ በውስጡ የነበሩትን ዘጠኝ ሚሲዮናውያን ገድሎ ነበር። መጋቢው ይህንኑ ታሪክ በዝርዝር ካወጋ በኋላ በዚያው ሳምንት ከሌላ የአውሮፕላን አደጋ የተረፈውን የቤተ ክርስቲያን አባል ከምእመናኑ ጋር አስተዋወቀ። ከአደጋው የተረፈው ሰውዬ ስለ ሁኔታው አብራርቶ ሲያበቃ፥ ማኅበረ ምእመኑ «ጌታ ይመስገን!» የሚል ምላሽ ሰጠ!

መጋቢውም፥ «ጌታ ሆይ፥ ወንድማችንን በሰላም ስላመጣህልንና ጠባቂ መላእክትህ እንዲከተሉት ስላደረግህ እናመሰግንሃለን» ሲል ጸለየ። «በአላስካ ከሞቱት ሰዎች ቤተሰቦች ጋርም እንድትሆን እንለምንሃለን።» ይህ ጸሎት በሪቻርድ ውስጥ እንደ ማቅለሽለሽ ዓይነት ስሜት ፈጠረበት። ሁለት ወዶ አይቻልም ሲል አሰበ።

እግዚአብሔር ለተረፈው ሰውዬ ከተመሰገነ ለሞቱት ሊወቀስ ይገባል። አብያተ ክርስቲያናት ግን የኃዘንተኞችን ምስክርነት አይቀበሉም። የሞቱት ሚሲዮናዊያን የትዳር ጓደኞች ምን ይሉ ይሆን? ስለ «አፍቃሪ አባት» ይናገሩ ይሆን?

ሪቻርድ በጣም ተበሳጭቶ ወደ አፓርታማው ተመለሰ። በአእምሮው ውስጥ የሚፈጠረው ጥያቄ ወደ አንድ ጥያቄ እያመራ ነበር፤ «ለመሆኑ እግዚአብሔር አለን?» ሪቻርድ ስለ እግዚአብሔር መኖር አስረግጦ የሚያስረዳ መረጃ አላገኘም።

♥

ሪቻርድ ታሪኩን ከዚህ ነጥብ ላይ አቋረጠው። ፀሐይቱ ለክፍሉ ጥላ ያዘለ ጨረሯን ከበተነች በኋላ በስተምሥራቅ ከግዙፍ ሕንፃ ጀርባ ዘልቃ ተሰውራለች። ሪቻርድ ዓይኖቹን ጨፍኖ የታች ከንፈሩን ይበላው ጀመር። በጣቶቹ ዓይኖቹን ይጠነቁለው ገባ። የአእምሮውን ምስል ለማስተካከል የሚጥር ይመስላል።

«ከዚያስ ምን ሆነ?» ስል ጠየቅሁት ከተወሰነ ጸጥታ በኋላ። «በዚያን ምሽት ነበር እምነትህ የከዳህ?»

በአምንታ ራሱን ወዘወዘና መናገሩን ቀጠለ። የድምፁ ቅላፄ ግን ርግብግቢት አበዛ። «በዚያን ምሽት ቁጭ ብዬ አመሸሁ። ጎረቤቶቼ ወደ እንቅልፍ ዓለም ከፈለሱ ቆይተዋል። የምኖረው ከከተማ ወጣ ብሎ በሚገኝ ስፍራ በመሆኑ፥ በዓለም ውስጥ ብቻዬን የምኖር መስሎ ተሰማኝ። አንድ አስፈላጊ ነገር ሊከሰት የደረሰ መስሎኝ ነበር። ልቤ ተጎዳ። ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር አሳዝኖኛል። እግዚአብሔርን ብጠላውም ከመፍራት አላመለጥሁም። የሥነ-መለኮት ተማሪ ነበርሁ፥ ገባህ? ምናልባትም እግዚአብሔር ኖሮ እኔው ተሳስቼ ይሆናል። እንዴት ላውቅ እችላለሁ? ከመጀመሪያው ጀምሬ ጠቅላላ ክርስቲያናዊ ሕይወቴን ገመገምሁ።

«በዩኒቨርሲቲ እምነትን ሀሌ ብዬ የጀመርሁበትን ሁኔታ አስታወስሁና ያን ጊዜ ብዙም አጥብቆ ለማሰብ የማልችል ወጣት ነበርሁ። ምናልባትም ጥቂት ሐረጎች እንደሰማሁ ነበር። «በተትረፈረፈ ሕይወት» ወደ ማመኑ ያመራሁት።

የሴሎች ሰዎችን ልምምድ እየኮረጅሁ ሳልኖር አልቀረሁም። ስለ እግዚአብሔር ራሴን አታልዬ ይሆን?

«አሁንም ቢሆን ያን ጊዜ ያመንሁትን ሁሉ ለመተው አመነታለሁ። ለእግዚአብሔር አንድ የመጨረሻ ዕድል መስጠት እንዳለብኝ ተሰምቶኝ ነበር።»

«እናም በዚያን ሌሊት በተቻለኝ ሁሉ ትጋትና ታማኝነት ወደ እግዚአብሔር ጸለይሁ። በጉልበቶቼ ተንበርክኬና ከወለሉ ላይ ተዘርሬ ጸለይሁ። «እግዚአብሔር ሆይ፥ ስለ እኔ ግድ ይልሃል?» እያልሁ ጸለይሁ። «ዓለምን እንዴት እንደምታስተዳድር ልነግርህ አልፈልግም። መኖርህን የሚያረጋግጥልኝ አንድ ምልክት ብቻ ስጠኝ። የምጠይቅህ ይህንኑ ብቻ ነው!»

«ለአራት ዓመታት ከእግዚአብሔር ጋር የግል ግንኙነት ለማድረግ ስታገል ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ከማናቸውም ጓደኞቼ ካለው በከፋ ሁኔታ አስተናገደኝ። አሁን ሁሉም ነገር ወደ አንድ መጨረሻ ጥያቄ ተጣበበ፤ ሌላው አካል መኖሩን እንኳ ሳታውቅ ግላዊ ግንኙነት ልታደርግ የምትችለው እንዴት ነው? ስለ እግዚአብሔር መኖር ከቶውንም እርግጠኛ ልሆን አልችልም።

«ቢያንስ ለአራት ሰዓትት ጸልያለሁ። አንዳንድ ጊዜ የሞኝነት ተግባር የፈጸምሁ ይመስለኛል። በሌላ ጊዜ ግን የእውነተኝነትን ሥራ የሠራሁ መስሎ ይሰማኛል። የምደርስበትን ሳላውቅ በጨለማ ውስጥ

ከሸለቆ ጫፍ ራሴን እንደ ጣልሁ መስሎ ይሰማኛል። ይህ ነበር ስለ እግዚአብሔር የሚሰማኝ።

«በመጨረሻም፥ ከጠዋቱ አራት ሰዓት ላይ ወደ አእምሮዬ ተመለስሁ። የተከሰተ ነገር አልነበረም። እግዚአብሔር ምላሽ አልሰጠም። እንግዲህ ለምን ራሴን ሳሠቃይ ልኑር? ለምን እግዚአብሔርን ዘንግቼ እንደ አብዛኛዎቹ የዓለማችን ሰዎች ሕይወቴን አልገፋም?

«ወዲያውም የግጠቀለያ ፈተና እንዳለፍሁ ወይም የመንጃ ፈቃድ እንደተቀበልሁ ያህል እፎይታና ነጻነት ተሰማኝ። ትግሉ ተፈጸመ። ሕይወቴ የእኔው ሆነች።»

«ነገሩ ሞኝነት ቢመስልም ቀጥሎ ያደረግሁት ይህንኑ ነበር። መጽሐፍ ቅዱሴንና ሌሎች ጥቂት ክርስቲያናዊ መጻሕፍት ይዤ ወደ ውጭ ወጣሁ። ማንንም ሰው ላለመረበሽ ስል በሩን በዝግታ ከኋላዬ ዘጋሁ። ከወደ ጓሮ አንድ የከሰል ምድጃ ነበረና መጽሐፎቹን እዚያ ላይ ደረደርሁ። ከዚያም የላይተር ጋዝ አርከፍክፌ ክብሪት ለኮስሁባቸው። ጊዜው ጨረቃ የሌለችበት ሌሊት ስለነበረ፤ የእሳቱ ነበልባል ደምቆ እያበራ ይጨፍር ጀመር። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችና የሥነ-መለኮት መጻሕፍት ከተጠቀለሉና ከጠቋቆሩ በኋላ ወደ አመድነት ተለውጠው ወደ ሰማይ አቅጣጫ ተንሳፈፉ። እምነቴም ከእነርሱ ጋር በነነ።

«አሁንም ወደ ፎቅ ወጥቼ እጄ የቻለውን ያህል መጽሐፍ አመጣሁ። ለቀጣዩ ሰዓት ምናልባትም ስምንት ጊዜያት ያህል ተመላልሼ ሳጓጉዝ ቆይቻለሁ። ማብራሪያዎች፥ የሰሚናሪ የመማሪያ መጻሕፍት፥ በኢዮብ ላይ የጻፍሁት መጽሐፍ ረቂቅ ጽሑፍ ሁሉ ወደ ጭስነት ተለወጠ። ምናልባትም አንድ ቢጫ የዝናብ ልብስ የለበሰ የእሳት አደጋ ተከላካይ ወደ እኔ መጥቶ፤ «ምን ማድረግህ ነው? እያለ ባይበጠብጠኝ ያሉኝን መጻሕፍት በሙሉ አቃጥዬ ሳልጨርስ አልቀርም ነበር። የሆነ ሰው በስጋት ስልክ ስለደወለ ነበር የመጣው። ይቅርታ ለመጠየቅ ከተንገታገትሁ በኋላ ቆሻሻ እያቃጠልሁ መሆኔን ነገርሁት።

«የእሳት አደጋ ሠራተኛው ከእሳቱ ላይ አንዳንድ ኬሚካሎች ከረጨና ቆሻሻ ከጨመረበት በኋላ እንድሄድ አደረገኝ። ወደ ፎቁ ወጥቼ ጭስ ጭስ እየሸተትሁ ከአልጋዬ ውስጥ ገብቼ ተኛሁ። ጊዜው ሊነጋ ተቃርቦ ነበርና እኔም ሰላም ተሰማኝ። ትልቅ ሸክም ተቃሏል። ለራሴ ታማኝ ሆኛለሁ። ግብዝነቱ ስለለቀቀኝ ከእንግዲህ እርግጠኛ ያልሆንሁበትን የማመን ውጥረት አልነበረኝም። የተለውጥሁ መስሎ ተሰማኝ– ወደ እግዚአብሔር ሳይሆን ከእግዚአብሔር ወደ ራሴ ተለወጥሁ።»

♥

የማማከርን አገልግሎት ሙያዬ ብዬ ባለመያዜ ደስ ይለኛል። እንደ ሪቻርድ ከሚሠቃዩ ሰው አጠገብ ስቀመጥ የምለው ይቸግረኛል። በዚያ ከሰዓት በኋላ ብዙም የተናገርሁት አልነበረም። ያ ከሁሉ የተሻለ ነገር ነበር። ሪቻርድ የእግዚአብሔርን መኖር ለማረጋገጥ የተጠቀመውን መፈተኛ ስሕተት ማግኘቱ ሊረዳኝ አይችልም ነበር።

በተለይም እርሱ የተጨነቀው በቀጣይ ጥቂት ሳምንታት ታትሞ ስለሚወጣው መጽሐፍ ነበር። አሳታሚው የሪቻርድን የአሳብ ለውጥ ቢያውቅም፥ የመጀመሪያው እትም በጋዜጦች ታውጆ ነበር። ለመጽሐፍ የሰጠሁት ድጋፍ ከእርሱ ጋር ካለኝ ግንኙነት በላይ በመጽሐፉ ይዘት ላይ የሚያተኩር ነበር። «በተጨማሪም፥ ባለፉት አሥር ዓመታት ከጻፍኋቸው ነገሮች በአንዳንዶቹ ላይ የነበረኝን አቋም ቀይሬአለሁ» አልሁት።

ሪቻርድ ረዥም ንግግር በማድረግ የደከመ ይመስላል። ነገር ግን ለመሄድ ሲነሣ ነጻነት የተሰማው ይመስላል። «ምናልባትም ችግሮች ሁሉ የበቀሉት ከመጽሐፈ ኢዮብ ጥናት ይሆናል። ኢዮብን እወደው ነበር። ከእግዚአብሔር ጋር በግልጽ ለመነጋገር አይፈራም ነበር። እግዚአብሔርን ይፈታተን ነበር። እንደምገምተው በሁለታችን መካከል የተከሰተው ልዩነት በመጨረሻው ላይ የሆነው ነው። እግዚአብሔር ከዚያ ሁሉ ሥቃዩ በኋላ ለኢዮብ ደረሰለት። ለእኔ ግን አልደረሰልኝም» አለኝ።

ጊዜው በመምሸቱ መብራቶቹ ተቀጣጥለዋል። ሪቻርድ እጁን ጨብጦ ደረጃዎቹን ሲወርድ ልቤ በኃዘን ተወረረ። ጤናማ ወጣት ነበር። አንዳንድ ሰዎች እንደ እርሱ ያለ ወጣት የሚጨነቅበት ምክንያት እንደማይኖረው ሊገምቱ ይችላሉ። ነገር ግን ታሪኩን ከመስማት፥ እጆቹ ሲፈታተጉ ከማየትና ከፊቱ ላይ የውጥረት መስመሮችን ከማንበብ፥ በመጨረሻው የቁጣውን ምንጭ ተረድቻለሁ።

ሪቻርድ በሰው ልጅ ላይ የሚደርሱትን ማናቸውንም ከባድ ሥቃዮች በሚመስል ችግር ውስጥ ነበር። ይህም ክህደት በእርሱ ላይ መፈጸሙ ነበር። ድንገት ሲነቃ የሚወደው አምላኩ ከአጠገቡ ታጣ። ሕይወቱን ለእግዚአብሔር አሳልፎ የሰጠው ሲሆን፥ እግዚአብሔር ግን ምላሽ ባለመስጠት አሳዛነው።

ምዕራፍ 3

ሰው የማይደፍራቸው ጥያቄዎች

አንዳንድ ጊዜ ለሚበዛው የሕይወት ዘመናችን በአእምሮአችን ውስጥ ባልተጨበጠ መልክ እየተጉላሉ የሚኖሩ ጥያቄዎች በአንድ ቅጽበት ጎልተው ሊወጡ ይችላሉ። ለእኔ የሪቻርድ ጉብኝት እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ፈጥሮብኛል። በአንድ በኩል፥ ስለ ወላጆቹ መፋታት፥ የጤንነት ችግሮች፥ የእጮኛው መክዳት፥ ሥራ አጥነቱ ያነሣቸው ጉዳዮች በዓለም ከሁሉም የላቀ ቅይጣት የሚፈጥሩ አልነበሩም። ይሁንና፥ በዚያን ሌሊት ከምድጃው ላይ መጻሕፍትን ሲያቃጥል የነበረበት ሁኔታ ሁላችንንም የሚያሠቃየውን ጥርጣሬ ይቀሰቅሳል። እውነት እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ግድ ይለዋል? ከሆነ፥ ለምን እየተበላሹ ያሉትን ነገሮች አያቃናም? ሁሉንም ባይሆን አንዳንዶቹን እንኳ።

ሪቻርድ በቁጣውና በሥቃዩ ተውጦ ለጥርጣሬዎቹ ብልሃታዊ ድምፅ ሳይሰጥ ቀርቷል። እርሱ የተመለከታቸው የእምነት ጉዳዮች ሳይሆኑ የክህደት ስሜቶች አድርጎ ነው። ከሪቻርድ ጋር የነበረንን ውይይት በጥልቀት በማስብበት ጊዜ፥ ከስሜቶቹ በስተጀርባ አድብተው የመሠጉ የሚመስሉት ሦስት ጥያቄዎች ይታዩኛል። ይበልጥ ባሰብኋቸው ቁጥር እነዚህ ጥያቄዎች በሁላችንም ውስጥ እንደሰፈሩ ይገባኛል። ዳሩ ግን እነዚህን ጥያቄዎች ጮክ ብለው የሚያሰሙ ወገኖች እምብዛም አይደሉም። ምክንያቱም የጥያቄዎቹ ድምፅ ቢሻል የትሕትና ጉድለት፥ ቢከፋ ደግሞ መናፍቅነትን የሚያሳይ ስለሚመስል ነው።

<u>እግዚአብሔር ኢ-ፍትሐዊ ነውን</u>? ሪቻርድ እግዚአብሔርን ለመከተል ቢሞክርም ሕይወቱ ፈራርሶበታል። ይህም አዋኪ ገጠመኞቹን መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያቀርባቸው የደስታና የሽልማት የተስፋ ቃሎች ጋር ለማስታረቅ ዐቀበት ሆነበት። እግዚአብሔርን ከደው ሳለ የሚበለጽጉ ሰዎችስ ጉዳይ? ይህ የዳዊትንና የኢዮብን ዘመን ያህል የቆየ ጥንታዊ ጉልጉልምታ ነው። ዛሬም የእምነት መሰናከያ ሆኖ እንደቆመ ነው።

<u>እግዚአብሔር ዝም ባይ ነው</u>? በምሕረቱ፥ በሥራውና በፍቅር ሕይወቱ ሦስት ጊዜያት አጣብቂኝ ውሳኔዎች ባፈጠጡበት ወቅት ሪቻርድ እግዚአብሔር ግልጽ አቅጣጫ እንዲያመለክተው ተማጽኗል። የእግዚአብሔርን ፈቃድ የተረዳ በመሰለው ጊዜ ሁሉ ውሳኔው ወደ ውድቀት አፋፍ መርቶታል። እናም፥ «ይኼ ምን ዓይነት አባት ነው?» ሲል ጠይቋል። «በአፍጢሜ ስደፋ እያየ በመሳቅ ይደሰትብኝ ይሆን?

እግዚአብሔር እንደሚወደኝና ለሕይወቴ ድንቅ ዕቅድ እንዳለው ተነግሮኝ ነበር። ታዲያ ለምን የዚያኑ ዕቅድ ምንነት አይነግረኝም?

<u>እግዚአብሔር ድብቅ ነው</u>? ይህ ጥያቄ ከሁሉም በላይ የሪቻርድን ልብ ሞልቶታል። የእግዚአብሔርን ሕልውና ለማረጋገጥ ለሪቻርድ የማይታለፍ ሥነ-መለኮታዊ ዳርቻ መስሎ ታየው፤ «መኖሩን እንኳ ከማላውቀው አካል ጋር እንዴት ግንኙነት ሊኖረኝ ይችላል?» እግዚአብሔር ከሚፈልጉት ሰዎች ሳይቀር ሆን ብሎ ራሱን የሚደብቅ ይመስላል። የሪቻርድ የሌሊት ጸሎት ምላሽ ሳያስከትል ሲቀር በእግዚአብሔር ላይ ተስፋ ቆረጠ።

በደቡብ አሜሪካ የጽሑፍ ሥራዬን በማከናውንበት ጊዜ እነዚህ ሦስት ጥያቄዎች በተደጋጋሚ የማስተዋል እይታዬን ሲቦረቡሩት ኖረዋል። በፔሩ አንድ ሚሲዮናዊ አውሮፕላን አብራሪ ወደ አነስተኛ የሕንድ መንደር አመጣኝ። ከአውሮፕላኑ ከወረድን በኋላ በደኖች ውስጥ እየተጓዝን ወደ ከተማዪቱ «መጋቢ» መንገድ ደረስን። ይኸው መንገድ የዘንባባ ቅጠል ለብሰውና አጣና ተደግፈው በቆሙት አንድ ደርዘን ያህል ጎጆዎች የተከበበ የቆሻሻ ማከማቻ ነበር። እዚያ የወሰደኝ በመስፋፋት ላይ የምትገኘውን አርባ ዓመት ዕድሜ ያላትን ቤተ ክርስቲያን ሊያሳየኝ ነበር። ከዚህም በላይ ከዋናው መንገድ አጠገብ የሚገኘውን ሐውልትና የዚያችን ቤተ ክርስቲያን ምሥረታ እውን ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከተውን የአንድ ወጣት ሚሲዮናዊም ታሪክ አጫወተኝ።

የስድስት ወራት ልጅ በቅጽበታዊ ትውከትና ተቅማጥ ሲሞትበት፥ ወጣቱ ሚሲዮናዊ የሚፈነዳ መስሎ ነበር። በአካባቢው ከሚገኙ ድንጋይ ጥርብ ሠርቶ ምልክት በማበጀት ልጁን ቀበረው። ከመቃብሩ አጠገብ ዛፍ ተከለ። የቀኑ ሙቀት እጅግ መጥቆ ሰው ሁሉ ጥላ በሚሻበት ወቅት፥ ሚሲዮናዊው ወደ ወንዝ ወርዶ ለዛፉ ውኃ ያመጣለታል። ከዚያም ከመቃብሩ አጠገብ ይቆማል። በጥላነቱ መቃብሩን ከኃይለኛው የምድር ወገብ አካባቢ የፀሐይ ሙቀት የሚከላከል ይመስላል። አንዳንድ ጊዜ ያለቅሳል፤ አንዳንዴ ይጸልያል። ሌላ ጊዜ ደግሞ ዝም ብሎ እዚያው ተገትሮ መቃብሩን ይመለከታል። ሚስቱ፥ የሕንድ ቤተ ክርስቲያን ምእመናንና ሌሎችም ሚሲዮናውያን ሊያጽናኑት ሞክረው አልተሳካላቸውም።

በመጨረሻም፥ ሚስዮናዊው ራሱ ታመመ። አእምሮው ተሳከረ። የማያቋርጥ ተቅማጥ ያጣድፈው ጀመር። ወደ ሊማ በአውሮፕላን ቢወሰድም፥ ዶክተሮቹ የአሜባ ወይም ሌላ የትሮፒካል ተሐዋሲያን ምልክት አላገኙም። የሞከሩት መድኃኒት ሁሉ አልጠቀመውም። ችግሩ

«ከመጠን ያለፈ ተቅማጥ» እንደሆነ በመግለጽ፥ እርሱንና ባለቤቱን ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ላኩዋቸው።

የሕንድ ሴቶች የውኃ ማድጋዎቻቸውን ለማስቀመጥ ከሚጠቀሙበት እየፈረሰ ያለ ድንጋይ አጠገብ ስቆም፥ ራሴን በዚያ ወጣት ሚሲዮናዊ ስፍራ ለማስቀመጥ ሞከርሁ። በቀትር ፀሐይ እዚያ ቆሞ ምን ብሎ እንደጸለየ አስብ ጀመር። የሪቻርድም ሦስቱ ጥያቄዎች አእምሮዬን ከመጫር አልቦዘኑም። አስጎብኚዬ ወጣት በፍትሕ-አልባነት ጉዳይ እንደተሠቃየ ገልጾልኝ ነበር። ሕፃን ልጁ ምንም አላጠፋም ነበር። ሚስዮናዊው ቤተሰቡን ወደዚህ ጫካ ያመጣቸው እግዚአብሔርን ለማገልገል ነበር። ሽልማቱ ይኼ ነው? በተጨማሪም አንድ የእግዚአብሔር ሕልውና ምልክት፥ ቢያንስ የመጽናኛ ቃል እንዲመጣለት ፈልጎ ነበር። ዳሩ ግን ምንም አላገኘም። የእግዚአብሔርን ኃዘኔታ እንዳላመነ ሁሉ፥ ሚሲዮናዊው በገዛ ሰውነቱ የኃዘንን ሥቃይ የሚመስል ነገር መቀበሉን ቀጠለ።

እውነተኛ ከሃዲያን (ኤቲስቶች) ከእግዚአብሔር ጋር ቅይማት ይፈጥራሉ ብዬ አላስብም። ከእግዚአብሔር የሚጠብቁትም ሆነ የሚቀበሉት የላቸውም። ዳሩ ግን ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር የሚሰጡ ሰዎች በምላሹ ከእግዚአብሔር አንድ ነገር መጠበቃቸው ተፈጥሮአዊ ነው። እንዲህ ከእግዚአብሔር መጠበቁ ስሕተት ይሆን?

♥

ወዳጄን ሪቻርድን ለረዥም ጊዜ አላየሁትም ነበር። በመደበኛነት ብጸልይለትም፥ እርሱን ለማግኘት መጸለዬ ፍሬ አላመጣም። የስልክ መስመሩ የተቋረጠ ሲሆን፥ ከዚያ አካባቢ እንደ ለቀቀ ሰምቻለሁ። የኋላ ኋላ መጽሐፉን ያሳተመው ድርጅት አንድ ቅጂ የላከልኝ ሲሆን፥ በእምነት ጉዳዮች ላይ ፈጥኖ የመጻፉን አደጋ ለማስጠንቀቅ ከመደርደሪያዬ ላይ ተጎብሯል።

ከዚያም ከሦስት ዓመት በኋላ ሪቻርድን ድንገት በሺካጎ ከተማ አገኘሁት። ሁኔታው ደህና ይመስላል፤ ትንሽ ክብደት የጨመረ ሲሆን፥ ጸጉሩ ከበፊቱ በመጠኑ አድጓል። ከገጽታው ላይ ይታይ የነበረው ትርምስ የረገበ ይመስላል። እኔን በማግኘቱ የተደሰተ መሰለ። እናም የምሳ ቀጠሮ ያዝን።

«ባለፈው ጊዜ ስንገናኝ በደንብ ያስተናገድሁህ አልመሰለኝም» አለኝ ከጥቂት ቀናት በኋላ በሜክሲኮ ምግብ ቤት ስንገናኛኝ ፈገግታ ፊቱን ሞልቶት። «አሁን ሕይወት ደህና አድርጋ እያስተናገደችኝ

ነው።» ጥሩ ሥራ ያገኘ ሲሆን፥ የከዳችውንም ልጅ ጉዳይ ረስቶታል። ብዙም ሳንቆይ ስለ እግዚአብሔር አነሣን። አሁንም ሪቻርድ ገና ሙሉ ለሙሉ እንዳላገገመ ተከሰተልኝ። ምንም እንኳ ቁስሉ በወፍራም የሞኝነት ፋሻ ቢጋረድም፥ እንደ ሁሌው በእግዚአብሔር ላይ መቆጣቱ ግልጽ ነበር።

አስተናጋጇ ትኩስ ቡና አቀረበችለትና ሪቻርድ በሁለት እጆቹ ሲኒውን ሸፍኖ እንፋሎት የሚረጨውን ጥቁር ቡና ተመለከተው። «አሁን ስለዚያ የዕብደት ጊዜ አንድ ዓይነት አመለካከት አለኝ። ቢያንስ የተበላሸው ነገር ምን እንደሆነ ተረድቻለሁ። እግዚአብሔርን መጠራጠር የጀመርሁበትን ትክክለኛ ሰዓትና ደቂቃ ልነግርህ እችላለሁ። ይህ የሆነው በዊተን ኮሌጅ ወይም በመኝታ ክፍሌ ውስጥ ስጸልይ ባደርሁበት ሌሊት አልነበረም።» ከዚያም ቀደም ሲል በክርስትና ሕይወቱ ስለተከሰተው ገጠመኝ ያወጋኝ ጀመር።

«ከመጀመሪያው ጀምሮ አንድ ነገር ያጓጓኝ ነበር፤ የእምነት አሳብ። የትኛውንም እውነተኛ ጥያቄ ሊውጥ እንደሚችል ጥቁር ጉድጓድ ይመስለኝ ነበር። የኢንተርቫርሲቲን (ክርስቲያናዊ ድርጅት) መሪ ስለ ሥቃይ ስጠይቀው ስለ እምነት አንዳንድ ነገሮችን ይናገራል። «የምትወደው መስሎ ቢሰማህም ባይሰማህም እግዚአብሔርን እመን። ስሜቱ በኋላ ይከተላል።» ስሜቱን የተላበስሁት መስዬ ለመታየት ሞክርሁ። ዳሩ ግን አሁን እንደማየው ስሜቱ አልተከተለም ነበር። ዝም ብዬ በእንቅስቃሴ ውስጥ እያለፉሁ ነበርሁ።

«ከዚያ በፊት እንኳ የእምነት መተኪያ ይሆነኝ ዘንድ ስለ እግዚአብሔር ጠንካራ መረጃ ስፈልግ ኖሬአለሁ። አንድ ቀን በቴሌቪዥን መስታዋት ላይ አገኘሁት ። በዘፈቀደ የቴሌቪዥን ጣቢያ እያፈላለግሁ ሳለ፥ ካትሪን ኩልማን የምታካሄደውን ጀማ የፈውስ አገልግሎት አገኘሁ። የተለያዩ ሰዎችን ወደ መድረኩ እያመጣች ቃለ-ምልልስ ስታደርግላቸው ለጥቂት ደቂቃዎች ተመለከትሁ። እያንዳንዳቸው ስለ ልዕለ -ተፈጥሮአዊ ፈውስ አስገራሚ ታሪክ ይናገሩ ነበር። ካንሰር፥ የልብ ሕመም፥ ሽባነት. . . ነገሩ የሕክምና ኢንሳይክሎፒዲያ ይመስል ነበር።

«የኩልማንን ፕሮግራም እየተመለከትሁ ሳለ ጥርጣሬዬ ቀስ በቀስ ቀልጦ ተሰወረ። በመጨረሻው አንድ እውነተኛና ተጨባጭ ነገር አገኘሁ አልሁ። ኩልማን የመሣሪያ ተጨዋቹን የምትወደውን መዝሙር እንዲጫወትላት ጠየቀችው፤ መዝሙሩ «ዳሰኛል» የሚል ነበር። የሚያስፈልገኝስ ይኸው አይደል? አልሁ፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ

ግላዊ ዳሰሳ ማግኘት። ካትሪን ይህንኑ የተስፋ ቃል ሰጠች፤ እኔም ወደዚያው አዘመምሁ።

«ከሦስት ሳምንታት በኋላ ካትሪን ኩልማን በአቅራቢያችን ወደሚገኝ አስቴት ስትመጣ ክፍል ዘግቼ ከስብሰባዎቹ በአንደኛው ላይ ለመገኘት ግማሽ ቀን ተጓዝሁ። በለስላሳ የኦርጋን ሙዚቃ የታጀበው የጉባኤው ድባብ ልብ ያሰምጣል። ሰዎች ድምፃቸውን አጉልተው ይጸልያሉ። አንዳንዶቹ በልሳን። በየደቂቃው አንድ ሰው ብድግ ብሎ «ተፈውሻለሁ» ሲል የሚከተለውን አስደሳች ትዕይንት በተለይም አንድ ሰውዬ ትኩረቴን ሳበው፤ በቃሬዛ ተሸክመው ነበር ያስገቡት። ተፈውሶ ከመድረኩ ላይ ሲረግመድ ሁላችንም ራሳችንን መቆጣጠር ተስኖን ፎህን። ሰውዬው ሐኪም መሆኑን ሲናገር ይበልጥ ተደነቅሁ። የማይድን የሳንባ ካንሰር እንደነበረበት ስድስት ወራት ብቻ እንደቀሩት ሐኪሞች መናገራቸውን አስረዳ። አሁን ግን ለመጀመሪያ ጊዜ ቆሞ ለመሄድ መቻሉ ነበር። ከፍተኛ ደስታ ተሰማው። እግዚአብሔር ይመስገን!

«የሰውዬውን ስም ጻፍሁና እየተንሳፈፍሁ ከስብሰባው ወጥቼ ሄድሁ። ከዚህ በፊት እንዲህ ዓይነት የእምነት ማረጋገጫ አግኝቼ አላውቅም ነበር። ፍለጋዬ አከተመ። በነዚያ ከመድረኩ ላይ በወጡት ሰሞች ላይ የሕያውን አምላክ ማረጋገጫ ተመልክቻለሁ። በነዚያ ሰዎች ሕይወት ተጨባጭ ተአምራት ለመሥራት ከቻለ፤ ለእኔም ያለ ጥርጥር አንድ ግሩም ነገር አለው ብዬ አሰብሁ።

«በዚያን ጊዜ ከስብሰባው ላይ ካየሁት የእምነት ጀግና ጋር ለመገናኘት ፈለግሁና ከአንድ ሳምንት በኋላ ወደ መረጃ ክፍል ደውዬ የሐኪሙን አድራሻ አገኘሁ። ስደውል አንዲት ሴት ስልኩን አነሣች። «እባክዎ፥ ከዶክተር. . . ጋር ለመነጋገር ነበር» አልኋት።

«ረዥም ጸጥታ ነገሠ። በመጨረሻም፥ «እርስዋም ማን ልበል?» አለችኝ። የበሽተኞችን ጥሪ ወይም ሌላ ነገር የምታጣራ መሰለኝና ስሜን ነገርኋት። ከዚያም ዶክተሩን እንደማደንቃቸውና ከካትሪን ኩልማን የፈውስ ስብሰባ ዕለት ጀምሮ ላነጋግራቸው ስሻ መቆየቴን ገለጽሁላት። ታሪኩ በጣም ነበር ያስደነቀኝ አልኋት።

«ሌላ ግዙፍ ጸጥታ። ከዚያም እያንዳንዱን ቃል እየነጣጠለች። በሚሰባበር ድምፅ፥ «ባለቤቴ. . . ሞቷል. . .» አለችኝ። ይህችኑ አንዲት ዓረፍተ ነገር ተናግራ ስልኩን ዘጋችው።

«ያ ምን ያህል እንደጎዳኝ ልነግርህ አልችልም። ባከንሁ። እየተንገዳገድሁ እጎቴ ተቀምጣ ወዳለችበት ወደ ቀጣዩ ክፍል ገባሁ። ‹ሪቻርድ፥ ምን ሆነሃል?› ስትል ጠየቀችኝ። ‹በደህና ነው?› »

«ደህና አልነበርሁም። ይሁንና፥ ስለዚያ ልነግራት አልችልም ነበር። እያነባሁ ነበር። እጎቴና እናቴ ማብራሪያ እንድሰጣቸው ጎተጎቱኝ ግን ምን ልላቸው እችላለሁ? ሕይወቴን የሰጠሁት እርግጠኛነት በዚያች የስልክ ቃለ-ምልልስ መከኗል። ለአንድ ግሩም ሳምንት ሲያበራ የሰነበተው የእሳተ ነበልባል እንደ ሟች ኮከብ ተሰወረብኝ።»

ሪቻርድ ከቡና ሲኒው ላይ አፈጠጠ። በመሣሪያ የተቀነባበረው ሙዚቃ ከጆሮአችን ከፍ ብሎ ያቃጭላል። «ነገሩ አልገባኝም። ይህ የሆነው ወደ ዊተን ኮሌጅ ገብተህ በዲግሪ ከመመረቅህና መጽሐፍ ከመጻፍህ በፊት ነበር?» አልሁት።

«ልክ ነህ። ሁሉም ነገር የተጀመረው ግን ያኔ ድሮ ነበር» ሲል አቋረጠኝ። «ከዚያ በኋላ የተከተለው ነገር ሁሉ፥ ማለት የዊተን ኮሌጅ፥ በኢዮብ ላይ የተጻፈው መጽሐፍ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች ሁሉ ከዚያች የስልክ ንግግር ልማር የሚገባኝን ሐቅ ፉርሽ ለማድረግ የተደረጉ ጥረቶች ናቸው። ሰማይ ላይ ማንም የለም፥» አለኝ። ምናልባትም በሆነ አጋጣሚ አምላክ ካለ ከእኛ ጋር የአሻንጉሊት ጨዋታ ገጥሞአል ማለት ነው። ለምን ጨዋታውን ትቶ ራሱን አይገልጥልንም?»

♥

ሪቻርድ ወዲያው የውይይታችንን ርእስ ስለቀየረው ቀሪውን የምሳ ሰዓት ስላለፉት ሦስት ዓመታት እያነሣን ስናወጋ ቆየን። ሦስቱን ዓመታት በደስታ እንዳሳለፈ ሲነግረኝ ዋለ። ተቃውሞው የጸና ቢሆንም፥ እውነትም የተረጋጋ ይመስላል። በመጨረሻም፥ ከምሳ በኋላ የቀረበልንን አይስክሪም እያጣጣምን ሳለ ከሦስት ዓመታት በፊት ስለነበረን የፍጻሜ ስብሰባችን አነሣልኝ። «ከዚያ በፊት ተገናኝተን ሳናውቅ በድንገት ተገኝቼ የሕይወት ታሪኬን ስዘከዝክልህ ግማሽ እብድ እንደሆንሁ ሳትገምት አልቀረህም፥» አለኝ።

«በፍጹም» ስል መለስሁለት። «የሚገርመው ያንን ጊዜ ፍጹም ከአእምሮዬ ላወጣው አልቻልሁም። በመሠረቱ የአንተ በእግዚአብሔር ላይ ማጉተምተም የራሴን በተሻለ ሁኔታ እንድረዳው አድርጎኛል» ስል ገለጽሁለት።

ከዚያም ለሪቻርድ ስለ ሦስቱ ጥያቄዎች አስረዳሁት። ከዚያም፥ እነዚህ ጥያቄዎች በእግዚአብሔር ላይ የነበረውን ማጉረምረም ያጠቃልሉለት እንደሆነ ጠየቅሁት።

«እህ. . . የእኔ ጥርጣሬ የስሜት ዓይነት ነው። የተታለልሁ መስሎ ይሰማኛል። እግዚአብሔር እኔ ስወድቅ ለማየት ሲል ያታለለኝ ይመስለኛል። ግን ደግሞ ልክ ነህ። እነዚያ ጥያቄዎች ከስሜት በስተጀርባ ቆመው ነበር። አለጥርጥር እግዚአብሔር ፍትሕ አልባ ነበር። ሁልጊዜም ድብቅና ዝምተኛ ይመስል ነበር። አዎ፥ ልክ ነው። በትክክል እንደዚያ ነው!።» አለኝ።

«እግዚአብሔር ለምን እነዚያን ጥያቄዎች አይመልስም?» ሪቻርድ ድምፁን አጉልቶና እጁን አንሥቶ እንደ ፖለቲከኛ ተናገረ–እንደ ወንጌላዊ። ደግነቱ ከምግብ ቤቱ ውስጥ የነበሩት ተመጋቢዎች ወጥተው ሄደው ነበር። «እግዚአብሔር እነዚህን ጥያቄዎች ቢመልስ፥ አንዱን ጥያቄ ብቻ ቢመልስ እንበልና፥ ሰዎች ሁሉ ይሰሙ ዘንድ አንድ ጊዜ ብቻ ቢናገር አምነው ነበር። ምናልባትም ዓለሙ ሁሉ ያምነው ነበር። ለምን አያደርገውም?»

ምዕራፍ 4

. . . ቢሆን

ሪቻርድ እግዚአብሔር እነዚህን ሦስት ችግሮች ብቻ ቢያቃልል እምነቱ እንደ ጥቅምት አበባ ፍንትው ብሎ እንደሚያብብ ተናግሯል። አያብብም?

በዚያው ዓመት ከሪቻርድ ጋር ሜክሲኮ ምግብ ቤት በተገናኘንበት ጊዜ የዘጻአትንና የዘኍልቁን መጻሕፍት ሳጠና ነበር። ምንም እንኳ አሁንም የሪቻርድ ጥያቄዎች በጭንቅላቴ ውስጥ ተኮፍሰው ቢኖሩም፥ ከእርሱ ሁኔታ ጋር የሚመሳሰለውን አሳብ ለማየት ጊዜ ወስዶብኛል። አንድ ቀን ግን በቅጽበት ልረዳው ቻልሁ፤ ሪቻርድ የፈለገው ዓለም አስከ ነፍሱ በዘጻአት ውስጥ ተገልጾአል። እግዚአብሔር በየቀኑ ማለት ይቻላል ወደ ሰዎች ታሪክ ጠልቆ ሲገባ ይታያል። በከፍተኛ ፍትሐዊነት ከመሥራቱም በላይ ሰዎች ሁሉ ይሰሙት ዘንድ ይናገራል። እነሆ፥ ራሱን ለብዙዎች ያሳየበትም ጊዜ ነበር።

በእስራኤላውያንና በእኛው ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን መካከል ያለው ንጽጽር እግዚአብሔር ዓለምን እንዴት እንደሚያስተዳድራት እንዳስብ አደረገኝ። እናም ወደ ሦስቱ ጥያቄዎች ተመለስሁ። እግዚአብሔር በፍትሐዊነት ተግባሩን ለማከናወን፥ በጉልህ ድምፁን ለማሰማትና የሰዎችን ሁሉ ዓይን ሊያጠግብ በሚችል መልኩ ለመታየት ከቻለ፥ ለምን ይሆን ዛሬ በታሪክ ውስጥ ገብቶ ለመዋኘት የማይሻው? ምናልባት የእስራኤላውያን የበረሃ ጉዞ ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ፍንጭ ይሰጠን ይሆናል።

ጥያቄ፦ እግዚአብሔር ሉዲልዎሊዊ ነውን? ለምን ክፉዎችን በመቅጣትና ደጎችን በመሸለም ተከታታይ ተግባር አይከውንም? ያለምንም ልዩነት በደጎችና በክፉዎች ላይ የክፋት በትር እኩል የሚወድቀው ለምንድን ነው?

ዓለም የተዋቀረችው ክፉ ባደረግነ ጊዜ የሥቃይ፥ በጎ በሠራን ጊዜ ደግሞ የደስታ ገጠመኝ በሚያስከትል መልኩ ነው እንበል። የትኛውም የጥፋት ተግባር የመብረቅ አደጋ የሚያስከትልበትንና የሐዋርያትን የእምነት መግለጫ መድገም ለአእምሮአችን የደስታ ስሜት የሚፈጥርበትን ዓለም አስቡ።

ብሉይ ኪዳን እንዲህ ዓይነት «የባሕርይ ማረሚያ» ለእስራኤላውያን መደረጉን በግልጽ ያስረዳል። ይህም እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የገባው ቃል ኪዳን ነው። በሲና ተራራ እግዚአብሔር ሕዝቡን

በፍትሐዊ ጥብቅ ሕግ ለመሸለምና ለመቅጣት ወሰነ። እስራኤላውያን የሰጣቸውን ሕግጋት ብቻ እንዲጠብቁ በማዘዝ በገዛ እጁ የዋስትና ፊርማ አኖረ። ከዚያም ሙሴ የዋስትናውን ሰነድ ለሕዝቡ እንዲተነትን አደረገ።

የመታዘዝ ውጤቶች	ያለመታዘዝ ውጤቶች
ከተማውና ገጠሩ ሁሉ ይበለጽጋሉ	ከፋት፥ ወንጀልና ድህነት ይበረክታሉ
ወንዶችና ሴቶችም ሆኑ እንስሳት አይመክኑም	ሰዎችና እንስሳት ይመክናሉ
የእርሻ ስኬት	እህል አይኖርም፤ አንበጣዎችና ትላትሎች ይነሣሉ
አስተማማኝ የአየር ንብረት	የአየር መዛባትና ድርቅ
የጦርነት ድል	በሌሎች አገሮች መገዛት
በሽታን የመከላከል ብቃት	ትኩሳትና የቆዳ እብጠት፤ እብደት፥ ዕውርነትና የአእምሮ መታወክ

ከታዘዙት እግዚአብሔር በምድር ከሚገኙ አገሮች ሁሉ በላይ ከፍ እንደሚያደርጋቸው ሙሴ ገለጸላቸው። ሁልጊዜም ራስ እንጂ ጅራት አይሆኑም ነበር። እስራኤላውያን ከየትኛውም የሰው ልጅ ሥቃይና ቅይማት እንደሚጠበቁ የተስፋ ቃል ተገባላቸው። በሌላ በኩል፥ ሳይታዘዙ ቢቀሩ፥ እግዚአብሔር በሚሰዳቸው አገሮች ሁሉ ለመሳለቂያና ለጥፋት ይሆናሉ. . . ምክንያቱም በብልጽግናቸው ጊዜ እግዚአብሔር አምላካቸውን በደስታ አላገለገሉትምና። ስለሆነም፥ በረሃብና በጥም፥ በራቁትነትና በድህነት እግዚአብሔር የሚያመጣባቸውን ጠላት ያገለግላሉ።

ይህንኑ በሽልማትና ቅጣት ላይ የተመሠረተውን «ፍትሐዊ» መዋቅር ለመመልከት የኢያሱንና የመሳፍንትን መጻሕፍት ጭምር አነበብሁ። በሃምሳ ዓመታት ውስጥ እስራኤላውያን ለሥርዓት አልበኝነት ተጋልጠዋል። የሚበዛው የብሉይ ኪዳን ክፍል የሚተነትነው የተተነበየው በረከት ሳይሆን ርግማን ተግባራዊ መሆኑን ነው። ከዚያ ሁሉ ማለፊያ የቃል ኪዳን ጥቅሞች ባሻገር፥ እስራኤል የእግዚአብሔርን መመዘኛ ሳታሟላ ቀረች።

ከዓመታት በኋላ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ወደ ኋላ ተመልሰው ሲመለከቱ፥ የቃል ኪዳኑ አሠራር እግዚአብሔር በፍጹማዊ ቀጣይነትና ፍትሐዊነት ከሕዝቡ ጋር ግንኙነት ያደረገበት ምሳሌያዊ ሞዴል አድርገው አልተከተሉትምና ይልቁንም፥ ብሉይ ኪዳን ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር የገቡትን ውል ለመጠበቅ እንዳልቻሉ የሚያሳይ የማስተማሪያ መሣሪያ እንደሆነ ገልጸዋል። በይቅርታ ጸጋ ላይ የተመሠረተ አዲስ ኪዳን አስፈላጊ መሆኑን በትክክል ተረድተዋል። ለዚህም ነው አዲስ ኪዳን የተሰጠን።

ጥያቄ፦ እግዚአብሔር አይናገርም? ፈቃዱን ስለ መፈጸማችን የሚገደው ከሆነ፥ ያንኑ ፈቃዱን ለምን ይበልጥ በግልጽ አያሳየንም?

ዛሬ የተለያዩ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚሰሙ ይናገራሉ። ከነዚህ ሰዎች አንዳንዶቹ «በእግዚአብሔር ታዝዣለሁ» ብሎ የሚካኤል አንጀሎን ምርጥ የጥበብ ሥራ (ማርያም በመቃብር ቤት ለጌታ ስታለቅስ የሚያሳየውን) በመዶሻ እንደበረቃቀሰው ወይም በፕሬዘዳንቱ ላይ እንዲተኩስ እግዚአብሔር እንደተናገረው የገለጸውን ፖለቲካዊ ግድያ ፈጻሚ ዓይነት እብዶች ናቸው። ሌሎች ደግሞ እውነተኞች ቢመስሉም አቅጣጫቸውን የሳቱ ናቸው። እነዚህም ደራሲዋን ጆኒ ኤረክሰንን ለማግባት እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው የተናገሩትን ስድስት ሰዎች ዓይነት ናቸው። አሁንም ሌሎች የእግዚአብሔርን ቃል ለሕዝቡ በማስተላለፍ በእውነተኛ የነቢያትና የሐዋርያት ትውፊት የተካኑ ይመስላሉ። ታዲያ የምንሰማው ነገር በትክክል ከእግዚአብሔር ዘንድ መምጣቱን እንዴት እናውቃለን?

እስራኤላውያን በሲና ምድረ በዳ መሽገው ሳለ እግዚአብሔር የምሪትን ጉዳይ ቀለል ባለ መንገድ አቅርቦላቸዋል። <u>*ድንኳናችንን ጠቅልለን እንነሣ ወይስ እዚሁ እንቀመጥ*</u>? ጠያቂው እስራኤላዊ የዚህን ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት የሚጠበቅበት ነገር ቢኖር ከመገናኛው ድንኳን ላይ ያለውን ደመና መመልከት ብቻ ነው። ደመናው ከተንቀሳቀሰ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዲንቀሳቀስ ፈልጎአል ማለት ነው። እዚያ ተቀምጦ ከቀረ ሕዝቡ እንዲቆይ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑ ይታወቃል። (በጊዜ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ይቻል ነበር፤ ማታ ደመናው እንደ እሳት ግንብ ያብረቀርቃል።)

በተጨማሪም፥ እግዚአብሔር ፈቃዱን በቀጥታ ለማስተላለፍ እንደ ዕጣ መጣልና ኡሪምና ቱሚም ዓይነቶችንም መንገዶች አዘጋጅቷል። ይሁንና፥ አብዛኛዎቹ ነገሮች አስቀድመው የተወሰኑ ነበሩ። እግዚአብሔር በደንቦች አማካኝነት ፈቃዱን ተናግሮአል። እነዚህም ከግድያ እስከ የፍየልን ወጠጤ በእናቱ ወተት መቀቀል ያሉትን

የባሕርይ አካላት የሚያካትቱ 613 ሕግጋት የሚገኙበት ነበሩ። በዚያን ዘመን ሰዎች እምብዛም የእግዚአብሔር ምሪት ግልጽ አልሆነልንም ብለው አያማርሩም ነበር።

ለመሆኑ ከእግዚአብሔር ግልጽ ትእዛዝ መቀበላቸው ታዛዥነታቸውን ጨምሮት ይሆን? ያልጨመረው ይመስላል። እግዚአብሔር «ከአሞራውያን ጋር ለመዋጋት አትውጡ፤ እኔ ከእናንተ ጋር አልወጣም። ጠላቶቻችሁ ያሸንፉአችኋል» አለ። እስራኤላውያን ግን በቀጥታ ወደ ጠላቶቻቸው ተጉዘው ውጊያ ገጠሙ። እናም ተሸነፉ። አርፋችሁ ተቀመጡ ሲባሉ ገሥግሠው ይወጣሉ፤ ፈጥነው እንዲሄዱ ሲነገራቸው በፍርሃት ይሸሻሉ፤ በሰላም እንዲኖሩ ሲታዘዙ ጦርነት ያውጃሉ፤ ጦርነት አውጁ የተባሉ እንደሆነ ለሰላም ይሮጣሉ። 613ቱን ትእዛዛት ለማፈራረስ ሲሉ ብሔራዊ በዓላት ማዋቀር ያዙ። ግልጽ ያልሆነ ምሪት ለእኛው ትውልድ የሆነውን ያህል፥ ለእነርሱም በትክክል የተላለፈው ምሪት ከብራቸውን የሚነካ ስድብ ሆኖ ተቀየረ።

ከዚህም በላይ በብሉይ ኪዳን ታሪኮች ውስጥ ፈቃዱ የሚገለጽበትን የአነጋገር ዘይቤ አስተውያለሁ፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ ግልጽነት የእስራኤላውያንን የእምነት ዕድገት የማቀብ ውጤት ነበረው። ራሱን በሚገባ ከገለጸላቸው ዘንዳ ለምን የሙጥኝ ይሉታል? እግዚአብሔር ለውጤቶች ዋስትና ከሰጠ ዘንዳ ለምን ሲሉ በእምነት ይወጣሉ? እግዚአብሔር ለአጣብቂኞች መፍትሔ ከላከላቸው ዘንዳ ለምን ከሚጋጩ አጣብቂኞቹ ጋር ይታገላሉ? በአጭሩ፥ እስራኤላውያን እንደ ሕፃናት መኖር ሲችሉ ለምን እንደ አዋቂዎች መኖር ያሻቸዋል? እነርሱም ይህንኑ ነበር ያደረጉት። በመሪዎቻቸው ላይ ማጉረምረም፥ የመናን ጥብቅ ትእዛዛት ማጭበርበር፥ ስለ ሁሉም የምግብና የውኃ እጥረት ማልጎምጎም ሥራቸው ሆኖ ተገኘ።

የእስራኤላውያንን ታሪክ በማጠናበት ጊዜ፥ ስለ ግልጽ ምሪት ሌላ አሳብ መጣልኝ። ይህ በቅርቡ ነፃ የተለቀቁትን ባሪያዎች ጥላቻ በነገሠበት በረሃ ውስጥ እንደማሻገር ዓይነት ዓላማ ሊኖረው ቢችልም፥ መንፈሳዊ ዕድገትን የሚያበረታታ አይመስልም። እንዲያውም፥ ለእስራኤላውያን የእምነትን አስፈላጊነት አጥፍቶባቸዋል። ግልጽ ምሪት እያንዳንዱን ምርጫ ከእምነት ይልቅ የመታዘዝ ጉዳይ በማድረግ ነጻነት አሽቀንጥሮ ጥሏል። በአርባዎቹ የመቅበዝበዝ ዓመታት ውስጥ እስራኤላውያን የመታዘዝን ፈተና ከፉኛ ስለ ወደቁ እግዚአብሔር ከአዲስ ትውልድ ጋር እንደገና ለመጀመር ተገዱል።

ጥያቄ፦ እግዚአብሔር ተደብቋል? ምን አለ አንድ ጊዜ ብቅ ብሎ ጥርጣሬያችንን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ቢያስወግድ?

የሶቭየት ጎብረቱ ጠፈርተኛ ከሕዋው ውስጥ ሆኖ በመንኮራኩሩ ቀዳዳ ሊመለከት፥ ወዳጂ ሪቻርድ ብቻውን በክፍሉ ውስጥ ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ሊሠቃይ የፈለገው የዘመናችንን ረሃብ ቀስቃሽ መሻት ነው (አሁንም ለሚራቡ ወገኖች)። ስለ እርሱ የሰማነው አምላክ የምንመለከተው አምላክ ይሆንልን ዘንድ ማረጋገጫ፥ መረጃና አካላዊ እንሻለን።

አሁን እኛ የምንራበው ነገር በአንድ ወቅት ተፈጽሞአል። በአንድ ወቅት እግዚአብሔር በአካል ተገኝቶ ከሰው ጋር ፊት ለፊት ተነጋግሯል። ከእስራኤላውያን ካምፕ ወጣ ብሎ በሚገኘው ድንኳን ውስጥ እግዚአብሔርና ሙሴ ተገናኙ። ሰብሰባው ምሥጢር አልነበረም። ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገር ወደ ድንኳኑ በሚሄድበት ጊዜ ሁሉ የካምፑ ነዋሪዎች በሙሉ ለመመልከት ይወጡ ነው። የእግዚአብሔርን ይፋዊ መገኘት ምልክት የሆነው የደመና ዓምድ የድንኳኑን መግቢያ ይዘጋዋል። ከውስጥ ምን እንደሚከሰት ከሙሴ በቀር የሚያውቅም ሆነ ለማወቅ የሚፈልግ ሰው አልነበረም። እስራኤላውያን መቆም የሚገባቸውን ርቀት ያውቁ ነበር። ለሙሴ፥ «እንዳንሞት እግዚአብሔር አይናገረን። አንተ ተናገረን፥ እንሰማለን» ይሉት ነበር። ከእያንዳንዱ ሰብሰባ በኋላ ሙሴ ከሕዋ እንደመጣ ሁሉ ፊቱ እያበራ ይወጣ ነበር። ፊቱን እስኪሸፍን ድረስ፥ ሕዝቡ ገለል ይሉለታል።

በዚያም ዘመን ከሃዲያን ቢኖሩ እንኳ ጥቂቶች መሆን አለባቸው። ማንኛውም እስራኤላዊ እግዚአብሔርን ጠብቆ ሊያገኝ አለመቻሉን አልተናገረም። ከመገናኛው ድንኳን ውጪ ወይም ከሲና ተራራ ላይ በሰፈሩት ግዙፍ የማዕበል ደመናት የእግዚአብሔርን ግልጽ ማረጋገጫ ሊመለከቱ ይችሉ ነበር። ተጠራጣሪ ሰው ቢኖር ወደሚንቀጠቀጠው ተራራ ወጥቶ ሊነካና ይህንን ከማድረጉ ከአንድ ሰኮንድ በፊት ከጥርጣሬው ሊላቀቅ ይችል ነበር።

ይሁንና፥ በዚያን ጊዜ የተከሰተው ነገር ከሞላ ጎደል እምነትን ይጥሳል። ሙሴ በእግዚአብሔር መገኘት ምልክቶች ማዕበል ከሚፈጥረው ተራራ ላይ ሲወጣ የተመለከቱ፥ የግብፅን አሥር መቅሠፍቶች ያለፉ፤ ቀይ ባሕርን በየብስ የተሻገሩ፥ ከዓለት ውስጥ የፈለቀውን ውኃ የተጎነጩ፥ በወቅቱ የመናን ተአምራት ያኘኩ፥ እነዚያው ሰዎች ተሰላችተው ወይም ትዕግሥት አጥተው ወይም ዓምፀው ወይም ቀንተው ስለ አምላካቸው ሁሉንም ነገር ዘነጉ። ሙሴ ከተራራው ሲወርድ ከወርቁ ጥጃ ፊት እንደ አረማውያን ይጨፍሩ ነበር።

እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር ድብብቆሽ አልተጫወተም። ሊጠየቅ የሚቻል የእግዚአብሔር ሕልውና ማረጋገጫ ሁሉ ነበራቸው። ዳሩ ግን በሚያስደንቅ ሁኔታ፥ እያነበብሁ እንኳ ለማመን በሚያስቸግረኝ መንገድ የእግዚአብሔር ቀጥተኛነት የተፈለገውን ውጤት ተገላቢጦሽ ያስከተለ ይመስላል። የእስራኤላውያን ምላሽ አምልኮና ፍቅር ሳይሆን፥ ፍርሃትና ግልጽ ዓመፅ ነበር። የእግዚአብሔር በግልጽ መገኘት ዘላቂ እምነትን ለማሻሻል ያበረከተው አስተዋጽኦ አልነበረም።

♥

ሪቻርድ ስለ እግዚአብሔር ያነሣውን ማልነምነም በሦስት ክፍሎች አጥርቼ ከፍያለሁ። ነገር ግን ለነዚያ ሦስት ጥያቄዎች ፈጣን ምላሾችን ማግኘቱ ከእግዚአብሔር ጋር የምንፈጥረውን ቅይማት መሠረታዊ ችግሮች ላያቃልሉ እንደሚችሉ ከዘጸአትና ዘኍልቁ ተምሬአለሁ። ምንም እንኳ እስራኤላውያን በማይደበዝዝ የእግዚአብሔር ደማቅ ብርሃን መካከል ቢኖሩም፥ በማናቸውም ዘመናት እንደነበሩት ሰዎች ወለም ዘለም ሲሉ ቆይተዋል። መንገድ በሌለበት የሲና በረሃ ለአሥር ጊዜያት በእግዚአብሔር ላይ ተቆጥተው ተነሥተዋል። ወደ ተስፋዪቱ ምድር ሊገቡ በተቃረቡ ጊዜ ከፊታቸው የነበረውን በረከት እንኳ ትተው በግብፅ ስላሳለፉዋቸው «መልካም የጥንት ጊዜያት» ያላዝኑ ነበር።

እነዚህ አሳዛኝ ውጤቶች እግዚአብሔር ዛሬ ለምን በበለጠ ቀጥተኛነት በሕይወታችን ላይ ጣልቃ እንደማይገባ ግንዛቤ ሊያስጨብጡን ይችላሉ። አንዳንድ ክርስቲያኖች በተአምራትና የእግዚአብሔርን ህልውና አጉልተው በሚያሳዩ ምልክቶች ያሸበረቀች ዓለም ለማየት ይናፍቃሉ። በቀይ ባሕር መከፈል፥ በአሥሩ መቅሠፍቶች፥ ብሎም በምድረ በዳ በየዕለቱ ይወርድ ስለነበረው መና ሰባኪው እግዚአብሔር ይህንኑ ዛሬ እንዲያደርግ የሚመኝ የሚያስመስሉትን አሳዛኝ ስብከቶችን እሰማለሁ። ዳሩ ግን የእስራኤላውያን ምሳሌነት ቆም ብለን እንድናስብ ሊያደርገን ይገባል። የተአምራት መትረፍረፍ እምነትን ያበዛልን ይሆን? ይህ እግዚአብሔር ለማየት የሚፈልገውን ዓይነት እምነት የሚያመጣልን አይመስልም። ምልክቶች የምልክት እንጂ የእግዚአብሔር ሱሰኞች እንደማያደርጉን እስራኤላውያን በግልጽ ያረጋግጡልናል።

እስራኤላውያን ከባርነት የወጡ ጥንታውያን ሕዝቦች መሆናቸው እውነት ነው። ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ይህንኑ የሚመስል

ተደጋጋሚ ድርጊት እንደፈጸሙ ያሳየናል። ፍሬድሪክ ቡችነር እንዳለው፥ እስራኤላውያን «እንደ ሌላው ሰው» ወደመሆኑ አዘነበሉ።

ከጥናቴ ስመለስ ግራሞትና ግራ መጋባት አብረውኝ ነበሩ፥ የተገረምሁት ከእግዚአብሔር ጋር እንድንቀያየም የሚያደርጉን ሦስት ዐበይት ምክንያቶች ማለትም አድልዎአዊነት፥ ዝምታና ድብቅነት ሊነሡ የሚመጣው ለውጥ አናሳ መሆኑን ስለተገነዘብሁ ነበር። የተደናገርሁት ደግሞ እግዚአብሔር በምድር ላይ በሚፈርድባቸው ጉዳዮች ላይ በሚነሡት ጥያቄዎች ነበር። እርሱ ተለውጠ ይሆን? እርሱ ወደ ኋላ ተመልሶ ይሆን?

ሪቻርድ በመጀመሪያው ዕለት ከመኖሪያ ቤቴ ተቀምጠ ታሪኩን ሲያወጋኝ ወደ ላይ እየተመለከተ በከፍተኛ ድምፅ፥ «እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ውስጥ ምን ያህል ሥቃይ እያስከተለ እንዳለ የሚያውቅ አይመስልም!» ብሎኝ ነበር። እግዚአብሔር ምን እየሠራ ነው? የሰብአዊ ቤተ ሙከራ ትርጉም ምንድን ነው? ከእኛ የሚፈልገው ምንድን ነው? እኛስ ከእርሱ ምን ልንጠብቅ እንችላለን?

በሂደቱ ውስጥ በመጠኑ ሳያጠፋኝ እግዚአብሔር ለፕርጣሬ ስፍራ በማይለቅ መልኩ ራሱን ሊገልጽልኝ የሚችለው እንዴት ነው? ለፕርጣሬ ስፍራ ከሌለ፥ ለእኔ ስፍራ የለም ማለት ነው

– ፍሬድሪክ ቡችነር

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፦ ዘዳግም 9፥ 7፥ 28፤ ሮሜ 3፤ ገላትያ 3፤ ዘጸአት 28፤ 40፤ ዘዳግም 1–2፤ ዘጸአት 19–20፥ 32–33፤ ዘዳግም 1።

ምዕራፍ 5

ምንጩ

የሪቻርድን ሦስት ጥያቄዎች በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከተመለከትሁት እውነት አንጻር ለመመርመር ስል ለሁለት ሳምንታት በኮሎራዶ ትንሽዬ ቤት ውስጥ መሸግሁ። ለጥናት ይሆነኝ ዘንድ ሻንጣ ሙሉ መጻሕፍት ይዤ መጥቼ ነበር። ይሁንና፥ እዚያ በቆየሁባቸው ጊዜያት ሁሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ በቀር ሌላ መጽሐፍ አልገለጥሁም።

የበረዶ ክምር ሲጋገር የዋለ ዕለት ከሰዓት በኋላ ከዘፍጥረት ጀመርሁ። የነበርሁበት መቼት ዘፍጥረትን ለማንበብ ፈጽሞ ተስማሚ ድባብ ፈጠረልኝ። ከአድማስ ላይ ውብ ምስል ሠርታ ልታልፍ ለምትፈጥነው ፀሐይ ደመናት ለጊዜው ስፍራ ለቀቁላት። ከበረዶው የሚነሣው ትነት የተራራውን ጫፍ አልብሶታል። ማታ ደመናውም በረዶውም እንቅስቃሴያቸውን ዳግም ጀመሩ።

መጽሐፍ ቅዱሴን ዝግ እያልሁ ከዳር እስከ ዳር አነበብሁ። ከኦሪት ዘዳግም ዘንድ ስደርስ በረዶው የታችኛውን ደረጃ ሸፍኖታል። ከነቢያት ዘንድ ስደርስ በረዶው ከፖስታ መላኪያው ሣጥኑ አካባቢ ቀርጿል። በመጨረሻም ከዮሐንስ ራእይ ላይ ስደረስ መንገዱን ይጠርግልኝ ዘንድ የበረዶ ማስወገጃ መኪና መጥራት ነበረብኝ። መጽሐፍ ቅዱሴን እያነበብሁና በጣፋጭ ነገሮች የደመቀውን አረንጓዴ መስክ በመስኮቱ በኩል እየተመለከትሁ ባሳለፍኳቸው የሁለት ሳምንታት ጊዜያት ውስጥ ከሰባ ሁለት ኢንች የሚልቅ አዲስ በረዶ ወርዷል።

ስለ እግዚአብሔር ያለን ተለምዶአዊ ግንዛቤ ምናልባትም መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል ከሚነግረን አምላክ የተለየ መሆኑ አጥብቆ ተሰማኝ። በትክክል ምን ይመስል ይሆን? በቤተ ክርስቲያንና በክርስቲያን ኮሌጅ እግዚአብሔር የማይለወጥ፥ ሁሉን ቻይነት፥ ሁሉን አዋቂነትና ስሜት-አልባነት የመሳሰሉትን ብቃቶች የያዘ የማይታይ መንፈስ እንደሆነ እንዳስብ ሆኜ ተምሬአልሁ። የእግዚአብሔርን አመለካከት እንድንገነዘብ የታሰቡት እነዚህ ዶክትሪኖች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሊኖሩ ቢችሉም፥ ጎድጉደው ተሰውረዋል።

ዝም ብዬ መጽሐፍ ቅዱሴን ሳነብ ያገኘሁት ነገር ቢኖር ውኃ - አዘል ትነት ሳይሆን እውነተኛ አካል ነበር። ይህም እንደ ማንኛውም ሰው ልዩና የደመቀ ነበር። እግዚአብሔር የጠለቁ ስሜቶች አሉት። በትንቢት መጻሕፍት ውስጥ ራሱን ምጥ ከያዛት ሴት ጋር እያነጻጸረ ሲያለቅስ እንመለከታለን፥ «እጮኻለሁ፥ አጠፋለሁ፤ በአንድነትም እጨርሳለሁ።» እግዚአብሔር በሰው ልጆች ባሕርይ ደግሞ ሲደነግጥ

እንመለከታለን። እስራኤላውያን ሕፃናትን በመሠዊያው ሲያሳልፉ በድንጋጤ የራደ ይመስላል፤ ይህ ሁሉን አዋቂው አምላክ የሚናገረው ቃል ነው፤ «እኔ አላዘዝኋቸውም፤ ወይም ስለዚህ ነገር አልተናገርሁም፤ ወደ አሳቤም አልገባም።» የኃዘን ድምፁን አጉልቶ፥ «ሌላ ምን ላደረግ እችል ኖሯል?» ሲል ይጠይቃል። ይገባኛል አምላክ በባሕርይና በስሜት የሰውን ልጅ እንደሚመስል የሚያስረዳ ቃል "Anthropomorphism" (እግዚአብሔር በሰውኛ) እነዚያን ሰብአዊ-መሰል ባሕርያት ሁሉ ማስረዳት እንዳለበት ታስቦ ነበር። ይሁንና፥ እግዚአብሔር ከሰብአዊ ልምምድ «የሚዋሳቸው» አምሳሎች ይበልጥ ወደ ላቀ እውነታ ይጠቁማሉ።

ከበጋው መጠለያዬ ሆኜ መጽሐፍ ቅዱሴን ሳነብ፥ እግዚአብሔር ምን ያህል ሰዎች በእርሱ ላይ ተጽዕኖ እንዲያደርሱ እንደፈቀደ በመገንዘብ ተደነቅሁ። እኔ ለሥቃዩም ለደስታውም ራሴን አላዘጋጀሁም ነበር። በአጭሩ፥ ለአጽናፈ-ዓለሙ አምላክ ስሜታዊ ልምምድ እንግዳ ነበርሁ «ስለ እግዚአብሔር በማጥናትና በፊደላት ቅደም-ተከተል ሊደረደሩ በሚችሉ ቃላትና ጽንሰ-አሳቦች እርሱን ዝቅ በማድረግ እግዚአብሔር ከሁሉም አብልጦ የሚሻውን የተሟሟቀ ግንኙነት አጥቼ ነበር። እንደ አብርሃም፥ ሙሴ፥ ዳዊት፥ ኢሳይያስ፥ ኤርምያስ፥ ከእግዚአብሔር ጋር የላቀ ግንኙነት የነበራቸው ሰዎች በሚያስደንቅ ቀረቤታ ነበር ያስተናገዱት። ከአጠገባቸው ካለው ወንበር ላይ የተቀመጠ ያህል ነበር ከእግዚአብሔር ጋር የሚነጋገሩት። ሰው ከአማካሪው፥ ከአለቃው፥ ከወላጁ፥ ወይም ከፍቅረኛው በሚነጋገርበት ዓይነት መንገድ።

ያ የኮሎራዶ ጉዞ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያቀያይሙንን ሦስት ጥያቄዎቻችንን በአዲስ ብርሃን ያሳየኝ ጀመር። እነዚህ በአሳብ መስክ ወይም በኮምፒዩተር ፕሮግራሚንግ ወይም በፍልስፍና የምትጋፈጣቸውና መፍትሔ ፍለጋ የምትንከራተትባቸው እንቆቅልሾች አልነበሩም። ይልቁንም እነዚህ በሰዎችና ሰዎችን ለማፍቀርና ለመፈቀር እጅግ በሚሻው አምላክ መካከል የሚገኙ የግንኙነት ችግሮች ናቸው።

በሁለት ሳምንታት ቆይታዬ ጥቂት ሰዎችን ተመልክቻለሁ። በአብዛኛው ከቤቶች ደጃፍ ከበረዶ ግድግዳ ኋላ ተቀምጬ ሳነብ ነበር። ምናልባትም ከደረስሁበት መደምደሚያ ላይ እንድደርስ የረዳኝ ይኸው ብቸኝነቴና ከሰው መነጠሌ ሳይሆን አይቀርም፥ ሁልጊዜም አንዱን ማለትም ሰብአዊውን አመለካከት ብቻ ሳጠና ኖሬአለሁ። ሰው የመሆንን አጣብቂኝ የሚያትቱ መደርደሪያ ሙሉ መጻሕፍት አሉኝ። ከነዚህም አንዳንዶቹ ተንገፍግፈዋል፤ ሌሎቹ ምጸታም፤ ሌሎች የሰቀዘ

ፍልስፍናዊ ይዘት አላቸው። ይሁንና፥ ሁሉም አንድ መሠረታዊ አመለካከት ይገልጻሉ። «ሰው መሆን ማለት እንዲህ ነው።» ከእግዚአብሔር ጋር የተቀያየሙ ሰዎችም በሰብአዊ የእይታ መነጽር ላይ ያተኩራሉ። ጥያቄዎቻችንን እየዘገንን፥ እግዚአብሔር ለምን ፍትሕ-አልበኝነትን ያስፋፋል? እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል? ለምን ይደበቃል? ስንል እግዚአብሔር ለምን ለእኔ ፍትሕ-አልባ ይሆንብኛል? ዝም የሚለኝ ለምንድን ነው? ከእኔ ለምን ይደበቃል? ማለታችን ነው።

ጥያቄዎችንና ግላዊ ቅይማቶቼን ለአፍታ ገለል አድርጌ የእግዚአብሔርን የእይታ መነጽር ላጤን ሞክሬአለሁ። ቀድሞ ነገር ከሰብአዊ ሰው ጋር ተራክቦን የሚሻው ለምንድን ነው? ከእኛ ውስጥ የሚሻውና ከዚያ መሻት ጋር የሚያጋጨው ምንድን ነው?

የእግዚአብሔርን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ እንደሚሰማ ሰው ሆኜ ወደዚያው ተመለስሁ። እዚያ እርሱ ለራሱ ይናገራል። እኔም ቀደም ሲል ብዙም ትኩረት ሰጥቼ እንዳልሰማሁት ተገነዘብሁ። በራሴ ስሜቶች ስለ ተሞላሁ የእርሱን ስሜቶች ለማጤን አልቻልሁም ነበር።

♥

ስለ እግዚአብሔር በጣም የተለየ ግንዛቤ ጨብጬ ከኮሎራዶ ተመለስሁ። ከሁለት ሳምንታት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በኋላ፥ እግዚአብሔር እርሱን የሚመረምሩት ሰዎች ጉዳይ ብዙም እንደማያሳስበው ተረዳሁ። በዋናነት ሊፈቀር ይሻል። እያንዳንዱ የቃሉ ገጽ ማለት ይቻላል ይህንኑ መልእክት በለሆሳስ ያስተጋባል። በመጨረሻም፥ የሕዝቡን ፍቅር በሚራበው አምላክና በራሳቸው በሰዎቹ መካከል የሚገኘውን ግንኙነት ማወቅ እንዳለብኝ ተገንዝቤ ወደ ቤቴ ተመለስሁ።

ከእግዚአብሔር ጋር ቅይማት የተፈጠረባቸው ስሜቶች ሁሉ ግንኙነት ከተቋረጠበት ጊዜ ይነሣሉ። ስለሆነም፥ ከዚህ በፊት ጠይቄ ለማላውቀው ጥያቄ ምላሽ ወሰንሁ፤ አምላክ መሆን ምን ይመስላል?

ብዙ ሰዎች እግዚአብሔርን የሚፈሩትና ዳሩ ግን በልባቸው የሚጠሉት ልቡን ስለሚጠረጥሩና እንደ ሰዓት ያለ አእምሮ አድርገው ስለሚያስቡት ነው።

ሄርማን ሜልቫይል

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፡- ኢሳይያስ 42፤ ኤርምያስ 19:9።

ክፍል ሁለት
ተራክቦ፡–አብ
ምዕራፍ 6
ኪሳራ

አምላክነት ምን እንደሚመስል ለመረዳት ልንጀምር የምንችልበት አንድ ስፍራ ብቻ አለ፤ የፍጥረት ወቅት። አእምሮአችን በምዕራፍ 3 ወደሚገኘው ታላቅ የውድቀት ታሪክ ወይም በዘፍጥረት ውስጥ ከግልጋሎት ላይ ስለዋለው ሂደት ወደሚነሡ ሙግቶች ስለሚቸኩል፥ ብዙውን ጊዜ ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 እንደ መግቢያ በጥድፊያ ይነበባል። ነገር ግን ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ስለዚያ ሂደትም ሆነ ስለ ቀጣዩ አሳዛኝ ክስተት የሚለው የለውም። ይልቁንም ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 የዓለማችንን እጅግ ግልጽ የሆነ ንድፍ ያስቀምጣል። ፀሐይና ከዋክብት፥ ውቅያኖሶችና ተክሎች ዓሣዎችና እንስሳት፥ ወንድና ሴት። ይህም ከእያንዳንዱ አዲስ ፍጥረት በኋላ የእግዚአብሔርን አስተያየት ያካተተ ነበር።

«እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ።» ይኸው ቃል አምስት ጊዜያት እንደ ከበሮ ምት ያስተጋባል። በመጨረሻም፥ «እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፤ እነሆም፥ እጅግ መልካም ነበረ።» ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይህንኑ ጊዜ እጅግ በላቀ ሁኔታ ይገልጻሉ። «አጥቢያ ኮከቦች በአንድነት ሲዘምሩ፥ የእግዚአብሔር ልጆች [መላእክት] ሁሉ እልል ሲሉ. . .» እያለ እግዚአብሔር በኩራት ለኢዮብ ይገልጽለታል። መጽሐፈ ምሳሌ በከፍተኛ ድባብ እንዲህ ሲል ይገልጻል፤ «የዚያን ጊዜ እኔ በእርሱ ዘንድ ዋና ሠራተኛ ነበርሁ፤ ዕለት ዕለት ደስ አሰኘው ነበርሁ፤ በፊቱም ሁልጊዜ ደስ ይለኝ ነበርሁ። ደስታየም በምድሩ ተድላየም በሰው ልጆች ነበረ።»

ይህ ፍጥረት ለእግዚአብሔር እንዴት ዓይነት ስሜት እንደነበረው ያሳያል፤ ከዚያን ጊዜ አንሥቶ የጥበብ ሰው [አርቲስት] ሁሉ የዚያን ፍጥረት ማሚቶ፥ እይታዊ ውዝዋዜ ስሜት እየተቋደሰ ይገኛል፤ ከፍጻሜው የደረሰውን ሥራ ተመልከቶ «በጣም ግሩም» እንደሆነ የሚናገር አንጥረኛ፥ አድማጩ በአድናቆት ሲሞላ አይቶ ፈገግታውን ሊገታ ያልቻለ ተዋናይ፥ ብሎም በምትበላው ከረሜላ የምትፈነጭ ሕፃን ልጅ ሊጠቀሱ ይችላሉ።

አንትሮፖሎጂስትና የወግ ጽሑፍ አዘጋጅ የነበረው ሎረን አስሊ በመጀመሪያው ፍጥረት ሐሜት ስላደረገበት ዕለት ይናገራል።

በሽምግልናው ዘመን ሰው በሌለበት የባሕር ዳርቻ አካባቢ ሲዟዟር ከተሰበረ ጀልባ ሥር በውኃ የረጠበ መጠለያ አግኝቶ ተኛበት።

ከእንቅልፉ ነቅቶ ዓይኖቹን ሲገልጥ ሁለት ትናንሽ ጆሮዎችና ጉጉት የሚስተዋልበት ፊት ያለው ትንሽ ቀበሮ ታየው። በጣም ትንሽ በመሆኑ ፍርሃትን ገና አላወቀም ነበር። እዚያው ከጀልባዪቱ ጥላ ውስጥ ታዋቂው የተፈጥሮ አሳሽና የቀበሮ ቡችላ ተፋጠጡ። ከዚያም ትንሹ ቀበሮ የፈገግታ ጨረር እየረጨ ከተከማቸው አጥንት አንዲት የዶሮ አጥንት መዝዞ በማውጣት ጥርሱን ያሠራው ጀመር። ከመቅጽበት ኢስሊ ጎንበስ ብሎ ሌላውን ጫፍ ሲነካ ጨዋታው ተጀመረ።

ሎረን ኢስሊ እንዲህ ይላል፤ «አንድ ሰው ከአጽናፈ ዓለሙ አካባቢ ሊቀርብ እንደማይችል ተደጋግሞ ሲነገር ቆይቷል። ሰው የተፈጥሮን ሩቅ ገጽታ ብቻ እንዲገነዘብ ተወስኗል። እዚህ ግን በአጥንቶች መሀል ግዙፍ ዓይኖች ያሉት ንጹሕ ቀበሮ ከእርሱ ጋር እንድጫወት እየጋበዘኝ ነበር። አጽናፈ-ዓለሙ ገጽታውን ለማሳየት በአንዳች ግሩም ፉሽን እየተዟዟረ ነው። ገጽታው በጣም ትንሽ በመሆኑ አጽናፈ-ዓለሙ ራሱ ይስቃል። ይህ ለሰብአዊ ክብር ጊዜው አይደለም።

«ለአንድ አፍታ ከቀበሮ ዋሻ ውስጥ በጀርባዬ ተንጋልዬ የዶሮ አጥንት እየተሻማሁ አጽናፈ-ዓለሙን ልጨብጥ ችያለሁ።» በኋላም፥ «ይህ ለመቼውም ላከናውነው የምችለው ከሁሉም የላቀ ተግባር ነበር» ሲል ተናግሯል። ይህም በመጨረሻው ለነገሮች ሁሉ በሚጀምርበት መልኩ የአጽናፈ-ዓለሙ ጨረፍታ ለማየት ስለቻለ ነበር። «እንደ እውነቱ ከሆነ፥ ይህ ትንሽና የሚያስቅ የሕፃን ልጅ አጽናፈ-ዓለም ነው።»[1]

ከአጽናፈ-ዓለማችን ባዶነትና ሥቃይ ባሻገር፥ ከዚያ የዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ጅማሬ አንድ ነገር ጥንቱ ሽቶ ማወዱን ይቀጥላል። እኔም ይህንኑ ተገንዝቤአለሁ። ለመጀመሪያ ጊዜ ዮስማይት ሸለቆን ስጎበኝ፥ ውብ ፉአፉአቴ መስተዋትማ በረዶ ከተነጠፈበት ድንጋይ ላይ ሲወርድ ተመለከትሁ። አምስት ሚሊዮን ስደተኛ ቢራቢሮዎች ዕረፍት በሚያደርጉባት የአንታሪዮ ትንሽ የባሕር ወሽመጥ ውስጥ ቀጫጭን ክንፎቻቸው እያንዳንዱን ዛፍ በደማቅ ብርቱካንማ ቀለም ያጌጠዋል። በሺካጎው ሊንከን ፓርክ ውስጥ በሚገኘው የልጆች መካነ አራዊት የማይወለድ እንስሳ የለም፤ ጎሪላ፥ አርድቫርክ፥ ወይም ጉማሬ ይወለድበታል። በዚሁ መካነ አራዊት ውስጥ ሕይወት የምትጀምረው በቀልድና በጨዋታ ነው።

ኢስሊ ትክክል ነው፤ ከፍጥረት ቅጽበት የተላለፈው ፈገግታና ደስታ ከአጽናፈ-ዓለሙ እምብርት ላይ ይረማመዳል። ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ ሕፃን የወለዱ ባለትዳሮች ይህንን በሚገባ ያውቁታል። እግዚአብሔር

የሠራውን ሁሉ ተመልክቶ መልካምነቱን ሲገልጽ ይኸው ነበር ያደረበት ስሜት። በጅማሬው መጀመሪያ ቅይማት አልነበረም። ደስታ ብቻ።

አዳምና ሔዋን

ይሁንና፥ ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ የፍጥረትን ጠቅላላ ታሪክ አይነግረንም። ቀጣዩን ለመረዳት፥ ለራስህ አንድ ነገር ማዘጋጀት አለብህ።

የመጫወቻ ዕቅዶቹን ከሚሠራ ሕፃን አንሥቶ እስከ ማይክል አንጀሎ ድረስ፥ የትኛውም ፈጣሪ መፍጠር ራስን መወሰንን እንደሚያካትት ይገነዘባል። ስትፈጥር ከዚህ በፊት ያልነበረ አንድ ነገር ታስገኛለህ፤ ይህንን የምታደርገው ግን እግረ መንገድህን ሌሎች ነገሮችን በማስወገድ ነው። አንድ የሸክላ ሣጥን ከዝሆን ፊት ላይ ብታጣብቅ ወደ ኋላም ሆነ ወደ ጎን ዝንፍ አይልም። እርሳስህን አንሣና መሣል ጀምር፤ በዚህ ጊዜ ራስህን በነጭና ጥቁር ወስነሃል፤ ሌሎች ደማቅ ቀለማትን አትጠቀምም ማለት ነው።

የትኛውም ታላቅ የጥበብ ሰው ከዚህ ውስንነት ውጭ ሊሆን አይችልም። ሚካኤል አንጀሎ የትኛውም መሣሪያ በቅርጻ ቅርጽ ሥራው በቫቲካን ለሚገኘው ለሲስቲን ቻፕል መሥሪያ የተጠቀመበትን ባለ ሦስት አቅጣጫ እውነታ (three-dimensional reality) እንደሚያስገኝለት ያውቅ ነበር። በፕላስተር ላይ ለመሥራት ወስኖ መሣሪያውን ሲመርጥ፥ ራሱን ውስን አድርጓል።

እግዚአብሔር የፈጠረው ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ፥ መሣሪያውን መርጧል። በምናቡ ውስጥ የነበረውን ብቻ ወደ ህላዌነት ሲጠራው፥ ከሁሉም ነፃ ምርጫ ጋር ውስንነት ተከስቷል። በጊዜና በቦታ የተወሰነች ዓለም ለመፍጠር ወሰነ፤ ይህም ልዩ እገዳ የተጣለበት አሠራር ነው፤ መጀመሪያ ሀ ይከሰታል፤ ከዚያ በኋላ ለ፤ ከዚያ ሐ። የወደፊቱን፥ ያለፈውንና የአሁኑን ጊዜ የሚያመለክተው አምላክ አንድ ሠዓሊ ሸራውንና ለሥራው የሚያስፈልገውን መሣሪያ እንደሚመርጥ ሁሉ ቅደም-ተከተላዊ የጊዜ አሠራር መርጧል። ምርጫውም ከተፈጠርንበት ጊዜ አንሥቶ የኖርንበትን ውስንነት አስከትሏል። (እግዚአብሔር ራሱን ለሚወስንበት ሁኔታ የሄዚዲክ ምሁራን «ዝምሳም» የሚል ግሩም ቃል ይጠቀማሉ።)

«እግዚአብሔር አለ፦ ውኃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ. . .» ከዚህ ዓረፍተ ነገር በስተጀርባ ሺህ ውሳኔዎች አሉ፤ በሳንባ ምትክ ስንጥብ፥ በፀጉር ፈንታ ቅርፊት፥ በእግር ፈንታ ክንፍ፥ በዛፎች ውስጥ በሚመላለስ ፈሳሽ ፈንታ ደም ያላቸው ዓሣዎች

ይፈጠሩ ነበር። በእያንዳንዱ ደረጃ ላይ ፈጣሪው አምላክ አማራጮችን በማስወገድ ምርጫዎችን አድርጓል።

ዘፍጥረት ስለ እግዚአብሔር የምርጫዎች ስብስብ ይናገራል፤ ከዚያም ለአፍታ ያቆማል፤ በመቀጠልም የማጠናከሪያ መረጃዎችን አሰባስቦ በበለጠ ዝርዝር እንደገና ይናገራል። በስድስተኛው የፍጥረት ዕለት፥ ከሌሎች ሁሉ የሚለዩ ሁለት ፍጥረታት ተከሰቱ–ወንድና ሴት። እግዚአብሔር የራሱን አንድ ነገር ከእነርሱ ውስጥ ለማየት በመሻቱ በራሱ አምሳል ፈጠራቸው። እነርሱ እንደ መስተዋት ሆነው የራሱን አምሳል ወደ ኋላ ያንጸባርቁ ነበር።

ዳሩ ግን አዳምና ሔዋን ሌላም ልዩነት ነበራቸው፤ ከእግዚአብሔር ፍጥረታት ሁሉ በፈጣሪያቸው ላይ የማመፅ ሥነ–ምግባራዊ ችሎታ የነበራቸው እነርሱው ብቻ ነበሩ። ቅርጻ ቅርጾቹ ቀራጺውን ሊቃወሙ ይችሉ ነበር፤ ከተውኔቱ ውስጥ የሚገኙ ባሕርያት የተውኔቱን ጽሑፍ መልሰው ሊጽፉ ይችሉ ነበር። እነርሱ ነፃ ነበሩ።

«ሰው የእግዚአብሔር ኪሳራ ነው» ብሏል አንድ የሥነ–መለኮት ምሁር። ፈላስፋው ሶረን ኪርክጋርድ እንዲህ ብሏል፤ «እግዚአብሔር ራሱን በራሱ እልባት ውስጥ አስሯል።» ስለ ሰው ነጻነት የሥነ–መለኮት ምሁራን የሚናገሩት ሁሉ በመጠኑ ትክክል ሲሆን፥ በመጠኑ ደግሞ ትክክል አይደለም። ሉዓላዊ አምላክ እንዴት ራሱን ሊያከስር ወይ ሊያስር ይችላል? ይሁንና፥ እግዚአብሔር ወንድና ሴት መፍጠሩ ወደዚያ ዓይነት ራሱን የሚወስን አስገራሚ አቅጣጫ አቅርቦታል።

ከዚህ በታች ዊሊያም ኢርዊን ቶምሰን የሚያትቱትን ልብወለዳዊ የፈጠራ ታሪክ ተመልከት።

> እግዚአብሔር በሰማይ የውዳሴን ዜማ በሚያቀርቡለት መላእክት ታጅቦ እንዳለ በምናብህ አስብ. . . «እኔ ፍጹም የሆነ ዓለም ብፈጥር ምን እንደሚመስል አውቃለሁ። ፍጹም በሆነ ፍጹማዊነቱ እንደ ፍጹም ማሽን መሥራቱን ይቀጥላል፤ ከቶውንም ከእኔ ፍጹማዊ ፈቃድ ዝንፍ አይልም።» የእግዚአብሔር ምናብ ፍጹም ስለሆነ፥ እንዲህ ዓይነቱን አጽናፈ–ዓለም መፍጠር አያስፈልገውም፤ ጠቅላላውን ዝርዝር ለማየት ምናባዊ አሠራር መጠቀሙ ይበቃዋል። እንዲህ ዓይነቱ አጽናፈ–ዓለም ለሰውም ሆነ ለአምላክ አስገራሚ ስለማይሆን፥ መለኮቱ በተመሰጦዎቹ እንዲገፉ ልንገምት እንችላለን። «ዳሩ ግን እኔ ነፃ የሆነ አጽናፈ–ዓለም ብሠራስ? ከእኔም እንኳ ነፃ የሆነ። ፍጥረታ በእኔ የሚያርድ መገኘት ሳይደናቀፉ የራሳቸውን ግላዊ ሕይወት ይመሩ ዘንድ መለኮታዊነቴን ብጋርደውስ? ፍጥረታት ይወዱኝ ይሆን? ለዘላለም ይወድሱኝ ዘንድ ያልቀረጽኋቸው ፍጥረታት ይወድሱኝ ይሆን? ፍቅር ከነጻነት ሊመነጭ ይችላል? መላእክቴ ያለማቋረጥ ይወዱኛል፤ ነገር ግን ሁልጊዜም ሊያዩኝ ይችላሉ። ነፃ የሆኑትን ፍጥረታት በራሴ አምሳል ብፈጥራቸውስ? ዳሩ ግን ነጻነቴን ለዚህ አጽናፈ–ዓለም ባስተዋውቅ፥ ጥፋትንም የማስተዋወቅ አደጋ ውስጥ መውደቄ ነው፤ ምክንያቱም ነፃ ከሆኑ፥ ከፈቃዴ ለማፈንገጥ ነፃ ናቸው። እህ! ዳሩ ግን ከዚህ ኃይለኛ አጽናፈ–ዓለም

ጋር መስተጋብሬን ብቀጥልስ? እኔና ፍጥረታቱ በአንድነት የአንድ ታላቅ ዓለም–አቀፍ ድራማ ፈጣሪዎች ብንሆንስ? ለእያንዳንዱ የክፉት አጋጣሚ የግይገመት የመልካምነት ምላሽ ብሰጥስ? ይህስ መልካምነት እርሱን ለማውደም ከሚደረጉ የክፉት ጥረቶች ሁሉ በመውጣት ክፉትን የሚያሸንፉ ቢሆንስ? በዚህ ጊዜ እነዚህ አዳዲስ የነጻነት ፍጥረታት ይወዱኝ ይሆን?»

አዳምና ሔዋን ለምን ለማመፅ ፈለጉ? በዔድን ገነት ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ሲሆን፥ አንድ ችግር ቢኖርባቸው ከእግዚአብሔር ጋር ልክ እንደ ጓደኛቸው ተነጋግረው ሊፈቱት ይችሉ ነበር። ነገር ግን አንድ የተከለከለ ዛፍ ነበረ፤ «መልካሙንና ክፉውን የሚያሳውቅ» የሚል ፈታኝ ስም የነበረው ዛፍ። እግዚአብሔር አንድ ነገር ከእነርሱ የሚደብቅ ይመስላል። ከዚያ ስም በስቲያ ምን ምሥጢር ነበር? ካልሞከሩትስ እንዴት ያውቁታል? አዳምና ሔዋን የራሳቸውን «የፈጠራ» ምርጫ አካሄዱ፤ ፍሬውን በሉ፤ ምድር ከዚያ በኋላ የቀድሞ እርኲነታን ልትይዝ አልቻለችም።

አዳምና ሔዋን ትእዛዙን በጣሱ ጊዜ እግዚአብሔር ምን ዓይነት ስሜት እንዳደረበት ዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ያሳየናል፤ በፈራረሰው ግንኙነት አዘነ፤ በክህደታቸው ተቆጣ፤ የሚያስገርም ስጋት ዓይነት ስሜት ተጫነው። «እነሆ፥ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፤ አሁንም እጁን እንዳይዘረጋ፥ ደግሞም ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ፥ ለዘላለምም ሕያው ሆኖ እንዳይኖር።» አለ።

ንጹሕ ነጻነት የሚመስለው ፍጥረ ውስንነትንም አካትቷል። ነጻነትን የሚመስለው ዓመፀኛነትም ውስንነት እንዳለበት ብዙም ሳይቆይ አዳምና ሔዋን ተገንዝበዋል። በራሳቸው ምርጫ በእግዚአብሔርና በእነርሱ መካከል መጋረጃ ሠሩ። በፊት ከእግዚአብሔር ጋር ይመላለሱና ይነጋገሩ ነበር። አሁን ግን ድምፁን ሲሰሙ በአትክልት ውስጥ ተደበቁ። አንድ መጥፎ መለያየት ቀረቤታውን ለማበላሸት ሰርጎ ገባ። እኛ ከእግዚአብሔር ጋር በምናደርገው ግንኙነት ውስጥ የሚከሰተው አንዳንድ የቅይማት ክስተት ከዚያው የመጀመሪያ ዓመፅ የመነጨ ነው።

«ምናልባት ውሰን ነፃ ፈቃደኞችን ከሁሉን ቻይነት ጋር አብሮ ለማኖር አስቸጋሪ መሆኑን ላንገነዘብ እንችላለን። ይህ በሁሉም ወቅት ላይ «መለኮታዊ ሽረትን» የሚያካትት ይመስላል።»

– ሲ. ኤስ. ሉዊስ

[1] Loren Eiseley, *The Star Thrower, 64-65*

[2]William I. Thompson, *The Time Falling Bodies Take to Light, 24-25*

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፡– ኢዮብ 38፤ ምሳሌ 8፤ ዘፍጥረት 1–3።

ምዕራፍ 7

ወላጅ

ከኮሎራዶ ከተመለስሁ በኋላ፥ ዘፍጥረትን ደጋግሜ አነበብሁ። ይህንንም ያደረግሁት እግዚአብሔር ለዚህ ዓለም ምን አሳብ እንዳለው የጅግሬዎች መጽሐፍ የሆነው ኦሪት ዘፍጥረት ፍንጭ እንዲሰጠኝ ነበር። ከዚያ ከመጀመሪያ ዓመፅ በኋላ እንኳ እግዚአብሔር ፍጥረቱን ከፊቱ አላራቀውም። እግዚአብሔር ከሰው ልጅ ጋር ግላዊ ግንኙነት ማድረግ መቀጠሉን የሚያሳዩ አስደናቂ ታሪኮች ከዘፍጥረት ውስጥ ይገኛሉ።

የዘፍጥረትን «መዋቅር» በአንድ ዓረፍተ ነገር መጻፍ ቢኖርብኝ የሚከተለውን የሚመስል ይሆናል፤ «እግዚአብሔር ወላጅ ለመሆን በመማር ላይ ነበር።»*በዔድን የተካሄደው ረብሻ አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ጋር ያደርጉት የነበረውን ቀረቤታ በማውደም ዓለምን ለዝንተ-ዓለሙ ለወጣት። ለታሪክ የወደፊት ሩጫ የሰውነት ማሟሟቂያ በሚሆን መልኩ፥ እግዚአብሔርና የሰው ልጆች እርስ በርሳቸው የግድ መላመድ ነበረባቸው። ሰዎች ሕግጋትን ሁሉ በማፈራረስ እርምጃቸውን ሲቀጥሉ፥ እግዚአብሔር በግል ደረጃ በመቅጣት ምላሽ ይሰጣቸው ጀመር። አምላክ መሆን ምን ዓይነት ስሜት ያሳድራል? የሁለት ዓመት ሕፃን አባት መሆን ምን ይመስላል?

እግዚአብሔር ቀደም ባሉት ዘመናት በሰዎች ሕይወት ውስጥ ጣልቃ አይገባም ነበር ብሎ የሚያማው የለም። ቀረብ ብሎ ከልጆቹ ላይ የሚሰፍፍ አምላክ ነበር። አዳም ኃጢአት በሠራ ጊዜ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር በግል ተገናኝቶ ፍጥረት ሁሉ አዳም ወደ መረጠው የሕይወት አቅጣጫ ማዘንበል እንዳለበት አብራርቶለታል። ከአንድ ትውልድ አዲስ ዓይነት ሥቃይ፥ ይኸውም የነፍስ ማጥፋት ተግባር በምድር ላይ ተከሰተ። «ምን አደረገህ?» ሲል እግዚአብሔር ቃየንን ጠየቀው። «ትሰማለህ? የወንድምህ ደም ከምድር ወደ እኔ ይጮሃል።»

---

* ብዙውን ጊዜ ስለ መማር የምናስበው ካለማወቅ ወደ ማወቅ የሚደረግ አእምሮአዊ ሂደት አድርገን በመሆኑ፥ «እግዚአብሔር ይማራል» የሚለው ሐረግ እንግዳ ሊሆን ይችላል። በመሠረቱ፥ እግዚአብሔር በጊዜ ወይም ባለማወቅ የታሰረ አምላክ አይደለም። «ይማራል» ስንል ነፃ ሰብአዊ ሰዎችን እንደ መፍጠር ዓይነት አዳዲስ ገጠመኞች ይሻገራል ማለታችን ነው። የዕብራውያን ጸሐፊም ቃሉን በተመሳሳይ መልኩ በመጠቀም ኢየሱስ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን እንደተማረ ይናገራል።

አሁንም እግዚአብሔር ከጥፋተኛው ጋር ተገናኝና የሚገባውን ቅጣት በየነለት።

የምድርና የጠቅላላው የሰው ዘር ሁኔታ ወደ ቀውስ እያዘመመ መጣ፤ ይህንንም መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ በሚያሳዝን ዓረፍተ ነገር እንዲህ ሲል ይገልጻል፤ «እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፥ በልቡም አዘነ።» እግዚአብሔር እንደ ወላጅ የተሰማው ኃዘንና ድንጋጤ ከዚህች ዓረፍተ ነገር በስተጀርባ ተሰውሯል።

እንዲህ ዓይነት የሥቃይ ስሜት የማያድርበት ሰብአዊ ወላጅ አለ? ታዳጊ ወጣት የሆነ ልጅ በዓመፅ ተይዞ ከወላጁ ይፋንናል። «እጠላሃለሁ!» ሲል እጅግ የጠለቀ የስሜት ቁስለት የሚያስከትሉትን ቃላት እየፈለገ ይጮኻል። ይህም የወላጆቹን አንጀት በጩቤ እንደ መተርከክ ነበር። እግዚአብሔር ከአንድ ልጁ ብቻ ሳይሆን ከጠቅላላ የሰው ዘር የተቀበለው የተቀባይነት ማጣት እንዲህ ዓይነት ነበር።

ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር የፈጠረውን አጠፋው። የዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ደስታ ሁሉ በጥፋት ውኃው ተወሰደ።

ነገር ግን ኖኅ ነበር፤ «አረማመዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገ» አንድ የእምነት ሰው። ከዘፍጥረት ምዕራፍ 3 እስከ 7 ከተገለጸው ጸጸት በኋላ፥ እግዚአብሔር በእፎይታ ሲተነፍስ የሚታይ ይመስላል፤ ይኸውም ኖኅ ከመርከቡ እንደ ወረደ በቀዳሚነት ያዳነውን አምላክ ሲያመልክ ነበር። በመጨረሻ ለሕንጻው መሠረት የሚሆነው ሰው ተገኘ። (ከዓመታት በኋላ እግዚአብሔር በሕዝቅኤል ባስተላለፈው መልእክት ኖኅን ከሦስት እጅግ ጻድቅ ሰዎች አንዱ እንደሆነ ገልጾአል።) ጠቅላላው ምድር ታጥቦና ጸድቶ በአዲስ ሕይወት ሲያቆጠቁጥ፥ እግዚአብሔር ለኖኅ ብቻ ሳይሆን ለፍጥረት ሁሉ የሚሆን ቃል ኪዳን ገባ። ቃል ኪዳኑ አንድ ተስፋ ብቻ ይሰጣል፤ እግዚአብሔር ዳግም ፍጥረታትን ሁሉ እንደማያጠፋ።

ከኖኅ ጋር የተደረገው ቃል ኪዳን የግንኙነት መሠረታዊ ነገር እንደሆነ ልትመለከት ትችላለህ፤ አንደኛው ወገን ሌላኛውን ላለማጥፋት ቃል ይገባል። በዚያ ቃል ኪዳን ውስጥ እንኳ እግዚአብሔር ራሱን ይወስናል። በአጽናፈ-ዓለሙ ውስጥ የክፋት ቀንደኛ ጠላት የሆነው እግዚአብሔር በዚህች ምድር ላይ ክፋትን ለመቀነስ ወስኗል። ወይም ከማጥፋት በተለየ መንገድ ችግሩን ለማቃለል ፈለገ። እንደ ኮበለለ ልጅ አባት በትዕግሥት ወደ መጠበቁ ድርሻ ራሱን አሻገረ (ኢየሱስ ስለ ጠፋው ልጅ የሚናገረው አስገራሚ ታሪክ ይህንን በሚገባ ይገልጻል።) ብዙም ሳይቆይ ሌላ ሕዝባዊ ዓመጽ ባቢሎን በተባለ ስፍራ ተነሥቶ

የእግዚአብሔርን መፍትሔ ተፈ
የገባውን ቃል ኪዳን ጠበቀ።

በጥንቱ ታሪክ እግዚአብሔር በ
ስለ ድብቅነቱ ወይም ዝምተኛነቱ
እነዚህ የጥንቱ ጣልቃ-ገብነቶች አን
እያንዳንዱ ጣልቃ-ገብነት ለሰዎች
እግዚአብሔር ከነፃ የሰው ልጆች
ይፈልግ ነበር፤ ነገር ግን ተከታታ
እንደ ሕፃን እያወኩት ከበሰሉ አ
ግንኙነት ሊመሠርት የሚችለው እ

ዕ

ዘፍጥረት ምዕራፍ 12 ወሳኝ
ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ እግዚአብ
ታሪክ አዲስ ዕቅድ ለማስተዋወቅ ጣ

ያሰበው ነገር ስውር አልነበረ
ብሏል፤ «ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ
የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረ
13፥15፥16 እና 17 እንዲሁም በ
ምንባቦች ውስጥ ተጠቅሷል። በአንድ
ከመሻት ይልቅ እግዚአብሔር ከሌ
ፈር-ቀዳጅ ተግባር ሊከውን መረጠ
ቃሎች ተመስጦ ቤቱን በመልቀ
የሚቆጠሩ ጉዞ አደረገ።

የዚህ የአዲሱ ዘር አባት የመ
አብርሃም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስ
ሁኔታ የተቀያየመ ሰው ምሳሌ ሆነ።

መላእክትን በቤቱ አስተናግዱ
ምሥጢራዊ ራእዮችን አልሟል። ይ
ከተስፋ ቃሉና ከራእዩ ብልጭታ በ
የረዥም ዓመታት ዝምታ።

«ሂድና የሰጠሁህን ምድር ውሰ
ነገር ግን በአብርሃም እይታ ከነዓን
ነዋሪዎቿ በረሃብ የሚረግፉበት። በ
ግብፅ ኮበለለ።

«ዘርህ እንደ ሰማይ ከዋክብት ይሆናል» አለው እግዚአብሔር። ከዚህ በላይ አብርሃምን ሊያስደስት የሚችል የተስፋ ቃል አልነበረም። በሰባ-አምስት ዓመት ዕድሜው ድንኳኑ በልጆች የጨዋታ ድምፅ እንዲሞላ ይጠባበቅ ነበር። በዘጠና ዘጠኝ ዓመት ዕድሜው የተስፋ ቃሉ የተሟጠጠ ይመስል ነበር። እግዚአብሔር ሊያረጋግጥለት ሲወጣ አብርሃም በፊቱ ሳቀ። በዘጠና ዘጠኝ ዓመቱ ልጅ ሊወልድ? ሣራ በዘጠና ዓመቷ የእርጉዝ ሴት ልብስ ልትለብስ? ሁለቱም በዚህ አሳብ ተገርመው ከጣሪያ በላይ ሳቁ። ሳቃቸው የስላቅና የሥቃይ ጣምራ ይዘት ነበረው። እግዚአብሔር በመካን ባለትዳሮች ፊት ደማቅ የመውለድ ሕልም አንጠልጥሎ ሲያበቃ ሰውነትን ወደሚያዝለው እርጅና ሲገሠግሡ ዝም ብሎ ይመለከት ጀመር። ምን ዓይነት ጨዋታ እየተጫወተ ነበር? ምን እየፈለገ ነበር?

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር እምነትን እንደፈለገ ይናገራል። አብርሃምም በመጨረሻው የተማረው ይህንኑ ነበር። ለማመን የሚያስችል ምክንያት በሌለበት ጊዜ ማመንን ተማረ። ከዋክብት ሰማይን እንደሚሞሉ ሁሉ ዕብራውያን ምድርን ሲሞሉ ለመመልከት ዕድሜው ባይፈቅድለትም፥ አብርሃም ሣራ አንድ ልጅ እስክትወልድ ድረስ በሕይወት ቆቷል። ይኸውም አንድ ልጅ የፍጹም እምነትን ትውስታ ጠብቆ ያቆየ ነበር፤ ስሙ ይስሐቅ «ሳቅ» የሚል ፍች ነበረውና።



ይኸው የአሠራር ፈለግ ቀጠለ፤ ይስሐቅ መካን ሴት አገባ፤ ልጁ ያዕቆብም እንዲሁ። የቃል ኪዳኑ ሁነኛ የእምነት እናቶች ማለትም ሣራ፥ ርብቃና ራሄል ልጅ ለመውለድ ከሁሉም የሚሻሉትን የወጣትነት ዘመናት በጭንቀትና በጉድለት አሳልፈዋል። በእነርሱም ሕይወት ውስጥ ብቸኝነት ያጠላባቸውን ጸሊም ጊዜያት ያስከተሉ የመገለጥ ብርሃናት ፈንጥቀው አልፈዋል። እነዚያ ጸሊም የመጠበቅ ጊዜያት ከእምነት በስተቀር በምንም ሊሞሉ አይችሉም ነበር።

አንዱ ቁማርተኛ እግዚአብሔር ነገሮችን እንዳዛባበት ሊናገር ይችላል። በነገ ፍካት የማይተማመን ተጠራጣሪ ሰው እግዚአብሔር ሊወዳቸው የሚገባቸውን ፍጥረታት መሳለቂያ እንዳደረገ ሊገልጽ ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ያለፉበትን መንገድ ለመግለጽ «በእምነት» የሚል ምሥጢራዊ ሐረግ ብቻ ይጠቀማል። እግዚአብሔር ያከበረው ያንኑ እምነት ነበርና ብዙም ሳይቆይ ሰዎች ለእግዚአብሔር

ያላቸውን ፍቅር የሚገልጹበት ከሁሉም የተሻለው መንገድ እምነት እንደሆነ ተረጋገጠ።

ዮሴፍ

ዘፍጥረትን በአንድ ቁጭታ ብታነበው፥ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ስለተዛመደበት ሁኔታ መገንዘብህ አይቀርም። በመጀመሪያ ከእነርሱ ጋር በዔድን ገነት ውስጥ አብሮ በመንሸራሸር፥ ኃጢአት በሚሠሩበት ጊዜ በመቅጣት፥ በቀጥታ በመናገር፥ ባለማቋረጥ ጣልቃ በመግባት ቀረብ ብሎ ቆየ። በአብርሃም ዘመን እንኳ ከሰማይ የተላኩ መልእክተኞች እንዲጎበኙት ያደርግ ነበር። በያዕቆብ ዘመን ጊዜ ግን መልእክተኞቹ በጣም አደናጋሪዎች ነበሩ፥ ከሰማይ ወደ ምድር የሚደርሰው ምሥጢራዊ መሰላልና ከእግዚአብሔር ጋር ያዕቆብ ያካሄደው የሌሊት ትግል ሊጠቀሱ ይችላሉ። ወደ ዘፍጥረት ፍጻሜ አካባቢ አንድ ዮሴፍ የተባለ ሰው በሚያስደንቅ መንገድ ምሪትን ይቀበላል።

ዘፍጥረት ከዮሴፍ ዘንድ ሲደርስ ተግ ይልና እግዚአብሔር ከትእይንቱ በስተጀርባ ሆኖ ሲሠራ ያሳየናል። እግዚአብሔር ለዮሴፍ የተናገረው እጅግ ፍትሕ-አልበኛ በነበረው የግብፅ ፈርዖን ሕልሞችን በመሳሰሉ መንገዶች እንጂ በመላእክት አልነበረም።

ማንም ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ለመቀያየም በቂ ምክንያት ካለው፥ ይህ ሰው በጎነት ለማድረግ የወሰደው ቆራጥ እርምጃ ከመከራ በቀር ምንም ያላስገኘለት ዮሴፍ መሆን አለበት። የወንድሞቹን ሕልም በፈታላቸው ጊዜ ከጉድጓድ ውስጥ ጣሉት። የወሲብ ኃጢአት ለመፈጸም ባለመፈለጉ ከግብፅ ወጎኒ ቤት ውስጥ ራሱን አገኘው። በዚያም አብሮት በአንድ ክፍል ውስጥ የነበረውን እስረኛ ሕይወት የሚያተርፍ የሕልም ፍች ሰጠ፤ ሰውዬው ግን ከተፈታ በኋላ ዘነጋው። ዮሴፍ ለሰናይ ምግባሩ በግብፃውያን እስር ቤት ውስጥ ሲማቅቅ የሪቻርድ ዓይነት ጥያቄዎች በአእምሮው ውስጥ ተከስተው ይሆን? እግዚአብሔር አድልዎአዊ ነው? ዝምተኛ? ድብቅ?

ለአንድ አፍታ እስኪ ወላጅ ወደሆነው እግዚአብሔር የእይታ አቅጣጫ እናዘንብል። የዮሴፍ እምነት ከአዲስ የብስለት ደረጃ ላይ ይደርስ ዘንድ ሆን ብሎ ይሆን መከራን የከመረበት? ለዚህ ይሆን በዘፍጥረት ከሌላው ሰው ሁሉ በላይ የዮሴፍ ታሪክ በሰፊው የተጻፈው? በመከራዎቹ ሁሉ ዮሴፍ መታመንን ተማረ፤ ይህም እግዚአብሔር ከመከራ እንደሚጠብቀው ሳይሆን በመከራው እንደሚቤዠው ነበር። ዮሴፍ ከእንባው ጋር እየታገለ እምነቱን

ለነፍሰ-ገዳይ ወንድሞቹ ለማብራራት ሞከረ፤ «እናንተ ክፉ ነገርን አሰባችሁብኝ፤ እግዚአብሔር ግን . . . ለመልካም አሰበው።»

«የሚበዛው የብሉይ ኪዳን አሳብ ምናልባትም የእግዚአብሔር የብቸኝነት አሳብ ተብሎ ሊጠራ ይችላል።»

- ጂ. ኪ. ቸስተርተን

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፦ ዘፍጥረት 1-11፤ ዕብራውያን 5፤ ሕዝቅኤል 14፤ ዘፍጥረት 12-21፥ 15፥30፤ ዕብራውያን 11፤ ዘፍጥረት 37፥39-41፥45።

ምዕራፍ 8

በቀጥታ የሚተላለፍ የፀሐይ ብርሃን

የዘፍጥረት ታሪክ የሚጠቃለለው በአንድ ቤተሰብ ነው። የቤተሰቡ ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ወዳጃቸው በሆነችው የግብፅ ምድር የሚጠለሉትን ልጆች ሁሉ ለመዘርዘር ይችል ነበር። ቀጣዩ መጽሐፍ የሆነው ኦሪት ዘጸአት እጅግ በርካታ እስራኤላውያን ጠላታቸው በሆነው ፈርዖን አገዛዝ ሥር በባርነት ሲሠሩ በሚያሳይ ታሪክ ይከፈታል። በዘፍጥረት መጨረሻና በዘጸአት መጀመሪያ መካከል በነበሩት አራት መቶ ዓመታት መካከል ስለተፈጸመው ነገር ከየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የምናገኘው መረጃ የለንም።

በዮሴፍ ሕይወት ዙሪያ ብዙ ስብከቶችን ሰምቻለሁ፤ በሙሴና በዘጸአት ተአምራት ላይ ደግሞ ከዚያ በላይ ተሰብኳል። ነገር ግን በዘፍጥረትና በዘጸአት መጻሕፍት መካከል በነበሩት ዓመታት ላይ ያተኮረ ስብከት ሰምቼ አላውቅም። (ከቅይማቶች አንዳንዶቹ የሚመነጩት በመጽሐፍ ቅዱስ የድል ታሪኮች ላይ በማተኮር የዝምታን ዘመናት ከመዝለላችን ይሆን?) እስራኤላውያን ከባርነት ነፃ ወደ ተለቀቁባቸው አስደናቂ ታሪኮች ለመገሥገሥ የምንፈጥን ይመስላል። ግን እስኪ አስቡበት! የዩናይትድ ስቴትስን ዕድሜ ለሚያህል ጊዜ እግዚአብሔር ዝም ብሎ ነበር። በግብፅ የነበሩ ዕብራውያን ባሪያዎች ከእግዚአብሔር ጋር እንደተቀያየሙ ጥርጥር የለውም።

አንተ የአብርሃም ዘር የሆንህ እስራኤላዊ ነህ እንበል። እግዚአብሔር ለዚያ ታላቅ ሰው ስለሰጣቸው ድንቅ ተስፋዎች ስትሰማ አደግህ። «አንድ ቀን ዘርህ ታላቅ ሕዝብ ይሆንና በገዛ ምድሩ በሰላም ይኖራል።» እግዚአብሔር ይህንን መጀመሪያ ለአብርሃም፤ በኋላም ለይስሐቅና ለያዕቆብ በግል ምሎ አረጋግጦላቸዋል። በልጅነትህ እነዚያን የተስፋ ቃሎች በታዛዥነት በቃልህ አጥንተሃቸዋል። አሁን ግን እነዚያ የተስፋ ቃሎች ባዶ ተረት ሆነውብሃል። ነፃ ሕዝብ? አንተና ጎረቤቶችህ በምድር ላይ እጅግ ኃያል የነበረችው አገር ባሪያዎች ሆናችሁ፤ በየዕለቱ በግብፅ የሥራ አለቆች ስድብና ድብደባ ተሠቃየህ። ታናሽ ወንድምህ በፈርዖን ተገደለ።

ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣት የተስፋዪቱ ምድር በስተምሥራቅ አንድ ደርዘን በሚሆኑ ነገሥታት ተከፋፈለች።

♥

ማንኛውም ተጠራጣሪ እንዲሆን የተመኘው ነገር የሙሴ ዘመን ከመቅጽበት ከመከሰቱ በፊት አራት መቶ የዝምታ ዓመታት ተቆጠሩ። በመጀመሪያ እግዚአብሔር በቁጥጥሩ ውስጥ ተገኝቶ ራሱን ለሙሴ ስሙን በመናገር አስተዋወቀው። ድምፁን ከፍ አድርጎ፥ «ሕዝቤ መከራ ተቀብሏል» አለ። «አሁን የምሠራውን ታውቃላችሁ።» በመቀጠልም፥ ዓለም ካየችው ሁሉ በላቀ የመለኮታዊ ኃይል መገለጥ ሕዝቡን ነፃ አወጣ። አሥር ጊዜያት በከፍተኛ ደረጃ ጣልቃ ገብቶ በመሥራቱ በግብፅ ውስጥ የዕብራውያንን አምላክ መኖር የሚጠራጠር አንድም ሰው አልነበረም። በቢሊዮን የሚቆጠሩ ጓጉንቸሮች፥ ጊንጦች፥ ዝንቦች፥ በረዶዎችና አንበጦች ለፍጥረት ሁሉ ጌታ መኖር ተጨባጭ ማረጋገጫ ሰጡ።

ለቀጣዮቹ የአርባ ዓመታት የበረሃ ውስጥ ጉዞ ወቅት እግዚአብሔር ሕዝቡን አባት ልጁን እንደሚሸከም ተሸከመ። እስራኤላውያንን አለበሳቸው። በዕለታዊ ጉዞአቸው መገባቸው፤ ዕቅድ አወጣላቸው፥ ጦርነታቸውን ተዋጋላቸው።

♥

እግዚአብሔር አድልዎአዊ ነው? ዝምተኛ? በሙሴ ዘመን እግዚአብሔር መሸፈኛውን ከማስወገዱ በፊት እነዚህ ጥያቄዎች ዕብራውያንን ሳያስጨንቋቸው አይቀሩም። እግዚአብሔር ክፋትን ቀጣ፤ በጎነትን ደግሞ ሸለመ። ጎልቶ በሚሰማ ድምፅ ተናገረ። መጀመሪያ ለሙሴ በሚቃጠል ቁጥቋጦ፥ ቀጥሎም ለእስራኤላውያን በሙሉ በእሳትና በደመና ዓምድ ገለጠ።

ለዚህ ዓይነቱ ቀጥተኛ ጣልቃ-ገብነት እስራኤላውያን የሰጡት ምላሽ በሁሉም ኃይል ውስጥ ስልሚገን ውስንነት በጣም ጠቃሚ ግንዛቤ ያስጨብጠናል። ኃይል ከአንድ በጣም አስፈላጊ ነገር በስተቀር ሁሉንም ሊያከናውን ይችላል። ፍቅርን ግን ሊቆጣጠር አይችልም። በዘጸአት መጽሐፍ ውስጥ የምንመለከታቸው አጅር መቅሠፍቶች እግዚአብሔር በፈርዖን ላይ የገለጠውን ኃይል ያሳዩናል። ነገር ግን በዘጉልቁ መጽሐፍ ውስጥ በተዘረዘሩት አሥር ዐበይት ዓመፆች፥ እግዚአብሔር የፈለገውን ነገር ኃይል ሊያስገኝ እንዳልቻለ ያመለክታል። ይህም የሕዝቡን ፍቅርና ታማኝነት ነበር። የትኛውም ዓይነት እጅግ የላቀ የታላቅነት ተግባር እርሱን እንዲታመኑና እንዲከተሉ ሊያደርጋቸው አልቻለም።

ይህ የጥንቶቹ እስራኤላውያን ሊያስተምሩን የሚያስፈልገን ትምህርት አይደለም። ዛሬ ፈር የለቀቀ ከፍተኛ ኃይል በሚስተዋልባቸው ማኅበረሰቦች ውስጥ ልንመለከተው እንችላለን። በርካታ ምስክሮች እንዳረጋገጡልን፥ በእስር ቤት ውስጥ የጥበቃ ፖሊሶች የማይመጠን ኃይል ይጠቀማሉ። ኃይልን በመጠቀም አምላክህን እንድትክድ፥ ቤተሰብህን እንድትረግም፥ ያለ ክፍያ እንድትሠራ፥ የሰው ሰገራ እንድትበላ፥ እጅግ የሚቀርብህን ጓደኛ ወይም እናትህን ገድለህ እንድትቀብር ሊያደርጉህ ይችላሉ። ይህ ሁሉ በኃይላቸው ውስጥ ይገኛል። አንድ ነገር ብቻ እዚያ ውስጥ የለም፤ እነርሱን እንድትወድ ሊያስገድዱህ አይችሉም። ፍቅር በኃይል ደንበኞ ያለመገዛቱ እውነታ እግዚአብሔር ለምን አንዳንድ ጊዜ ኃይሉን ለመጠቀም እንደማይፈልግ ለማብራራት ሊረዳን ይችላል። የፈጠረን እንድንወደው ቢሆንም፥ በስውር የምንናፍቃቸው ዓይነት እጅግ አስደናቂ ተአምራቶቹ ያንን ፍቅር ለመጨመር የሚፈይዱት ነገር የላቸውም። ደግላስ ጆን ሆል እንደተናገሩት፥ «የእግዚአብሔር ችግር የተወሰኑ ነገሮችን ለማድረግ አለመቻሉ አይደለም። የእግዚአብሔር ችግር ማፍቀሩ ነው። ፍቅር ሁሉንም ሕይወት እንደሚያወሳስብ የእግዚአብሔርን ሕይወት አወሳስቦታል።»

ፍቀሩ ተቀባይነት ሊያጣ የአጽናፈ-ዓለሙ አምላክ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነገር ዋጋ እንዳጣበት ወላጅ በምስኪንነት ይዋጣል። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር የነበረውን የፍቅር ግንኙነት እንዲህ ሲል ይገልጻል፦

> «በተወለድሽበት ቀን ከሰውነትሽ ጉስቁልና የተነሣ በሜዳ ላይ ተጣልሽ እንጂ ከዚህ አንዳች ይደረግልሽ ዘንድ ዓይን አልራራልሽም፥ ማንም አላዘነልሽም።
>
> በአንቺ ዘንድ ባለፍሁ ጊዜ በደምሽም ውስጥ ተለውሰሽ ባየሁሽ ጊዜ፦ በደምሽ እንዳለሽ በሕይወት ኑሪ አልሁሽ፤ አዎን፦ በደምሽ እንዳለሽ በሕይወት ኑሪ አልሁሽ። በእርሻ ላይ እንዳለ ቡቃያ አበዛሁሽ፥ አንቺም አደግሽ፥ ታላቅም ሆንሽ፥ በእጅጉም አጌጥሽ፥ ጡቶችሽም አኀጠኑ፤ ጠጕርሽም አደገ፥ ነገር ግን ዕርቃንሽን ሆነሽ፥ ተራቁተሽም ነበርሽ። በአንቺ ዘንድ ባለፍሁና ባየሁሽ ጊዜ፥ እነሆ፥ ጊዜሽ የፍቅር ጊዜ ነበር፤ እኔም መጎናጸፊያዬን በላይሽ ዘረጋሁ፤ ኀፍረተ ሥጋሽንም ከደንኩ፥ ማልሁልሽም፤ ከአንቺም ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፥ አንቺም ለእኔ ሆንሽ።

«በውጃም አጠብሁሽ ከደምሽም አጠራሁሽ በዘይትም ቀባሁሽ። ወርቀዘቦም አለበስሁሽ፤ በአቆስጣ ቁርበትም ጫማ አደረግሁልሽ፤ በጥሩ በፍታ አስታጠቅሁሽ በሐርም ከደንሁሽ፤ በጌጥም አስጌጥሁሽ፤ በእጅሽም ላይ አንባር በአንገትሽም ላይ ድሪ አደረግሁልሽ። በአፍንጫሽም ቀለበት በጆሮሽም ጉትቻ በራስሽም ላይ የክብር አክሊል አደረግሁ።»

ነገር ግን ሁሉንም የሚመለከተው እግዚአብሔር የእስራኤላውያንን የመጨረሻ አሳዛኝ መድረሻ ያውቅ ነበር፤ «ዛሬ ወደማልሁላቸው ምድር ገና ሳላገባቸው የሚያስቡትን አሳብ አውቃለሁና።» ሕዝቡ ለውጥን በሚጠባበቅ ድባብ ከዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ ሲሰበሰብ፥ አምላክነት ምን ዓይነት ስሜት እንደሚያሳድር እግዚአብሔር በጨረፍታ አመልክቷል። በካምፑ ውስጥ ያለውን የጉጉት መንፈስም ሳይጋራ እግዚአብሔር ወደ መገናኛው ድንኳን በመዝለቅ ምክንያቱን ለሙሴ ገለጸለት።

ከምንም ነገር በላይ እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑ እንዲቀጥል ፈልጎ ነበር፤ «ለእነርሱ ለዘላለም ለልጆቻቸው መልካም ይሆንላቸው ዘንድ፥ እንዲፈሩኝ ሁልጊዜም ትእዛዜን ሁሉ እንዲጠብቁ እንዲህ ያለ ልብ ምነው በሆነላቸው!» ነገር ግን የምድረ በዳው ተደጋጋሚ ዓመፅ አስከፊ ውጤቶች ነበሩት። እግዚአብሔር መጥፎ ያለመታዘዝ ሁኔታ እንደሚከተልና እርሱም ለዚያ አለመታዘዝ የሚሰጠውን ምላሽ ተነበየ፤ «በዚያን ጊዜ ፊቴን እሰውርባችኋለሁ።» ሐሺሻም ልጁን ራሱን ከመጉዳት ሊመልስ እንዳልቻለው ምስኪን ወላጅ፥ እግዚአብሔር አሳዛኝ የመለየት አሳብ ተናገረ። እስካሁን የተሻለች ሰው ለመሆን የገባቻቸውን ቃል ኪዳኖች ሳትፈጽም ነገ ወይም በሚቀጥለው ቀን ራሴን አሻሽላለሁ እያለች የምታለቃቅስ የአልኮል ቁራኛ ሚስቱን ጩኸት እንደሚሰማ ባል ሆነ።

ከዚያም እግዚአብሔር ለሙሴ በጣም ያልተለመደ ትእዛዝ ሰጠው። «መዝሙር ጻፍና እስራኤላውያን እንደ ታሪክ ምስክርነት እንዲማሩት አድርግ። መዝሙሩ እግዚአብሔር ለዝማሬ ያለውን አመለካከት ያስረዳል፤ ይኸው እስከመተው ድረስ ያዘነው አፍቃሪ ሰቆቃ መሆኑ ነው። በመሆኑም ሕዝቡ የዮርዳኖስን ወንዝ በማቋረጡ እጅግ በተደሰቱበት ብሔራዊ የልደት ቀናቸው ላይ እስራኤላውያን ብሔራዊ መዝሙር ዘመሩ፤ መዝሙሩ ግን ከዚያ በፊት ከተዘመሩት ሁሉ በላይ እንግዳ መልእክት ነበረው። ምንም ዓይነት የተስፋ ቃላት አልነበሩትም፥ ጽልመት ብቻ።

መጀመሪያ እግዚአብሔር እጅግ ከተበላሸው ስፍራ አግኝቶ እንደ ዓይኑ ብሌን እነርሱን ስለተንከባከባቸው መልካም ጊዜያት ዘመሩ። ቀጥሎም ልደት የሰጣቸውን አምላክ ስለሚረሱበት የወደፊት አስከፊ ክህደት ዘመሩ። ስለሚደርስባቸው መርገሞች፥ ረሃብ፥ የከፋ መቅሰፍትና በደም ስለሚበከሉት ቀስቶች ዘመሩ። ይኸውም መራራ-ጣፋጭ መዝሙር የጆሮአቸውን ታምቡር እያርገበገበው እስራኤላውያን ወደ ተስፋዪቱ ምድር ገሠገሡ።

♥

በወንጀል ምርመራ ላይ እንደተሰማራ አዳኝ ውሻ፥ ፍንጭ ለማግኘት በምድረ በዳው የመቅበዝበዝ አካባቢ ሳንጥ-ብብ ቆየሁ። የመገናኛው ድንኳን በእግዚአብሔር መገኘት ሲያብረቀርቅ፤ ተአምራዊ ምግብ በየዕለቱ ሲወርድ፥ ኃዘንን እንደ መታጠቂያ የደራረቡ ሕዝበ-እስራኤላውያን በአሸዋማው የምድር በዳ መንገድ ላይ እየተጓተቱ ሲሄዱ. . . በደማቅ የተስፋ ቃልና በእነዚያ አርባ ዓመታት አዋኪ ከንቱነት መካከል ከእግዚአብሔር ጋር የመቀያየም ምሥጢር ነበር። ምን ችግር ተፈጠረ?

ሁልጊዜ እግዚአብሔር በቀጥታና በቅርበት እንዲሠራ ስናፍቅ ኖሬአለሁ። ራሱን ብቻ ቢገልጥ! ነገር ግን ከእስራኤላውያን የውድቀት ታሪኮች ውስጥ የእግዚአብሔር በቀጥታ መሥራት የሚያስከትላቸውን አንዳንድ «ጉዳቶች» ለመገንዘብ እችላለሁ። ወዲያው ያጋጠማቸው አንድ ችግር ግላዊ ነጻነታቸውን ማጣታቸው ነበር። እስራኤላውያን ከቅዱስ አምላክ ጋር ተቀራርበው በሚኖሩበት ጊዜ ምንም ነገር የማድረግ ነጻነት አልነበራቸውም፤ የፈቃደ ሥጋ ግንኙነት፥ የወር አበባ፥ አለባበስ ወይም አመጋገብ ከሕጉ ክልል ውጭ ሊወጣ ይችል ነበር። «ምርጥ ሕዝብ» መሆን ዋጋ ያስከፍላል። እግዚአብሔር በኃጢአተኛ ሕዝብ መካከል ለመኖር እንደተቸገረ ሁሉ እስራኤላውያንም ቅዱስን አምላክ በመካከላቸው አኑረው ለማስተናገድ ተቸገሩ።

ትናንሽ ነገሮች እስራኤላውያንን እጅግ የሚያስጨንቋቸው ይመስላል፤ ለምሳሌ፥ ስለ ምግብ አዘውትረው ማጉረምረማቸው ለዚህ ምስክር ነው። ከአንዳንድ አጋጣሚዎች በስተቀር አርባውንም ዓመት የተመገቡት አንዱን ዓይነት ምግብ ነበር። ይኸውም በየጠዋቱ ከምድር ላይ የሚወርድ መና (የቃሉ ቀጥተኛ ትርጉም «ምንድን ነው?» የሚል ነው) ነበር። አንድ ዓይነት ምግብ ደጋግሞ መመገቡ ከባርነት ከመውጣት ጋር የሚነጻጸር ባይመስልም እንዲህ ዓይነት የከረሩ ሮሮዎች ያሰሙ ነበር፤ «በግብፅ ያለዋጋ እንበላው የነበረውን ዓሣ፥ ዱባውንም፥

በጢኹንም፥ ኩራቱንም፥ ቀዩንም ሽንኩርት፥ ነጩን ሽንኩርት እናስባለን፤ አሁን ግን ሰውነታችን ደረቀች፤ ዓይናችንም ከዚህ መና በቀር ምንም አታይም አሉ።»

ከእነዚህ ተራ ጉዳዮች በተጨማሪ የከበደ ጫና ያዘለ ችግር ተከሰተ። እግዚአብሔር ወደ ሕዝቡ እየቀረበ ሲመጣ በአያዎአዊ ዘይቤ እነርሱ ከእርሱ የላቁ መስሎ ተሰማቸው። ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ የሚያስፈልጉትን ስሕተትን የሚያስወግዱትን አስደናቂ ሥርዓቶች አቋቋመ። እስራኤላውያን ከቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ የእግዚአብሔርን መገኘት ግልጽ መረጃ መመልከት ይችሉ ነበር፤ እነርሱ ግን አልደፈሩም። እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር ጋር ምን ዓይነት ግላዊ ግንኙነት» እንደነበራቸው ለማወቅ ብትሻ የራሳቸው የአምላኪዎቹን ቃል ሰማ፤ «እነሆ፥ እንሞታለን፥ እንጠፋለን፥ ሁላችንም እንጠፋለን። የሚቀርብ ሁሉ፥ ወደ እግዚአብሔር ማደሪያ የሚቀርብ፥ ይሞታል። እንደገናም፥ እንዳልሞት የአምላኬን የእግዚአብሔርን ድምፅ ደግሞ አልሰማ፥ ይህችን ታላቅ እሳት ደግሞ አልይ. . .»

♥

አንድ ጊዜ ታላቁ ሳይንቲስት አይዛክ ኒውተን የፀሐይ ምስል በመስተዋት ውስጥ ሲያንጸባርቅ እየተመለከተ የሙከራ ተግባሩን ያከናውን ጀመር። የፀሐይ ኃይል ሬቲና ወደተባለው የዓይኑ ክፍል ስለፈሰሰ ለጊዜው ዓይነስውር ሆኖ ተሠቃይቷል። ለሦስት ቀናት በጥላ ውስጥ ቢሸሸግም እንኳ ደማቁ የፀሐይ ጨረር ከእይታው ውስጥ ሊደበዝዝ አልቻለም ነበር። በኋላም ስለዚሁ ሲጽፍ፥ «ምናቤን ከፀሐይ ለመመለስ የምችለውን መንገድ ሁሉ ተጠቀምሁ፤ ነገር ግን በጨለማ ውስጥ ሆኜ እንኳ ምስሏን እመለከት ነበር» ብሏል። ኒውተን ለተጨማሪ ጥቂት ደቂቃዎች በሙከራው ገፍቶበት ቢሆን ኖሮ ምናልባትም ሕይወቱን በሙሉ ለዓይነ–ስውርነት ይዳረግ ነበር። እይታን የሚቆጣጠሩ ኬሚካሎች በቀጥታ የሚተላለፈውን የፀሐይ ጨረር ሙሉ ጉልበት ሊቋቋሙ አይችሉም።

ይኸው የአይዛክ ኒውተን ሙከራ እስራኤላውያን ከምድረ በዳው መቅበዝበዝ በኋላ ምን እንደ ተማሩ ለማብራራት ይረዳል። የአጽናፈ–ዓለሙ አምላክ በመካከላቸው ተገኝቶ እያዩት ሊኖሩ ሞክረው ነበር፤ ነገር ግን በመጨረሻው ከእነዚህ ሁሉ ከግብፅ ባርነት በደስታ እየፈነጠዙ ከወጡት በርካታ ሺዎች ሁለቱ ብቻ የእግዚአብሔርን መገኘት ተቋቁመዋል። የሻማን ብርሃን የማትቋቋም ከሆንህ እንዴት አድርገህ ፀሐይን ታያታለህ?

ነቢዩ ኢሳይያስ፥ «ከእኛ መካከል ከሚበላ እሳት ጋር ሊኖር የሚችል ማን ነው?» ሲል ጠይቋል። እግዚአብሔር በመሰወሩ ልናመሰግነው እንጂ ልንማረርበት አይገባ ይሆን?

[1] Douglas John Hall, *God and Human Suffering, 156.*

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፦ ዘጸአት 1–12፤ ዘዳግም 1፤ ሕዝቄኤል 16፤ ዘዳግም 31፥5፥ 31–32፤ ዘኍልቁ 11፥17፤ ዘዳግም 18፤ ኢሳይያስ 33።

ምዕራፍ 9

አንድ አንጻባራቂ ወቅት

ሊዎ ቶልስቶይ በዘጠኝ ዓመት ዕድሜው እግዚአብሔር ለመብረር እንደሚያስችለው በማመን ከሦስተኛው ፎቅ መስኮት ራሱን በመጣሉ ከእግዚአብሔር ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ከፍተኛ ቅያሜ ፈጥሮ ነበር። ደግነቱ ቶልስቶይ ከአደጋው በመትረፍ ከዓመታት በኋላ እምነቱን ለመፈተን በወሰደው የጅልነት ተግባር ላይ ሊስቅ በቅቷል።

ስለ ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይላት የፈጠራ አሳብ ያልወጠነ ልጅ የታለ? ጌታ ሆይ! በዚህ ሐይቅ ላይ እንድረግመድ እርዳኝ። ያንን ልጅ እንድደበድበው እርዳኝ። ሳላጠና ነበዝ ተማሪ አድርገኝ። እግዚአብሔር የምንፈልጋቸውን ነገሮች ሁሉ የሚሰጠን ቢሆን፥ ከአመስጋኝነት የተነሣ ልናስደስተው አንሞክርም ይሆን? በጽልመታም የቅይጣት ወቅቶች፥ በደመ-ነፍስ እንደዚህ አስባለሁ፤ <u>እግዚአብሔር ከዚህ ቢያወጣኝ . . . ነገሮች ቢረግቡልኝ. . . ደህና ብሆን . . . ከዚያ በኋላ እግዚአብሔርን እከተላለሁ።</u>

ወዳጄ ሪቻርድ በፍትሕ የሚሠራ፤ በግልጽ የሚናገርና ራሱን ገሃድ የሚያወጣ አምላክ ቢኖር ማንም ሰው እንደ ታማኝ ውሻ እንደሚከተለው ያምናል። የእስራኤላውያን የምድረ በዳ ሕይወት ይህንን አሳብ ውድቅ ያደርገዋል። ነገር ግን አንዳንድ ሰው ሙሴ «እባብና ጊንጥ ጥማትም ያለባት፥ ውኃም የሌለባት፥ ታላቂቱና የምታስፈራው ምድረ በዳ» ሲል ባስታወሰው ስፍራ እምነታቸው እንደዋዠቀ በመግለጹ ሊሟገቱ ይችላሉ።

በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታዎች ውስጥ ተስፋ የማይቆርጥ ሰው ይኖር ይሆን? እግዚአብሔር የቅርብ አምላክ መስሎ ፍላጎታቸውን በሚያሟላባቸው ጊዜያት የበለጠ አስደሳችነት የሚያመዝንባቸው ጊዜያት ነበሩ?

ዳዊት የሚለው ስም ሲነሣ ብሉይ ኪዳን ይፈካል። መዝሙር 78 ስለ እነዚያ ጊዜያት፥ «እግዚአብሔርም ከእንቅልፉ እንደሚነቃ ተነሣ፥ የወይን ስካር እንደ ተወው እንደ ኃያልም ሰው» ይላል። እግዚአብሔር በመጨረሻ እንደ ልቡ የሆነ ሰው አግኝቷል፤ ይህም ከእርሱ ዙሪያ ሕዝብ የሚመሠርትበት ዓይነት ሰው ነበር። ብርቱው ንጉሥ ዳዊት ከአንዱ በስተቀር በመጻሕፍት የሰፈሩትን ሕግጋት ሁሉ ተላለፈ፤ ያላፈረሳት አንዱ ሕግ አምላኩ እግዚአብሔርን በሙሉ ልቡ፥ አሳቡና

ነፍሱ መውደዱ ነበር። ዳዊት የእስራኤል ንጉሥ ሲሆን የቃል ኪዳኑ ሕልሞች የኋሊት ተጎተቱ።

የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ከዙፋኑ ላይ ሲወጣ እግዚአብሔር መሰናከሎችን ሁሉ አስወገደ። ልጆች በሕልም ብቻ የሚመኙትን ነገር ሰሎሞን አገኘው፤ ረዥም ዕድሜ፥ ብልጽግናና ማንኛውም ነገር ከዙሪያው ተሟልቶ ተገኘ። ሰሎሞን ጥበብን ሲመርጥ እግዚአብሔር እንደ ሀብት፥ ክብርና ሰላም ያሉትን ነገሮች እንደ ምርቃት ጨመረለት። ለረዥም ዘመናት በሥቃይ የኖረው የዕብራውያን ታሪክ ተለውጦ መረጋጋት በሞላበት ወርቃማ ዘመን ውስጥ ሊገዛ በቅቷል።

ሰሎሞን

በታዳጊ ወጣትነቱ ከእስራኤል ዙፋን ላይ የተቀመጠው ሰሎሞን ብዙም ሳይቆይ በዘመኑ ከነበሩት ሁሉ በላይ በብልጽግናው ልቆ ታወቀ። መጽሐፍ ቅዱስ በዚያን ዘመን ብር በኢየሩሳሌም እንደ ተራ ድንጋይ የበረከተ መሆኑን ይነግረናል። በርካታ የንግድ መርከቦች ለንጉሡ የግል ማከማቻ የተለያዩ አስደናቂ ነገሮችን ከሩቅ አገር ያመጡ ነበር፤ ከአፍሪካ ዝንጀሮዎች፥ የዝሆን ጥርስና ወርቅ በብዙ ቶኖች ይሰበሰቡለት ነበር። ሰሎሞን ጥበባዊ ዝንባሌም ነበረው፤ 1005 መዝሙሮችንና 3000 ምሳሌዎችን ጽፎአል።

የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማትና የገነባትን ውብ ከተማ ለማየት የአገር መሪዎች በመቶ ማይሎች የሚቆጠር ርቀት አቋርጠው ይመጡ ነበር። እንዲህ ያለ ገጠመኝ ከነበራቸው ሰዎች አንዱ ንግሥተ ሳባ የሚከተለውን ብላለች።

> «ስለ ነገርህና ስለ ጥበብህ በአገሬ ሳለሁ የሰማሁት ዝና እውነት ነው። እኔም መጥቼ በዓይኔ እስካይ ድረስ የነገሩኝን አላመንሁም ነበር፤ እነሆም፥ እኩሌታውን አልነገሩኝም ነበር፤ ጥበብህና ሥራህ ከሰማሁት ዝና ይብልጣል። በፊትህ ሁልጊዜ የሚቆሙ ጥበብህንም የሚሰሙ ሰዎችህና እነዚህ ባሪያዎች ምስጉኖች ናቸው። አንተን የወደደ፥ በእስራኤልም ዙፋን ያስቀመጠህ አምላክ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን።»

ይህ እንደ መሰነባበቻ ገጸ በረከት ለሰሎሞን አራት ተኩል ቶን ወርቅ ከሰጠችው ንግሥት የፈለቀ አስደናቂ ንግግር ነበር።

በእነዚያ ሰላማዊና አስደሳች ጊዜያት የእግዚአብሔር ስሜት እንዴ ያለ ነበር? እፎይታ፥ ደስታ፥ እርካታ። መጽሐፍ ቅዱስ ለእነዚህ ሁሉ ፍንጭ ይሰጣል። የእስራኤል ቀንደኛ አጉረምራሚዎች ከተወገዱ በኋላ

ሰሎሞን ለእግዚአብሔር የመወደድ ስሜት የሚፈጥር ተግባር አከናውኗል። ሰሎሞን የመንግሥቱን ገንዘብ በሁለት መቶ ሺህ ሠራተኞች በተገነባና ከዓለም አስደናቂ ነገሮች እንደ አንዱ ሆኖ በተመዘገበው የቤተ መቅደሱ ሥራ ላይ አፈሰሰው። ቤተ መቅደሱ እንደ ጥጥ አዝመራ ከርቀት ያብረቀርቅ ነበር።

ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ለእግዚአብሔር አሳልፎ በሰጠበት ዕለት የብሉይ ኪዳን ታሪክ ከላቀ ደረጃ ላይ ደረሰ። ሰብአዊ ፍጡራን ያልሆኑ ተዋንያን የሚሠሩትን እንደ አስገራሚ የፊልም ቅንብር በዓይነ-ሕሊናህ ተመልከት። በኢየሩሳሌምም የተፈጸመው ይህንኑ የሚመስል ነገር ነበር፤ የኢየሩሳሌሙ በተወሰኑ ሥልጡን ተዋንያን ከመድረክ ላይ የቀረበ ካለመሆኑ በቀር። በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች በታላቅ ሕዝባዊ በዓል ላይ ተገኝተው እየተመለከቱ ነበር። የእግዚአብሔር ክብር ቤተ መቅደሱን ለመሙላት ሲወርድ ካህናት ሳይቀሩ ከክብሩ ነጸብራቅ የተነሣ ወደ ኋላ ተመልሰው ነበር።

እግዚአብሔር የሰሎሞንን ቤተ መቅደስ በምድር ላይ የሚያደርገው እንቅስቃሴ እምብርት እያደረገው ስለነበር፥ ሕዝቡ በግብታዊነት ተጨማሪ የሁለት ሳምንታት በዓል ለማድረግ ወሰኑ። ከነሐስ መድረክ ላይ ተንበርክኮ ሰሎሞን እንዲህ አለ፤ «ለእስራኤልም አምላክ ለእግዚአብሔር ቤት ሠራሁ።» ከዚያም በአድናቆት ተሞልቶ እንዲህ ብሏል፤ «በውኑ እግዚአብሔር ከሰው ጋር በምድር ላይ ይኖራልን? እነሆ! ሰማይ ከሰማያትም በላይ ያለው ሰማይ ይይዝህ ዘንድ አይችልም፤ ይልቁንስ እኔ የሠራሁት ቤት እንዴት ያንስ!»

በኋላ እግዚአብሔር፥ «በፊቴ የጸለይኸውን ጸሎትህንንና ልመናህን ሰምቻለሁ፤ ለዘላለምም ስሜ በዚያ ያድር ዘንድ ይህን የሠራኸውን ቤት ቀድሻለሁ፤ ዓይኖቼና ልቤም በዘመኑ ሁሉ በዚያ ይሆናሉ» ሲል ምላሽ ሰጥቶአል። እግዚአብሔር አድርጎታል። እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለሙሴ የገባቸው የተስፋ ቃሎች በመጨረሻው ከፍጻሜ ደረሱ። በዚህ ጊዜ እስራኤላውያን መሬት፥ አስተማማኝ ዳርቻ የነበረው አገርና የሚያንጸባርቅ የእግዚአብሔር መገኘት ተምሳሌት በመካከላቸው ነበር። በዚያ አስገራሚ የቤተ መቅደስ ምረቃ ላይ ተገኝቶ ሲያበቃ እግዚአብሔርን ሊጠራጠር የሚችል ሰው አልነበረም፤ ሁሉም ሰው የመገኘቱን እሳትና ደመና ተመልክቷል። ይህ ሁሉ የሆነው እባብና ጊንጥ በሞላበት ምድረ በዳ ሳይሆን ወርቅና ብር በጠገበች አገር ነበር።

♥

የሰው አእምሮ ሊገምተው ከሚችለው በላይ ሁሉ ነገር እየተከናወነለት ሳለ መጀመሪያ ሰሎሞን እግዚአብሔርን በአመስጋኝነት የሚከተል ይመስል ነበር። በ 1ኛ ነገሥት ምዕራፍ 8 የጸለየው ጸሎት እስካሁን ከተጸለዩት ጸሎቶች ሁሉ የላቀ ግርማ የተላበሰ መሆኑ ግልጽ ነው። ይሁንና በንግሥናው መጨረሻ አካባቢ ሰሎሞን ከሞላ ጎደል ሁሉንም ነገር አባክኗል። የፍቅር ቅኔዎችን የተቀኘው የጥበብ ሰው ከብዙ ሴቶች ጋር የፈቃደ-ሥጋ ግንኙነት በማድረግ ሪኮርድ ሰበረ፤ ሰባት መቶ ሚስቶችና ሦስት መቶ ቁባቶች ነበሩት። ሰፊ ግንዛቤ የሚያስጨብጡትን በርካታ ፈሊጣዊ አነጋገሮች የጻፈው ሰውዬ ወደር በማይገኝለት መልኩ ተላልፎአቸው ተገኘ። ለእግዚአብሔር መቅደስ የሠራ ሃይማኖተኛ ሰውዬ አረማዊ ሚስቶቹን ለማስደሰት ሲል የመጨረሻውን አስከፊ እርምጃ ተራመደ፤ በእግዚአብሔር ቅድስተ ከተማ ውስጥ አምልኮተ ጣዖትን በፈር ቀዳጅነት አስፋፋ።

በአንድ የትውልድ ዘመን ሰሎሞን እስራኤላውያንን ውሎ ለማደር በእግዚአብሔር ላይ ከሚደገፉበት ደረጃ አንሥቶ እራሳቸውን ችለው ወደሚቆሙበት ፖለቲካዊ ኃይል አሸጋገራቸው። ይህንን ሲያደርግ ግን እግዚአብሔር እነርሱን የመራበትን የመጀመሪያ ራእይ ረሳ። ሰሎሞን በሞተበት ዘመን እስራኤላውያን ሾሽተው ያመለጧትን ግብፅን መስለው ተገኙ፤ ይኸውም በከፍተኛ ቢሮክራሲና በባሪያ ጉልበት፥ ብሎም በንጉሡ ትእዛዝ በሚመራ መንግሥታዊ ሃይማኖት የታወቀ መንግሥት መሆናቸው የእግዚአብሔርን መንግሥት ፍላጎት አጠበበባቸው። ለአጭር ጊዜ በርቶ የታየው የቃል ኪዳኑ ሕዝብነት ደብዝዞ እግዚአብሔር ማዕቀቡን ጣለ። ከሰሎሞን ሞት በኋላ እስራኤላውያን ለሁለት መንግሥት ተከፍለው ወደ መፈራረሱ ተንሸራተቱ።

ኦስካር ዋይልድ የተናገሩት ቃል ከሰሎሞን ሐውልት ላይ ቢቀረፍ ከሁሉም በላይ ተስማሚ ሳይሆን አይቀርም፤ «በዚህ ዓለም ሁለት ዓይነት ጭፍግ ገጽታዎች ብቻ አሉ። አንዱ የሚፈልጉትን አለማግኘት ሲሆን፥ ሌላው ደግሞ ማግኘቱ ነው።» ሰሎሞን፥ በተለይም የኃይልና የሥልጣንን ተምሳሌቶች አስመልክቶ የፈለገውን ሁሉ አግኝቷል። ቀስ በቀስ ከእግዚአብሔር ይልቅ በዙሪያው ባሉት ነገሮች ላይ እየተደገፈ ይሄድ ጀመረ፤ እነዚህም እጅግ የበዙ ሚስቶች፥ የቤተ መቅደሱን ሁለት እጥፍ የሚገዝፈው ቤት፥ በሰረገላዎች የታጀበ ሠራዊት፥ የደለበ ምጣኔ ሀብት ነበሩ። ስኬታማነት ከእግዚአብሔር ጋር የመቀያየሙን ቀውስ ያስወገደ ቢመስልም፥ ሰሎምን ለእግዚአብሔር የነበረውን ፍላጎት እስከናካቴው የገደለው ይመስላል። በዓለም መልካም ስጦታዎች ይበልጥ በተደሰተ መጠን ስለ ሰጪው ብዙም ሊያስብ አልቻለም።

♥

በምድረ በዳ ውስጥ እግዚአብሔር በእሳትና በደመና ዓመድ ውስጥ ቀረብ ብሎ በመኖሩ አንዳንድ ጊዜ ኃይሉ በሚያጠፋ ኃይል ተገልጾአል። በሰሎሞን ዘመን እግዚአብሔር ንጉሡ እርሱን ለሕዝቡ እንዲወክል የበለጠ ሥልጣን በመስጠት አጥፊ ኃይሉን የገደበው ይመስላል። በምድረ በዳ በእግዚአብሔር ፍርሃት የተዋጡት እስራኤላውያን ህልውና በቤተ መቅደሱ ውስጥ ማዕከላዊነቱን ከያዘ በኋላ የእግዚአብሔርን ጉዳይ ቸል ብለዋል። እግዚአብሔርን እንደ ንጉሣዊ ክልል አድርገው ተመለከቱ።

ለዚህ ለውጥ ምላሽ በመስጠት እግዚአብሔር ቀስ ብሎ ወደ ሌላ አቅጣጫ ዘወር አለ። የመጀመሪያዎቹን ሦስት የእስራኤል ነገሥታት፦ ሳዖል፥ ዳዊትና ሰሎሞንን ረዥም ታሪክ ከብሉይ ኪዳን ገረፍ ገረፍ እያደረግህ በማንበብ ይህንኑ እውነታ ልትረዳ ትችላለህ። ከሰሎሞን በኋላ ግን የነገሥታት ታሪክ ወደሚዘነጋበት አቅጣጫ እየፈጠነ ይሄዳል። እግዚአብሔር ወደ ነቢያቱ ዘወር አለ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፦ ዘዳግም 8፤ 2ኛ ሳሙኤል 7፤ 1ኛ ነገሥት 8-10።

ምዕራፍ 10

እሳትና ቃሉ

«በዙዎች መለኮታዊ ቅጣት አድርገው መውሰዳቸው አሳዛኝ ግጥምጥሞሽ ነበር። የ 59 ዓመት አዛውንት የሆነው ቄስ ዴቪድ ጀንኪንስ የክርስቶስ ከድንግል መወለድም ሆነ ከሞት መነሣት ቃል በቃል ሊተረጎም እንደማይገባ በይፋ ተናግሮ ነበር። ከሁለት ሳምንታት በፊት ይኸው ቄስ በዮርክ ሚኒስቴር የዱርሃም ጳጳስ ሆኖ መሾሙ ከፍተኛ የተቃውሞ ሁከት አስከትሏል። ሦስት ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ገና ከማለዳው የ 13 ኛው ክፍለ ዘመን ቅሪት የሆነው ካቴድራል የእንጨት ጣሪያ ደቡባዊ ክንፍ በመብረቅ ተመታ። ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ተኩል ላይ በሰሜን አውሮፓ እጅግ ታላቅ የሆነውና የመካከለኛው ዘመን ምርጥ ሕንጻ የነበረው ካቴድራል በእሳት እየጋየ ነበር። የጂንኪንስ ተቃዋሚዎች እግዚአብሔር ለአመለካከታቸው ፍትሐዊ ብያኔ እንደሰጠ ለመናገር ምንም ጊዜ አላጠፉም. . . በአዲሱ ጳጳስ የሹመት ሥነ-ሥርዓት ላይ የተቃውሞ ድምፅ በማሰማቱ ከስፍራው የተባረረው አንድ ቄስ እሳቱን ያስከተለው መለኮታዊ ጣልቃ-ገብነት ሊሆን እንደሚችል ተናግሯል። ሌሎች ደግሞ ከሰማይ እሳት ወርዶ በበአል ነቢያት ፊት የሠራውን መሠዊያ እንዲበላ ያደረገውን ነቢዩ ኤልያስን ጠቅሰዋል. . . » – (Time, July 23, 1984)

የካቴድራሉ በመብረቅ መመታት እንደ ልዩ ክስተት የሚታይ ነው። በአንድ ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ላይ እሳት ከሰማይ ወርዷል። የሙስሊም መስጊዶችንና የሒንዱ መቅደሶችን ትተን ክርስቲያኖች ነን የሚሉትን ዩኒቴሪያን (ሥላሴን የሚክዱ) አብያተ ክርስቲያናት እንኳ ብንመለከት ጤናማውን ዶክትሪን እየካዱ ምንም ሳይደርስባቸው ይኖራሉ።

በቀጥታ የስድብ ቃላት የሚያስተላልፈው በርትራንድ ራስል እስከ እርጅናው ድረስ ሳይቀጣ ዴቪድ ጂንኪንስ የእግዚአብሔርን ቁጣ የቀሰቀሰው ለምን ይሆን? እግዚአብሔር የተሳሳተ ትምህርት በተከሰተ ቁጥር መብረቅ የሚልክ ቢሆን ኖሮ ምድራችን እንደ ገና ዛፍ ታበራ ነበር።

በእርግጥ ከሠላሳ ምእተ ዓመታት አካባቢ በፊት አንድ ጊዜ እሳት ከሰማይ ወርዷል፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አገልጋዮች ያንን የቀርሜሎስ ተራራ ትእይንት ሲያስታውሱ ኖረዋል። ይኸው ታሪክ እውነት

የማይመስል ገጽታ ነበረው፤ ኤልያስ ብቻውን 850 የሐሰት ነቢያትን ለመግጠም ወደ በረሃማው የእስራኤል ተራራ አመራ።

በአፈንጋጭነቱና በማይጨበጥ ገጽታው የታወቀው ነቢዩ ኤልያስ የተሰበሰውን ሕዝብ እንደ ምትሐተኛ አስደመመው። አሥራ ሁለት እንስራ ሙሉ ውኃ ከመሠዊያው ስፍራ ላይ አፈሰሰ፤ ይህም ከሦስት ዓመታት የድርቅ ዘመን በኋላ የተገኘ ውድ ሀብት ነበር። ኤልያስ አንድ ግዙፍ ብሔራዊ ቀልድ እያዘጋጀ የሚገኝ እየመሰላቸው ሳለ ክስተቱ ተፈጸመ። አንዲት የእሳት ኳስ እንደ ተወርዋሪ ኮከብ ከጠራው ሰማይ ወረደች። ከሙቀቱ ኃያልነት የተነሣ መሬቱና ድንጋዮች ቀለጡ፤ ነበልባሉም ውኃውን እንደ ነዳጅ በላው። ሕዝቡ በድንጋጤና በመደነቅ ከመሬቱ ላይ ተደፋ። «እግዚአብሔር–እርሱ አምላክ ነው! እግዚአብሔር– እርሱ አምላክ ነው!» ሲሉም ጮኹ።

በሚያስደንቅ ይፋዊ ሙግት፥ እግዚአብሔር የክፉውን ኃይላት ደመሰሳቸው። ስለሆነም በእምነት ዘገባ ውስጥ ትዕይንቱ ከፍተኛ ስፍራ መያዙ የሚያስደንቅ አይሆንም። በኢየሱስ ዘመን የነበሩት ሰዎች ኤልያስ ዳግም ሥጋ ለብሶ እንደመጣ በመግለጽ መሳሳታቸውም አያስገርምም። በአሁኑ ዘመን እንኳ መብረቅ አንድን ካቴድራል ሲመታ ሰዎች ፈጥነው የቀርሜሎስን ተራራ ያስታውሳሉ።

ይሁንና፥ በኮሎራዶ በምትገኘው ትንሽ ክፍል ውስጥ ተቀምጬ መጽሐፍ ቅዱሴን ሳነብ የኤልያስን ሕይወት እጅግ በተለየ መንገድ ልመለከት ችያለሁ። እርሱና የተአምራት ሥራ መንትያው ኤልሳዕ የተገለጹት የብሉይ ኪዳን የነቢይ ሞዴሎች ሆነው ሳይሆን ለየት እንዳሉ አገልጋዮች ነው፤ ከእነርሱ በኋላ ከተነሡት ነቢያት እንደዚያ ዓይነት ተአምራት የሠሩ ብዙዎች አልነበሩም። ኃይላቸውን የምናፍቅ ከሆነ የተሳሳተ ነገር መናፈቃችን ነው። የኤልያስ ዘመን ምልክቶችና ድንቆች በእስራኤላውያን ላይ የረዥም ጊዜ ውጤት የሚያስከትሉ የዚያው ዘመን ነጸብራቆች ነበሩ። እንደ ሰደድ እሳት የሚቀጣጠሉ መነቃቃቶች አልተከሰቱም፤ ከመጠነኛ ሃይማኖታዊ መነቃቃት በኋላ ሕዝቡ ረዥም ወደሆነው ከእግዚአብሔር ዘንድ ገሸሽ ወደ ማለት አዝማሚያ ተመለሱ። የቀርሜሎስን ትእይትን በቦታው ተገኝቶ የታዘበው ንጉሥ አክዓብ ራሱ የእስራኤል እጅግ የከፋ ንጉሥ የመሆንን ቅርስ አስተላለፈ።

በኤልያስ ላይም ቢሆን የቀርሜሎሱ ተራራ የእሳት ኳስ የፈጠረው ዘላቂ ውጤት አልነበረም። ነቢዩ ለሕይወቱ በመስጋት የአክዓብ ሚስት ከሆነችው ኤልዛቤል የአርባ ቀናት መንገድ ሸሸ። በቀጣዩ ጊዜ እግዚአብሔር ከኤልያስ ጋር ሲገናኝ በእሳት ወይም በከፍተኛ ነፋስ

ወይም በመሬት መንቀጥቀጥ አልተገናኘውም። ይልቁንም ዝምታን በሚመስል የሹክሹክታ ድምፅ ተገናኘው፤ ይህም ወደፊት የሚከሰተውን ከፍተኛ ለውጥ የሚያመለክት ነበር።

ነቢያት

ኤልያስን መከተሉ ከባድ ሳይሆን አልቀረም። ከቀርሜሎስ ተራራ ድል በኋላ ሚክያስ የተባለ ሌላ ነቢይ በንጉሡ አክዓብ ፊት በተመሳሳይ ሁኔታዎች ውስጥ ቆሞ ተገኘ። እንደ ኤልያስ ሁሉ ከአራት መቶ የሐሰት ነቢያት ጋር ተጋፍጦ ከእግዚአብሔር ዘንድ ኃይለኛ መልእክት አስተላለፈ። በዚህ ጊዜ ግን እሳት ከሰማይ አልወረደም፤ ይልቁንም ነቢዩ በጥፊ ተጠፍጥፎ ወጎኒ ወረደ።

ከኤልያስና ኤልሳዕ በኋላ እግዚአብሔር ከተአምር ወደ ቃል በማዘንበል የልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይሉን ልጓም የገታ ይመስላል። እንደ ኢሳይያስ፥ ሆሴዕ፥ ዕንባቆም፥ ኤርምያስ፥ ሕዝቅኤል ያሉ አብዛኛዎቹ ነቢያት በአድማጮቻቸው ፊት አስደናቂ ትእይንት አልፈጠሩም፤ የቃላት ኃይል ብቻ ነበራቸው። እግዚአብሔር እየራቀ የሚሄድ ሲመስል፤ እነዚህ ነቢያት ራሳቸው ጥያቄዎችን ማንሣት ጀመሩ፤ ጥያቄዎቻቸው ግልጽና ተጨባጭ ሆነው ሥቃይን ያዘሉ ነበሩ። በዚህም በእግዚአብሔር የመተው ስሜት ያደረበትን ሕዝብ ጩኸት አስተጋቡ።

ሁልጊዜም የነቢያትን መጻሕፍት በተሳሳተ መንገድ ስረዳ ኖሬአለሁ። እንደ ኤልያስ በአረማውያን ላይ የፍርድ እሳት የሚጠሩ ዘመን ያለፈባቸው አዛውንቶች አድርጌ ሳያቸው ነበር። የሚገርመው የጥንቶቹ ነቢያት ጽሑፎች እንደ ማንኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እጅግ «ዘመናዊ» መሆናቸውን መረዳቴ ነው። የእነርሱም ትኩረት ያረፈው በእኛው ምእተ ዓመት ላይ እንደ ደመና በተንሰራፋው ጭብጥ ላይ ነው፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ዝምታ፥ የክፉት የይምሰል ሉዓላዊነት፥ የማይረግብ የዓለም ውስጥ ሥቃይ ነው። በመሠረቱ የነቢያት ጥያቄዎች የዚህ መጽሐፍ ጥያቄዎች ናቸው፤ የእግዚአብሔር ፍትሕ-አልበኛነት፥ ዝምታና ስውርነት።

በታሪክ ውስጥ ከማንም በላቀ ስሜታዊነት ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ቅይማት የገለጹት የእስራኤል ነቢያት ነበሩ። እግዚአብሔርን የማያውቁ ሕዝቦች ተንደላቀው የሚኖሩት ለምንድን ነው? ሲሉ ጠይቀዋል። በዓለም ውስጥ እንዲህ ያለ ድህነትና ጉስቁልና የሚስተዋለው ለምንድን ነው? ለምን ተአምራት አይከሰቱም? እግዚአብሔር ሆይ፥ ወዴት ነህ? «ለምን ሁልጊዜ ትረሳናለህ?» ለምን

ይህን ያህል ለረዥም ጊዜ ትተወናለህ? ራስህን ግልጽ፤ ዝምታህን ግፈፍ። «በሕግ አምላክ» ተግባራዊ እንቅስቃሴ አሳይ።

የላይኛው መደብ አባል ሆኖ ነገሥታትን ያማክር የነበረው የኢሳይያስ ጩኸት ያስተጋባ ነበር። ኢሳይያስ ከኤልያስ ግለሰባዊ መልክ ጋር ሲነጻጸር ዊንስተን ቸርችል ከጋንዲ እንደሚርቁ ዓይነት ነበር። «በእውነት አንተ ራስህን የምትሰውር አምላክ ነህ። ሰማዮችን ቀድደህ ምን ነው ብትወርድ! ተራሮችም ምን ነው ቢናወጡ!» ሲል ኢሳይያስ ተማጽኖአል።

ኤርምያስ ድምፁን ከፍ አድርጎ «የስኪትን ሥነ-መለኮት» ተቃውሞአል። በዚያን ዘመን፥ ነቢያት በጉድጓድ ውስጥ ይጣሉና በሰይፍ ለሁለት ይሰነጠቁ ነበር። ኤርምያስ እግዚአብሔርን ከደካማ ሰው ጋር ያነጻጽረዋል፤ «እንዳንቀላፋ ሰው፥ ያድንም ዘንድ እንደማይችል ኃያል ስለ ምን ትሆናለህ?» ቮልቴይር ከዚህ የተሻለ አገላለጽ አልነበረውም፤ ሁሉን የሚችልና ሁሉን የሚያፈቅር አምላክ እንዲህ የተመሰቃቀለ ዓለም እንዲኖር የሚፈቅደው ለምንድን ነው?

ዕንባቆም ለምን ፍትሕ እንደማይቆም እግዚአብሔርን ጠይቆአል፤

«አቤቱ፥ እኔ ስጮኽ የማትሰማው እስከ መቼ ነው?

ስለ ግፍ ወደ አንተ እጮኻለሁ፥

አንተም አታድንም።

በደልንስ ስለ ምን አሳየኸኝ?

ጠማማነትንስ ስለ ምን ትመለከታለህ?»

እንደ ሌሎች እስራኤላውያን ሁሉ ነቢያትም ያደጉት የድልን ታሪክ ሲጋቱ ነበር። በልጅነታቸው እግዚአብሔር እንዴት ሕዝቡን ከባርነት ነፃ እንዳወጣቸው፥ ከመካከላቸው ወርዶ እንደኖረና ወደ ተስፋዱቱ ምድር እንዳስገባቸው ሲተርክላቸው ኖሯል። አሁን ግን የወደፊቱን ሕይወት አሻግረው ሲመለከቱ እነዚያ ሁሉ ድሎች በዝግመታዊ ጉዞ ሲሰወሩ አዩ። ከሰሎሞን ዘመን የማይዘነጋ ትእይንት በተቃራኒው፥ የእግዚአብሔር ክብር ሲነሣ፥ ለአፍታ ከቤተ መቅደሱ ሲሰፍፍና ከዚያም ሲሰወር ሕዝቅኤል ተመልከቷል።

ሕዝቅኤል በራእይ የተመለከተውን ነገር ኤርምያስ በግልጽ እውነታ አይቶታል። የባቢሎን ወታደሮች ወደ መቅደሱ ገብተዋል— አረማውያን እጅግ በተቀደሰው ስፍራ! ከዚያም በዘበዙት፤ አቃጠሉት (የታሪክ ጸሐፊዎች ወታደሮቹ ከመቅደሱ ውስጥ ሲገቡ የማይታየውን አምላክ ፍለጋ አየሩን በጦር ይወጉት ነበር።) ከሄሮሺማ የበንብ አደጋ ተርፎ

በፍርስራሹ ውስጥ እየተንገዳገደ እንደሚያልፍ መንገደኛ ነቢዩ ኤርምያስ በድንጋጤ ተቃኝቶ ወደ ጦርነት ሜዳ በተለወጡት የኢየሩሳሌም ጎዳናዎች ላይ ይቅበዘበዝ ነበር። በዚህ ጊዜ የእስራኤል ንጉሥ ዓይኖቹን ታውሮ በሰንሰለት ተጠፍሮ ነበር። የአገሩ ልዑላን ታርደዋል። በመጨረሻው ወረራ የኢየሩሳሌም ሴቶች የራሳቸውን ልጆች ቀቅለው በልተዋል።

ያን ጊዜ ነቢይ መሆን ምን ዓይነት ስሜት እንደሚያጭር ኤርምያስ እንዲህ ስል ይገልጽልናል፦

«በሕዝቤ ሴት ልጅ ስብራት እኔ ተሰብሬአለሁ፤
ጠቁሬማለሁ፤ አድናቆትም ይዘኛል. . .
ተወግተው ስለሞቱ ስለ ሕዝቤ ሴት ልጅ ሰዎች
ሌሊትና ቀን አለቅስ ዘንድ ራሴ ውኃ፥
ዓይኔም የእንባ ምንጭ በሆነልኝ!
. . . ልቤ በውስጤ ተሰብሮአል፤
አጥንቶቼም ሁሉ ታውከዋል. . .
የወይን ጠጅ እንዳሸነፈው እንደ ሰካራም ሰው ሆኛለሁ።»

ይሁንና፥ የነቢያት እጅግ አስደናቂ ገጽታ «ዘመናዊ» አመለካከታቸው ወይም ከእግዚአብሔር ጋር ስለነበራቸው ቅይማት ድምፃቸውን አጉልተው መጮኻቸው አይደለም። እነዚህን አሥራ ሰባት የነቢያት መጻሕፍት በቅርበት መመልከት የሚገባን ለነቢያቱ ጠንካራ ጥያቄዎች የእግዚአብሔርን ምላሽ የሚያካትቱ በመሆናቸው ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፦ 1ኛ ነገሥት 17–19፤ ሰቆቃው ኤርምያስ 5፤ ኢሳይያስ 45፥64፤ ኤርምያስ 14፤ ዕንባቆም 1፤ ኤርምያስ 8–9፥23።

ምዕራፍ 11

የቆሰለ አፍቃሪ

እግዚአብሔር ዓለምን ስላስተዳደረበት መንገድ ማስተባበያ በመስጠት ምላሽ አቀረበ። ይህንንም በቁጣና በዕንባ ተናገረ፤ *«ዝም አላልሁም፤ በነቢያቴ በኩል ሰናገር ነበር።»*

ለእግዚአብሔር መገለጦች እንደ አመጣጣቸው አስደናቂነት ደረጃ በማውጣት፥ ራሱን በኃይል ለሚገልጥላቸው ክስተቶች ከሁሉም የላቀ ክፍራ የምንሰጥ ይመስላል፤ ለልዕለ-ተፈጥሮአዊ ተአምራት ከዚያ ትንሽ ወረድ ያለ ደረጃ ስንመድብ፥ የነቢያትን ቃል ከታች ዝቅ አድርገን እንመለከታቸዋለን። ለምሳሌ ያህል፥ በቀርሜሎስ ተራራ የተገለጠው የእሳት ኳስ ከኤርምያስ ስብከቶች የበለጠ አሳማኝነት ያለው ይመስላል። እግዚአብሔር ግን እንዲህ ባለ የደረጃ አወጣጥ ላይ አይስማማም። የአሳቢነቱን ማረጋገጫ ለመስጠት ወደ ራሳቸው ወደ ነቢያቱ አመለከተ፤ እነዚህም ነቢያት ዝም ስለ ማለቱ ሲጠይቁ የኖሩ ሰዎች ነበሩ። አንድ ሕዝብ እንደ ሕዝቅኤል፤ ኤርምያስ፥ ዳንኤልና ኢሳይያስ ያሉ ነቢያት እያሉለት እንዴት ስለ እግዚአብሔር ዝም ማለት ሊያማርር ይችላል?

እግዚአብሔር «ባዶ ቃላት» ከልዕለ-ተፈጥሮአዊ መገለጥ እንደሚያንሱ አድርጎ አይመለከትም። ተአምራትም ቢሆኑ በእስራኤላውያን እምነት ላይ ዘላቂ ውጤት አልነበራቸውም፤ ነቢያት ግን እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን ፍቅር ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ ዘላቂ መዝገብ ያሰናዳሉ። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ለፍቅሩ ማረጋገጫነት ቀደምት ተአምራትን ቢጠቅስም፥ በአብዛኛው የሚከተለውን ዓይነት ነገር ይናገራል፤ በተለመደው የተቆጣ ወላጅ ድምፅ፥ «አባቶቻችሁ ከግብፅ ምድር ከወጡበት ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ፥ በየዕለቱ እየማለድሁ ባሪያዎቼን ነቢያትን ሁሉ ልኬባችሁ ነበረ። ነገር ግን አንገታቸውን አደነደኑ እንጂ አልሰሙኝም፤ ጆሮአቸውንም አላዘነበሉም» ብሏል። እናም እግዚአብሔር ሕዝቡ ከእርሱ ቃል ለመስማት እንደማይፈልግ አድርጎ ደመደመ፤ እነርሱም ነቢያትን፥ «ጣፋጩንና አታላዩን ነገር እንጂ ቅኑን ነገር አትንገሩን. . . የእስራኤልንም ቅዱስ ከእኛ ዘንድ አስወግዱ» በማለት የእግዚአብሔርን አሳብ ትክክለኛነት አረጋግጠዋል።

እናም ራሴን አገለልሁ።

ነቢያት ድምፃቸውን አጉልተው ስለ እግዚአብሔር ስውርነት ሲጮኹ እንደተሳሳቱ በመግለጽ አልሞገታቸውም። የአሳባቸውን ትክክለኛነት ከገለጸ በኋላ ለምን እንደሚርቅ አብራራላቸው።

ለኤርምያስ እግዚአብሔር በእስራኤል ውስጥ የተመለከተውን ጸያፍ ነገር ገለጸለት፤ ይህም በማታለል የሚገኝ ትርፍ፥ ንጹሑን ደም ማፍሰስ፥ ጭቆና፥ ወዘተ. . . የሚገኙበት በደል ነበር። ስለሆነም ለጸሎት የተዘረጉትን እጆች ላለማየት ዓይኖቹን እንደጋረደ ይናገራል፤ እነዚያ እጆች በደም የተበከሉ ናቸውና።

ለሕዝቅኤል የእስራኤላውያን ዓመፅ ከገደብ እንዳለፈ ገልጾለታል፤ እንዲሁ ለኃጢአታቸው አሳልፎ ሰጣቸው። ሰዎች የራሳቸውን መንገድ እንዲመርጡና የምርጫቸውን ውጤት እንዲሸከሙ በመተው ፈቀቅ አለ።

ለዘካርያስ፥ «ስጠራቸው አልሰሙኝምና ሲጠሩኝ አልሰማቸውም» ብሏል።

ለተግባር መዘግየቱ የምሕረት እንጂ የድካም ምልክት አይደለም።

እግዚአብሔር ፈጣን ቅጣት ሳያስከትል ሲቀር የእስራኤል ሕዝብ ኃይሉ እንደ ደከመ ገመቱ፤ «ምንም አያደርግም! ምንም ጉዳት አይደርስብንም። ረሃብ ወይም ሰይፍ አይመጣብንም።» ይሁንና፥ አሳባቸው በስሕተት ጥላ ጠቁሯል። የእግዚአብሔር ከተግባር መታቀብ ለሕዝቡ የሚሰጠውን የምሕረትና የማስጠንቀቂያ ጊዜ የሚያመለክት ነበር። ምርጫ እንዳጠረው ወላጅ እግዚአብሔር ሳይፈልግ ወደ ቅጣቱ አዘመመ።

ለእስራኤላውያን ቅጣቱ የውጭ ኃይላት ወረራ ነበር። ይሁንና፥ ነቢያት በዘመን መጨረሻ ስለሚከሰተው «የጌታ ቀንም» ይናገራሉ። በአዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ዘገባዎች መካከል በቃላት ከተገለጹት ሁሉ የላቁ አንዳንድ ዘግናኝ የመጨረሻው ዘመን ሥዕላዊ ራእዮች ተጠቅሰዋል። ዲትሪች ቦንፌር የመጨረሻውን ቃል ከመስማታችን በፊት ለመጨረሻ አንድ የቀረውን መስማት አለብን ብለዋል። ነቢያት ስለ መጨረሻው ዘመን የጻፉትን ይበልጥ ባጠናሁ ቁጥር እግዚአብሔር በሰዎች ጉዳይ ጣልቃ ለመግባት የማይፈልግ መስሎ የሚታይበት ሁኔታ ይበልጥ ያረካኛል።

ራሴ ከእግዚአብሔር ጋር በምቀያየምባቸው ጊዜያት ኃይልን የተሞላ እርምጃ እንዲወስድ ጠርቼዋለሁ። ፖለቲካዊ ጭቆናን፥ አድልዎአዊነትንና ፍትሕ-አልባነትን በመቃወም ጸልያለሁ። የእግዚአብሔርን ህልውና የሚያረጋግጡ ተአምራት እንዲከሰቱ

ጸልያለሁ። ነገር ግን ነቢያት እግዚአብሔር በመጨረሻው ሁኔንም ሽፋን ስለሚያስወግድበት ጊዜ የሚሰጡን ገለጻ ሳነብ ቀጣዩ ጸሎት ሌሎችን ጸሎቶች ሁሉ ያሸንፋል፤ «ጌታ ሆይ፥ በዚያን ጊዜ እዚያ ቦታ እንደማልገኝ ተስፋ አደርጋለሁ።» እግዚአብሔር ኃይሉን ከመግለጥ እየታቀበ መሆኑን ይቀበላል፤ ነገር ግን ይህንን የሚያደርገው ለእኛው ጥቅም ሲል ነው። እግዚአብሔር በቀጥታ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚጠይቁ ችኩሎች ነቢያት አስደንጋጭ ምክር አላቸው–ጠብቁ የሚል።

ፍርዶቼ ኃይለኛ ቢመስሉም የእናንተ ጉዳይ ያሠቃየኛል።

እግዚአብሔር ጥልቅ ስሜቱን ለነቢያቱ ገልጾላቸዋል። ለምሳሌ፥ ከእስራኤል ጠላቶች አንዱ ስለሆነው የሞዓብ ውድመት የተሰማው እነሆ፥

«ለሞዓብ አለቅሳለሁ፤

ለሞዓብ ሁሉ እጮኻለሁ

. . . ልቤ ለሞዓብ እንደ እንቢልታ ይጮኻል።»

የተመረጠውን የእስራኤል ሕዝብ አስመልክቶ የትኛውንም ኃፍረትና ውርደት ቢጋፈጡ እግዚአብሔርም ይህንኑ ተጋፍጦአል። ባቢሎናውያን የቤተ መቅደሱን የዝግባ ዓምድ ሲያፈርሱ እስራኤላውያን በጭንቀት ተውጠው ተመለከቱ፤ ነገር ግን የወረሩት የእግዚአብሔርን ቤት በመሆኑ ግላዊ የርኵሰት ተግባር እንደተፈጸመበት ተሰምቶታል። የቤተ መቅደሱ መፈራረስ የራሱ የመኖሪያ ስፍራ መፈራረስ ነበር። አይሁዶች በምርኮኛነት ሲወሰዱ እርሱም ተማረከ። ወራሪዎቹ የእስራኤላውያንን ንብረት ሲበዘብዙ የተሳለቁት በእስራኤላውያን ላይ ሳይሆን በደካማው አምላካቸው ላይ ነበር። «በሄዱበት የአሕዛብ አገር ሁሉ ስሜን አሰደቡ፤ እነዚህ የእግዚአብሔር ሰዎች ናቸው፤ ነገር ግን ከምድሩ ለመልቀቅ ተገደዋል።» ተብሎላቸዋልና።

የትንቢተ ኢሳይያስ መጽሐፍ አንድ ግሩም ዓረፍተ ነገር የእግዚአብሔርን አመለካከት አጠቃሎ ያቀርባል፤ «በጭንቀታቸው ሁሉ እርሱ ተጨነቀ።» እግዚአብሔር ፊቱን ሰውሮት ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ያ ፊት በእንባ ረጥቦ ነበር።

ከሁሉም ነገር ባሻገር በየትኛውም ጊዜ ይቅር ለማለት ዝግጁ ነኝ።

ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር ስለ ጥፋታቸው እየወቀሳቸው እያለ በመካከሉ አቁሞ እስራኤላውያን በንስሐ ይመለሱ ዘንድ ይለምናሉ። እጅግ ኃጢአተኛ የነበረው የእስራኤል ንጉሥ አክዓብ ከቀርሜሎስ

ተራራ ሌላ ተጨማሪ ዕድል ተሰጥቶታል፤ ከዚያም ሌላ፥ አሁንም ሌላ ዕድል ነበረው። እግዚአብሔር ለሕዝቅኤል፥ «በኃጢአተኛው ሞት ደስ አልሰኝም!» ብሏል። «ተመለሱ! ከክፉ መንገዳችሁ ተመለሱ! ለምን ትሞታላችሁ፥ እናንተ የእስራኤል ቤት?» ለኤርምያስ በኢየሩሳሌም አንድ ታማኝ ሰው ቢያገኝ ከተማዪቱን በሙሉ እንደሚያድን ገልጾአል።

ከትንቢተ ዮናስ በላይ የእግዚአብሔርን ይቅር የማለት ናፍቆት የሚገልጽ ነገር አይኖርም። ይህ መጽሐፍ የሚይዘው አንድ የትንቢት መስመር ብቻ ነው፤ «ከአርባ ቀናት በኋላ ነነዌ ትገለበጣለች።» ነገር ግን ከዮናስ መከፋት በተቃራኒ፥ ይኸው ቀላል ማስታወቂያ በተጠላችው ነነዌ ላይ መንፈሳዊ መነቃቃትን አስከትሎ የእግዚአብሔርን የቅጣት ዕቅድ ለውጦታል። ዮናስ ከጠወለገችው ቅል ሥር ተጠልሎ እየተበሳጨ የእግዚአብሔርን ለስላሳ ልብ እንደተጠራጠረ ገልጾአል። «አንተ ይቅር ባይ፥ ታጋሽም፥ ምሕረትህም የበዛ፥ ከክፉው ነገርም የተነሣ የምትጸጸት አምላክ እንደሆንህ አውቄ ነበርና።» ከዚህ የተነሣ ነበር ዮናስ እግዚአብሔርን ባለማመኑ የእምቢተኛነትን እርምጃ የወሰደውና የዓሣ ነባሪው ታሪክ የተከሰተው። ዮናስ እግዚአብሔርን ያላመነው ነነዌን ጨክኖ ይቀጣታል የሚል እምነት ስላልነበረው ነበር። ታሪኩን ሮበርት ፍሮስት እንደቋጨት፥ «ከዮናስ በኋላ እግዚአብሔር ዳግም ምሕረት እንደማያደርግ ልታምን አትችልም።»

ሰሜት

ምንም እንኳ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ጥያቄዎች ቀጥተኛ ምላሽ ቢሰጥም፥ ማብራሪያዎቹ እስራኤላውያንን አላረኳቸውም። ከአንድ አደጋ በስተጀርባ የተሸሸገውን ምክንያት ማወቁ የሥቃይንና የክህደትን መልክ አይቀይረውም። እናም የእግዚአብሔር ምክንያታዊ «መከላከያ» ወደ ጎን የተተወ ይመስላል። ነቢያት የእግዚአብሔርን ስሜት የሚሹትን ያህል ስለ አእምሮአዊ ጥያቄዎች አይጨነቁም ነበር። አምላክ መሆን ምን ዓይነት ስሜት ያሳድራል? ይህንን ለመረዳት በነቢያት መጻሕፍት ውስጥ ተደጋግመው የተጠቀሱትን ሰብአዊ ምሳሌዎች ተመልከት፤ እግዚአብሔር እንደ ወላጅና፥ እንደ አፍቃሪ ተገልጾአል።

የመጀመሪያ ልጅ የወለዱትን አንዳንድ ወላጆች ተከታተል። ውይይታቸው የሚሽከረከረው በአንድ-ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ ይመስላል፤ ይኸውም ስለ ልጃቸው። እስካሁን ከተወለዱት ሕፃናት ሁሉ በላይ ውብ እንደሆነ በትምክሕት ይናገራሉ። በተለይም ምዕራባውያን ወላጆች ልጆቻቸው የሚያካሂዱዋቸውን የመጀመሪያዎቹን የቃላትና የእንቅስቃሴ ጥረቶች በቪድዮ ቀርጸው ለማስቀረት ብዙ መቶ ዶላሮችን

ይከሰክላሉ። በሕፃናት ላይ እንደ ብርቅ የሚታዩ ጥረቶች በምድር ላይ የሚገኙ አምስት ቢሊዮን ሕዝቦች የሚያዘወትሯቸው ተራ ተግባራት ናቸው። እንዲህ ያለው እንግዳ ባሕርይ ከሌላው ሁሉ በተለየ መንገድ ለመጀመሪያ ጊዜ ልጅ ያገኘውን ወላጅ ኩራትና ደስታ ይገልጻል።

እግዚአብሔር እስራኤልን ሲመርጥ እንዲህ ዓይነቱን ግንኙነት እየፈለገ ነበር። እርሱ የፈለገው የትኛውም ወላጅ የሚፈልገውን ነገር ነበር፤ ይኸውም ለወላጆቻቸው ፍቅር ምላሽ የሚሰጡ ልጆች የሚገኙበትን ደስተኛ ቤተሰብ ነበር። ስለ ቀደሙት ዘመናት እያሰበ ሲናገር ድምፁ በኩራት ያዜማል፤ «ኤፍሬም ደስ የምሰኝበት ውድ ልጄ አይደለምን?» ነገር ግን እግዚአብሔር ከመቅጽበት ከወላጅነት ወደ ቆሰለ አፍቃሪነት ሲለወጥ ደስታው ይደበዝዛል። «ምን አጠፋሁ?» ሲል ኃዘን ባጠላበት ድምፅ ይጠይቃል።

«. . . ካጠገብኋቸውም በኋላ አመነዘሩ

በጋለሞቶቹም ቤት ተሰበሰቡ።

እንደተቀለቡ ፈረሶች ሆኑ፤

እያንዳንዳቸውም ከባልንጀሮቻቸው ሚስቶች

ኋላ አሽካኩ።

በውኑ ስለነዚህ ነገሮች አልቀስፍምን?»

የነቢያትን መጻሕፍት በማነብበት ጊዜ አንድ አማካሪ ከእግዚአብሔር ጋር እንዳለ ባለ ጉዳይ ሲሆን በዓይነ ሕሊናዬ እመለከት ነበር። አማካሪው፥ «ምን ዓይነት ስሜት እንደሚሰማህ ንገረኝ» ሲል ይጠይቀዋል። ከዚያም እግዚአብሔር ይቀጥላል።

«ምን ዓይነት ስሜት እንደሚሰማኝ ልንገርህ፤ ልክ እንደተተወ ወላጅ ሆኖ ይሰማኛል። አንዲት ሕፃን ልጅ ከመንገድ ዳር ለሞት ተቃርባ አገኘኋት። ወደ ቤቴ ወስጄ ልጄ አደረግኋት። አጠብሁዋት፤ ትምህርት ቤት አስገባሁዋት፤ መገብኩዋት። ልብስና ጌጣ ጌጥም አልቀረባትም። ከዚያም አንድ ቀን ተነሥታ ኮበለለች። በጉስቁልና ላይ እንዳለች ሰማሁ። ስሜ ሲነሣ ትረግመኛለች።

«ምን ዓይነት ስሜት እንደሚሰማኝ እነግርሃለሁ። እንደተተወ ፍቅረኛ ሆኖ ይሰማኛል። ፍቅረኛዬን ተገፍታና ተጎሳቁላ አገኘሁዋት፤ ነገር ግን ወደ ቤቴ አምጥቼ ውበቷ እንደ ፀሐይ እንዲያበራ አደርግኩዋት። እርሷ ለእኔ ብርቅ ነች። ለእኔ በዓለም ከሴቶች ሁሉ በላይ ውብ ነች። ፍቅርና ስጦታ አርከፈከፍኩላት። ነገር ግን ተወችኝ። ጣላቶቼን፥ የቅርብ ጓደኞቼን፥ የትኛውንም ሰው ተከትላ ትሄዳለች።

ከመንገድ ዳርና ከዛፍ ሥር ትተኛለች፤ ከሴተኛ አዳሪ በከፋ መልኩ ሰዎች ከእርሷ ጋር ያመነዝሩ ዘንድ ገንዘብ ትከፍላቸዋለች፥ የተከዳሁ ሆኖ ይሰማኛል።

እግዚአብሔር ጉዳቱን አይደብቅም። እስራኤልን ከሴት ግመል ጋር እያነጻጸረ በሚያስደነግጡ ቃላት መናገሩን ይቀጥላል– «በመንገድም ላይ እንደተለቀቀች፥ እንደ ፈጣን ግመል ሆነሻል፤ በምኞትዋ ነፋስን እንደምታሽተት፥ በምድረ በዳ እንደለመደች እንደ ሜዳ አህያ ነሽ፤ ከምኞትዋ የሚመልሳት ማን ነው?»

ቃላት ብቻቸውን ስሜቱን ለመግለጽ እንደማይችሉ በማሰብ እግዚአብሔር ሆሴዕ የተባለ ነቢይ እውነተኛ የሕይወት ድራማ እንዲሠራ አድርጓል። በእግዚአብሔር ትእዛዝ ሆሴዕ ጎሜር የተባለች የጎደፈ ዝና ያላት ሴት አገባ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ምስኪኑ ሆሴዕ የድራማ ሕይወት ይገፋ ጀመር። ከጊዜ ወደ ጊዜ ጎሜር ትኮበልላለች፤ ከሌላ ሰው ጋር ታመነዝራለች፤ ቤቷን ጥላ ትሄዳለች። በእያንዳንዱ ጊዜ እግዚአብሔር ሆሴዕ ጎሜርን እንዲቀበላትና ይቅር እንዲላት ያዘዋል።

እግዚአብሔር የራሱን የቆሰለ ስሜት ለማብራራት ሲል የሆሴዕን አሳዛኝ ታሪክ ተጠቀመ። እግዚአብሔር እስራኤልን ያገኘበትን የመጀመሪያ የፍቅር ጥንስስ በምድረ በዳ የወይን ዘለላ እንደ ማግኘት አድርጎ ይገልጸዋል። ነገር ግን እስራኤል ደጋግማ እምነቷን ስታፈርስ የቆሰለውን ፍቅር የከፋ ኃፍረት ለመታገሥ ተገደደ። ቃላቱ ከራስ ኃዘን የራቀ ድምፀት የላቸውም፤ «እኔም ለኤፍሬም እንደ አንበሳ፥ ለይሁዳም ቤት እንደ አንበሳ ደቦል እሆናለሁና።»

እግዚአብሔር በነቢያት መጻሕፍት በየሰከንዱ ለምን «አሳቡን እንደሚቀያይር» የተተወ አፍቃሪ ኃይለኛ ምሳሌ በግልጽ ያሳየናል። እስራኤልን ለማጥፋት እየተዘጋጀ ነበር–ቆይ፥ አሁን እጆቹን ዘርግቶ እያነባ ነው፤ የለም፥ አሁን ኮስተር ብሎ ፍርድን እያወጀ ነው። በፍቅረኛው ለተተወ ሰው ካልሆነ በቀር እነዚህ ተለዋዋጭ ስሜቶች ኢ–አመክንዮአዊ ይመስላሉ።

የነቢያት ቃላት በቀጭን የቤት ግድግዳዎች ውስጥ የሚተላለፍ የፍቅረኛሞች ፀብ ይመስላሉ። የእኔ ጎረቤት የሆነች ሴት ለሁለት ዓመታት ያህል እንዲህ ዓይነቱን ግጭት ታግሣለች። በጎዳር ወር ውስጥ ታማኝነት የጎደለበት ባሏን ልትገድለው ነበር። በየካቲት ይቅርታ አደረገችለትና ወደ ቤት ተመልሶ እንዲመጣ ጋበዘችው። በሚያዝያ ለፍች ፍርድ ቤት አመለከተች። በነሐሴ ከሱን አቁሟ ባሏ ተመልሶ እንዲመጣ ጠየቀችው። ፍቅሯ ለዘላለም እንደተተወ የሚያሳየውን አስቀያሚ እውነት ለመጋፈጥ ሁለት ዓመታት ፈጀባት።

እግዚአብሔር ራሱ የተጓዘበት የቁጣ፥ የኃዘን፥ የይቅርታ፥ የቅንዓት፥ የሥቃይ ዑደት ይኸው ነበር። ነቢያት እግዚአብሔር ወደ ሕዝቡ የሚደርስ ቋንቋ ለማግኘት እንደታገለ ያሳያሉ። ጎረቤቴ ከራቀው ባለቤቷ ጆሮ ላይ ስልክ ልትዘጋበት እንደምትችል ሁሉ፥ እግዚአብሔር ለነቢያቱ ከእንግዲህ የእስራኤላውያንን ጸሎት እንደማይሰማ ሊናገር ይችላል። ጎረቤቴ ተመልሳ እንደምትለሳለስ ሁሉ፥ እግዚአብሔር ዳግም ተለሳልሶ መልሰው ይሞክሩ ዘንድ ይለምናቸዋል። አንዳንድ ጊዜ ፍቅሩና ቁጣው የሚጋጩ ይመስላል። ነገር ግን በመጨረሻው ሁሉም ምርጫዎች አከተሙ፤ እግዚአብሔር ጥረቱን ማቆም እንዳለበት ደመደመ፤ «ለሕዝቤ ኃጢአት ከዚህ ሌላ የማደርገው ምንድን ነው?»

♥

ወዳጄ ሪቻርድ እግዚአብሔር «በጣለው» ጊዜ የጠለቀ የመከዳት ስሜት እንዳደረበት ገልጾልኛል። እጮኛው ከመቅጽበት ስትተወው የከበደ ስሜት ወድቆበታል። ነገር ግን ነቢያት በተለይም ሆሴዕ ከሌሎቹ ሁሉ በላይ አንድ መልእክት ያስተላልፋሉ፤ ይኸውም የተካደው እግዚአብሔር እንደሆነ የሚያሳይ ነው። የክህደቱን ተግባር የፈጸሙት እስራኤላውያን እንጂ እግዚአብሔር አይደለም። የእስራኤል ነቢያት ተግባራዊ እርምጃ ባለመውሰዱ፥ ግድየለሽ በመሆኑ፥ ዝም በማለቱ ከእግዚአብሔር ጋር መቀያየማቸውን አጥብቀው ገልጸዋል። ዳሩ ግን እግዚአብሔር በተናገረበት ጊዜ ለምእተ ዓመታት የተገታውን ስሜት አፍስሶአል። የእውነተኛ ቅይማት ሰለባ የሆነውም ራሱ እግዚአብሔር እንጂ እስራኤላውያን አልነበሩም።

«ከዚህ ሌላ የማደርገው ምንድር ነው?» ሲል እግዚአብሔር ለኤርምያስ ያቀረበው የጠለቀ የኃዘን ስሜት ያጠላበት ጥያቄ ለነጻነት ከፍተት የለቀቀውን ሁሉን ቻይ አምላክ አጣብቂኝ ያመለክታል። የሰማይ ወፎች ወቅታቸውን ያውቃሉ፤ የውቅያኖስ ማዕበል በጊዜው ውጥን ይንቀሳቀሳል፤ በረዶ ሁልጊዜም ከፍ ያሉትን ተራሮች ይሸፍናል፤ ሰዎች ግን በተፈጥሮ ከሚገኙ ከየትኞቹም ነገሮች የተለዩ ናቸው። እግዚአብሔር ሊቆጣጠራቸው አይችልም። ይሁንና፥ እንዲሁ ዝም ብሎ ወደ ጎን ሊገፋቸውም አይችልም። ሰብአዊነትን ከአእምሮው ሊያወጣ አይችልም።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፦ ኤርምያስ 7፤ ኢሳይያስ 30፤ ኤርምያስ 5፤ ሕዝቅኤል 20፤ ዘካርያስ 7፤ ኤርምያስ 5፥ 48፤ ሕዝቅኤል 36፤ ኢሳይያስ 63፤ ሕዝቅኤል 33፤ ዮናስ 3–4፤ ኤርምያስ 31፥5፥2፤ ሆሴዕ 9፥5፤ ኤርምያስ 9።

ምዕራፍ 12

እውነተኛነት እጅግ መልካም ነው።

ኖሮ እንዳልኖረ
የጥንት አፈ-ታሪክ
ኃዘንም አንድ ቀን
ይሰወር ይሆናል

ጆርጅ ሄርበርት፥ «አበባ»

አንድ ቀን ታዋቂው የስኮትላንድ ሰባኪና ደራሲ ጆርጅ ማክዶናልድ ከልጃቸው ጋር እየተነጋገሩ ሳለ የውይይቱ አቅጣጫ ወደ መንግሥተ ሰማይና ነቢያት ስለ ነገሮች ሁሉ ፍጻሜ ወዳስተላለፉት አሳብ አዘመመ፤ «እውነት ቢሆን እጅግ መልካም ይመስላል» አለ ልጃቸው በአንድ ነጥብ ላይ። ፈገግታ የማክዶናልድን ፀጉራም ፊት አቋርጦት አለፈ። «አ! እውነት ሊሆን መገባቱ በጣም ጥሩ ነው»[1] ሲሉ መለሱለት።

ተስፋን ያህል ሰቅዞ የሚገባ ሰብአዊ ስሜት ይኖር ይሆን? በመጪረሻው ክፉዎች እንደሚሞቱና ንጹሐን የማምለጫ መንገድ እንደሚያገኙ በማመን ተስፋ ፈንጣቂ ተረቶች ለዘመናት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ ቆይተዋል። ዛሬም ተመሳሳይ መልእክት የያዙ የቴሌቪዥን ካርቱኖች ከትንሽነታቸው የተነሣ የፍጻሜውን አይሞከሬነት ተረድተው ሊሳለቁ ለማይችሉ ጉጉ ሕፃናት ሲቀርቡ እንመለከታለን። በእውነተኛ ሕይወት፥ በጦር ቀጣና ውስጥ የተገኘች እናት ልጇን ወደ ጡቶቿ አስጠግታ ራሱን እያሻሸች በለሆሳስ «አይዞህ፥ ምንም አትሆንም» ትለዋለች– ምንም እንኳ የቦምቡ ፍንዳታ እየቀረበ ቢመጣም።

እንዲህ ዓይነቱ ተስፋ ከየት መጣ? ዘመን የማይሽራቸውን የተረታተረት ቃላት ሲመረምሩ ከቆዩ በኋላ ቶኪን የሚከተለውን ተናግረዋል።

> «ተረት. . . የኃዘንና የውድቀትን መኖር አይክድም፤ ለአርነቱ ደስታ የእነዚህ መኖር አስፈላጊ ነው፤ ነገር ግን ካሉት ብዙ መረጃዎች የተነሣ የመጪረሻውን አጽናፈ-አቀፋዊ ሽንፈትን ይክዳል. . . ይህንንም የሚያደርገው ኃዘንን ከሚያጭሩት የዓለም ግድግዳዎች ባሻገር መጠነኛ የደስታ ጨረፍታ በማሳየት ነው።»[2]

ይህ የመጪረሻው መልእክት ያልታከለበት የትንቢት መጻሕፍት ማጠቃለያ የተሟላ ሊሆን አይችልም። ይኸውም ዓለም በደስታ እንጂ «በአጽናፈ-አቀፋዊነት ሽንፈት» እንደማትደመደም ድምፃቸውን አጉልተው መጮኻቸው ነው።

ብዙውን ጊዜ በፍርሃት ለታጀቡት አድማጮቻቸው ስለሚመጣው ክፉ ዘመን ይናገሩ ነበር፤ በአመዛኙ ስለ ድርቅ፥ የአንበጣ መቅሠፍት፥ የጠላት ወረራ የሚሰጡት ትንበያ በዚያ ፍርሃት ላይ ነዳጅ ይጨምራል። ይሁንና፥ ነቢያት በአሥራ ሰባቱ መጽሐፎቻቸው ሁሉ ውስጥ ተስፋ የምትለውን ቃል ይጨምሩ ነበር። ኢሳይያስ የቆሰለው ፍቅረኛ ከቁስሉ እንደሚያገግም የተስፋ ቃል ይሰጣል፤ «ጥቂት ጊዜ ተውሁሽ፥ በታላቅም ምሕረት እሰበስብሻለሁ።»

ነቢያቱ የኋላ ኋላ ከዓለም ግድግዳዎች በስቲያ ስለሚገኘው ደስታ ወደ ማብራራቱ ሲመለሱ ድምፃቸው እንደ ዘማሪ ወፎች ያስገመግማል። በዚያን ቀን እግዚአብሔር ዓለምን እንደ ምንጣፍ ጠቅሎ በማንጣት ያድሳታል። ተኩላዎችና በጎች አብረው ሣር ይግጣሉ፤ አንበሳም ከበሬ አጠገብ በሰላም ይመገባል።

ሚክያስ አንድ ቀን ተፈትተው እንደተለቀቁት ጥጆች እንደምንፈነጭ ይነግረናል። በዚያን ጊዜ የፍርሃትና የሥቃይ አድራሻ አይታወቅም። የሕፃናት ሞት ወላጆችን አያንገበግባቸውም፤ በአገሮች መካከል ሰላም ስለሚሰፍን የጦር መሣሪያዎቻቸውን ወደ እርሻ መሣሪያነት ይለውጣሉ። ያን ጊዜ ማንም ስለ እግዚአብሔር ለውርነት አያማርርም። ፀሐይ የፈዘዘች እስኪመስል ድረስ ከብሩ በምድር ላይ ደምቆ ያበራል።

ለነቢያት የሰው ልጅ ታሪክ በራሱ ፍጻሜ ሳይሆን የሽግግር ጊዜ ነው፤ ይኸውም በሜድን ገነትና እግዚአብሔር በሚሠራቸው አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር መካከል የሚገኝ ክፍተት ነው። ነገሮች ሁሉ ከቁጥጥር ውጭ የሆኑ በሚመስልበት ጊዜ እንኳ እግዚአብሔር ከዙፋኑ ላይ ነውና አንድ ቀን ራሱን ይገልጣል።*

---

* አንዳንድ ሰዎች ከነቢያቱ የወደፊት ዓለም ራእይ ውስጥ የሚያጽናና ነገር አያገኙም። ይህ «ላም አለኝ በሰማይ» እንደ ግለት ነው ሊሉ ያጥላላሉ። «ቤተ ክርስቲያን የባርነትን፥ የጭቆናንና የሁሉንም ዓይነት ፍትሕ-አልበኝነት ትክክለኛነት ለማስመስከር ለበርካታ መቶ ዓመታት ይህንኑ ስትል ኖራለች። ከምድር ላይ ብዙ ነገር እንዳይጠይቁ ለመከላከል ከድሆች ላይ የምንገሥተ ሰማይን ተስፋ በግድ ይጭኗሉ።» ቤተ ክርስቲያን የነቢያቱን ራእይ በአግባቡ ስላልተጠቀመች ትችቱ ተገቢ ሊሆን ይችላል።

ነገር ግን «ላም አለኝ በሰማይ» የሚለውን አመክንዮ ከራሳቸው ከነቢያቱ ለግግኘት አይቻልም። አሞጽ፥ ሆሴዕ፥ ኢሳይያስና ኤርምያስ መበለቶችን፥ አጓለማውታዎችንና እንግዶችን ስለመንከባከብ አስፈላጊነት አጥብቀው የተናገሩ ሲሆን፥ ምግባረ ሠብሕ ችሎቶችንና ሃይማኖታዊ መዋቅሮችን ለማንጻት ጥረት አድረገዋል። የእግዚአብሔር ሕዝብ እግዚአብሔር የተበላሸውን ሁሉ የሚያስተካክልበትን ዘመን የሚጠባበቁ ብቻ ሳይሆኑ፥ የአዲስ ሰማይና የአዲስ ምድር ሞዴል ሊሆኑ ይገባል። ይህንንም በማድረግ እግዚአብሔር አንድ ቀን የሚፈጽመውን ነገር ናፍቆት ሊቀሰቅሱ ያሻል።

ነገር ግን አሁንስ? ከእግዚአብሔር ጋር ለምንጋፈጠው ቅይማት ተገቢውን ምላሽ ለማግኘት ከሞት ባሻገር ያለውን ሕይወት መጠበቅ አለብን? እስከ መቼ እንዲኖር የሚያውቅ በእኛ ውስጥ የለም። አቤቱ፥ ጠላት እስከ መቼ ይሳደባል?»

ነቢያት ከሞቱ በኋላ እንደገና የእግዚአብሔር ዝምታ በመስፈኑ ሕዝበ እስራኤል ይህንኑ ጥያቄ አንግቦ ተነሣ፤ «ምልክታችንን አናይም፤ ከእንግዲህ ወዲህም ነቢይ የለም፤

አይሁዶች ከአገራቸው በመፈናቀላቸውና እንደገና ለባርነት በመሸጣቸው ነቢያት ነፃ ስለሚያወጣቸው መሢሕና የወደፊት ሰላማዊ ዓመታት፥ ብሎም ምእተ ዓመታት እየተጠቀለሉ ሲነጉዱ መንግሥታት–ባቢሎን፥ ፋርስ፥ ግብፅ፥ ግሪክ፥ ሶርያ፥ ሮም– በፍልስጥኤም ሜዳዎች ላይ እየተሳደዱ ሲነሡና ሲወድቁ ቆዩ። እያንዳንዱ አዲስ መንግሥት እግሮቻቸውን ከበር ላይ በተቀመጠ የቆሻሻ ማጽጃ ጨርቅ እንደሚጠራርጉ ሁሉ አይሁዶችን ከመርገጥ አልተመለሱም። አንዳንድ ጊዜ ጠቅላላው የአይሁድ ዘር ሊጠፋ የታቀረበበት ጊዜ ነበር።

ሙሴ ሕዝቡን አይሁዶችን ከባርነት ነፃ ለማውጣት አልተነሣም። ኤልያስም ከሰማይ እሳት አላወረደም። ከኢየሩሳሌሙ ቤተ መቅደስ የደመና ዓምድ አንጸባርቆ አልታየም። ሄሮድስ ሕዝቡን የሚያስደንቅባቸውን ሕንጻዎች ለመገንባት እስከተነሣሣበት ጊዜ ድረስ፥ የቤተ መቅደሱ ስፍራ ከክብር ይልቅ ኃፍረትን በሚያስታውስ የፍርስራሽ ክምር ታጅቦ ቆየ።

ከብሉይ ኪዳን ፍጻሜ ላይ እግዚአብሔር ድብቅ ነበር። ፊቱን እንደሚሰውር ተናግሮ ነበርና ይህንኑ ሲያደርግ በምድር ላይ ጥቁር ጥላ አጠላ። ከሃያ አምስት ምእተ ዓመታት በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር የምንፈጥረው ቅይማት እግዚአብሔር ጀርባውን ባዞረ ጊዜ አይሁዶች የተጋፈጡት ስሜት ደብዛዛ ነጸብራቅ ነው። ዛሬ ወደ ኋላ ዘወር ብለን አንዳንድ አጽናኝ ትምህርቶች ልናገኝ እንችላለን። የእግዚአብሔር ጣልቃ–ገብነት ያስከተላቸውን «ጉዳቶች» ልንመለከት እንችላለን፤ የሰው መገኘት ከመጠን ያለፈ ብርሃን ስለሚረጭብን የቃጠሎ ምልክት ያስከትልብናል፤ ርቀትን ይፈጥራል፤ ከሁሉም በላይ እምነትን የሚጨምር አይመስልም። እንዲሁም ደግሞ ሥቃይና ኃዘን ወደሌለበት የዘላለም ሕይወት አሻግረን በመመልከት መጽናናትን ልናገኝ እንችላለን፤ ይህም የእግዚአብሔርን መገኘት ለመቋቋም

ወደምንችልበት ደረጃ ከተለወጥን በኋላ በአዲስ አቅጣጫ የምንጓዝበት ይሆናል። እስከዚያውስ? እነዚህ ክፉ ጊዜያትስ? እንደ አይሁዶች የእግዚአብሔር ስውርነት የቅይማትና ልብን የሚረብሽ የጥርጣሬ ስሜት ይፈጥርብናል።

በብሉይ ኪዳን የሚልከያስና በአዲስ ኪዳኑ የማቴዎስ ቃላት መካከል አራት ምእተ ዓመታት ታጥፈዋል። እነዚህ ጊዜያት «አራት መቶ የዝምታ ዓመታት» ተብለው የሚጠሩ ሲሆን፥ ይኸው ሐረግ ከእግዚአብሔር ጋር የተደረገውን የቅይማት ምዕራፍ ለይቶ ያሳያል። እግዚአብሔር ያን ጊዜ ለሕዝቡ ግድ ይለው ነበር? አሁንም ከሁሉም ነገር ባሻገር የመፂሑን መምጣት በናፍቆት ተጠባበቁ፤ ሌላ ተስፋ አልነበራቸውም።

«ሌላ ምን ላደርግ እችላለሁ?» ሲል ጠይቆአቸው ነበር እግዚአብሔር። ሌላ ነገር ነበር። በኃይል የማይቻለውን በሥቃይ ሊያሸንፍ ይችል ነበር።

«አንድ ቀን ከእርሱ ጋር እንስቅ ዘንድ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ያለቅሳል።»

– ጄርገን ሞልትማን

[1]Greville MacDonald, *George MacDonald and His Wife*, 172

[2]J.R.R. Tolkien, *The Tolkien Reader*, 68-69

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፡– ኢሳይያስ 54፤ ሚልከያስ 4፤ መዝሙር 74።

ክፍል ሦስት

ቅርበተ-ወልድ

ምዕራፍ 13

ዝቅታ

«ንጉሡ አንዱን ደንገጡር ያፈቅራል እንበል» ሲል ኪርክ ጋርድ ጨዋታውን ይጀምራል።

«ንጉሡ እንደ ማንኛውም ተራ ንጉሥ አልነበረም። የትኛውም የመንግሥት ባለ ሥልጣን ከፊቱ ይንቀጠቀጣል። ጠላቶቹን ሁሉ የሚደባየት ኃይል ሰለነበረው ሰለ እርሱ ከፉ ቃል ለመተንፈስ የሚከጅል ሰው አልነበረም። ይሁንና፥ ይኸው ኃያል ንጉሥ በአንዲት ምስኪን ደንገጡር ፍቅር ቀለጠ።

«ለእርሷ ያለውን ፍቅር ምን ብሎ ሊያውጅ ይችላል? በሚያስገርም ሁኔታ ንግሥናው እጅቹን አሠረበት። ደንገጡሯን ወደ ቤተ መንግሥት አስመጥቶ ከራሷ ላይ የጌጣጌጥ አክሊል ቢደፋና ከሰውነቷ ላይ ንጉሣዊ አልባሳት ቢጀቡን፥ ከቶውንም ልትቃወመው አትችልም፤ ማንም እምቢ ሊለው ደፍሮ አያውቅም። ዳሩ ግን ትወደው ይሆን?

«አፈቅርሃለሁ ማለቷ የማይቀር ነው፤ ግን ከልቧ ታፈቅረው ይሆን? መይስ ጥላ ለመጣችው የራሷው ሕይወት እያዘነች በፍርሃት ትኖር ይሆን? ከነኑ ደስ ብሏት ትተኛ ይሆን? እንዴት ሊያውቅ ይችላል?

«በጫካ ወደ ተከበበ ጎጆዋ ከንጉሣዊ ተሽከርካሪ ላይ ተቀምጣና በታጠቀ ሠራዊት ታጅባ ብትሄድም ያው መፍሯቷ አይቀርም። እርሱ ግን እርሷን በሚያስፈራ ነገር ሊቀርባት አልፈለገም። የሚፈልገው በእኩልነት የምትመለከተውን አፍቃሪ ነበር። የእርሱን ንግሥናና የራሷን ደንገጡርነት ረስታ የጋራ ፍቅር በመካከላቸው እንዲፈስ እንድታደርግ ፈለገ።

«እኩል ያልሆነው እኩል የሚሆነው በፍቅር ነውና» ሲል ኪርክጋርድ ይደመድማል። ንጉሡ የደንገጡሯን ነጻነት ሳይገፍ ከፍ ሊያደርጋት እንደማይችል ተገነዘበ። እናም ራሱን ዝቅ ሊያደርግ ወሰነ። እንደ ለማኝ ለባብሶ ንጉሥነቱን በመደበቅ ከጎጆዋ ከተፍ አለ። ልብሱ ለቀቅ ብሎ ከሰውነቱ ላይ ይወዛወዛል። ይህ ሌላ ሰው ለመምሰል የተደረገ ጥረት ብቻ ሳይሆን አዲስ ማንነትም ነበር። ይህችን ሴት ለማግኘት ዙፋኑን ተወ።[1]

ኪርክጋርድ በምሳሌ መልክ ያቀረበውን ሐዋርያው ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስ በተናገራቸው ቀጣይ ቃላት ውስጥ ገልጾአል፤

«እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ

ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት

እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም፥

ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ

በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፥

በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፥

ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት

እንኳ የታዘዘ ሆነ።»

እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ብዙ ጊዜ ራሱን ዝቅ አድርጓል። ብሉይ ኪዳን ከሰዎች ጋር ለመሆን ራሱን ዝቅ ያደረገባቸው ሁኔታዎች ረዥም ዘገባ ሆኖ ይታየኛል። እግዚአብሔር ለአብርሃም፥ ለሙሴ፥ ለሕዝበ እስራኤላውያንና ለነቢያት ለመናገር ራሱን ዝቅ አድርጎ ወርዷል። ነገር ግን ከአራት መቶ ዓመታት የዝምታ ጊዜ በኋላ የተከሰተውን የሚያህል ራስን ዝቅ የማድረግ ሁኔታ ታይቶ አይታወቅም። በኪርክጋርድ ታሪክ ውስጥ እንደተጠቀሰው ንጉሡ፥ እግዚአብሔር አዲስ መልክ የያዘ ሰው ሆነ። ይህ ሊታሰብ ከሚችለው ሁሉ የላቀ ዝቅ ማለት ነበር።

ሉቃስ

በሁሉም የገና ወቅት ሕጻናት ዘርፋፋ ልብስ ተጎናጽፈው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለ ኢየሱስ ልደት የሚተርከውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በድራማ መልክ ሲያቀርቡ ይኸው ቃል ተደጋግሞ ይደመጣል። የስድስት ዓመቱ መልአክ ወካይ ገጸ-ባሕርይ አንሶላውን ከመሬት ላይ እየጎተተና ክንፉን እያርገበገበ «አትፍሩ!» ሲል ያናገራል። በልብሶቹ እየተከለለ ጨረፍ አድርጎ የተውኔቱን ጽሑፍ ያነብና «ታላቅ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ» ይላል። ወዲያውም ወደ ዘካርያስ (ሰው ሠራሽ ጺም ያደረገ ታላቅ ወንድሙ) እና ማርያም (የሁለተኛ ክፍል ተማሪ) በመቅረብ ይህንኑ የመጽናኛ ሰላምታ ያቀርብላቸዋል።

እግዚአብሔር መጀመሪያ ለአብርሃም፥ ለአጋርና ለይስሐቅ የተናገረውም ይህንኑ ነበር። መልአኩም ለጌዴዎንና ለዳንኤል ሰላምታ ሲያቀርብ ይህንኑ ቃል ተናግሯል። ለልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኑባሬዎች ይህ

ቃል ልክ እኛ «ጤና ይስጥልን? እንደምን አለህ?» እንደምንለው ይመስላል። ይህ ብዙም አያስደንቅም። ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኑባሬ በሚናገርበት ጊዜ ሰብአዊ ፍጡራን ብዙውን ጊዜ ራሳቸውን እንደ ሳቱ ሆነው ይወድቁ ነበር። እግዚአብሔር ከምድራችን ጋር ሲገናኝ፥ አንዳንድ ጊዜ እንደ ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ክስተት እንደ ነጎድጓድ፥ አንዳንድ ጊዜ እንደ ነፋስ ማዕበል፥ ብሎም እንደ ድኝ የሚቃጠልበት ጊዜ ሞልቷል። ሁልጊዜም የፍርሃት ስሜት ይጭር ነበር ማለት ይቻላል። ነገር ግን ዘካርያስንና ማርያምን፥ እንዲሁም ዮሴፍን የጎበኘው መልአክ እግዚአብሔር በሚያስፈራ መንገድ ሊገለጽ እንደሆነ ነግሮአቸዋል።

አካለ ጎደሎና ዓይነ-ስውር ሆኖ ከተወለደስ ልጅ ያነሰ ፍርሃት የሚያጭር ነገር ምን ይሆን? በግርግም ተወለደ ከመመገቢያ ስፍራ በተቀመጠው ኢየሱስ አማካኝነት እግዚአብሔር በመጨረሻ ሰው የማይፈራበትን የመገናኛ መስመር ፈጠረ። ንጉሡ ንጉሣዊ አልባሳቱን አውልቆ ጥሏል።

በዚህ ውስጥ የተካተተውን ራስን ዝቅ የማድረግ ሁኔታ አጢነህ ተመልከት፤ ታሪክን ለሁለት የከፈለው ትስብእት (የቀን መቁጠሪያዎቻችንን እንኳ ሳይወስዱ የሚቀበሉት ሐቅ) ከሰዎች የበለጠ የእንስሳት ምስክርነት አለው። ይኸው ትስብእት ስላስከተለውም አደጋ አክለህ አስብ። በትስእብት አማካኝነት እግዚአብሔር እርሱን ከሰብአዊ ፍጡራኑ ያራቀውን ሰፊ ገደል ድልድይ ሠርቶ ያስተካከለ ቢሆንም፥ ያንኑ ግርዶሽ ማስወገዱ ኢየሱስን በከፍተኛ ሁኔታ ደካማ አድርጎታል።

> «በሴሊት ሕፃኑ በእንስሳት መካከል ተወለደ። የእንስሳቱ ጣፋጭ ትንፋሽና እንፋሎት የሚተፋ እበት አስተናገደው። ከዚህ በኋላ ሁኔታዎች ከቶውንም ዳግም ተመሳሳይ አልነበሩም።
>
> በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሰዎች ደግሞ በዚያ መንገድ እርግጠኞች ሊሆኑ አይችሉም። ከብቶች ማደሪያው ውስጥ ከተመለከቱት ወዲያ ለሰው ልጅ ካለው ፍቅር የተነሣ የት እንደሚታይ ወይም ምን ያህል ርቀት እንደሚሄድ ወይም በምን ያህል ጥልቀት ራሱን የማዋረድ እርምጃ እንደሚወስድ እርግጠኞች ሊሆኑ አይችሉም. . .
>
> በእግዚአብሔር ለሚያምኑ ሰዎች ይህ ማለት እግዚአብሔር ራሱ ከእኛ ነፃ አይደለም ማለት ነው። ይህም የገና ጥቁር ገጽታ፥ የዝምታው ሽብር መሆኑ ነው። ሁልጊዜም ልንጥለው በምንችልበት መልኩ መጣ፤ ይህም የአንድን ሕፃን ልጅ

ሞንቅላት እንደ እንቁላል ቅርፊት እንደመሰባበር ወይም ሊያድግ በምስማር እንደምንቸነክረው ማለት ነው።»[2]

የገና በዓል ለእግዚአብሔር ምን ዓይነት ስሜት ያሳድራል? እስኪ ደግሞ ተመልሶ ሕፃን የመሆንን አሳብ አጢን፤ የቋንቋና የሰውነት ቁጥጥርን ማጣት፤ ጠንከር ያለ ምግብ ያለመብላትና የሽንት መቆጣጠር ብቃትን መነጠቅ። እግዚአብሔር በማኅፀን ውስጥ እንዳለ ጽንስ! እስኪ ራስህን ተመልሰህ የእበት ትል እንደምትሆን አስብ–ምናልባትም ይኼኛው ምሳሌ ቀረብ ሳይል አይቀርም። በዚያን ቀን በቤተ ልሔም የሁሉም ፈጣሪ የሆነው አምላክ ምስኪንና ጥገኛ የሆነውን የሕፃን ልጅ መልክ ወሰደ።

ክርስቶስ ከመለኮት ጠቀሜታዎች ራሱን ባዶ ማድረጉን ለማብራራት የሥነ–መለኮት ምሁራን «ኪኖሲስ» (Kenosis) የሚል ቃል ይጠቀማሉ። ቅኔያዊ በሆነ ገጽታው፥ ራስን ባዶ ማድረግ ብዙ ውርደትን ቢያካትትም ነጻነት ዓይነት ነገርም ነበረው። የህልቆ መሳፍርትነትን (infinity) «ጉዳቶች» ተመልክተናል። ክርስቶስ ያለነዚያ «ጉዳቶች» ነፃ በሆነው አካላዊ ሰውነቱ እንደ ሰው ሊሠራ ይችል ነበር። ድምፁ ተራሮችን ሳያንቀጠቅጥ የሚፈልገውን ሊናገር ይችል ነበር። በማዕበላዊ ሕልውናው ምድርን ከማንቀጥቀጥ ይልቅ ንጉሥ ሄሮድስን ቀበሮ እያለ በመዝለፍ ወይም በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚነግዱትን ሰዎች በጅራፍ በማባረር ቁጣውን ሊገልጽ ይችል ነበር። አስቀድሞ «አትፍሩ» የሚል ማስታወቂያ ሳይናገር ከማንም ጋር ሊነጋገር ይችል ነበር–ከጋለሞታ ሴት፥ ከዓይነ–ስውሩ፥ ከመበለቷ፥ ከለምጻሙ።

«መጀመሪያ ሰው እንደ እግዚአብሔር ሆኖ መፈጠሩ ትልቅ ነገር ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር እንደ ሰው ሆኖ መገለጡ ከዚያ በላይ ነው።»

– ጆን ዶን – "Holy Sonet 15"

[1]Paraphrase of Soren Kierkegaard, *Philosophical Fragments*, 31-43.

[2] Frederick Buechner, *The Hungering Dark*, 13-14.

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ፤ ፊልጵስዩስ 2።

ምዕራፍ 14

ታላላቅ ተስፋዎች

በየዓመቱ በገና በዓል አካባቢ አየሩ በመሊሑ አጓጊ ተስፋዎች ይርገበገባል። ከሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች አንሥቶ እስከ ታዋቂ ዘማርያን ድረስ ወደ ቅድስት አገር የሚጓዙ ይመስል ለመዝሙር ልምምድ አሮጌ ደብተሮቻቸውን አንግበው ይተማሉ። አሁን አሁንማ ሚስተር ሃንድል በዝማሬ መልክ የቀመራቸውን እውቅ የትንቢት ቃላት ለመዘመር የመዘምራን ቡድን (ኳዬር) አባል የመሆን ግዴታ አይኖርብህም፥ አብዛኛዎቹ ምዕራባውያን ታላላቅ ከተሞች ሁሉም ሰው የሚዘምርበትን ሁኔታ አመቻችተዋል።

ለመሆኑ በግዙፍ የዝማሬ በዓል መልክ የምናከብረው ነገር ምንድን ነው? የመዝሙሮች ቀማሪ የሆነው ሚስተር ሃንድል ከመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች የወሰዳቸው አሳቦች የሚከተሉት ናቸው።

«ሸለቆው ሁሉ ከፍ ይላል፤ ተራራውና ኮረብታው ዝቅ ይላል፤ ጠማማው ይቃናል፤ ስርጓጉጡም ይስተካከላል።»

«በጨለማ የሄደ ሕዝብ ብርሃን አየ፤ በሞት ጥላ መካከልም ለኖሩ ብርሃን ወጣላቸው።»

«ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድም ልጅም ተሰጥቶናልና፥ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።»

እነዚሁ ተመሳሳይ ቃላት በእግዚአብሔር የዝምታ ወቅት በታማኝ አይሁዶች አፍ ውስጥ ነበሩ። ቅይማት ብሎም ጭንቀት በእስራኤል ታሪክ ውስጥ እየተስፋፋ በመሄዱ ከአንዱ በቀር ሁሉንም ተስፋዎች ገድሏል፤ ያልተገደለው አንድ ተስፋም ነቢያት ስለ ነገሥታት ንጉሥ የተናገሩት ነበር። መሢሑ በሚመጣበት በመጨረሻው ጊዜ ፍትሕ እንደ ወንዝ ይፈስሳል፤ የተሳፈሩበት ጀልባ የተገለበጠባቸው የውኃ ላይ ተጓዦች ከተንሳፋፊ ጉማዎች ላይ የሙጥኝ እንደሚሉ ሁሉ አይሁዶችም ያንኑ የተስፋ ቃል አጥብቀው ይዘውት ቆይተዋል።

ከመጨረሻው የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢይ አራት መቶ ዓመታት በኋላ እንግዳ ወሬዎች ይዛመቱ ጀመር፤ ወሬዎቹም መጀመሪያ በበረሃ አካባቢ አገልግሎቱን ስለሚያበረክተው ዮሐንስ ስለተባለው ነቢይ ሲሆን ከዚያ በመቀጠል ደግሞ ከናዝሬት ስለመጣው ስለ አናጺው ልጅ ስለ ኢየሱስ

የሚነገሩ ነበሩ። ስለ ኢየሱስ ተአምራት ሰዎች እየተናገሩ ሲመጡ ስለ ማንነቱ የሚሰነዘሩ ግምታዊ አስተያየቶች በረከቱ። እርሱ ይሆንን? አንዳንዶች መሢሑ ይኸው ነው፤ ሲሉ ክርር ብለው ተናገሩ። ኢየሱስ የዓይነ-ስውሩን ዓይኖች ሲያበራና ሽባውን ሲያስሮጥ በገዛ ዓይናቸው ተመልክተዋል። ወጣቱን ከሞት ሲያስነሣ ባዩ ጊዜ፦ «እግዚአብሔር ሕዝቡን ሊረዳ መጥቷል!» ሲሉ አወጁ። ሌሎች ጥርጣሬያቸውን ይዘው መኖራቸውን ቀጠሉ። ኢየሱስ መሢሓዊ የተስፋ ቃሎችን ፈጽሟል፤ ይህንን ያደረገው ግን ማንም ሰው ባልጠበቀውና አስፈላጊ በማይመስል አኳኋን ነበር።



ከእግዚአብሔር ጋር ቅይማት የሚፈጠርባቸውን ምልክቶች እየፈለግሁ መጽሐፍ ቅዱሴን በማንበብ ከወንጌላት ዘንድ ስደርስ ከፍተኛ ለውጥ ለማግኘት ጠብቄ ነበር። የሃንድል መዝሙር ቅኝት እንደሚያመለክተው ነቢያት የተነበዩለት መሢሕ እንዲህ ዓይነቱን የቅይማት ስሜት የሚያናጥብ ይመስላል። ከዚህ በተቃራኒ ግን በኢየሱስ ዘመን ቅይማት ከምድረ ገጽ አልተወገደም፤ ዛሬም እንኳ ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላ ከቅይማት ጋር በመታገል ላይ እንገኛለን። ምን ስሕተት ተፈጠረ? ወይም ጥያቄውን በሌላ መልኩ እናንሣው፤ የዚህ መጽሐፍ ዋነኛ አካል ለሆኑት ሦስት ጥያቄዎች ኢየሱስ ያበረከተው አስተዋጽኦ ምን ነበር?

<u>እግዚአብሔር ዝም ይላል?</u> «ተከተለኝ!» «ስትጸልዩ እንዲህ በሉ።» በተወሰነ ረገድ፥ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከዚህ በፊት ከነበረው በላይ ግልጽ አድርጓል። በሚያስገርም ሁኔታ ራሱን ለሳይንሳዊ ምርምር ከፍቶ ሰጥቷል፤ ይህም ከፈሪሳውያን፥ ሰዱቃውያን ሌሎች ተጠራጣሪዎች የተጋፈጠው ነበር። ማንም ሰው ወደ እግዚአብሔር ልጅ ሄዶ ጥያቄ ሊጠይቀው ወይም ሊሞግተው ይችል ነበር። ወንጌላት እንደሚነግሩን፥ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ እግዚአብሔር ዝምታውን በሚያሳምንና ጎላ ባለ መልኩ አስወግዶት ነበር፤ ቃልም ሥጋ ሆነ።

<u>እግዚአብሔር ድብቅ ነው?</u> ከኢየሱስ ጋር እግዚአብሔር ፊት፥ ስምና አድራሻ በመያዝ በዓለም ቅርጽ ይዟል። እርሱ ልትዳስሰው፥ ልታሸተው፥ ልታዳምጠውና ልትመለከተው የምትችለው አምላክ ነበር። «እኔን ያየ አብን አይቶአል» ሲል ተናግሯል።

ይሁንና፥ የኢየሱስ መታየትና ተራ ሰው ሆኖ መገለጽ በሊና ተራራና በቀርሜሎስ ተራራ ታሪኮች ተኮትኩተው ባደጉት አይሁዶች

ላይ አዲስ ችግር ከስቷል። ጢሱ፥ እሳቱ፥ የብርሃን ነጸብራቅ ይታያል? ኢየሱስ አምላክ ሊያሟላ ይገባል ብለው የሣሉትን ምስል አላሟላም ነበር። በእነርሱ አመለካከት ኢየሱስ ከተነሳቆለችው የናዝሬት ከተማ የመጣ የማርያም ልጅ፥ ተራ አናጺ ብቻ ነበር። ከራሳቸው ልጆች ጋር እየተጫወተ ሲያድግ የተመለከቱት የማርያም ጎረቤቶች ከቶውንም እንደ መሢሑ ሊቀበሉት አይችልም ነበር። ማርቆስ በወንጌሉ እንደዘገበው፥ የኢየሱስ ወንድሞች እንኳ «አብዱል» ሲሉ ደምድመው ነበር። ይህንን ከተናገሩት መካከል መልአኩ ገብርኤል የተናገረውን ከሰማች በኋላ የውዳሴ ቅኔ የተቀኘችው እናቱ ማርያም ትገኝበታለች፤ እንዲሁም ከማንም በላይ ከእርሱ ጋር ሰፊ ጊዜ ያሳለፉ ወንድሞቹም ይህንኑ ተናግረዋል፤ እነዚህ ወገኖች የኢየሱስን ተአምራዊና ተለምዶአዊ እንግዳ ጥምረት ሊያስታርቁ አልቻሉም ነበር። የኢየሱስ ሥጋ መልበስ ግራ መጋባትን አስከተለባቸው።

<u>እግዚአብሔር ያደላል?</u> አይሁዶች መሢሑ በዓለም ውስጥ የተበላሸውን ሁሉ እንደሚያስተካክል ያምኑ ስለነበር፥ ይኸው ጥያቄ ስለ ኢየሱስ አብዛኛውን ጥርጣሬ ሳያስከትል አልቀረም። ነቢያቱ ጌታ ሞትን እንደሚውጥና ከፊት ሁሉ ላይ እንባን እንደሚያብስ አልተናገሩም ነበር? በርግጥ ኢየሱስ አንዳንድ ሰዎችን ፈውሶአል፤ ይሁንና፥ ብዙዎች ሳይፈወሱ የተመለሱም ነበሩ። አልዓዛርን ከሞት ያስነሣ ሲሆን፥ እርሱ በምድር ላይ እያለ ብዙ ሰዎች ሞተዋል። እናም ከፊት ሁሉ ላይ እንባን አላበሰም።

የአድልዎአዊነት ጉዳይ በኢየሱስ ሕይወት የተማረኩትን በርካታ ሰዎች ያሳስባቸዋል። ለምሳሌ ታላቁ የሥነ-መለኮት ምሁር የሆኑት ኦገስቲን በወንጌላት ውስጥ ፈውስ በዘፈቀደ ለምን እንደተካሄደ በማሰብ ግራ ተጋብተዋል። ኢየሱስ ኃይል ካለው ለምን ሁሉንም በሽተኛ አልፈወሰም? በተለይም ከዮሐንስ ወንጌል ውስጥ አንድ ታሪክ የኦገስቲንን ልብ ማርኮአል።

የኢየሩሳሌም አካለ-ስንኩላን፥ ማለትም ዓይነ-ስውራን፥ ሽባዎች፥ ወዘተ. . . ፈውስ ለማግኘት በከተማዪቱ ውስጥ ወደሚገኝ አንድ የውኃ ጉድጓድ ይጎርፉ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ውኃው ይናወጥና ሩጠውም ይሁን ተንፋለቅቀው ከዚያው ውስጥ ይገቡ ነበር። አንድ ቀን ኢየሱስ እዚያ ተኝቶ ከነበረ ምስኪን ሰውዬ ጋር ይነጋገር ጀመር። ለሠላሳ ስምንት ዓመታት ሽባ ሆኖ ቢኖርም ከውኃው ውስጥ ሊገባ እንዳልቻለ ለኢየሱስ ገለጸለት። ውኃው በተናወጠ ጊዜ ሌላ ሰው ቀድሞት ይገባል። ኢየሱስ ቀና ብሎ እንኳ ሳያየው ሰውዬው ብድግ ብሎ እንዲሄድ አዘዘው «ወዲያውም ሰውዬው ዳነ፤ አልጋውንም

ተሸክሞ ሄደ።» ለሠላሳ ስምንት ዓመታት ሽባ ሆኖ የኖረ ሰውዬ እየተራመደ ሊሄድ ቻለ! ደስታው ቅጥ አልነበረውም።

ይሁንና፥ ተራኪው ዮሐንስ አንድ ጠቃሚ ዝርዝር ያክልልናል፤ ከዚያም ኢየሱስ ከሕዝቡ መካከል ገብቶ ተሰወረበት። ከነዚያ ሁሉ አካለ ስንኩላን አንዱን ብቻ ፈውሶ ሄደ። «ለምን?» ሲሉ ይጠይቃሉ ኦገስቲን። «ቃል በመናገር ሁሉንም ሊያድናቸው ሲችል አንዱን ብቻ ፈውሶ ሄደ።»[1]

መጥምቁ ዮሐንስም በኢየሱስ አድልዎአዊነት ተጨንቆ ነበር። እውነተኛ አማኝ የነበረው ዮሐንስ ሕዝቡ ስለ ኢየሱስ የነበራቸውን ተስፋዎች ሲያነቃቃ ኖሯል። ቀደም ሲል ሰዎች ዮሐንስ ራሱ መሢሕ እንደሆነ ተጠራጥረው ሲጠይቁት፥ «እኔ የጫማውን ጠፍር ልፈታ የማይገባኝ፥ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ ይልቅ ይከብራል» እያለ ይመልስላቸው ነበር። ያ የተስፋ ቃል የተገባለት የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ያጠምቀው ዘንድ ወደ ዮሐንስ ዘንድ መጣ፤ ዮሐንስም የእግዚአብሔር መንፈስ እንደ ርግብ ከሰማይ ሲወርድበት በግራሞት ተመለከተ። ስለ ኢየሱስ ሰዎች የያዙዋቸውን ጥርጣሬዎች ሁሉ ለማስወገድ የታሰበ ይመስል ከሰማይ እንደ ነጎድጓድ ያለ ድምፅ ተሰማ።

ከሁለት ዓመታት በኋላ ግን ዮሐንስ ራሱ ከእግዚአብሔር ጋር ተቀያየመ። እግዚአብሔርን በታማኝነት ያገለገለው ይህ ሰው ከሄሮድስ ወኅኒ ቤት ውስጥ ራሱን አገኘው። የሞትን መስመር ይዞ እያዘገመ፤ «የምትመጣው አንተ ነህ ወይስ ሌላ እንጠብቅ?» የሚል መልእክት ወደ ኢየሱስ ላከ። ያች የዮሐንስ አንዲት ጥያቄ በኢየሱስ ዙሪያ የነበረውን ግራ መጋባት፥ ጥርጣሬና መናወጥ ያመለክታል።

የእግዚአብሔር መንግሥት በሕዝቡ መካከል

ኢየሱስ አንዲት ስሜት ቀስቃሽ ቃል ማለትም «መንግሥት» አስወግዶ ቢሆን ኖሮ ሌላ መልክ በያዘ ነበር። ይህን ቃል በተናገረ ቁጥር ሰንደቅ ዓላማዎች፥ ያሸበረቀ ሠራዊት፥ የሰሎሞን ዘመን ወርቅና ጌጣጌጥ፥ ወደሚያስደምም የቀድሞ ደረጃው የተመለሰ ሕዝብ ማስተዋለ–እይታቸውን ይሞላዋል። ይሁንና እነዚያን ሁሉ ተስፋዎች የሚያወድም አንድ ነገር ይከሰትና እንደገና የቅይማት ስሜቶች ሁሉ ይታደሳሉ። «መንግሥት» የሚለው ቃል ለሕዝቡ አንድ ትርጉም፥ ለኢየሱስ ደግሞ ሌላ ትርጉም ነበር።

ሕዝቡ የፈለገው እዚያና እዚህ አልፎ አልፎ የሚከሰት ተአምር ሳይሆን፥ ኃይልና ክብር የሞላበትን አካላዊ መንግሥት ነበር። ኢየሱስ

የሚናገረው ግን ስለ ሰማያዊና የማይታይ መንግሥት ነበር። ምንም እንኳ በዙሪያው የነበሩትን አንዳንድ የዓለም ችግሮች እንዳቃለለ ቢታወቅም፥ በአብዛኛው ኃይሉን የተጠቀመው የማይታዩትን ኃይላት ለመዋጋት ተግባር ነበር። አንድ ጊዜ ለመፈወስ እጅግ የጓጓ ሽባ ሰውዬ አራት ወዳጆቹን ለምኖ ጣሪያውን ቀድደው ኢየሱስ ወዳለበት ቦታ እንዲያደርሱት አድርጓል።

ኢየሱስ፥ ለሽባው «ኃጢአትህ ተሰረየችልህ» ከማለትና «ተነሣ፥ አልጋህን ተሸክመህ ሂድ» ከማለት የትኛው ይቀላል ሲል ተናግሯል። የትኛው እንደሚቀልም አሳይቷል። የትኛውም አካላዊ ስንኩልነት የፈውሱን ኃይል አይቋቋመውም ነበር። እውነተኛ ጦርነት የሚካሄደው ከማይታዩ መንፈሳውያን ኃይላት ጋር ነበር።

ኢየሱስ በየዕለቱ ወደ አባቱ በጸሎት እንዲቀርብ ያደርጉ የነበሩት እንደ እምነት፥ የኃጢአት ይቅርታ፥ የከፉው ኃይል የመሳሰሉ ጉዳዮች ነበሩ። እንዲህ ዓይነቱ አጽንኦት በቀዳሚነት እንደ ድህነት፥ በሽታ፥ ፖለቲካዊ ጭቆና ለመሳሰሉት ችግሮቻቸው መፍትሔ ለሚሹት አይሁዳውያን አደናጋሪ ሆኖ ተገኘ። በመጨረሻም ኢየሱስ ከአንድ ንጉሥ የሚጠብቋቸውን መመዘኛዎች ሳያሟላ ቀረ። (አሁንስ የተለወጠ ነገር አለን? ብዙ ሰባኪያን በሥጋዊ ፈውስና ብልጽግና ላይ እንደሚያተኩሩና ጥቂቶች ብቻ እንደ ትዕቢት፥ ግብዝነትና ሕግ አጥባቂነት በመሳሰሉት ጥልቅ ሰብአዊ ችግሮች ላይ እንደሚሠሩ አውቃለሁ። እነዚህ ችግሮች ኢየሱስንም ያሳሰቡ ጉዳዮች ነበሩ።)

የኢየሱስ ተከታዮች የሚጠብቁት አዲስና ታላቅ መንግሥት በኢየሩሳሌም የተከሰተውን ሁኔታ ሲመለከቱ በንኖ ጠፋባቸው። ከሮማውያን ግዙፍ የበዓል ሥርዓቶች ጋር ሲነጻጸር የዋልት ትርኢት ከሚመስለው «የድል አቀባበል» ብዙም ሳይቆይ ኢየሱስ ታስሮ ከችሎት ፊት ቀረበ። እርሱም ለሮማው ባለሥልጣን ንጉሥ እንደሆነና መንግሥቱ ግን ከዚህ ዓለም እንዳልሆነች ገልጾአል፤ «መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም፤ መንግሥቴስ ከዚህ ዓለም ብትሆን፥ ወደ አይሁድ እንዳልሰጥ ሎሌዎቼ ይዋጉልኝ ነበር፤ አሁን ግን መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም።»

የኢየሱስ ሐምራዊ ልብስ ከድብደባው የተነሣ ሰውነቱ ባፈለቀው ደም ርሷል፤ የእሾህ አክሊል ከራሱ ላይ ተደፍቶአል፤ በዓለም ላይ የቀልድ ንጉሥ ተደርጎ ለሰዎች መሳለቂያነት የዋለ ንጉሥ ቢኖር ኢየሱስ ነው። ከመቅጽበት የደረሰው አደጋ ታማኝነታቸውን ስላራደባቸው ደቀ መዛሙርቱ ሸሹ። ኢየሱስ ራሱን ሳይጠብቅ እነርሱን መጠበቅ ለምን አስፈለገው? የሚታየው የሮማውያን ዓለም

ከማይታየው ሰማያዊ መንግሥት ጋር ተገናኝቶ ለጊዜው ያከሰመው ይመስል ነበር።

የዘመኑ የልብወለድ ደራሲ ካርተ ቮንጋት በገና ሰሞን ከአንድ የፊዚክስ ባለሙያ ቤተ ሙከራ አካባቢ ስለነበረው ሁኔታ የሚከተለውን ጽፎአል። የቢሮው ሠራተኞች በሙሉ አንድ ላይ ተሰብስበው የገና መዝሙር ይዘምራሉ። ሠራተኞቹ «የዓመታት ሁሉ ተስፋዎችና ፍርሃቶች ዛሬ ምሽት-በአንተ ተሳክተዋል» ሲሉ ዘመሩ። ትእይንቱ ኃይለኛ ነበር - በኢየሱስ ዘመን አይሁዶች የተጋፈጡት ቅይጣት ዘመናዊ አቻ። እውን ያልሆነውን ቁልፍ ቢጫን ከመቅጽበት የሚሰወሩ የዓመታት ሁሉ ተስፋዎችና ፍርሃቶች፥ ለሠላሳ ሦስት ዓመታት ብቻ እንዲኖር በተወሰነለት የቤተ ልሔሙ ሕፃን ላይ በሚጣል እምነት ላይ እንደሚደገፍ ከልባቸው ያምኑ ነበር?

[1]Colin Brown, *Miracles and the Critical Mind,* 10.

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፦ ሉቃስ 7፤ ዮሐንስ 14፤ ማርቆስ 3፤ ዮሐንስ 5፤ ዮሐንስ 1፤ ማቴዎስ 11፤ ዮሐንስ 18።

ምዕራፍ 15

መለኮታዊ ገለልተኛነት

ፕሮጀክቴ የሀልዎተ-እግዚአብሔርን (የእግዚአብሔር መኖር - አለመኖር) ጥያቄ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከፍጻሜ ላይ ለማድረስ የተካሄደ በታሪክ የመጀመሪያ ሙከራ ነው። ነገሮች አሁን እንደሚታዩት፥ የእግዚአብሔርን መኖር የሚያመለክቱ ምልክቶች ሊኖሩ ቢችሉም፤ ሁለቱንም አቅጣጫዎች የሚጠቁሙ ናቸው። ይህም አንድ የተቆረጠ ምላሽ ስለማይሰጥ ምንም ነገር ለማረጋገጥ አልተቻለም። ለምሳሌ፥ የአጽናፈ-ዓለም ድንቅ ነገሮች ከድንቃድንቆቹ ጋር የተላመዱትን ሰዎች አያሳምኑም፥ ሳይንቲስቶች ራሳቸውም በዚህ አያምኑም። ይህ የሳይንቲስቶቹን ደደብነት ወይም የእግዚአብሔርን ራሱን የመደበቅ ስኬት የሚያመለክት መሆኑ ለውጥ አያመጣም።

- ዎከር ፔርሲ፥ ዳግም ምጽአት

የእግዚአብሔርን መኖር አለመኖር ጥያቄ ለመቋጨት የደረሰ ጊዜ ቢኖር ኢየሱስ በምድር ላይ የተመላለሰበት ነበር። ኢየሱስ ተቺዎችን ለዘላለም ጸጥ ለማሰኘት አንድ ግሩም ዕድል ነበረው።

ለምሳሌ ያህል፥ ወዳጁ ሪቻርድ በኢየሱስ ዘመን ቢኖር ኖሮ ማረጋገጫ ይጠይቅ ነበር። «የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ትላለህ። መልካም ማረጋገጫ ስጠኝ እስኪ!» ኢየሱስ ሁልጊዜም እንዲህ ዓይነት ተግዳሮት ይቀርብበት ስለነበር በዚህ ጊዜ ምን ሊከሰት እንደሚችል መገመት አይኖርብንም። የሃይማኖት መሪዎች ተአምር እንዲያሳያቸው ሲጠይቁት፥ «ክፉና አመንዝራ ትውልድ» ከሚል ስያሜ ጋር ነበር በቁጣ የመለሰላቸው። ጉጉት ያደረበት ንጉሥ ተአምር ለማየት በጠየቀ ጊዜ፥ ኢየሱስ በጅ አላለም - ምንም እንኳ ይህ ሕይወቱን ሊያተርፍ የሚችል ነገር ቢሆንም።

መለኮታዊ ማዕቀብ ለምን? ለዚህ ጥያቄ ምናልባትም ከኢየሱስ አገልግሎት መጀመሪያ «ክስተት» ውስጥ ፍንጭ ማግኘት ይቻል ይሆናል። ይህም እርሱን ለይፋዊ አገልግሎት ለማዘጋጀት የቀረበ እንደ የማጠቃለያ ፈተና ዓይነት ነገር ነበር።

ከዚህ የላቀ ኃይለኛ የመጋፈጥ ሁኔታ ሊኖር አይችልም፤ ኢየሱስና የመጨረሻው ተጠራጣሪ ራሱ ሰይጣን ነበሩ ተጋጣሚዎቹ። አባጣ ጎርባጣው የፍልስጥኤም ተራራ የትእይንቱ መካሄጃ መድረክ ሆኖ ያገለግላል። ሰይጣን አንዳንድ ማረጋገጫዎችን ፈለገ፤ «የእግዚአብሔር

ልጅ ከሆንህ. . .» ሰይጣን ኢየሱስ ድንጋዩን ወደ ዳቦ እንዲለውጥ፥ ራሱን የመከላከል ኃይሉን ለአብነት ሠርቶ እንዲያሳይና ይህንን በማድረግ የዓለምን ሥልጣን ሁሉ እንዲጨብጥ በመናገር ተገዳደረው።

የሰይጣን ተግዳሮት ቀደም ሲል ታስቦበት ከመድረክ ላይ እንደሚታይ ድራማ ሳይሆን፥ እውነተኛ ፈተና እንደነበር አምናለሁ። ለአርባ ቀናት የጾመ ማንኛውም ሰው በእንጀራ መፈተኑ ተፈጥሮአዊ ነው። የሥቃይና የሞት አደጋ ለተጋረጠበት ሰው የአካላዊ ደኅንነት ዋስትና መስህባዊ መሆኑ አይጠረጠርም። የምድርን መንግሥታት ሁሉ መውረስስ ቢሆን ነቢያት ለመሢሑ የተነበዩት አልነበረምን? ሦስቱም ፈተናዎቹ በኢየሱስ እጅ ውስጥ ነበሩ፤ እነዚህ የእርሱ መብቶች ነበሩ። ሰይጣን መሢሐዊ ግቦቹን በአቋራጭ መንገድ እንዲመታ ለማድረግ እየጣረ ነበር።

የሩሲያው የልብ ወልድ ደራሲ ፍዮዶር ዶስቶቪስኪ ይህንኑ ታሪክ «ዘ ብራዘርስ ካራማዞቭ» (The Brothers Karamazov) በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ ስለ ምድረበዳው ፈተና ጽፎአል። ከመጽሐፉ ገጸ ባሕርያት አንዱ የሆነው ኢቫን ካራማዞቭ ፈተናው በምድር ላይ ከተፈጸሙት ተአምራት እጅግ የላቀው እንደሆነ ይገልጻል፤ ይህም የመለኮታዊ መገለል ተአምር ነው። ኢየሱስ ለፈተናው እጁን ቢሰጥ ኖሮ ከእንከን ነፃ በመውጣት ከሰይጣን ጋር ብቻ ሳይሆን ከእስራኤልም ዘንድ ከፍተኛ ከበሬታ ባገኘ ነበር። በዶስቶቪስኪ አመለካከት፥ ሰይጣን እምነትን ለማነሣሣት ሦስት ቀላል መንገዶችን አቅርቧል፤ ክርስቶስ ግን የትኛውንም አልተቀበለም። በኢቫን ካራማዞቭ አገላለጽ፥ «አንድን ሰው በተአምር ለባርነት ልትገዛው አትችልም፤ የተወደደ እምነት የሚገኘው በነፃ እንጂ በተአምር አይደለም።»[1]

ማቴዎስ ስለ ክርስቶስ መፈተን የጻፈውን አጭር ታሪክ ከዶስቶቪስኪ ረዥም መዋቅር ጋር እያነጻጸርሁ በማነብበት ጊዜ፥ አንድ የሚረብሽ ጥያቄ ከመቅጽበት አእምሮዬ ውስጥ ተጫረ። የምድረ በዳው ፈተና በሪቻርድ አፓርታማ ውስጥ ከተፈጸመው እንዴት ይለያል? እርሱም ልዕለ-ተፈጥሯዊ ጣልቃ ገብነት እንዲከሰት ተማጽኖ ነበር፤ እንደ ብርሃን፥ ድምፅ የእግዚአብሔርን ኃይል በማሳየት የሰውን አፍ የሚዘጋ ተአምር እንዲገለጽ ፈልጎ ነበር። ወይም ነገሩን ይበልጥ ወደራሳችን ቀረብ እናድርገውና የኢየሱስ ፈተና እግዚአብሔር በመለኮታዊ ኃይሉ ተገልጾ ከገባሁበት አጣብቂኝ እንዲያወጣኝ ከምማጸንበት ሁኔታ እንዴት ይለያል?

በርግጥ ልዩነቶች አሉ፤ ራስን የመከላከል ስሜትም በፍጥነት መረጃዎችን ያቀብለኛል። ሪቻርድ እውነተኛ እንደሆነ እገምታለሁ፤

እኔ ምስኪን ነበርሁ፤ እግዚአብሔር እንዲረዳን ከመጠየቃችን ውጭ እየቀለድንበት ወይም እንዲያመልከን እየጠየቅን አልነበርንም። ይሁንና፥ «ራስህን ከተራራ ላይ ወርውር!» ከሚለው የሰይጣን ፈተናና «ራስህን አሳይ!» በሚለው የሪቻርድ ተግዳሮት መካከል ያለውን ተመሳሳይነት በቀላሉ ላስወግድ አልችልም። በሁለቱም ጊዜ ተግዳሮቱ አንድ ዓይነት ነው፤ እግዚአብሔር የቀረበለትን ጥያቄ ለመቀበል አልፈለገም።

ሌላም መለኮታዊ ገለልተኛነት ትዝ ይለኛል። ነገሩ የተፈጸመው በኢየሩሳሌም ከሦስተኛው የሰይጣን ተግዳሮት ቀረብ ብሎ ነው። ኢየሱስ ከፍ ካለ ኮረብታ ላይ አሽቆልቁሎ እየተመለከተ፥ «ኢየሩሳሌም ሆይ፥ ነቢያትን የምትገድል ወደ እርስዋ የተላኩትንም የምትወግር፥ ዶሮ ጫጩቶቿን ከክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ አልወደዳችሁምም» ሲል አልቅሶአል። ያ በኢየሩሳሌም ላይ የተለቀሰው ለቅሶ የገለልተኛነት ይዘት አለው። በአንድ ቃል ብቻ ኢየሩሳሌምን ሊያጠፋ የሚችለውና በግዴታ ያስገዙለት ዘንድ የመላእክትን ጭፍራ ሊጠራ የሚችለው ኢየሱስ ክርስቶስ ከተማዪቱን ተመልክቶ ያነባል።

እግዚአብሔር ወደ ኋላ ይመለሳል፤ ራሱን ይደብቃል፤ ያለቅሳል። ለምን? ምክንያቱም በኃይል ሊፈጸም የማይችለውንም ነገር ስለሚፈልግ ነው። እርሱ ባርነትን ሳይሆን ፍቅርን የሚሻ ንጉሥ ነው። ስለሆነም እንደ ኢየሩሳሌም፥ ሮምና ሌሎችም ዓለማዊ ኃይላትን በኃይሉ ከማጥፋት ይልቅ ዘገምተኛውን ከባዱን የትስእብት፥ የፍቅርና የሞት መንገድ መረጠ። ከውስጥ የሚነሣ አሸናፊነት።

ጆርጅ ማክዶናልድ የክርስቶስን አሠራር እንደሚከተለው አጠቃለው አቅርበዋል፤ «በመለኮታዊ ኃይል የክፋትን ኃይል ከማውደም፥ ፍትሕን በጉልበት አስፍኖ ክፋትን ከማጥፋት፥ በፍጹማዊው አለቃ አገዛዝ ሰላምን በምድር ላይ ከማስፈን፥ የኢየሩሳሌምን ልጆች ቢወዱም ባይወዱም በክንፎቹ አዝሎ ትንቢታዊት ነፍሱን ካስጨነቁት አበሳዎች ከማዳን፥ ክፋት በሕይወት ኖሮ ፈቃዱን እንዲፈጽም ፈቀደ፤ ዘገምተኛና ወሳኝ እገዛዎችን በማድረጉ ብቻ ረካ፤ ሰይጣንን በመቆጣጠር ብቻ ሳይሆን በማስወጣት፥ ሰዎችን መልካም አደረገ. . . ጽድቅን መውደድ ማለት መቀበል ሳይሆን እንዲያድግ ማድረግ ነው. . . በምድር ላይ ሕይወቱ ሁሉ፥ አነስተኛ ጥቅም የሚያደርገውን የትኛውንም ፍላጎት ገትቷል፤ እርጅና፥ ንጽሕናና ጽድቅ ተረግጠው ሲመለከት ይህንኑ አድርጓል።»[2]

ተአምራት

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉንም ታሪክ እንዳላወራሁ እውነት ነው። በርግጥ የእርሱ ሰብአዊነት ሥጋ-ለበስ አምላክነቱን የሚያመለክት ነው፤ በተለይ ከብሉይ ኪዳኑ የእግዚአብሔር ክብር ጋር ሲነጻጸር ይህ እውነት ነው። አዎን፥ ኢየሱስ ሕዝቡን በከፍተኛ ኃይል ለማስደነቅ አሻፈረኝ በማለት ገለል ማለትን አሳይቷል። ይሁንና፥ በወንጌላት ውስጥ ተመዝግበው የሚገኙ ሦስት ደርዘን ተአምራቱስ? ለአምስት ሺህ ሰዎች ምግብ ሊያድል ወይም አልዓዛርን ከመቃብር ውስጥ ሊጣራ፥ ወይም ማዕበሉን ጸጥ ሊያደርግ የተመለከተ ማንም ቢሆን በቀላሉ ስለ «መለኮታዊ ገለልተኛነት» ሊናገር አይችልም።

ይሁንና፥ ከፈለገ በየትኛውም ቀን ተአምር ሊሠራ የሚችለው ኢየሱስ ለተአምር ጉጉት ያለው አይመስልም። ለደቀ መዛሙርቱ ተአምራቱን የማንነቱ ማረጋገጫ አድርጎ አቅርቦላቸዋል፤ «እኔ በአብ አብም በእኔ እንዳለ እመኑ፤ ይህም ባይሆን የተአምራቱን መረጃ እመኑ።» ነገር ግን ተአምራቱን በሚፈጽምበት ጊዜ እንኳ ትኩረት የሚሰጥባቸው አይመስልም። የአይሁዳዊውን ባለሥልጣን ሴት ልጅ ከፈወሰ በኋላ ለማንም እንዳይናገሩ አጥብቆ አዞአል። ማርቆስ ኢየሱስ የፈወሳቸው ሰዎች ለማንም እንዳይናገሩ ያዘዘባቸውን ሰባት አጋጣሚዎች በወንጌሉ ውስጥ ጠቅሶአል።

ኢየሱስ በሙሴና በኤልያስ ዘመን የተፈጸሙት ተአምራት ያንን ያህል ስኬታማ እንዳልነበሩ ያውቃል፤ ምንም እንኳ ብዙ ሰዎች ተአምራት አይተው ቢመጡም ዘላቂ እምነት አልነበራቸውም። ይዘ የመጣው ለስሜታውያን የሚሆን ሳይሆን፥ ታዛዥነትና መሥዋዕትነትን የሚጠይቅ ጠንካራ መልእክት ነበር። (በክርስቶስ ዘመን የነበሩ አንዳንድ እውነተኛ ተጠራጣሪዎች እንደ ዛሬዎቹ ሰዎች ኃይሉን ላለመቀበል የማማኻኛ ማብራሪያ ሰጥተዋል። እግዚአብሔር ከሰማይ ድምፁን ቢያሰማ ነጎድጓድ ነው ይላሉ። ሌሎች ስጦታዎች ከሰይጣን እንደመጡ ይናገራሉ። የኢየሱስ እውነተኛ ጠላቶች ተጨባጭ መረጃ አያለ እንኳ ሊያምኑት አልፈለጉም። አንድ ጊዜ ኢየሱስ ያስገኘውን የፈውስ ጉዳይ ለማጥፋት የፍርድ ችሎት አቋቋሙ። ከዚያ በኋላም፥ «አንድ ነገር አውቃለሁ። በፊት ዓይነ ስውር ነበርሁ፤ አሁን ግን አያለሁ» የሚለውን ተጨባጭ ምስክርነት ትተው የተፈወሰውን ሰድበው ከችሎቱ አስወጡት። በተመሳሳይ ሁኔታ አልዓዛር ለአራት ቀናት ከመቃብር ቤት ቆይቶ ሲመለስ፥ እነዚያ ጠላቶቹ እንደገና ሊገድሉት ሴራ አካሄደዋል።)

የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ዛሬ ብዙዎቻችን የምንናፍቃቸው አስደናቂ ተአምራቶች የጠለቀ እምነት እንደማያስከትሉ በሚያስገርምና

ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ያሳያሉ። ይህንን ለማረጋገጥ የኢየሱስ ፊት እንደ ፀሐይ ካብረቀረቁትና ልብሶቹም «አጣቢ በምድር ላይ ሊያነጣው እስከማይችል» ካንጸባረቁበት ሁኔታ ርቀን ልንሄድ አይገባም። ደቀ መዛሙርቱ እስኪደነቁ ድረስ፥ ከረዥም ጊዜ በፊት የሞቱት የአይሁድ ታሪክ ጀግኖች–ሙሴና ኤልያስ– በደመና ውስጥ ተገለጹ። እግዚአብሔር ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ። መለኮታዊ ኃይሉ ከዓቅማቸው ስላለፈ፥ ደቀ መዛሙርቱ ፈርተው ወደቁ።

ይሁንና፥ ይህ አስደናቂ ክስተት በኢየሱስ ሦስት የቅርብ ወዳጆች፥ ማለትም በጴጥሮስ፥ ያዕቆብና ዮሐንስ ላይ ምን ውጤት አስከተለ? በዘለቄታዊነት ጥያቄዎቻቸውን መልሶ በእምነት ሞላቸው? ይልቅስ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ኢየሱስ እጅግ በሚፈልጋቸው ሰዓት ሁሉም ሊረዱት አልቻሉም ነበር።



ተአምራቱ ኢየሱስ ለዓለም ችግሮች መፍትሔ እንደሆነ አድርገው በማቅረብ የተጣራጣሪዎችን ጩኸት ዝም ለማሰኘት ታስበው የተጻፉትን መጻሕፍት አንብቤአለሁ። ይሁንና፥ ከነዚህ ሙግቶች አብዛኞቹ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ቅይማት የማያጤኑ ናቸው። እነዚህ ሰዎች ለመናገር የሚፈልጉት ኢየሱስ ስላላደረጋቸው ተአምራት ነው። የተበላሸውን ለማስተካከል የሚያስችል ኃይል ያለው አምላክ አንዳንድ ጊዜ ይህንኑ ላለማድረግ የሚመርጠው ለምንድን ነው? በቤተ ሳይዳ ለምን አንድ ሽባ ሰው ፈወሰ? ለምን አንድ ብቻ?

ለአንድ ጥሩ ምክንያት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካልተገለጸው የኢየሱስ እንግዳ ታሪክ ፍንጭ ሊገኝ ይችላል። ስለ ኢየሱስ የልጅነት ታሪክ የተጻፈው የፈጠራ ወንጌል ያልታወቁ አሳቦችን ለማውጋት ይከጅላል። ታሪኩ ኢየሱስን ሰው እንዲሆን እንደሚፈልገው አድርጎ ያቀርበዋል። ይኸው ጥንታዊ መጽሐፍ እንደሚለው ኢየሱስ ሰዎች ሲጠይቁት ወዳጆቹን ለማስደነቅ ሲል አስገራሚ ነገሮችን ይፈጥር ነበር፤ ይህ ደግሞ እውነተኛው ኢየሱስ ሁልጊዜም ለማድረግ ያልፈለገው ነገር ነበር። በመጽሐፉ ውስጥ የተፈጠረው ኢየሱስ እንደ አስማተኛ ተገልጾአል። አባቱ ዮሴፍ የአናጺነት ሥራውን በሚያዛባበት ጊዜ ኢየሱስ ጣልቃ ገብቶ በተአምር ያስተካክለው ነበር።

ይኸው አፈ–ታሪካዊ ኢየሱስም ኃይሉን ለበቀል ለመጠቀም ወደ ኋላ አይልም። አንዲት ሴት ከኢየሱስ ጋር አብረው ከሚጫወቱት ልጆች አንዱን በመጉዳቷ ከጉድጓድ ውስጥ ወድቃ ጭንቅላቷ ተሰብሮ

ሞታለች። ኢየሱስ ወደ አንድ ከተማ በሚጠጋበት ጊዜ በዚያ የሚገኙ ጣዖታት ወደ ድንጋይ ቁራጭነት ይለወጣሉ።

እነዚህ ባለ ሁለት አቅጣጫ ታሪኮች በወንጌላት የተጠቀሰው ኢየሱስ ባሕርያት አይደሉም፤ ኢየሱስ ኃይሉን የተጠቀመው የሰው ልጆችን ጉድለት ለመሙላት ካለው ርኅራኄ የተነሣ እንጂ የትእይንቱን ተመልካቾች ለማስፈንደቅ አልነበረም። ፈውሰን ባሉት ጊዜ በቀጥታ ፈውሶአል። የሠርግ እድምተኞቹ ሲጠሙ ወይን አጠትቶአቸዋል። ደቀ መዛሙርቱ እርሱን ባልተቀበለችው ከተማ ላይ የበቀል እርምጃ እንዲወስድ በጠየቁት ጊዜ ገሥጾአቸዋል። ወታደሮች ሊይዙት ሲመጡ ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይሉን የተጠቀመው አንድ ጊዜ ብቻ ነበር፤ ይኸውም ሊይዙት ከመጡት ሰዎች ጆሮው ተቆርጦ የወደቀበትን ሰውዬ ለመፈወስ። በአጭሩ፥ በእውነተኛ ወንጌል ውስጥ የሚገኙ ተአምራት የሚያተኩሩት በፍቅር ላይ እንጂ በኃይል ላይ አልነበረም።[1]

እንኳ የኢየሱስ ተአምራት ሁሉንም ሰብአዊ ቅይማት ለመድረስ የታለሙ ባይሆኑም፥ የተልዕኮውና እግዚአብሔር አንድ ቀን ለፍጥረቱ ሁሉ የሚያደርገው በጎነት ቅድመ -እይታ ምልክቶች በመሆን አገልግለዋል። ሔልማት ቴልክ እንዳሉት፥ ተአምራቱ «የሚመጣውን የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያሳዩ አመልካች ችቦዎች ናቸው።»[2] የተአምራቱ ተካፋዮች ለነበሩት ሰዎች ፈውሶቹ እግዚአብሔር ራሱ ምድርን በመጎብኘት ላይ በመሆኑ ተሰቅሎ የቆሸሸው አምጡል ለመጠረግ እንደሚወርድ ሁሉ የሰዎችም በሽታ ከላያቸው ላይ ይነሣ ነበር። የተአምራቱ ተካፋዮች ላልነበሩት ጭምር ደግሞ የመጨረሻው ተሐድሶ ሥቃይና ሞትን እስኪውጥ ድረስ የሚፈጸሙትን ናፍቆቶች ቀስቅሰዋል።

የተአምራቱ ውጤት ልክ ኢየሱስ እንደተነበየው ነበር። በእርሱ ለማመን ለፈለጉት ሰዎች ይበልጥ አጥጋቢ መረጃዎችን ሰጥቷቸዋል። እርሱን ለመካድ ለመረጡት ግን ተአምራቱ የፈየዱት ነገር አልነበረም። አንዳንድ ነገሮች ለመታየት የግድ መታመን አለባቸው።

[1]Fyodor Dostoyevsky, *The Brothers Karamazov*, 235.

[2]Geroge MacDonald, *Life Essential: The Hope of the Gospel*, 24.

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፦ ማቴዎስ 12፤ 16፤ ሉቃስ 4፤ ማቴዎስ 23 እና ሉቃስ 13፤ ዮሐንስ 14፥ 9፤ ማርቆስ 9።

ምዕራፍ 16

የተላለፈ ተአምር

የፍራንኮች ንጉሥ የነበረው ቻርልማኝ ስለ ኢየሱስ መታሰርና መገደል ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሰማ በቁጣ ጦፈ። ሰይፉን መዝዞ፥ «ምን ነው እኔ እዚያ በነበርሁ? ጭፍሮቼን አስተባብሬ በፈጀሁዋቸው ነበር» ሲል ጮኸ። የቻርልማኝ የጦር ታማኝነት ወይም ኢየሱስን ለማገዝ ሰይፉን የመዘዘው የስምዖን ጴጥሮስ ታሪክ ሊያስፈግገን ይችላል። ይሁንና፥ ከእነርሱ ቁጣ በስተጀርባ አንድ ጥቁር ጥያቄ አለ። ቻርልማኝ በጌቴሰማኒ አልነበረምና የእርዳታ እጁን ሊዘረጋ አይችልም። ነገር ግን መርዳት ይችል የነበረው እግዚአብሔር አብ የተኮነነ ልጁን ለማገዝ አልተንቀሳቀሰም።

እግዚአብሔር ለምን እርምጃ አልወሰደም? ከእግዚአብሔር ጋር ስለመቀያየም የሚያስብ ማንም ሰው በጌቴሰማኒ፥ በጲላጦስ ቤተ መንግሥትና በጎልጎታም ቆም ብሎ ሊያገናዝብ ይገባል፤ እነዚህም የኢየሱስን መታሰር፥ መመርመርና መገደል የሚያመለክቱ ትእይንቶች የተካሄዱባቸው ስፍራዎች ናቸው። «ምክንያቱም በነዚያ ስፍራዎች ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር እንደ መቀያየም ዓይነት ሕይወት አሳልፎአል።»

አዋኪው ገጠመኝ የተጀመረው እንቅልፍ የተጫናቸው ሦስት ደቀ መዛሙርቱ ከአጠገቡ ሆነው ኢየሱስ በቀዝቃዛው የአትክልት ስፍራ ነበር። ከአትክልት ስፍራው ውስጥ ሁሉም ነገር ሰላማዊ ይመስል ነበር፤ ከበስተ ውጭ ግን የሲኦል ኃይላት ተለቅቀው ይርመሰመሳሉ። ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ ክዶታል፤ ሰይጣን በእንቅስቃሴ ላይ ሲሆን፥ በሰይፎችና በጦሮች የታጠቀ እጅግ በርካታ ሕዝብ ወደ ጌቴሰማኒ እየገሠገሠ ነበር።

ኢየሱስ ለሦስቱ ደቀ መዛሙርቱ፥ «ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ ታወከች» ሲል ተናገረ። ምንም እንኳ ኢየሱስ ይዋጉለት ዘንድ መላእክትን ሊጠራ እንደሚችል ቢናገርም አላደረገውም። በሥጋና ደም ዓለም ውስጥ ለመኖር መጥቷልና በዚያው ሕግጋት ይሞታል። ይሁንና፥ አንድ ጊዜ ተደፍቶ የማምለጫ መንገድ ለማግኘት ጸልዮአል። ላቡ እንደ ደም እየተንጠባጠበ ይወርድ ነበር።

እግዚአብሔር ግን ዝም አለ።

♥

በኢላጦስ ቤተ መንግሥት ዝምታው ቀጠለ። እጅግ ቀጥተኛ በሆነ መንገድ የእግዚአብሔር እጆች ለኢየሱስ ታስረዋል። አንዳንዶቹ ተአምር እንዲሠራ በመሳለቅ፥ «የመታህ ማን ነው? ትንቢት ተናገር!» አሉት። ቡጢያቸው በጨርቅ ከተሸፈኑት ዓይኖቹ ላይ ሲያርፍና ምራቃቸው ከፂሙ ላይ እየተንጠረገገ ሲወርድ የሰው ልጅ (ኢየሱስ) ያሳየው የተቃውሞ ምልክት አልነበረም።

ቀጣዩ የጎልጎታ ትእይንት ብዙ ጊዜ ስሜታዊነት በገነነባቸው ድራማዎች፥ ሥዕሎችና ስብከቶች በምናብ የታዩልን በመሆኑ፥ ስሜታችንን ሊቀሰቅሰውም ሆነ ትእይንቱን ራሳችን ለራሳችን በምናባችን እንድናየው ሊያደርገን አልቻለም። ለከፍተኛ ኃዘን የተዳረግህበትን ጊዜ በማስታወስ ጀምር። በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር እንዳሉ አድርገህ ባሰብሃቸው ከካንሰር እንደ መዳን፥ ወይም የጤነኛ ልጅ መወለድ፥ ወይም የጋብቻን ችግሮች ማቃለል በመተማመን ሁሉንም ነገር ከአደጋ ላይ ጥለሃል። ነገር ግን እንዳሰብኸው ሳይሆን ቀርቶ ሁሉም ነገር ተበላሸ። ጸሎትህ አልሰማ ብሎ ካንሰሩ ወዳጅህን ገደለ፤ ሕፃኑ ከተነዳ አእምሮ ጋር ተወለደ፤ የፍች ወረቀት በፖስታ ቤት በኩል ደረሰህ። ጎልጎታን እንደዚህ ዓይነት ጊዜ አድርገህ አስበው። ወይም ደግሞ ሪቻርድ ከወለሉ ላይ ተንበርክኮ እግዚአብሔርን ሲማጸን እንደነበረበት ሌሊት አድርገህ አስበው። ተአምር እንዳልተሠራበት ጊዜ አድርገህ አስበው።

በዚያን ጊዜ ተአምር ሊያይ ያልቋመጠ ሰው አልነበረም፤ ልብን የሚሰቅሉ ወሬዎች የደረሱዋቸው ሄሮድስና ኢላጦስ፥ ከገሊላ ጀምሮ የኢየሱስን ጹካ ስትከተል የመጣቸው ሴት፥ በጨለማ ውስጥ የተሸሸጉት ደቀ መዛሙርት ሁሉ ተአምራት ሊያዩ ናፍቀው ነበር። ሞት ከተፈረደባቸው ሌቦች አንደኛው ተአምር ለማየት ሲለምን፥ ሌላኛው ተሳለቀበት፥ በዚህ ጊዜ የትእይንቱ ተመልካቾች፥ «እስኪ ከመስቀሉ ይውረድና እናምንበታለን. . . ይወደውስ እንደሆነ እስኪ እግዚአብሔር አሁን ያድነው» እያሉ ያስተጋቡ ጀመር።

ነገር ግን ተአምርም ሆነ ማዳን አልተከሰተም። ዝምታ በትረ መንግሥቱን ዘርግቷል። ቻርልስ ዊሊያምስ ትእይንቱን በማስታወስ «ምንም ነገር ሊያደርግ በማይችልበት ሰዓት በክርስቶስ ላይ የተሰነዘረው ስላቅ፥ ‹ሌሎችን አዳነ፤ ራሱን ግን ሊያድን አልቻለም› የሚል ነበር። ይህን እንደ የትኛውም የሕክምና ትምህርት ቤት ብያኔ የተመጠነ ነበር»[1] ብለዋል።

«አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ» ሲል ክርስቶስ በመጨረሻው ጮኸ። ይህም ከመዝሙረ ዳዊት የተወሰደ የመጨረሻው የቅይማት ጩኸት ነበር። ታሪክ ጎዳናውን እንዲያቀና፥ በዓለም ስሕተት የሆነው ሁሉ ትክክለኛውን እንዲረታ በመፍቀድ፥ እግዚአብሔር ጀርባውን ሰጠ፤ ወይም ሁኔታው እንደዚያ መሰለ። ተፈጥሮ ራሱ ተነቃነቀ፤ የምድር መንቀጥቀጥ እንደደረሰ ሁሉ መሬት ተናወጠች፤ መቃብሮች ተከፈቱ። ፀሐይ ብርሃኗን ነፈገች፤ ሰማዩ በጽልመት ተጋረደ።

እሑድ ጠዋት

ከሁለት ቀናት በኋላ እንደ ርዕደ-መሬትና እንደ መብረቅ ኃይልን የተላበሰ የትንሣኤ ክስተት ተካሄደ። ይኸው ትንሣኤ የእግዚአብሔርን ፍትሕ አስረግጦ በማሳየት የቅይማትን ችግር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሊፈታው አይገባምን?

ምንኛ ሳይጨበጥ የቀረ መልካም ዕድል ነው? ከሞት የተነሣው ኢየሱስ እየጠፋ ያለውን እሳት በጠላቶቹ ላይ ለማቀጣጠል እንደገና ከጲላጦስ ግቢ ቢታይ ኖሮ፥ ያ ተጨባጭ መረጃ ይሆንላቸው ነበር! ዳሩ ግን ከትንሣኤ በኋላ ለደርዘን ያህል ጊዜያት የታየባቸው ሁኔታዎች ግልጽ አካሄድ ነበራቸው፤ ይኸውም ክርስቶስ ራሱን ያቀረበው ቀደም ብለው በእርሱ ላመኑት ሰዎች ብቻ መሆኑ ነው፤ እስከምናውቀው ድረስ፥ ከሞቱ በኋላ አንድም ያላመነበት ሰው ኢየሱስን አላየውም።

ብዙ ቢጠብቁ ኖሮ ከሞት የተነሣውን ክርስቶስን ሊመለከቱ ይችሉ የነበሩትን ሁለት ሰዎች አስብ። ያ የተአምራት ሁሉ ተአምር በተከሰተ ጊዜ እነዚያ ሸካራ የሮም ወታደሮች ከመቃብሩ ውጭ ቆመው ነበር። ወዲያውም በድንጋጤ ርደው እንደ ሞተ ሰው ሆኑ። ከዚያም በአፋጣኝ ፈርጥጠው ከባለሥልጣናቱ ዘንድ ደረሱ፥ በዚያው ዕለት ከሰዓት በኋላ የእውነተኛው ትንሣኤ ምስክሮች የሆኑት እነዚሁ ሁለት ሰዎች ያዩትን እውነት ለመሸፋፈን ተስማሙ። እውነቱን በውሸት ለውጠው የሚቀበሉት ገንዘብ ከእግዚአብሔር ልጅ በለጠባቸው። እናም እነዚያ የዚያ ታላቅ ዕለት የዓይን ምስክሮች የነበሩት የተዘነጉት የፋሲካ ሰዎች ሳያምኑ የሞቱ ይመስላል።

♥

ዛሬ የኢየሱስ ሕይወት ዐበይት ክስተቶች ማለትም ገና፥ ስቅለትና ፋሲካ፥ በዓለም ዙሪያ በቀን መቁጠሪያዎች ላይ በተለየ ቀለም ይጻፋሉ። ከነዚህ ከሦስቱ መካከል ዓለም ሁሉ እንዲያየው ተደርጎ በግልጽ የተፈጸመው ስቅለቱ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ረዳት አጥቶ

የወደቀ በሚመስልበት ሰዓት የታሪክ ካሜራዎች ዘገባቸውን በማጧጧፍ ላይ ነበሩ። እጅግ በርካታ ሕዝብ እያንዳንዱን ሰቅጣጭ ዝርዝር ጉዳይ ተመልክቷል። እናም አራት ሰዎች የኢየሱስን ሕይወት በዘገቡ ጊዜ ለዚያ የይምሰል ውድቀት ከወንጌላቸው አንድ ሦስተኛውን እጅ ሠውተዋል።

ከኢየሱስ ሕይወት እጅግ ይፋዊ የሆነው የመስቀሉ ትዝብት የራሱን ማንነት በኃይልና በፍቅር በሚያረጋግጠው አምላክ መካከል ያለውን ሰፊ ልዩነት ያሳያል። ሌሎች እንደ ሮም አማልክት ዓይነቶች ተከታዮቻቸውን በግድ ያስመልኳቸው ነበር፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ እንኳ ለቁማር ባለመስገዳቸው በርካታ አይሁዶች ታርደዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ማንንም በእርሱ እንዲያምን አላስገደደም። ሰዎችን ከራሳቸው ወደ ራሱ በመሳብ በፍቅር መሥራቱን መረጠ።

ለመረዳት በሚያዳግት ሁኔታ ያ የደካማነት ትእይንት አዲስ ተስፋ ቆስቁሷል። ሐዋርያው ጳውሎስ «ለአንድ ልጁ ሳይሰስት ለሁላችንም አሳልፎ በሰጠው» በእግዚአብሔር ላይ እምነቱን በማሳረፍ፥ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?» ሲል ይደመድማል። ጌታችን ራሱ እንደተናገረው፥ «ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም።» ይሁንና፥ የዘላለማዊ ደስታ አማራጭ ይህንኑ የዝምታና ከፍተኛ የቅይጣት ጊዜን ጠይቋል።

[1]Charles Williams, *He Came Down from Heaven*, 115.

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፡- ማቴዎስ 26-27፤ ሮሜ 8፤ ዮሐንስ 15።

ምዕራፍ 17

እድገት

«ማዳም፥ አምላካችን አረማዊ አምላክ ወይም የምሁራን አምላክ ቢሆን (ለእኔ ሁለቱም ያው ናቸው)፤ እጅግ ወደራቀው ሰማዩ ይበርና ታዘናችን እንደገና ወደ ምድር ይመልሰው ነበር። ነገር ግን ታውቂያለሽ፥ የእኛው አምላክ በመካከላችን ሊኖር መጣ። በቡጢ ነርቺው፤ ፊቱ ላይ ትፊበት፤ ግረፊው፤ በመጨረሻም ስቀዪው፤ ምን ለውጥ ያመጣል? የእኔ ልጅ፥ ይህ ሁሉ በእርሱ ላይ ተፈጽሟል።» አልኋት።

– ጆርጅ በርናኖስ፥ የባላገር ቄስ ማስታወሻ

እስኪ በግልጽ ልናገር፤ ከእግዚአብሔር ጋር ባለን የቅይማት ስሜት ላይ ኢየሱስ ምን ለውጥ ያመጣል? እርሱም ራሱ ቅይማትን እንደቀመሰ ማወቃችን የሚረዳን እንዴት ነው?

ሐዋርያው ጳውሎስን ተከትለው የሥነ-መለኮት ምሁራን በአብዛኛው የክርስቶስን አስተዋጽኦ የሚያብራሩት ሕግ-ነክ ቃላት በመጠቀም ነው፤ እነዚህም ጽድቅ፥ እርቅ፥ ስርየት የመሳሰሉት ናቸው። ይሁንና፥ እነዚህ ቃላት የተፈጸመውን ከስተት ፍንጭ ከመስጠት ዘልቀው አያልፉም። ለቅይማት ችግር ኢየሱስ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ለመረዳት፥ እነዚህን ቃላት እግዚአብሔር የሰውን ልጅ አጥብቆ ከሚፈልግበት መሠረታዊ ታሪክ ውስጥ ልንመለከታቸው ይገባል።

በትንቢት መጻሕፍት ውስጥ ከሚገኙ ዐበይት ምሳሌዎች አንዱን መለስ ብለህ ተመልከት፥ ይህም ስጋት የሚንጠው አባት ስለ ኮብላይ ልጁ ሁኔታ የሚያዝንበት ነው። ኢየሱስ ስለጠፋው ልጅ የተናገረው ታሪክ የኋላ ኋላ ፍጻሜውን አስደሳች ያደርገዋል። አባቱ ልጁን ለረዥም ጊዜያት ጠብቆታል፤ ዋናውን በር በሰፊው ከፍቶ ያለምንም ጥያቄ ልጁን ለመቀበል ይሮጣል።

የተቀደደው መጋረጃ

ኢየሱስ ያመጣው ለውጥ ምን ነበር? ለእግዚአብሔርም ሆነ ለእኛ ከዚህ በፊት ኖሮ የማያውቀው ቅርበት እንዲከሰት አድርጓል። የተቀደሰውን የቃል ኪዳን ታቦት የነኩ እስራኤላውያን ይሞቱ ነበር፤ ነገር ግን በሥጋ የተገለጠውንና የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን የዳሰሱት ሰዎች ተፈውሰው ወደ ቤታቸው ተመልሰዋል። የእግዚአብሔር ስም የተጻፈባቸውን ፊደላት አፍ አውጥተው

ለመናገርና በቀለም ተጠቅመው ለመጻፍ ለማይደፍሩ አይሁዶች ኢየሱስ አዲስ ወደ እግዚአብሔር የመቅረቢያ መንገድ አስተምሮአል፤ ይኸውም ወደ እርሱ እጅግ ቀርበው «አባ አባት» ብለው እንዲጠሩ ነው። በኢየሱስ አማካኝነት እግዚአብሔር ወደ ሰዎች ቀረበ።

አገስቲን «ኑዛዜ» (Confessions) በሚል ርእስ የጻፉት መጽሐፍ ይኸው መቀራረብ እንዴት እንደለወጣቸው ይገልጻል። አገስቲን ፍጹም፥ ዘመን-ዘለል፥ የማይጠፋ ሆኖ ስለሚኖረው አምላክ ከግሪክ ፍልስፍና ተምረዋል፤ ይሁንና፥ እንደ እርሳቸው በብዙ የፈቃደ-ሥጋ ተግባር የረከሰና ሥርዓት-አልባ የሆነው ሰው ከእንዲህ ዓይነቱ አምላክ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ሊገባቸው አልቻለም። አገስቲን በዘመናቸው የነበሩትን የተለያዩ የሐሰት ትምህርቶች ለመከተል ቢሞክሩም፥ በተራው ሰውና ፍጹም በሆነው አምላክ መካከል በድልድይነት ከሚያገለግለው የወንጌላቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ከመገናኘታቸው በፊት የትኞቹም ኑፋቄዎች ሊያረኳቸው አልቻሉም ነበር።

የዕብራውያን መጽሐፍ ይህንኑ አዲስና አስገራሚ የቅርበት ሁኔታ ያስሳል። መጀመሪያ የዕብራውያኑ ጸሐፊ በብሉይ ኪዳን ዘመን ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ለመቅረብ ምን ምን ማድረግ ያስፈልግ እንደነበር ይገልጻል። በዓመት አንድ ቀን ማለትም በስርየት ቀን አንድ ሰው – ሊቀ ካህኑ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ሊገባ ይችል ነበር። በዚህ ጊዜ የመተጣጠብ ሥርዓት፥ ልዩ አልባሳትና አምስት የተለያዩ የእንስሳት መሥዋዕቶችን ማቅረብ የግድ ነበር፤ ይህም ሆኖ፥ ሊቀ ካህኑ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የሚገባው በፍርሃት እየራደ ነበር። ከልብሱ ላይ መታጠቂያ የሚደረግ ሲሆን፥ ከእግሩ ላይ ገመድ ይታሰራል፤ የገመዱ ዓላማ ምናልባት ሊቀካህኑ በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ቢቀሠፍና የደውሉ ማቃጨል ቢገታ፥ ሌሎች ካህናት አስከሬኑን ጎትተው እንዲያወጡት ነበር።

ከዚህ በመነሣት የዕብራውያን ጸሐፊ ግልጽ ንጽጽር ያካሄዳል፤ ይኸውም አሁን ያለፍርሃት ወደ ጸጋው ዙፋን በድፍረት ልንቀርብ እንደምንችል ነው። ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ያለፍርሃት መግባት ለአይሁዳውያን አንባቢዎች ከዚህ የበለጠ የፍርሃት ስሜት የሚያሳድር ነገር አይኖርም። ነገር ግን ኢየሱስ በሞተ ጊዜ ከመቅደሱ ውስጥ የነበረው መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ለሁለት ተከፍሏል፤ በዚህም ቅድስተ ቅድሳኑ ተከፍቷል። የዕብራውያን ጸሐፊ ከዚሁ ላይ በመንደርደር «እንግዲህ ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ» ይለናል።

ኢየሱስ በመጨረሻው ከእግዚአብሔር ጋር ለሚደረገው ቅይጣት ይህንን አስተዋጽኦ አበርክቷል፤ ይኸውም ከእርሱ የተነሣ በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ልንመጣ እንደምንችል ነው። እግዚአብሔር ራሱ የእግላጅነቱን ሚና ስለተጫወተ፤ ከእንግዲህ የሰው አማላጅ አያስፈልገንም።

ፊት

በብሉይ ኪዳን ማንም ሰው የእግዚአብሔርን ፊት እንዳየ ሊናገር አይችልም ነበር። ሰው በቀጥታ የእግዚአብሔርን ፊት አይቶ በሕይወት አይኖርም ነበር። የእግዚአብሔር ክብር ጨረፍታ ያረፈባቸው ሰዎች እንደ አማልክት የሚያብረቀርቁ ሲሆን፥ የሚመለከቷቸውን ሁሉ በፍርሃት ይደበቁ ነበር። ኢየሱስ ግን ሰዎች የእግዚአብሔርን ፊት እንዲያዩ አድርጓል። «እኔን ያየ አብን አይቶአል» ብሎ ነበር። ኢየሱስ የሆነው ሁሉ እግዚአብሔር የሆነው ነው። እንደ ማይክል ራምሴ አገላለጽ፥ «በእግዚአብሔር ምንም ዓይነት ክርስቶስን ያለመምሰል የለም።»

ሰዎች እግዚአብሔርን ምን ዓይነት እንደሆነ ሁሉንም ዓይነት አሳቦች ይዘው ያድጋሉ። እግዚአብሔርን እንደ ጠላት፥ ወይም ፖሊስ ወይም ደግሞ ልጆቹን እንደሚበድል ወላጅ ሊመለከቱት ይችላሉ። ወይም ደግሞ ዝምታውን ከመስማት በቀር እግዚአብሔርን አይተው አያውቁም ይሆናል። ይሁንና፥ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣ ከእንግዲህ እግዚአብሔር ምን ዓይነት ስሜት እንደሚሰማው ወይም ምን እንደሚመስል በማሰብ ልንደነቅ አይገባም። ጥርጣሬ በሚያድርብን ጊዜ ደምሳሳ እይታችንን ያስተካከለው ዘንድ ወደ ኢየሱስ ልንመለከት እንችላለን።

እግዚአብሔር አካለ ስንኩላንን እንዴት እንደሚመለከት ለማወቅ ከፈለግሁ፥ ኢየሱስን ከሽባዎች፥ ከዓይነ-ሥውራንና ከለምፃሞች ውስጥ ላየው እችላለሁ። ስለ ድሆች ባስብና እግዚአብሔር ለሥቃይ ሕይወት ወስኗቸው እንደሆነ ለማወቅ ብፈልግ፥ ኢየሱስ በተራራው ስብከት ውስጥ የጠቀሳቸውን አሳቦች ልመለከት እችላለሁ። ለሥቃይና መከራ ልንሰጥ ስለሚገባው «መንፈሳዊ» ምላሽ ለማወቅ ብፈልግ፥ ኢየሱስ በመከራው ጊዜ የሰጣቸውን ምላሾች አጤናለሁ፤ የእርሱ ምላሽ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ፥ በከፍተኛ ጩኸትና በእንባ የታጀበ ነበር።

ገና

በሐዋርያት ሥራ አካባቢ የመጽሐፍ ቅዱስ ድባብ በፍጥነት ሲለውጥ ተመልክቻለሁ። የተቀረውን የአዲስ ኪዳን ክፍል ብታስብ፥

የኢዮብን ቁጣ፥ ወይም የመክብብን ጭንቀት ወይም የሰቆቃው ኤርምያስን መንገፍገፍ አታገኝም። የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ኢየሱስ አጽናፈ-ዓለሙን ለዘላለሙ እንደለወጠ እርግጠኞች ነበሩ። ለምሳሌ፥ ሐዋርያው ጳውሎስ የዓረፍተ ነገር ቁርጥራጮችን እየቀጣጠለ ሊጽፍ የልቀት ደረጃ የሚያመለክቱ ቃላት አልተጠቀመም፥ «ሁሉም በእርሱ [በክርስቶስ] ተጋጥሞአል. . . በእርሱም በኩል. . . በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአልና. . . ከአለቅነትና ከሥልጣንም ከኃይልም ከጌትነትም ሁሉ በላይና በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሊመጣ ባለው ዓለም ደግሞ ከሚጠራው ስም ሁሉ በላይ በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ሲያስቀምጠው. . .»።

ነገር ግን እነዚህን ቃላት በሚጽፍበት ጊዜ የሮም መንግሥት የጦረኝነትና የጭቆና አገዛዙን በማስፋፋት ላይ ነበር፤ በሁሉም ስፍራ ሰዎች በመዋሸት፥ በመግደልና በመስረቅ ላይ ነበሩ፤ በሽታ በመስፋፋት ላይ ነበር፤ ክርስቲያኖች ራሳቸው እየተገረፉ ወደ ወኅኒ በመውረድ ላይ ነበሩ። እነዚህ የተለመዱ የጥርጣሬና የቅይማት ምክንያቶች በሐዋርያው ጳውሎስ ኢየሱስ የተስፋ ቃል እንደሰጠው ዳግም በኃይልና በታላቅ ክብሩ እንደሚመለስ የተናገረውን ከማመን እንዲታቀብ ሊያደርገው አልቻለም ነበር። ነገሩ የጊዜ ጉዳይ ብቻ ነበር። በአንድ ወቅት ተጠራጥረውት ነበር፤ ከትንሣኤ በኋላ ግን ሊጠራጠሩት አይችሉም ነበር።

ይሁንና፥ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች የተረጋገጠ ድምፀት ችግር መፍጠሩ አልቀረም፤ ይህም ከሐዋርያው ጳውሎስ ሃያ ምእተ ዓመታት በኋላ ሙሉ መጽሐፍ ከእግዚአብሔር ጋር ስለመቀያየም የመጻፍ ችግር ነው። አሳዛኝ ገጠመኞቻቸውን ያወጉኝስ ሰዎች? የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎችን ጠንካራ ማረጋገጫ ለምን አጡ? ቅይማታችን ሁሉ ለምን ቀልጦ አልቀረም?

ስለነዚህ ነገሮች ሳስብ ሳለሁ ወደ አንዲት የአድልዎአዊነት ጥያቄ አመራሁ። እግዚአብሔር አድልዎአዊ ነው? ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር ስውርነትና ዝምታ ችግሮች በሚያስደንቅ መንገድ ቀጥተኛ ምላሽ ሰጥቷል። የአድልዎአዊነት ችግር ግን ወደ ባሰ ደረጃ የተሸጋገረ ይመስላል።

የኢየሱስ ምድራዊ ሕይወት የተፈጸመው በታሪክ ከሁሉም በላይ ፍትሕ-አልበኝነት በነገሠበት ሁኔታ ነበር፤ ከሁሉም በተሻለ ሁኔታ ኖሮ ከሁሉም የተስፋ ቅጣት ተቀብሏል። የጨካኝ ምድር ሴላው ለለባ! ከእርሱ ሞት በኋላ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የእስራት፥ የሥቃይና

የመሥዋዕትነት «ሽልማት» እየተቀበሉ ስለኖሩ፥ ሁኔታው መሻሻልን አላሳየም ነበር። የፍትሕ-አልበኝነት ችግር አልተወገደም።

የሚገርመው የዕብራውያን ጸሐፊ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር መቀያየጣቸውን እንደሚቀጥሉ የሚጠባበቅ ይመስላል። ምዕራፍ ሁለት እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ከኢየሱስ በታች እንደሚያስገዛ በሚያሳዩ ታላላቅ የመዝሙረ ዳዊት ጥቅሶች ይጀምራል። ከዚያም ቀጣዩ ለየት ያለ ዓረፍተ ነገር ይከተላል፤ «አሁን ግን ሁሉን ነገር እንደተገዛለት ገና አናይም።»

እውነት እንደሆነ የሚያምኑትን አሳብ ከጻፉ በኋላ «እውን ይህን የምለው ከልቤ ነውን?» እያሉ መብሰልሰል የደራሲነት አበሳ መሆኑን እረዳለሁ። የዕብራውያኑ ጸሐፊም ከመዝሙረ ዳዊት የወሰዳቸውን መጠነ-ሰፊ የሥነ-መለኮት አሳቦች ካሰፈረ በኋላ ቆም ብሎ የሚያስብ ይመስላል። አዎ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን መቆጣጠሩ እውነት ነው፤ ይሁንና፥ «ሁሉም ነገር ከእግሩ በታች ተገዝቶለት አንመለከትም።» ያች አንዲት ዓረፍተ ነገር ፍትሕ-አልባነትን ሁሉ ታካትታለች፤ ይህም ጦርነቶችና የጭካኔ ተግባራት ጥላቻና ምኞት፥ ክፋት በበጎነት ላይ የሚቀዳጀው ድል፥ በሽታና ሞት፥ እንባና ቃተታ፥ የዚህ ዓለም ቅይማትና ጭንቀት ሁሉ የሚካተቱበት ነው። ምናልባትም ይህ ዓረፍተ ነገር ከመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ «እጅግ እውነት» የሆነው ይሆናል።

አንቀጹ አሳቡን እየተነተነ እንዲህ ሲል ይቀጥላል፤ «ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ ስለ ሰው ሁሉ ሞትን ይቀምስ ዘንድ. . . ኢየሱስን. . . እናየዋለን።» የዕብራውያን ጸሐፊ የኢየሱስ መልክ የተለወጠበትን ተራራ የድል ታሪክ ወይም ከሞት የተነሣውን አካል ክብር እያወጋ አልነበረም። መልእክቱ ኢየሱስን ከመስቀሉ ላይ ያሳየናል። ከዚያም ጸሐፊው በአዲስ ኪዳን ሁሉ እጅግ ምሥጢራዊ የሆኑትን አገላለጾች ይጠቀማል። ኢየሱስ ከተቀበለው መከራ «ፍጹም እንደተደረገ» እና «ታዛዥነትን እንደተማረ» ይገልጻል። የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ ጸሐፊዎች ከእነዚህ ቃላት ዳር እየተሸከረከሩ መልእክቱን ሳያስተላልፉልን ይቀራሉ፤ ለዚህም ምክንያቱ እግዚአብሔር የማይለወጥና ስሜት -አልባ እንደሆነ የሚዘክረውን ባሕላዊ አስተሳሰብ ይዞ ቃላቱን ከአውዳቸው ጋር ማስታረቁ ከባድ መሆኑ ነው። ነገር ግን በዕብራውያን መጽሐፍ ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር ለሚደረገው ቅይማት ኢየሱስ በቀጥታ ያበረከታቸው አስተዋጽኦዎች ሆነው ስለቀረቡ፥ እንደዚያ ብሎ ማለፍ ትክክል አይሆንም።

ከዕብራውያን መጽሐፍ፥ ትሰብእት ለእኛም ሆነ ለእግዚአብሔር ትርጉም ያለው ይመስላል። ይህ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚተባበርበት የላቀው መንገድ ነው። መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር ከዚህ በፊት በአካል ዓለም ውስጥ ታስሮ አያውቅም ነበር፤ ለስላሳና ደካማ በሆነው የሰው ልጅ ሥጋ ውስጥ አድሮ አያውቅም። ኢየሱስ ያንን ሁሉ ለወጠው። ኢየሱስ ከልደት ደምና ሥቃይ አንሥቶ እስከ ሞት ደምና ሥቃይ ድረስ ሰብአዊውን የሕይወት ተሞክሮ አቋርጦ አልፎአል።

አምላክ መሆን ምን ዓይነት ስሜት እንደሚያሳድር ከብሉይ ኪዳን ሰፊ ግንዛቤ ልናገኝ እንችላለን። አዲስ ኪዳን ግን እግዚአብሔር ሰው መሆን ምን ዓይነት ስሜት እንደሚያሳድር በተማረ ጊዜ ስለተከሰተው ነገር ይዘግባል። የሚሰማን ስሜት ሁሉ ለእግዚአብሔርም አዲስ አይደለም። ከተፈጥሮአችን ስለ ሥቃይ የሚያውቅ ብቻ ሳይሆን የሚካፈልም አምላክ እንዲኖረን እንሻለን፤ የራሳችን ሥቃይ የሚያሠቃየውን አምላክ እንፈልጋለን። ወጣት የሥነ-መለኮት ምሁር የነበሩት ዲትሮች ቦኒፈር ስለ ናዚ የእስር ቤት፥ «እግዚአብሔር ብቻ ሊረዳው የሚችል ሥቃይ» ሲሉ ጻፈዋል። ከኢየሱስ የተነሣ እንዲህ ዓይነት አምላክ አለን። የዕብራውያን ጸሐፊ አሁን እግዚአብሔር በድካማችን ሊራራልን እንደሚችል ይገልጻል። ቃሉ ራሱ የድርጊቱን አፈጻጸም ያመለክታል፤ “sym pathos” ከሚባሉ ሁለት የግሪክ ቃላት የተገነባው ይህ ቃል «አብሮ መሠቃየት» የሚል ፍች አለው።

ከኢየሱስ ከርስቶስ የተነሣ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያለንን የቅይማት ስሜት ይረዳል ማለቱ ማጋነን ይሆን? ከዚህ ውጭ የኢየሱስን እንባ፥ ወይም የመስቀል ላይ ጩኸቱን ምን ብለን እንፈታዋለን? የዚህን መጽሐፍ ሦስት ጥያቄዎች፥ «አምላኬ፥ አምላኬ፥ ስለምን ተውኸኝ?» ከሚለው አሠቃቂ ጩኸት ውስጥ መጨመር ይቻላል። የዕብራውያኑ ጸሐፊ የእግዚአብሔር ልጅ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን እንደተማረ ይነግረናል። አንድ ሰው ታዛዥነትን ሊማር የሚችለው ላለመታዘዝ ሲፈተን ብቻ ነው፤ ጀግንነትንም ሊማር የሚችለው ለመሸሽ ሲፈተን ብቻ ነው።

ኢየሱስ በጌቴሰማኒ ለምን ሰይፍ አለመዘዘም? ለምን የመላእክትን ጭፍራ እርዳታ አልጠራም? ሰይጣን ዓለምን ለማስደነቅ ያቀረበውን ተግዳሮት ለምን አላዘቀጠም? ይህንን ያደረገው ለሚከተለው ምክንያት ነበር፤ እንደዚያ አድርጎ ቢሆን ኖሮ እጅግ የላቀ ተልእኮውን ከዳር ሳያደርስ ይቀር ነበር፤ ይኸውም ከእኛ እንደ አንዱ የመሆን፥ ከእኛ እንደ አንዱ መኖርና መሞት ነበር። ይህ እግዚአብሔር በፍጥረት ባቋቋማቸው «ሕግጋት ውስጥ» የሚሠራበት ብቸኛው መንገድ ነበር።

በመጽሐፍ ቅዱስ፥ በተለይም በትንቢቶች ውስጥ በእግዚአብሔር ዘንድ ግጭቶች ሲከሰቱ እንመለከታለን። በአንድ በኩል የፈጠራቸውን ሰዎች ከልቡ ወዶአቸዋል፤ በሌላ በኩል በባርነት የገዛቸውን ክፉውን የሚጥሱት ጉጉት ነበረው። በመስቀሉ ላይ ለዚያ ውስጣዊ ግጭት እልባት ሰጥቷል። ልጁ አጥፊውን ኃይል ወደ ራሱ ስቦ ወደ ፍቅሩ ለውጦታልና።

> «ክፉትን ለማሸነፍ የሚቻልበት ከሁሉም የላቀው መንገድ ቢኖር በፈቃድ፥ በመኖር፥ በሰብአዊነት ውስጥ እንዲጠፋ ግድረግ ብቻ ነው። በስፖንጅ እንደተመጠጠ ደም ወይም ወደ ሰው ልብ እንደተሠወረ ጦር ወደዚያው ዘልቆ ሲገባ፥ ኃይሉን ያጣና መድረሻ ቢስ ይሆናል።»
>
> – ጌል ዲ. ዌብ፥ The Night and Nothing (ሌሊትና ባዶነት)

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፦ ዕብራውያን 4፥ 10፤ ዮሐንስ 14፤ ቆላስይስ 1፤ ኤፌሶን 1፤ ዕብራውያን 2–5።

ክፍል አራት

መለወጥ፡-

መንፈስ ቅዱስ

ምዕራፍ 18

ሽግግር

የመጀመሪያው ዕለት የሥራ ውሎህ ሆድህን ያገላብጠዋል። እችለው ይሆን? የተሳሳተ ነገር ባደርግስ አለቃው ይወደኝ ይሆን? ዙሪያህን ስትቃኝ ሌሎች ከደማቂ ፀሐይ ለመከላከል በከፊል ዓይኖቻቸውን ጨፍነው ከአሸዋው ላይ በጫማዎቻቸው ቅርጻ ቅርጽ ይሠራሉ። ሰባዎቻችሁም አንድ ላይ ተግባር እንድታከናውኑ ታዛችኋል።

ኢየሱስ ባሕርዩን የሚያንጸባርቅ ልባዊ ንግግር በማድረግ ላይ ነበር። የተጨነቀ ይመስላል፤ ድምፁ የስጋትን መልእክት ያስተላልፋል፤ «እነሆ፥ እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ። ኮረጆም ከረጢትም ጫማም አትያዙ። በመንገድም ለማንም እጅ አትንሡ።» ወደ መጨረሻው አካባቢ ሲደርስ ድምፁ የአዛዥነትን ሞገስ እየተጎናጸፈ መጣ፤ «የሚሰማችሁ እኔን ይሰማል፤ እናንተንም የጠላ እኔን ይጠላል፤ እኔንም የጠላ የላከኝን ይጠላል።» ያ ምን ለማለት የተላለፈ መልእክት ነበር? ቡድኑ መበታተን ጀመረ። አንተም ጥርጣሬዎችህን እየዋጥህ ከተመደበልህ ጓደኛ ጋር ወደ ተልእኮው ትሰማራለህ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ኢየሱስን ስታየው ፊቱ የተለወጠ ይመስላል። ያ ሁሉ ጭንቀትና ስጋት ተለይቶታል። ታሪክህን እንድታብራራለት እየጠየቀህ በፈገግታ ይምነሸነሻል። ስለ ፈውስ፥ የአጋንንት መውጣትና የተለወጡት ሰዎች በቂ ዝርዝሮችን የሚይዝ አይመስልም። ወደ ተራራማው አገር የተደረገው ይኸው አደገኛ ተልእኮ የተሣካ ነበርና ኢየሱስ ከልቡ ተደሰተ።

ነገሩ የድል ፓርቲ ነበር። በደንብ ትሰማውና የማትችለው ነገር እንደማይኖር ታምናለህ፤ በእባቦችና በጊንጦች፥ በማናቸውም ችግሮች ላይ ትረማመዳለህ ይልሃል።

ከዘገባህ መሃል ጣልቃ እየገባ ያቋርጥሃል። ሊጠብቅህ አይችልም። እንዲህ ተደስቶ ያየህበት ቀን ትዝ አይልህም። «ሰይጣን እንደ መብረቅ

ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ።» ብሎ ያውጃል። ምን ማለቱ እንደሆነ ባይገባህም ከመቅጽበት በመደነቁ ኮራ ብለሃል–የሆነ ግዙፍ ጥርመሳ የተከሰተ ይመስላል። ከዚያም ወደ አንተ ቀረብ ብሎ በጥድፊያ የሚከተለውን ተናገረ፤ «እላችኋለሁና፥ እናንተ የምታዩትን ብዙዎች ነቢያትና ነገሥታት ሊያዩ ወደዱ አላዩምም፥ የምትሰሙትንም ሊሰሙ ወደዱ አልሰሙም።»

የግጠቃለያ ፈተና

ከስድስት ወራት በኋላ ሌላ ትእይንት ተከተለ። በዚህ ጊዜ ከሌሎች አሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርት ጋር በኢየሩሳሌም ከምግብ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠሃል። የታፈነ አየር ስፍራውን ተቆጣጥሮታል። ከምግብና ከወይኑ በኋላ መጠነኛ የመሟሟን ስሜት አደረብህ። ሁሉም ነገር በከፍተኛ ፍጥነት እየተካሄደ ነበር። በዚህ ሳምንት መጀመሪያ አካባቢ፥ ኢየሱስ ብዙ ጊዜ የማያደርገውን ሕዝባዊ አጀብ በመፍቀድ በድል ወደ ኢየሩሳሌም ገብቶ ነበር። ይኸው ትእይንት ሕልምህ ሁሉ እውን እንደሚሆን አመልክቶሃል። የዛሬው ድባብ ግን አንድን አስፈሪ ነገር የሚያመለክት ይመስላል።

መጀመሪያ ኢየሱስ ጴጥሮስን ያሳፈረበት የእግር መተጣጠብ ሥርዓት ተካሄደ። ከዚያ በኋላ እንኳ ኢየሱስ በሚናገርበት ጊዜ ስሜታዊ መመሰቃቀል ይታይበታል። አሁን የትዝታና የማጽናናት ስሜት ይታይበትና ወዲያው ደግሞ ፈዛዛና እምነት አልባ ሆነህ በመገኘትህ ይገሥጽሃል። የክህደቱን ጉዳይ ደጋግሞ ይጠቃቅሰዋል። ከሚናገረው ውስጥ አንዳንዱን ለመረዳት አትችልም። ነገር ግን ሁሉ ቢታወሙትም ስለ አንድ ጉዳይ አጥብቆ ይናገራል፤ ይኸውም የመሄድ ጉዳይ ነበር። ሌላ አንድ አካል መጥቶ ይተካዋል። ያም አጽናኙ ሲል የጠራው ነው።

ነፋስ ቅጠላ ቅጠሎችን እንደሚያረግፍ ሁሉ ከፍሉ ከመቅጽበት ይታመስ ጀመር። ለበርካታ ወራት ኢየሱስ የመንግሥቱን የአዛዥነት ሥልጣን ከተግባር ላይ እንዲያውል ስትጠባበቅ ነበር። አሁን ግን ሁሉንም ነገር ለእናንተው ለአሥራ ሁለታችሁ አሳልፎ እንደሰጠ ይናገራል። የጠረጴዛውን ዙሪያ በመቃኘት የፍጻሜን ቃና ባዘለ ድምፅ፥ «አብ እንደ ሰጠኝ መንግሥትን ሰጥቻችኋለሁ» አለ።

መለየት

መልካም፥ ወድቃችኋል፤ ሁላችሁም ወድቃችኋል፤ ከታላቁ ክህደት ጥቂት ቀደም ብሎ ስለ ታማኝነቱ የፎከረው ጴጥሮስም ሳይቀር ወድቋል። ኢየሱስ በዚያን ሌሊት ከትንሿ ክፍል ውስጥ፥ «እኔ ዓለምን

አሸንፌአለሁ!» ሲል ተናገረ። ነገር ግን እነዚህን ቃላት ያን ሌሊት ቀጥሎ ከተከሰተው ሁኔታ ጋር በቀጥታ ማስማማት አይቻልም። ሃያ አራት ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከመስቀል ላይ ተንጠልጥሎ ተገኘ። የሕዝቡ አዳኝ፥ የነገሥታት ንጉሥ? ይህን ማመኑ ለማንም ሰው ቀላል አልነበረም።

ያ የሆነው ዓርብ ዕለት ነበር።

እሑድ ዕለት፥ እጅግ በሚቀራረበው የአልቃሾች ሰፈር አንድ የዕብደት ወሬ ይንሰራፋ ጀመር። ከዚያም በሳምንቱ ውስጥ እርሱን አየኸው ወሬው እውነት ነበር! በራስህ እጆች እጆቹን ዳሰስህ! ኢየሱስ ግንም ሰው ከዚህ በፊት አድርጎት የማያውቀውን ነገር አድርጓል፤ በፈቃዱ ወደ ሞት ውቅያኖስ ገብቶ ተመልሶ ወጥቷል። ከእንግዲህ መቼም ልትጠራጠረው አትችልም።

ለአርባ ቀናት ኢየሱስ በፈቃዱ ሲታይና ሲሰወር ኖረ። በሚታይበት ጊዜ ስለተፈጸመው ነገር የሚናገረውን ትንፋሽህን ውጠህ ትከታተላለህ። ሲሄዱ ደግሞ ስለ አዲሱ መንግሥት ዕቅድ ትወጥናለህ። እስኪ አስበው፤ በመጨረሻው ኢየሩሳሌም ከሮማውያን አገዛዝ ነፃ ስትወጣ።

ጓደኞችህ በዚህ ገበሬ ሰባኪ ትምህርት እንዲህ በመጠመድህ ሲሳለቁብህ ኖረዋል። አሁን ልክህን ታሳያቸዋለህ። ከእንግዲህ ግን ወደ ዳር ይገፋሃል? እስራኤልን ወደ ዳር ሊገፋ የሚችል አይኖርም። ጴጥሮስ፥ ያዕቆብና ዮሐንስ የመጀመሪያውን የሥልጣን እርከን መጨበጣቸው አይቀርም፤ ነገር ግን ለመንግሥቱ ብዙ መሪዎች ያስፈልጉታል፤ አንተም ብትሆን ለሦስት ዓመታት ኢየሱስን ተከትለሃል። መሢሑ፥ እውነተኛው መሢሕ እጅግ ከሚቀርቡት ደቀ መዛሙርት መካከል አድርጎሃል።

በእነዚያ አርባ ቀናት ትኩስ ስሜትህ አልበረደም። እንዴት ሊበርድ ይችላል? እያንዳንዱ የኢየሱስ መገለጥ አንድ ተአምር ነበር። በመጨረሻው ሁሉም የሚጋጥበትን አሳሳቢ ጥያቄ አንደኛው ደቀ መዝሙር አነሣ፥ «ጌታ ሆይ፥ በዚህ ጊዜ ለእስራኤል መንግሥትን ትመልሳለህ?» አንድ ምልክት ለማየት ትንፋሽህን ውጠህ ጠበቅህ፤ ምናልባትም የውጊያ ዕቅድ። ሮማውያን መቼም ያለ ጦርነት በፈቃዳቸው ለቅቀው አይሄዱም።

የኢየሱስን ምላሽ የጠረጠረ አልነበረም። መጀመሪያ ምላሹ ጥያቄውን ያልሰማ አስመሰለው። ጉዳዩን ገለል አድርጎ ስለ እስራኤል ሳይሆን ስለ ጎረቤት አገሮችና ርቀው ስለሚገኙትም ስፍራዎች ይናገር

ጀመር። የእርሱ ምስክር ሆነህ ወደ እነዚህ ስፍራዎች እንደምትሄዱ ነገረህ። አሁን ግን ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰህ የመንፈስ ቅዱስን መምጣት ልትጠብቅ ይገባህ ነበር።

ከዚያ በኋላ እጅግ አስደናቂ ነገር ተከሰተ። እዚያው ቆመህ እየሰማኸው ሳለ ድንገት ሰውነቱ ወደ ላይ ከፍ ከፍ ይል ጀመረ። ለአፍታ ከባቢ አየሩ ላይ አረፈ፤ ከዚያም ደመና ጋረደው። ከዚያ በኋላ ኢየሱስን አይተኸው አታውቅም።

ሦስት ትእይንቶች

ሦስት ትእይንቶች ማለትም የሰባዎቹ መላክ፥ የመጨረሻው የጌታ እራትና ዕርገት ኢየሱስ ለምን ወደ ዓለም እንደመጣና ለምን ተመልሶ እንደሄደ ይገልጻሉ። መለኮታዊ ፍትሕ ለመመሥረትና ለእኛ እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ለማሳየት እንደመጣ እውነት ነው። ይሁንና፥ ለእግዚአብሔር መንፈስ አዲስ የመኖሪያ ስፍራ የምትሆን ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረትም ነበር የመጣው።

ለዚህ ነው ሰባዎቹ ተመልሰው የሥራቸውን ዘገባ ባቀረቡለት ጊዜ ኢየሱስ እጅግ የተደሰተው። «እናንተን የሚሰማ እኔን ይሰማኛል» ሲል ነግሮአቸው ነበርና ዕቅዱ እውነትም የሚሠራ መሆኑ ተረጋገጠ። የራሱ ተልእኮና ከዚያም በላይ የራሱ ሕይወት በሰባ ተራ ሰዎች አማካኝነት እየተስፋፋ ነበር።

ጌታ ኢየሱስ ለመጨረሻው እራት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በተቀመጠ ጊዜ ከፍተኛ የመጣደፍ ስሜት አሳይቷል። አሁን ፈጥነው የታማኝነት ቃላት የሚደረድሩና ትንሽ ቆይተው ደግሞ የሚክዱት እነዚሁ ደቀ መዛሙርት ነበሩ። ከዓለም ሁሉ የኢየሱስ የቅርብ ወዳጆች ነበሩ፤ እናም ጠቅላላውን ተልእኮ ለእነርሱ የሚሰጥበት ጊዜ ደርሶ ነበር። እንዳልገባቸውም እያወቀ፥ «አብ እንደላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ» ሲል ተናገረ። ይኸው ጥቂት ሰዎች የሚገኙበት ቡድን መልእክቱን ወደ ኢየሩሳሌም፥ ወደ ይሁዳና ሰማርያ፥ እርሱ ራሱ ሄዶ ወደማያውቅባቸው ስፍራዎች ወደ ምድር ዳርቻ ሁሉ ያደርሱ ነበር።

በዕርገት የኢየሱስ አካል ደቀ መዛሙርቱ ተደንቀው እየተመለከቱ ምድርን ለቅቆ ተነሣ። ወዲያው ግን በዕለተ በዓለ ኀምሳ የእግዚአብሔር መንፈስ በእነርሱ ሰውነት ውስጥ መኖር ይጀምራል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፡—ሉቃስ 10፤ ዮሐንስ 13—17፤ የሐዋርያት ሥራ 1።

ምዕራፍ 19

የነፍስ መለወጥ

ስለ ሃይማኖት ጥናታዊ ፊልም ለመሥራት ተፈለገ። «በዘመናት ሁሉ የአምላክን አምሳሎች አስሱ» ወይም እንዲህ ዓይነት አጠቃላይ አሳብ ፈልጉ ተባለ። መልካም። እነዚህን ተግባራት ማከናወን የሚችል ማን ነው? ለሠራተኞቹ ዋናው ገጸ ባሕርይ ሰውር ነው።

አንድ ሰው ከራሱ ከእግዚአብሔር ጋር ቃለ ምልልስ የሚያካሂድበትን መንገድ እስኪያመቻች ድረስ ስለ እግዚአብሔር ባሕርያት የሚያስረዱትን ገለጻዎች ሠራተኞች መሰብሰብ ይኖርባቸዋል።

አሥራ አራተኛው ዓመተ ዓለም ከሲና ተራራ ላይ ሄሊኮፕተር በመላክ መጀመር። አካባቢው ሰው የማይኖርበት በመሆኑ የቴሌቪዥን አንቴና ለመትከል፥ ወዘተ. . . ያስቸግራል። ጥንታዊ ዕብራውያንን ተመስሎ ወደ ቤድዊን ተራሮች መሄድ እንዴት እንደሚመገቡና ምን እንደሚለብሱ ምስላቸው ሳይታይ እንዲናገሩ ማድረግ። አንድን የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ከጨዋታው አቋርጦ ለሚቀርቡት ጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጥ መጥራት።

«እስኪ ስለ አምላክ ንገረኝ። ምን ይመስላል? ተራኪው ይጠይቃል? የልጁ ዓይኖች ተጎለጎሉ። «ማለት. . . ማለት. . .» አንድም ቃል ለመናገር አልቻለም።

«አዎ፥ ልክ ነው፤ ያህዌ፥ እናንተ የምታመልኩት አምላክ።»

«እርሱ ምን ይመስላል? እዚያ ማዶ ያለው ተራራ ይታይሃል? [እየተመመ የሚወጣው የእሳተ-ጎሞራ ጢስ]። እዚያ ነው የሚኖረው። ወደዚያ ብትጠጋ ትሞታለህ እርሱ. . . እርሱ. . . ከሁሉም በላይ እርሱ አስፈሪ ነው። በጣም ያስፈራል።»

አንደኛ ክፍለ ዘመን። በሰፊውና ሜዳማው የፍልስጥኤም አድማስ ዙሪያ መንቀሳቀስ። እነዚያው የቤድዊን ሰዎች በበረሃ ውስጥ በቡድን ቡድን ሆነው ወዲያ ወዲህ ይላሉ። በአካባቢው የውኃ ጉድጓድ ነበር። ስብስብ ብለው ከቆሙት ሰዎች ቀጥሎ አንዲት ሴት የበረሃ ዛፍ ተደግፋ ተቀምጣለች።

«እግዚአብሔርን እስካሁን ገና ልለየው እየሞከርሁ ነኝ። የማውቀው ይመስለኝ ነበር፤ ይህንን አስተማሪ መከተል ስጀምር ግራ ተጋባሁ። መሢሕ ነኝ ባይ ነው። ጓደኞቼ ይስቁበታል። እኔ ግን አምስት ሺህ ሰው በመገበበት ዕለት በቦታው ነበርሁ፤ ይህን ሊያደርግ የሚችል ሌላ ማን አለ? ከዓሣው አንድ ቁራጭ በልቻለሁ። ዓይነ-ስውሩን ሲፈውስ በዓይኔ በብረቱ ተመልክቻለሁ።

«እንደሚመስለኝ እግዚአብሔር እዚያ ጋ እንዳለው ኢየሱስ ነው።»

20ኛው ክፍለ ዘመን በአሜሪካን አገር ውስጥ በምትገኝ አነስተኛ ከተማ ወዳለች አንዲት ማራኪ ቤተ ክርስቲያን የፊልም ሠራተኞችን መላክ። ከዚያም በአግዳሚ ወንበሮች ላይ የተቀመጡትን ሰዎች ፊት ማጤን።

«እግዚአብሔር አሁንስ ምን ይመስላል?» ሲል ተራኪው ይጠይቃል።

አዲስ ኪዳን የዚህ ጥያቄ ምላሽ የሚገኘው ተራ ሰዎች ከተሰበሰቡባት ተራ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነ እንድናምን ይጠይቀናል። እግዚአብሔር በክርስቶስ በእኛ ውስጥ ተገኝቷል። ይህንን አስደንጋጭ እውነታ ለመረዳት ብቸኛው መንገድ በእነዚያ በረዱማ ጊዜያት በኮሎራዶ እንዳደረግሁት መጽሐፍ ቅዱስን በቀጥታ ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ማንበብ ነው።

ስሜትን፥ እሳትንና ቅድስናን የተሞላው የአጽናፈ-ዓለሙ ታላቅና አስፈሪ ጌታ የመጀመሪያዎቹን ዘጠኝ መቶ ገጾች በዋናነት ይቆጣጠራል። ከዚያም አራቱ ወንጌላት ይከተላሉ፤ እነዚህም ወደ አንድ መቶ ገጾች የሚሆኑና የኢየሱስን የምድር ላይ ሕይወት የሚተርኩ ናቸው። ከሐዋርያት ሥራ በኋላ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ተከታታይ የግል ደብዳቤዎች ይሸጋገራል። ደብዳቤዎቹ ግሪኮችን፥ ሮማውያንን፥ አይሁዶችን፥ ልጆችን የሚያካትቱ ሲሆን፥ እያንዳንዱ ደብዳቤ አንባቢዎቹ የአዲሱ ማንነት አካል እንደሆኑ ያመለክታል። ሁሉም «በክርስቶስ» ናቸው።

«ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ በትክክል የተቀረጸበት የማኅበረሰብ ክፍል ነች» ብሏል ዲትሪች። ሐዋርያው ጳውሎስ «የክርስቶስ አካል» በሚለው ሐረጉ በጣም ተመሳሳይ አሳብ ገልጾአል። ጳውሎስ እንደተመለከተው ከሆነ፥ እግዚአብሔር ራሱ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የሚኖርበት አዲስ የሰው ዘር ከምድር ላይ እየበቀለ ነበር።

እነዚህ ሰዎች በምድር ላይ የእግዚአብሔርን ክንዶች፥ እግሮችና ዓይኖች ያስፋፋሉ። ከዚህም በላይ ሐዋርያት ጳውሎስ ይኸው አሠራር የእግዚአብሔር ዋንኛው ዓላማ እንደሆነ ገልጾአል።

«የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ፥ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን?» ሲል ለአስቸጋሪዎቹ የቆሮንቶስ ሰዎች ጽፎላቸዋል። በመሠረቱ፥ ቤተ መቅደስ ለአይሁዶች የእግዚአብሔር ሕልውና የሚያድርበት ማዕከላዊ ስፍራ ነበር። ጳውሎስ እግዚአብሔር የስፍራ ለውጥ እንዳደረገ በግልጽ ለማስቀመጥ እየሞከረ ነበር?

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሦስት መቅደሶች አሉ፤ እነዚህም በአንድ ላይ ሲወሰዱ ሂደታዊ ዕድገትን ያመለክታሉ፤ መጀመሪያ እግዚአብሔር ራሱን እንደ አብ፥ ከዚያም እንደ ወልድ፥ ቀጥሎም እንደ መንፈስ ቅዱስ ገልጾአል።*የመጀመሪያው መቅደስ ቀደም ብሎ በሰሎሞን ከዚያም በሄሮድስ የታነጸው ውብ ሕንጻ ነበር። ሁለተኛው የኢየሱስ አካል ቤተ መቅደስ ነበር («ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱትና በሦስት ቀን መልሼ እሠራዋለሁ።» ብሏቸው ነበር)። አሁን ደግሞ ሦስተኛው ቤተ መቅደስ ከእያንዳንዱ ሰብአዊ ግለሰብ የተቀረጸ ሆኗል።

ውክልና

«ለፍጥረታቱ ሊወክል የሚችለውን ነገር ከቶውንም በራሱ የሚፈጽም አይመስልም። በቅጽበተ ዓይን ውብ አድርጎ ሊሠራ የሚችለውን ነገር እኛ በዝግታ እየተጓተትን እንድንወጣ ያዘናል።

«ፍጥረት በከፍተኛ ደረጃ የውክልና ተግባር ይመስላል። ይህ የሆነው ደግሞ እርሱ ሰጪ ስለሆነ ይመስለኛል።»

የአብ፥ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ሂደታዊ ዕድገት የቅርበትን ወደ ከፍተኛ ደረጃ መሸጋገር ያመለክታል። በሲና ተራራ ሰዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ በመሸሽ ሙሴ በእነርሱ ምትክ ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርብ ለምነውታል። በኢየሱስ ዘመን ግን ሰዎች

---

* የአሐዱ-ሥሉስነት ዶክትሪን ቀላል እንዳልሆነና የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ተግባራት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሁሉ እንደሚገኙ ይገባኛል። ይሁንና፥ ምናልባትም ስለ አሐዱ-ሥሉስነት ከትስእብትና ከበዓለ ጎምሳ በተለየ መንገድ መናገር አይኖርብንም ይሆናል። እያንዳንዱ ክስተት ስለ እግዚአብሔር ከዚህ ቀደም ያልታወቀ አንድ ነገር የሚገልጽ ሲሆን፥ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር በያዙት አሳብ ላይ ነውጥን አስከትሏል።

ከእግዚአብሔር ልጅ ጋር ሊወያዩ ይችሉ ነበር፤ ሊዳስሱትና ሊጎዱት እንኳ ይችሉ ነበር። ከበዓለ ኀምሳ በኋላ ከኢየሱስ የፍርድ ችሎት የሸሹት እነዚያው ደካማ ደቀ መዛሙርት የሕያው አምላክ ተሸካሚዎች ሆኑ። ከአእምሮአችን ውጭ በሆነ የውክልና ተግባር፥ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለእነዚያው ደቀ መዛሙርትና ለእኛም አሳልፎ ሰጥቷል።

ይሁንና፥ እነዚሁ ሁሉ ስለ መንፈስ ቅዱስ የምናወጣቸው ድፍርስ አሳቦች ከተጨባጭዋ ቤተ ክርስቲያን ግልጽ እውነታ ጋር መስማማት አለባቸው። በየትኛውም ቤተ ክርስቲያን ወንበሮች ላይ የተኮለኮሉትን ሰዎች ተመልከት። የእግዚአብሔር አሳብ ይኸው ነው?

የትኛውም ድርጅት እንደሚያውቀው፥ ውክልና ሁልጊዜም አደጋ አለው። አንድን ሥራ ለወኪል አሳልፈህ ከሰጠህ በኋላ አንተ አትጨነቅበትም። ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሚለው፥ እግዚአብሔር «በእኛ በኩል ሰዎችን ሲለምን» የከፋ አደጋ ውስጥ ገብቷል፤ ይኸውም እኛ እርሱን በትክክል ልንወክል አለመቻላችን ነው። የባሪያ ንግድ፥ የመስቀል ዘመቻ፥ በአይሁዶች ላይ የተደረገ ጭፍጨፋ፥ ቅኝ ግዛት፥ ጦርነቶች. . . የመሳሰሉ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ለተግባራቸው የክርስቶስን ማዕቀቦች ዋቢ ጥቅሰዋል። እግዚአብሔር ለማፍቀር የሚሻው ዓለም፥ እግዚአብሔር የሚለምነው ዓለም፥ ከቶውንም ላያየው ይችላል፤ የራሳችን ፊት መልእክቱን ሊያውከው ይችላል።

ይሁንና እግዚአብሔር ይህንኑ አደገኛ አቅጣጫ ስለመረጠ፥ ዓለም እርሱን የሚያውቀው በቀዳሚነት በክርስቲያኖች አማካኝነት ነው። የመንፈስ ቅዱስ ዶክትሪን የቤተ ክርስቲያን ዶክትሪን ነው፤ የእግዚአብሔር ከእኛ ጋር መኖር። ጳውሎስ በአንድ ስፍራ እንደጠቀሰው፤ እንዲህ ዓይነቱ ዕቅድ «የእግዚአብሔር ሞኝነት» ነው፤ ጸሐፊው ፍሬድሪክ ቡችነር በዚህ ሞኝነት ይደነቃል፤ «በዓለም ውስጥ ላለው የተቀደሰ ተግባሩ. . . በአእምሮአችን የደከምነውን፥ ከሌላው የማንገጥመውን፥ እንከን ፈላጊዎችን፥ ተመጻዳቂዎችን፥ ኋላ ቀርና ራስ ወዳዶችን፥ ብሎም በስሜታችን የደነዘዝነውን መምረጡ በእጅጉ የሚያስደንቅ ነው።»[2]

ይሁንና፥ ጳውሎስ ደግሞ «ከሰው ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይጠበባልና» ብሎ ይቀጥላል። ደካማ በሆኑ ተራ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን መካከል የምንኖር፥ አስተውሎት የጎደለንንና ከሌላው የማንገጥም ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቶስ አካል የሚናገራቸውን የተጋነኑ አሳቦች ለማሻሻል እንፈልግ ይሆናል። ለዚህም ምክንያቱ እግዚአብሔርን ምን ያህል በተበላሸ መልኩ እንደምንገልጽ የምናውቅ

መሆኑ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ግን በጣም ግልጽ ነው። የሚከተሉትን ሁለት ምሳሌዎች ተመልከት።

1. *በምድር ላይ የእግዚአብሔርን ቅድስና እንወክላለን።* ከሁሉም በላይ ቅድስና በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ርቀትን ይፈጥራል። እጅግ የተቀደሰውን ስፍራ እግድ ያደረገው ይሽው ቅድስና ነው። አዲስ ኪዳን ግን ከፍተኛ ለውጥ እንደተከሰተ ይነግረናል። ፍጹም የሆነው አምላክ ፍጹምነት በጎደላቸው ሰዎች መካከል ያድራል። መንፈስ ቅዱስ ነጻነታችንን ስለሚያከብር ራሱን ለባሕርያችን «ያስገዛዋል»። አዲስ ኪዳን ልንዋሸው ወይም ልናሳዝነው ወይም ልናጠፋው ስለምንችለው መንፈስ ቅዱስ ይነግረናል። እናም የተሳሳተ ምርጫ በምናካሂድበት ጊዜ፥ እግዚአብሔርን የዚያው የተሳሳተ ምርጫ ተገዥ እናደርገዋለን።

ይህንን እንግዳ እውነት ከ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 6 በላይ በጉልሕ የሚያሳይ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አይኖርም። ይህም ጳውሎስ ሴሰኞቹን የቆሮንቶስ ሰዎች ከጋለሞታዎች ጋር ለሚያደርጉት አግባብነት የሌለው ተግባር የሚገሥጽበት ክፍል ነው። አመክኒዮአቸውን ሁሉ አንድ በአንድ ያመክነዋል። ከዚያም በመጨረሻው ከሁሉም የባሰ አሳዛኝ ማስጠንቀቂያ ያስቀምጣል፤ «ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደሆነ አታውቁምን?» ጳውሎስ ይህንን የሚለው እጅግ በላቀ ቀጥተኛ መንገድ ይመስላል፤ ከቀጣዩ አስደናቂ መደምደሚያም አያፈገፍግም፤ «እንግዲህ የክርስቶስን ብልቶች ወስጄ የጋለሞታ ብልቶች ላድርጋቸውን? አይገባም።»

ንጽጽሩን ለይተህ ለማውጣት የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁር የመሆን ግዴታ አይኖርብህም። በብሉይ ኪዳን ዝሙት አድራጊዎች የእግዚአብሔርን ሕግ በመተላለፋቸው በድንጋይ ተወግረው ይገደሉ ነበር። በመንፈስ ቅዱስ ዘመን ግን እግዚአብሔር ስሙንና ባሕርዩን ለእኛ በውክልና ስለ ሰጠን፥ እግዚአብሔርን ለብስነው ለዓለም እናሳየዋለን፤ በእኛ ላይ የሚደርሰው በእርሱ ላይ ይደርሳል።

2. *ሰዎች በምድር ላይ የእግዚአብሔርን ሥራ ያካሄዳሉ።* ወይም በቀጥታ እውነቱን ለመናገር፥ እግዚአብሔር ሥራውን የሚያካሄደው በእኛ አማካኝነት ነው፤ ውጥረትን የሚጀምረው ይህንኑ አሳብ ለማብራራት ስትሞክር ነው። ኦገስቲን እንዳሉት፥ «ያለ እግዚአብሔር እኛ አንችልም። ያለ እኛም እግዚአብሔር አያደርገውም።» ጳውሎስም በተመሳሳይ ሁኔታ፥ «በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ መዳናችሁን ፈጽሙ» ካለ በኋላ፥ በሚቀጥለው ሐረግ ደግሞ፥«በእናንተ የሚሠራው እግዚአብሔር ነውና» ብሏል።

ከዚህ የተለየ ምንም ትርጉም ቢኖራቸው፥ እነዚህ ቀጥተኛ ያልሆኑ ክፍሎች «ለእግዚአብሔር ተወው» የሚለውን አመለካከት እንደሚቃረኑ ጥርጥር የለውም።

እግዚአብሔር በምድረ በዳ ለሚቅበዘበዙ እስራኤላውያን ምግብን የሰጣቸው ሲሆን፥ ጫማቸውም እንዳይነትብ አድርጓል። ኢየሱስም የተራቡትን አብልቷል፤ ጉድለታቸውን ሞልቶላቸዋል። እነዚያን አስደናቂ ታሪኮች ያነበቡ ብዙ ክርስቲያኖች ያንኑ ቀደምት ዘመን የሚያስቡት በናፍቆት ወይም በቅይማት ነው። «አሁን እግዚአብሔር ለምን እንደዚያ አይሠራም? ለምን በተአምራዊ መንገድ ጉድለቶቼን አይሞላም?» ሲሉ ያስባሉ።

ነገር ግን የአዲስ ኪዳን መልእክቶች የተለየ አሠራር የሚያመለክቱ ይመስላል። ጳውሎስ በቀዝቃዛ ክፍል ውስጥ ታስሮ እያለ የረዥም ጊዜ ወዳጁ ሥጋዊ ፍላጎቱን እንዲያሟላለት ጠይቋል። «በርኖሱንና መጻሕፍቱን ይልቁንም በብራና የተጻፉትን አምጣልኝ። ማርቆስ ለአገልግሎት ብዙ ይጠቅመኛልና ይዘኸው ከአንተ ጋር አምጣው።» በሌላ በኩል፥ ጳውሎስ በቲቶ ጉብኝት «የእግዚአብሔርን መጽናናት» አግኝቷል። በኢየሩሳሌም ረሃብ በተነሣ ጊዜ፥ ጳውሎስ ራሱ እርሱ ከመሠረታቸው አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ገንዘብ አሰባስቧል። እግዚአብሔር የእስራኤላውያንን ጉድለቶች እንዳሟላ ሁሉ የጨቅላዋንም ቤተ ክርስቲያን ጉድለት እያሟላ ነበር፤ ይህንን ያደረገበት መንገድ ግን በተዘዋዋሪ መንገድ በአካሉ ክፍሎች አማካኝነት ነበር። ጳውሎስ «ቤተ ክርስቲያን ይህንን አደረገች፤ እግዚአብሔር ያንን አደረገ» የሚል ልዩነት አላወጣም። እንዲህ ዓይነቱ ክፍፍል ብዙ ጊዜ ያስቀመጠውን እውነት ዋጋ ቢስ ያደርጋል። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናትና፥ እርሷ ካደረገችው እግዚአብሔር አድርጎታል ማለት ነው።

ጳውሎስ ከዚህ እውነት ላይ የሙጥኝ ማለቱ ከእግዚአብሔር ጋር ከተገናኘበት የመጀመሪያው ኃይለኛ ሁኔታ ጋር ሊዛመድ ይችላል። በዚያን ጊዜ ጳውሎስ ክርስቲያኖችን እያዳነ የሚያሳድድ ጨካኝ ሰው ነበር። ነገር ግን በደማስቆ መንገድ ለሦስት ቀናት የሚያሳውር ብርሃን አጋጠመው፤ «ሳውል፥ ሳውል፥ ስለ ምን ታሳድደኛለህ?» የሚል ድምፅ ከሰማይ ሰማ።

«አንተን ላሳድድ? ማንን? እኔ የማሳድደው እነዚያን መናፍቅ ክርስቲያኖች ብቻ ነው።»

«አንተ ማነ ነህ፥ ጌታ ሆይ?» ሲል ጠየቀ ጳውሎስ ከመሬት ላይ ተዘርሮ።

«አንተ የምታሳድደኝ ኢየሱስ ነኝ» የሚል ምላሽ መጣ።

ይኸው ዓረፍተ ነገር እንደማንኛውም ሌላ ነገር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የተከሰተውን ለውጥ ያጠቃልለዋል። ኢየሱስ ከወራት በፊት ተገድሎ ነበር። ሳውል የሚያሳድደው ክርስቲያኖችን እንጂ ክርስቶስን አልነበረም። ነገር ግን ሕያው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚያ ክርስቲያኖች የእርሱ አካል መሆናቸውን ለጳውሎስ ገልጾለታል። እነርሱን የሚነዳ ነገር እርሱንም ይነዳዋል። ይህ ሐዋርያው ጳውሎስ የማይዘነጋው ትምህርት ነበር።

♥

ይህንን አሳብ እጅግ ግላዊ በሆነ መንገድ ከሕይወታችን ጋር ልናዛምደው ይገባል። ለዚህ መሠረታዊ ጥያቄዎች የመንፈስ ቅዱስ ዶክትሪን ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ወዳጄ ሪቻርድ፥ «እግዚአብሔር የታለ? አሳየኝ። ላየው እፈልጋለሁ!» ሲል ጠይቋል። ቢያንስ ለሪቻርድ ጥያቄ ከፊሉ መልስ እንዲህ የሚል ነው፤ *እግዚአብሔርን ለማየት ብትሻ የእርሱ የሆኑትን ሰዎች ተመልከት–እነርሱ የእርሱ «አካላት» ናቸው።* እነርሱ የክርስቶስ አካላት ናቸው።

«በአዳኛቸው ማመን ካለብኝ የእርሱ ደቀ መዛሙርት ይበልጥ የዳኑ ሆነው መታየት አለባቸው» ሲል ተናግሯል ኒቼ–ለዚህ ዓይነቱ ተግዳሮት። ነገር ግን ሪቻርድ እንደ ማዘር ቴረዛ የፍቅርንና የጸጋን ብቃቶች የያዘ ቅዱስ ሰው ቢያገኝ፤ ምናልባት ያን ጊዜ ያምን ይሆናል። *«እያትማ? ሴትዮዋ የእግዚአብሔርን ሥራ እያከናወነች ነው።»* እግዚአብሔር እኮ እንዲህ ነው።

ሪቻርድ ማዘር ቴረዛን አያውቃቸውም፤ እኔን ግን ያውቀኛል። ይህ ደግሞ ራስን እጅግ ዝቅ የሚያደርግ የመንፈስ ቅዱስ ዶክትሪን ገጽታ ነው። ምልናባትም ሪቻርድ ለጥያቄዎቹ ሁሉ ምላሽ የሚሰጠውን የዐውሎ ነፋስ ድምፅ ላይሰማ ይችላል። በዚህ ሕይወቱ የእግዚአብሔርን ጨረፍታ ላያገኝ ይችላል። እኔን ብቻ ያየኛል።

[1]C.S. Lewis, *The World's Last Night*, 9.

[2]Frederick Buechner, *A Room Called Remember*, 142.

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፦ 1ኛ ቆሮንቶስ 3፤ ዮሐንስ 2፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 5፤ ፊልጵስዩስ 2፤ 2ኛ ጢሞቴዎስ 4፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 7፤ ሮሜ 15፤ የሐዋርያት ሥራ 9።

ምዕራፍ 20

ፍጻሜ

ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ከዚህ በፊት የያዝናቸውን አሳቦች ሁሉ ለአፍታ አስወግደን ያንን ግዙፍ መጽሐፍ እንደ አንድ ታሪክ ብናነበው፤ መዋቅሩ የሚከተለውን ሊመስል ይችላል።

በመጀመሪያ መንፈስ የሆነው አምላክ ግዙፉን ቁሳዊ ዓለም ፈጠረ። ከእነዚያ ሁሉ ድንቅ ሥራዎች መካከል «የእግዚአብሔር አምሳል ተብለው ሊጠሩ የሚችሉ የእርሱን መልክ የያዙት የሰው ልጆች ብቻ ነበሩ። ይህ የእግዚአብሔር አምሳል በአንድ በኩል ታላቅ ስጦታ፥ በሌላ በኩል ግን ታላቅ ሸክም ነበር። የመንፈስ ኑባሬ የሆኑት ወንድና ሴት ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ ሊነጋገሩ ይችሉ ነበር። ነገር ግን ከፍጥረታት ሁሉ መካከል በእግዚአብሔር ላይ የማመፅ ነጻነት ያላቸውም እነዚሁ ሰዎች ነበሩ።

ዓመፃውን በፈጸሙበት በዚያን አደገኛ ዕለት ከአዳምና ሔዋን ውስጥ አንድ ነገር ሞተ። ምንም እንኳ ሰውነታቸው ለረዥም ጊዜ በቅይጣት ቢቆይም፥ መንፈሳቸው ከእግዚአብሔር ጋር ያደርግ የነበረውን ነፃና ግልጽ ግንኙነት አጣ።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ያንን የወደቀ መንፈስ ከቦታው ለመመለስ ስላደረጋቸው ጥረቶች የሚነግረን አለው። ከግለሰብ ቤተሰቦች ጋር መሥራቱን ቀጠለ፤ መጀመሪያ ከአዳም ቤተሰብ፥ ቀጥሎም ከኖኅ ቤተሰብ፥ በመጨረሻም የአብዛኛው ብሉይ ኪዳን ማዕከላዊ አጽንኦት ከሆነው የአብርሃም ቤተሰብ ጋር ሠራ። መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔርን ልጆቹን እንደሚያሳድግ አባት፥ አንዳንድ ጊዜ በትኩስ ፍቅር እንደሚቃጠል ፍቅረኛ አድርጎ ይገልጸዋል። ነገር ግን ሁልጊዜም ያንን የጠፋውን ነገር ከቦታው ለመመለስ ወደ ሰው ልጆች ጠርሶ ለመግባት እንደሚሻ አምላክ አድርጎ ያሳየዋል።

ከአንዳንድ ለየት ያሉ አንጸባርቂ ሁኔታዎች ባሻገር ብሉይ ኪዳን ውድቀቶችን ብቻ ይዘግባል። አዲስ ኪዳን ግን በእግዚአብሔር ሥር-ነቀል እርምጃ ይጀምራል፤ ይኸውም የክርስቶስ ልደት «ወረራ» ነበር። ኢየሱስ ጠቅላላውን አዲስ ጅማሬ ያሳያል። እርሱም የአዲስ ዘር መሪ እንደ መሆኑ፤ «ዳግማዊ አዳም» ተብሎ ተጠርቷል። ኢየሱስ በመጨረሻው ግርዶሾቹን ሁሉ በጣዖሱ፥ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ስምምነትን ተግባራዊ አደረገ።

ኢየሱስ ከሄደ በኋላ፥ በዕለተ በዓለ ኀምሳ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ ሰዎችን ሞልቷቸዋል። እናም የወደቀው መንፈሳቸው

በመጨረሻው ተመለሰ። እግዚአብሔር በዔድን ገነት ከሰዎች ጋር ከመንሸራሸር በበለጠ አሁን በውስጣቸው እየኖረ ነው።

አስደናቂው ክስተት ለማግኘት የአዲስ ኪዳን መልእክቶችን ከዚህ አልፈህ መሄድ የለብህም። ሐዋርያው ጳውሎስ ራሱ ከዚህ በበለጠ ጥንካሬ ሊገልጸው አይችልም ነበር፤ «ፍጥረት ራሱ የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጠ በናፍቆት ይጠባበቃል።» ጠቅላላው አጽናፈ-ዓለም በምድር ላይ የሚከሰቱትን ነገሮች ለማየት ለአፍታ ቆም እንደሚል አድርጎ ገልጾአል፤ «ብዙ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ አሁን በቤተ ክርስቲያን በኩል በሰማያዊ ስፍራ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት ትታወቅ ዘንድ» ነበር። ጴጥሮስ መላእክትም እንኳ እነዚህን ነገሮች ለማየት እንደሚናፍቁ ገልጾአል።

በዚህ መሀል ጥቂት አባላት የሚገኙበት የክርስቲያኖች ቡድን ወደ ሰማርያ፥ ግሪክ፥ ኢትዮጵያ፥ ሮምና ስፔይን ተበተነ። አዲስ ኪዳን እንደሚለው፥ እነዚህ ሰዎች ፍጥረትን ሁሉ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ በከፍተኛ የታሪክ ለውጥ ላይ ተጠምደው ነበር።

ለምን የተሻለ?

ገና ከመጽሐፉ ጅማሬ ላይ ታማኝ ለመሆን ቆርጠው ነበር፤ የምጽፈው ደግሞ የሚጠብቁት ተስፋ ለላሸቀባቸው ሰዎች ነው። ስለሆነም በቅይማት ለተያዙት ሰዎች የአዲስ ኪዳንን ጸሐፊዎች ጉጉት መጋራቱ ከባድ ነው። ለምሳሌ ወዳጄ ሪቻርድ እግዚአብሔር እጅግ ግልጽ ባልሆነ መንገድ ስለሚሠራ እምነቱን እንዳጣ ይናገራል። እንደሚቃጠል ቁጥቋጥ ወይም እንደ ቀይ ባሕር መከፈል ዓይነት አሳማኝ ክስተት ለማየት ይፈልጋል። «ብዙ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ አሁን በቤተ ክርስቲያን በኩል» ይሠራል? በቅርብ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደህ ነበር? ኢየሱስ አስደናቂ ይሆን ነበር፤ የእግዚአብሔር ክብር ደመና ከመሬት ላይ በዘረረህ ነበር።

የአዲስ ኪዳንን የመጠቁ አገላለጾች በዙሪያችን ካለው ዕለታዊ እውነታ ጋር እንዴት ልናዛምደው እንችላለን? አንዳንድ ሰዎች ለዚህ ጥያቄ ፈጣን ምላሽ አላቸው፤ «አ! ጳውሎስ የሚለው ግን ስለ አዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ነበር፤ እኛ ከዚያ አምሳል የትና የት እንርቃለን።» ይላሉ። በበኩሌ ከዚህ አሳብ ጋር ልስማማ አልችልም። የነሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቶች የተጻፉት ከመላእክት አምልኮ፥ ከሴብነት፥ ከአምልኮተ ጣዖት፥ ከሐሜትና ከግልሙትና ለተለወጡት ሰዎች ነበር፤ እግዚአብሔር ያደረው በእነዚህ ሰዎች ውስጥ ነበር። እንደ ቆሮንቶስ ባለች ከተማ ጳውሎስ ስለ «ፍጹማዊት ቤተ ክርስቲያን» የሚሰጠውን ገለጻ አንብብ። እነዚህ ሰዎች በጥባጮች፥ የማይጨበጡና

ከቅድስና በመራቃቸው በታሪክ ከየትኛውም ቤተ ክርስቲያን ጋር የማይወዳደሩ ናቸው። ይህም ሆኖ፥ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል እንደሆነች የሚያስረዳውን እጅግ የሚያነቃቃ ገለጻ ያካተተው ለእነዚህ ሰዎች በጻፈው መልእክት ውስጥ ነበር።

ጥያቄውን በተዋበ መልኩ ለማቅረብ የሚቻልበት መንገድ ስለሌለ፤ እንዲሁ መጠየቁ ይሻላል፤ እግዚአብሔር ለዘመናት የወጠነው ዕቅድ ምን ተግባር ፈጸመ? ይህንን ዕቅድ ኮርፖሬሽኖች «የትርፍ-ኪሳራ ግምገማ» በሚሉት መልክ ብናየው፥ የዚህ ዓይነቱ ዕቅድ «ጥቅሞች» እና «ጉዳቶች» ለእኛና ለእግዚአብሔር ምንድን ናቸው?

የቤተ ክርስቲያን ግልጽ ጉድለቶች ለእግዚአብሔር እጅግ ከፍተኛ ኪሳራ ሊመስሉ ይችላሉ። ለእስራኤላውያን ስሙን ሰጥቷቸው በጭቃ እንደለወሱት ሁሉ፥ አሁንም መንፈሱን ለተበላሹ ሰብአዊ ፍጡራን ሰጥቶአቸዋል። ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ፍጹም ዕቅድ እንደግታጊላ ለማረጋገጥ ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን፥ ከደቡብ አፍሪካው ዘረኝነት፥ በሰሜን አየርላንድ ከሚታየው የደም መፋሰስ፥ በዩናይትድ ስቴትስ በክርስቲያኖች መካከል ከሚከሰቱ ቅሌቶች አልፈህ አሩቅ መሄድ አይኖርብህም። ታዛቢው ዓለም ስሙን በሚሸከሙት በእነዚህ ክርስቲያኖች ላይ ተመሥርቶ በእግዚአብሔር ላይ ይፈርዳል። በሌሎች ክርስቲያኖች ባሕርይ ግራ ከመጋባት የሚመነጨው ቅይማት እጅግ ከፍተኛ ነው።

በዶርቲ ሳዮርስ ግንዛቤ እግዚአብሔር የሰውን ዘር ለመመለስ ባደረገው ጥረት ሦስት ታላላቅ ውርደቶች ደርሰውበታል። ከእነዚህም ውርደቶች የመጀመሪያው በሥጋዊ አካል ውስጥ የታሰረበት ትስእብት ነበር። ሁለተኛው በአደባባይ ተገድሎ ይፋዊ ኃፍረትን የተቀበለበት መስቀል ነበር። ሦስተኛው ውርደት ቤተ ክርስቲያን ነች። በሚያስገርም ራስን የመካድ ተግባር፥ እግዚአብሔር ዝናውን ለተራ ሰዎች በአደራ ሰጥቷል።

ይሁንና፥ ለእኛ በማይታይ መንገድ እነዚህ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ተራ ሰዎች አጽናፈ-ዓለሙን ከእግዚአብሔር አገዛዝ ሥር ወደ ነበረበት የቀድሞ ስፍራው ለመመለስ በመረዳት ላይ ናቸው። ንስሐ ስንገባ መላእክት ይደሰታሉ። በጸሎታችን ተራሮች ይናወጣሉ። የእግዚአብሔር ትርፍ ቀደም ሲል ከተጠቀሰው ምንባብ ሊታይ ይችላል፤ «ሰይጣን ከሰማይ እንደ መብረቅ ሲወድቅ አየሁ» ሲል ተናግሯል ኢየሱስ ሰባዎቹ ስኬት ይዘው በተመለሱ ጊዜ አባቱ ከገመተው በላይ ታላቅ ተግባር ሲያከናውኑ እንደተመለከተ ኩሩ አባት ነበር ምላሹ።

እግዚአብሔር የእኛን ትብብር የመፈለጉን ጉዳይ ይበልጥ ልናተኩርበት አይገባም። ይልቁንም በዚህች ምድር ላይ ፍጥረቱን መልሶ የራሱ ለማድረግ እኛን እንደ አማራጭ መንገድ እንደተጠቀመ ልንረዳ ይገባል። የእኔ ጭንቅላት ይህችን ዓረፍተ ነገር ለመጻፍ ጣቶቼን፥ እጄንና በጣቶቼና በእጄ መካከል የሚገኘውን መገጣጠሚያ እንደሚጠቀም ሁሉ፥ እግዚአብሔር ሰውን እንደ መሣሪያ ለዓላማው መሳካት ይጠቀማል። ይህ ምሳሌ ዛሬ ክርስቶስ በዓለም ውስጥ የሚጫወተውን ሚና ለመግለጽ ሐዋርያው ጳውሎስ በተደጋጋሚ የሚጠቀምበት ነው። ይኸውም ብልቶቹ ፈቃዱን ይፈጽሙ ዘንድ እንደሚመራቸው የአካል ራስ እንደሆነ ነው።

የእግዚአብሔርን ትርፍ ለመረዳት የነቢያቱን ምሳሌዎች መለስ ብለህ አስብ፤ እነዚህም እግዚአብሔር እንደ ወላጅና አፍቃሪ የተገለጸባቸው ምሳሌዎች ናቸው። እነዚህ ሁለቱም ግንኙነቶች እግዚአብሔር ሁልጊዜም ከሰው ልጆች ሊፈልጋቸው የነበሩትን ነገሮች ያካትታሉ። «መደገፍ» የሚለው አንድ ቃል ቁልፉን ያሳያል–በጋራ ያሏቸውና የሚለያዩባቸው ነገሮች ቁልፍ።

ለአንድ ሕፃን ልጅ መደገፍ ሁሉም ነገር ነው፤ አንድ ሰው ጉድለቱን ሁሉ ካላሟላለት ልጁ ይሞታል። ወላጆች ሌሊቱን ሁሉ ነቅተው ትውከቱን ያጸዳሉ፤ ስለ መጸዳዳት ያስተምሩታል፤ የልጃቸውን ድጋፍ መሻት ስለሚያስደስታቸው ነገሮች ያደርጉለታል። ነገር ግን– የዚህ ዓይነቱ አሠራር ለሁልጊዜም አይቀጥልም። ንስር ልጆቿ ተነሥተው እንዲበሩ ለማድረግ ጎጆዋን ትቆሰቁሳለች፤ እናት ለልጇ ምግብ ለማስለመድ ጡቶቿን ትሸፍናለች።

ማንኛውም ጤነኛ ወላጅ ልጁ ለዘላለም የእርሱ ጥገኛ እንዲሆን አይሻም። ይሁንና፥ አንድ አባት ሕፃን ልጁን ከባቡር መንገድ ላይ አውጥቶ አይጥልም። ነገር ግን አንድ ቀን ራሷን ችላ እንደምትሄድ በመገንዘብ እንዴት መራመድ እንዳለባት ያስተምራታል። መልካም ወላጆች ልጆቻቸውን ከጥገኝነት ወደ ነጻነት ይመራሉ።

ፍቀረኞች ግን አሠራሩን ይቀለብሱታል። አንድ አፍቃሪ ሙሉ ነጻነት ቢኖረውም ነጻነቱን አሳልፎ በመስጠት በተፈቃሪው ላይ ይደገፋል። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «አንዱ ለሌላው ይገዛ» ይላል፤ አብሮ የመኖሩ የዕለት ተዕለት ሂደት ይኸው እንደሆነ የትኛውም ባለትዳር ሊነግርህ ይችላል። በጤነኛ ትዳር ውስጥ፥ ከፍቅር የተነሣ አንደኛው ለሌላኛው ፍላጎቶች በፈቃዱ ይገዛል። ጤነኛ ባልሆነ ትዳር ግን መገዛት ኃይልን ለመቀዳጀት የሚደረግ የትግል አካል ይሆናል፤ በሁለት ተፎካካሪ ስግብግቦች መካከል የሚካሄድ ግብግብ።

በእነዚህ ሁለት ግንኙነቶች መካከል የሚገኘው ልዩነት እግዚአብሔር በረዥም ታሪኩ ከሰው ዘር ሲፈልግ የኖረውን ነገር ያሳያል ብዬ አምናለሁ። እግዚአብሔር የሚፈልገው ምርጫ የሌለውን ሕፃን ፍቅር ሳይሆን፥ በነፃ የሚቀርብለትን የበሰለና ነፃ የፍቅረኛን ፍቅር ነው። በዘመናት ሁሉ «ሲያፈቅረን» ኖሯል።

እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን እንዲህ ዓይነት የበሰለ ፍቅር አላገኘም። ዘገባው እግዚአብሔር ወጣቶቹን እስራኤላውያን ወደ ብስለት መግፋቱን ያሳያል፤ እስራኤላውያን ወደ ተስፋዪቱ ምድር በገቡበት ዕለት መናው መውረዱን አቆመ። እግዚአብሔር አዲስ ምድር ሰጥቷቸዋል፤ እናም እስራኤላውያን የራሳቸውን መግብ ዘርተው ማብቀል ይጠበቅባቸው ነበር። ፍጹም ሕፃንነትን በተላበሰ ምላሽ፥ እስራኤላውያን የልምላሜን አማልክት ያመልኩ ጀመር። እግዚአብሔር ፍቅረኛን ቢሻም ያገኘው ግን ሁልጊዜም ወደ አደገኛ አቅጣጫ የሚሮጠውን ልጅ ነበር።

አሁንስ? በመንፈስ ቅዱስ ዘመን? አሁን እግዚአብሔር ከልጅ የተሻለ ፍቅረኛ አለው? የሚገርመው አዲስ ኪዳን አምንታዊ ምላሽ የሚሰጥ ይመስላል። እነዚህ ለአብነት የቀረቡት የአዲስ ኪዳን ሐረጎች እግዚአብሔር እንዴት እንደሚመለከትን ይገልጻሉ፤ «ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደዳት . . . እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ»፤ «የሕይወትን ቃል እያቀረባችሁ በዓለም እንደ ብርሃን ትታያላችሁ»፤ «በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ. . . ቀርባችኋል»፤ «ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባለገሮችና የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም. . . በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ።»

መጽሐፍ ቅዱስ የተራ ሰዎችን ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር መዋሃድ የፍጥረት የላቀ ስኬት አድርጎ ያቀርባል። የእግዚአብሔር ዋነኛ ዓላማ በዓለም ውስጥ ዓላማውን እንድንፈጽም ማስታወቅ ነበር። አንድ ቀን ያ ዘገምተኛና አስቸጋሪ ሂደት ምድርን ሙሉ ለሙሉ ይለውጣታል።

ትርፋችን

ይህም ሆኖ፥ ስለ እግዚአብሔር ወኪሎች፥ የፍጥረት የላቀ ስኬት የሚነሡ ግዙፍ አሳቦች በእኛ ዘንድ የሌላውን መለኮታዊ የአመለካከት አቅጣጫ የሚያሳዩ ናቸው። በምድር ላይ ላለነው ለእኛ የእግዚአብሔር ዕቅድ ትርፎችና ኪሳራዎች ምንድን ናቸው? አሁንም የምኖረው በሥቃይ፥ በኃዘንና ቅይማት በተረገመች ምድር ላይ ነው።

እግዚአብሔር ከሲና ምድረ በዳ ጢስ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ አካልና የመንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ ማደር በከፍተኛ ደረጃ ወደ ሰዎች እንደቀረበ ተደርጎ በዚህ መጽሐፍ የቀረበው አሳብ በምፀታዊ ግንዛቤ እግዚአብሔር ከቀጥተኛ ተሳትፎ ራሱን እንዳገለለበት አሠራር ሆኖ ሊታይ ይችላል።

አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር ይበልጥ በቀጥታ ስለሚሠራባቸው «የጥንቱ ወርቃማ ቀናት» በማሰብ ይተክዛሉ። ብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለሥጋዊ ደኅንነትና ብልጽግና ዋስትና በመስጠት በተወሰኑ ቅድመ-ሁኔታዎች ሥር እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ስለተፈራረማቸው ስምምነቶች ይናገራል፤ በአዲስ ኪዳን እንዲህ ዓይነት ስምምነት አልተጠቀሰም። እግዚአብሔር በምድረ በዳ ለዓይን ይታይ ከነበረበት ህልውና ወደ መንፈስ ቅዱስ የማይታይ ህልውና የተደረገው ሽግግር የተወሰኑ ነገሮችን እንደሚያስወግድ ተጨባጭ ማረጋገጫ ማጣታችን ነው። በአሁኑ ጊዜ ለማረጋገጫ ቀና ብለን እንመለከት ዘንድ እግዚአብሔር በደመና ዓምድ ከላያችን ላይ አይሰፍም። እንደ ሪቻርድ ላሉ አንዳንድ ሰዎች ይህ ደግሞ ትልቅ ጥፋት ይመስላቸዋል።

እንዲያውም የእግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ላይ መደገፍ የሰዎች ከእርሱ ጋር መቀያየም ዘላቂና የከፋ እንደሚሆን ዋስትና የሚሰጥ ይመስላል። በጥንቱ የብሉይ ኪዳን ዘመን፥ ስለ ወታደራዊ ስምሪት ወይም ለቤተ መቅደሱ ምን ዓይነት እንጨት መጠቀም እንደሚያስፈልግ ዕብራውያን ለማወቅ ቢሹ፤ ሊቀ ካህናቱ መልሱን ፈልፍለው የማውጣት ችሎታ ነበራቸው። በአሁኑ ጊዜ ግን በዩናይትድ ስቴትስ የሚገኙ 1,275 የወንጌል አማኞች የእምነት ክፍሎች (ዲኖሚኔሽኖች) ብቻ በየትኛውም ጉዳይ ላይ በቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመለየት እንደምትቸገር ሊያሳዩ ይችላሉ። የዘመናዪቱ ቤተ ክርስቲያን ግራ የተጋባ ድምፅ የኪሳራው አካል ነው፤ ይህም ከዛሬ ይልቅ ከዕብራውያን ጋር በምድረ በዳ ወይም ኢየሱስን ከተከተሉት ደቀ መዛሙርቱ ጋር ለመኖር ያለመቻላችን ጉዳት ነው። ታዲያ ምኑ ነው ትርፉ? አዲስ ኪዳን በተለይም በዕብራውያን፥ በሮሜና በገላትያ መልእክቶች ላይ ይህንን የሚገልጸው በከፍተኛ ስሜት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ «ደም ፍላት» ባለ ስሜት፥ «ትርፉ ምንድን ነው?» ለሚለው ዓይነት ጥያቄ ሲመልስ ትእይንቱን ከጽሑፎች ውስጥ ለመመልከት ይቻላል።

> አብዳችኋል እንዴ? እስኪ ወደ ኋላ ተመልሳችሁ ዘሌዋውያንን፥ ዘኍልቁንና ዘዳግምን በአንድ ቁጭታ እንብቡት። እነዚያን ጊዜያት «ወርቃማ ዘመናት» ብላችሁ ትጠራላችሁ? እንደዚያ ለመኖር የሚሻው ማን ነው? በየቀኑ ስለ ዘላለማዊ ፍጻሜያችሁ እያሰባችሁ በመጨነቅ ልትኖሩ ትፈልጋላችሁ? እነዚያን ሁሉ ሕግጋት

መጠበቃችሁን ለማረጋገጥ ቀኑን ሙሉ እየፈጋችሁ ለመኖር ትሻላችሁ? ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ለመቅረብ በእነዚያ በረዥም ሥርዓቶች፥ የእንስሳት መሥዋዕቶችን አጊጦ በለበሰው ሰብአዊ ሊቀ ካህን በኩል ለማለፍ ትፈልጋላችሁ? እኔ ግማሽ ዕድሜዬን የፈጀሁት እነዚህን ሕግጋት ለማጒላት ደፋ ቀና ስል ነበር፤ እናንተም ከፈለጋችሁ ልታደርጉት ትችላላችሁ። በሕግና በመንፈስ መካከል ያለው ልዩነት በሞትና በሕይወት፥ በባርነትና በነጻነት፥ በጮርቃነትና በበሳልነት መካከል እንዳለው ያህል ነው። ሰው ወደዚያው ለመመለስ ለምን ይሻል?»

በጳውሎስ አገላለጽ፥ የብሉይ ኪዳን መንገድ «በፊደላት በድንጋዮች ላይ የተቀረጸ የሞት አገልግሎት» ነው። ይህም ወደ ክርስቶስ እንዲመራን የታሰበ ሞግዚት ብቻ ነበር። ለዘላለም በመዋዕለ ሕፃናት ለመኖር የሚፈልግ ማን ነው? ጳውሎስ እንዳለው፥ «የዚያንም ይሻር የነበረውን መጨረሻ ትኩር ብለው የእስራኤል ልጆች እንዳይመለከቱ፥ በፊቱ መጋረጃ እንዳደረገ እንደ ሙሴ አይደለንም. . . ጌታ ግን መንፈስ ነው፤ የጌታም መንፈስ ባለበት በዚያ አርነት አለ።»

የእግዚአብሔር ዕቅድ ለሁለቱም ወገኖች የሚያስከትለው ኪሳራ አለው። ይህም ለእኛ፥ እምነትንና ታዛዥነትን የሚፈልግብንን የሚታይ አምላክ ለመከተል ራሳችንን አሳልፈን በመስጠት በራስ መቆማችንን መጣል ማለት ነው። ለእግዚአብሔር ደግሞ እኛም እንደ እስራኤላውያን የማናድግ ጨቅላዎች ሆነን በመቅረት «ልናከስረው» የምንችል መሆናችን ነው። ምናልባትም ሳናፈቅረው ቀርተን እናከስረው ይሆናል። ይሁንና፥ ይህ ሊቀበለው የሚገባው አደጋ እንደሆነ አስቧል።

የድምፆች አሐዱ–ሥሉስነት

የእግዚአብሔርን ዕቅድ እንደ ተከታታይ ድምፆች አድርገህ አስብ። የመጀመሪያው ነጎድጓዳዊ ድምፅ የተወሰኑ ጠቀሜታዎች ነበሩት። በሚንቀጠቀጥ የሲና ተራራ ላይ ድምፅ ሲሰማ፥ ወይም በቀርሜሎስ ተራራ እሳት ወርዶ መሥዋዕቱን ሲበላ እየተመለከተ፥ ማንም የእግዚአብሔርን ኃይል ሊክድ አይችልም ነበር። የሚገርመው ግን የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምተው የፈሩት እስራኤላውያን እንኳ እዚያው በሲናና በቀርሜሎስ ወዲያው ረስተውታል። የድምፁ ግዙፍነት ማዕቀብ ጣለባቸው። ጥቂቶች ያንን ድምፅ ፈለጉት፥ ድምፁ ዝም ካለ በኋላ በእምነታቸው የሚጸኑት ደግሞ የጥቂቶቹ ጥቂቶች ብቻ ነበሩ።

በኢየሱስ ጊዜ ያ ድምፅ ዝግ አለ፤ ቃል ሥጋ ሆነ። ለጥቂት አሥርተ–ዓመታት የእግዚአብሔር ድምፅ በፍልስጥኤም የሚኖረውን የአንድ ባላገር የድምፅ ጥራት፥ መጉላትና ቃና ይዞ ቆየ። ይህ የተለመደው የሰው ልጅ ድምፅ ነበር፤ እናም ምንም እንኳ በሥልጣን

ቢናገርም፥ ሰዎች በርግገው እንዲሸሹ አላደረገም። የኢየሱስ ድምፅ ሰዎች እስከ.ምግቱትና እስኪገድሉት ድረስ ለስላሳ ነበር።

ኢየሱስ ካረገ በኋላ ያ ድምፅ ሌላ አዲስ መልክ ያዘ። በዕለተ በዓለ ኀምሳ በታዕግኝነት ጌታን በሚከተሉት ሰዎች ላይ ልሳናት–ወረዱ፤ ከዚያም የእግዚአብሔር አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ቅርጽ መያዝ ጀመረች። ያ የመጨረሻው ድምፅ እንደ ትንፋሽ የቀረበና እንደ ፉጨት ለሆሳስነትን የተላበሰ ነበር። ከሁሉም ድምፆች የለሰለሰ በመሆኑ፥ ችላ ለማለት በጣም ይቀላል። መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስን «ማጥፋት» ወይም «ማሳዘን» እንደሚቻል ይናገራል፤ ሙሴ የተመለከተውን የቁጥቋጦ እሳት ወይም የሲና ተራራ የቀለጡ ዓለቶች ለማጥፋት መሞከር ይችል ይሆን? ይሁንና፥ መንፈስ ቅዱስ እጅግ የቀረበ ድምፅ ነው። ምን እንደምንጸልይ በማናውቅበት የድካማችን ጊዜ በውስጣችን የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ በቃላት በማይገለጽ መቃተት ይማልድልናል። እነዚያ ቃተታዎች የአዲስ ፍጥረት የምጥ ጣሮች ናቸው።

መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ቅይማት በሙሉ አያስወግደውም። ለመንፈስ ቅዱስ የተሰጡት ስሞች ራሳቸው–አማላጅ፥ ረዳት፥ አማካሪ፥ አጽናኝ–ችግሮች እንደሚኖሩ ያመለክታሉ። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ «ወደፊት ለሚመጣው ነገር ዋስትና የሚሆን መያጣ» ነው፤ ይህም ጳውሎስ ከዘመኑ የንግድ ቋንቋ የተዋሰው ምድራዊ ቋንቋ ነው። መንፈስ ቅዱስ እንዲህ ዓይነቶቹ ቅይማቶች ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም ከመኖራችን በፊት የሚከሰቱ ጊዜያዊ ነገሮች መሆናቸውን ያስታውሰናል። እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ዳግም ከመፍጠሩ በፊት መንፈሳዊ መያያዝ ከስፍራው መመለስ እንዳለበት አስዷል።

አዲስ ኪዳን በሁለት ስፍራዎች በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን መጠጥ ጠጥቶ ከመስከር ጋር ያነጻጽረዋል። በመካከላቸው መሠረታዊ ልዩነት እንዳለ ቢታወቅም፥ ሁለቱም ክስተቶች የሕይወትን አበሳዎች የምትመለከትበትን መነጽር ይለውጣሉ። ብዙ ሰዎች የሥራ አጥነት፥ የሕመምና የግላዊ ጎዘን ቅይማታቸውን ለማስታመም ወደ መጠጥ ያዘነብላሉ። ይሁንና የሰከረ ሰው ከፈንጠዝያው ዓለም ተመልሶ ካልተለወጠው እውነታ ጋር እንደሚፋጠጥ ግልጽ ነው። መንፈስ ቅዱስ ግን ለዘላለም ነቅተን የምንኖርበት እውነተኛ ደስታ እንዳለ በለሆሳስ ይነግረናል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፡– ሮሜ 8፤ ኤፌሶን 3፤ 1ኛ ጴጥሮስ 1፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 12፤ ኤፌሶን 5፤ ፊልጵስዩስ 2፤ ኤፌሶን 2፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 3፤ ገላትያ 3፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 3፥5።

በድቅድቅ መመልከት

ነፍሴ ሆይ፥ ዝም በዪ፥ የእግዚአብሔርንም
ጽልመት ተጋፈጪ
ነፍሴ ሆይ፥ ዝም በዪ፥ ያለ ተስፋ ቆዪ
የተስፋ ተስፋነቱ ትክክል ላልሆነ ነገር ነውና፤
ያለ ፍቅርም ኑሪ፥
የፍቅር ፍቅርነቱ ትክክል ላልሆነ ነገር ነውና፤
ይሁንና እምነት አለ
ዳሩ እምነት፥ ፍቅርና ተስፋ ሁሌ በመጠባበቅ ውስጥ ናቸው።

–ቲ. ኤስ. ኤልየት "East Coker"

ምዕራፍ 21

ጣልቃ

አንድ ሌሊት በምድር ቤት ከሚገኘው ቢሮዬ ውስጥ ተቀምጬ የዚህን መጽሐፍ ቀጣይ ክፍል ማውጫ እሠራ ጀመር፤ ይህም ከለሳና ማጠቃለያ እንዲሆን ያሰብሁት ነበር። ለበርካታ ዓመታት በዚሁ ከእግዚአብሔር ጋር በመቀያየም ርእሰ-ጉዳይ ላይ ብዙ አሳቦችን አሰባስቤ ስለነበር፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ ከተማርሁት አንጻር እየከለስሁ አነባቸው ጀመር።

ይህንኑ ተግባር በማከናውንበት ጊዜ፥ ሪቻርድ መጀመሪያ ከቤቴ ስለመጣበትና ሦስቱን ታላላቅ ጥያቄዎችን ስላነሣበት ሰዓት አሰብሁ። እነዚህ ስለ እግዚአብሔር ፍትሐዊነት፥ የራሴው ጥያቄዎች በመሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ መፍትሔ እንድፈልግ አድርገውኛል። ይህንኑ ፍለጋ በጀመርሁበት ወቅት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የልብሱን እጀታ አጣጥፎ ለሰዎች በሚታይ ኃይል ወደ ሕይወቴ የሚጠልቀውን ተንቀሳቃሽ አምላክ ስሻ ነበር። ቢያንስ ቢያንስ ምሥጢራዊነቱን በማጥበቅ ስውርና ዝምተኛ ሆኖ የማይቆይ አምላክ ፈልጌ ነበር። ይህ በመሠረቱ፥ ብዙም እግዚአብሔርን ማስቸገር አልነበርም።

ይሁንና፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዳንድ አስገራሚ ነገሮች አሉ፤ ይኸውም እነዚያ ተአምራት በተደጋጋሚ የተፈጸሙባቸው ጊዜያት ብዙውን ጊዜ ዘለቄታዊ እምነት አለማስከተላቸው ነው። እንዲያውም እውነቱ የተገላቢጦሽ ነው፤ ብዙዎች የእምነት አልባነት ምሳሌዎች ሆነዋል። መጽሐፍ ቅዱስን ይበልጥ ባጠናሁ ቁጥር ዕለት በዕለት መና የሚወርድባቸውንና ከሰማይ እሳት የሚወረወርባቸውን «ጥንታዊ ወርቃማ ጊዜያት» መናፈቁ እየቀነሰ መጣ።

ከሁሉም በላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔርን የአመለካከት ጨረፍታ አግኝቻለሁ። የእግዚአብሔር ዓላማ (አገላለጹ ትክክል ከሆነ) ተጠራጣሪዎችን ሁሉ ብርሃን በሚተፋ ብርሃን ማዛል አይደለም፤ ቢፈልግ ኖሮ ይህንን በአንድ ቅጽበት ሊያደርግ ይችል ነበር። ይልቁንም፥ እግዚአብሔር እርቅን ይሻል-ሊወደድ ይፈልጋል። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ኃይልን ሳይጠቀም ወደ ሰዎች ለመድረስ ያደረጋቸውን ግልጽ ጥረቶች ያሳያል፤ ይኸውም በወላጅነት ከዕብራውያን ላይ ከሰፈፈው እግዚአብሔር አብ የእግዚአብሔርን ፍቃድ «ከታች ወደ ላይ» ወዳስተማረው እግዚአብሔር ወልድ፥

ከዚያም በእግዚአብሔር ህልውና ወደሚሞላን ወደ መንፈስ ቅዱስ እያደገ መሄዱ ነው። በአሁኑ ዘመን የምንኖር ክርስቲያኖች የሚያስደንቅ ዕድል ተጠቃሚዎች እንጂ ያልታደልን አይደለንም፤ ለዚህም ምክንያቱ እግዚአብሔር በምድር ላይ ፈቃዱን ለመፈጸም እኛን ቀዳሚ መሣሪያዎች አድርጎ የመረጠን ስለሆነ ነው።

በዚያን ምሽት አስተዋጽኦዬን ስሠራ እነዚህን አሳቦች የከለስሁት እያደገ በሚሄድ ጉጉት ነበር። አሁንም ቀስ እያልሁ ሌላ ወረቀት ሳገላብጥ ከሜግ ዉድሰን የተጻፈልኝን ደብዳቤ አገኘሁ።

ሜግን ከአሥር ዓመታት ለሚልቅ ጊዜ አውቃታለሁ። ጌታን የምትወድ ትጉ ክርስቲያን፥ የመጋቢ ሚስትና ገላጭ ብዕረኛ ነች። ይሁንና፥ ስለ ሜግ ባሰብሁ ቁጥር የኃዘን ሾተል ይወጋኛል።

ሜግና ባለቤቷ፥– ፔጊ እና ጆይ የሚባሉ ልጆች ወልደው ነበር። ሁለቱም ልጆች የ«ፌብሮስስ» ሕመም ተጠቂዎች ነበሩ። ፔጊና ጆይ ምንም ያህል ቢመገቡ ቀጫጫ ከመሆን አላመለጡም። በሽታው ባለማቋረጥ የሚያስላቸው ሲሆን፥ መተንፈስም ይቸግራቸው ነበር። ልጆቹ በየዓመቱ ለበርካታ ሳምንታት በሆስፒታል ውስጥ ያሳልፉ ነበር። በዚህ ዓይነት ምናልባትም ለታዳጊ ወጣትነት ዕድሜ ሳይደርሱ እንደሚሞቱ እየተገነዘቡ አደጉ።*

ንቁና ደስተኛ የነበረው ጆይ በ 12 ዓመቱ ሞተ። ፔጊ ከዚያ በኋላ ብዙ ጊዜ በሕይወት በመቆየት መላምቱን ፉርሽ አደረገች። ምንም እንኳ ከዚህ በሽታ በተአምር ስለተፈወሰ ሰው የሰማነው ዘገባ ባይኖርም፥ ለፔጊ ፈውስ መጸለያችንን አላቋረጥንም። ፔጊ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አያሌ የጤንነት ችግሮችን ካሳለፈች በኋላ ወደ ኮሌጅ አመራች።

ይበልጥ እየተጠናከረች የምትሄድ መስላ በመታየቷ ከልባችን ውስጥ ተፈውሳ ይሆናል የሚል ተስፋ ተጫረ።

---

* ሜግ ስለ ሁለቱ ልጆቿ ጠንከር ያለና ስሜትን የሚነካ መጽሐፍ ጽፋለች፥– *"Following Joey Home; I'll Get to Heaven Before You Do! and The time of Her Life."*

ነገር ግን የፈውስ ተአምር አልተከሰተም ነበር፤ ፔጊ በሃያ ሦስት ዓመቷ ሞተች። በዚያን ሌሊት ከፔጊ ሞት በኋላ እናቷ የጻፈችልኝን ደብዳቤ ነበር ያገኘሁት።

«ስለ ፔጊ አሟሟት ልነግርህ ፈለግሁ። ስለ ጉዳዩ ተናገሪ የሚል ከፍተኛ ግፊት ከሚሰማኝ በቀር ምክንያቱን አላውቅም። ጓደኞቼ ከአንድ ጊዜ በላይ በዚህ ጉዳይ እንዲታወኩ ስለማልፈልግ፥ የልቤን የማጫውተው ሰው አልነበረም።

«ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ሆስፒታል ከሄደችበት የሳምንቱ የመጨረሻ ቀን ቀደም ብሎ ፔጊ፦ አገልጋዩ ከዊሊያም በርክሌ ጽሑፍ ውስጥ ባገኘው ጥቅስ በጣም ተደስታ ነበር የመጣችው። በአሳብ እጅግ ስለተመሰጠች ጥቅሱን በካርድ ላይ ገለበጠችልኝ፤ «ትዕግሥት አንድን ከባድ ነገር መሸከም መቻል ብቻ ሳይሆን፥ ወደ ክብር መለወጥም ነው።» ፔጊ አገልጋዩ በዚያን ጊዜ ከባድ ሁኔታ ሳያጋጥመው እንዳልቀረ ገምታለች። ይህንንም የተገነዘበችው ከበርክሌይ የወሰደውን ጥቅስ ከተናገረ በኋላ፥ ምስባኩን በቡጢ ሲነርትና ጀርባውን ለምእመናኑ አዙሮ ሲያለቅስ ስለተመለከተችው ነበር።

«ፔጊ ከሆስፒታሉ ውስጥ ከቆየችና ነገሮች እየከበዱ ከሄዱ በኋላ፥ ዙሪያዋን የከበቧትን የሞት አጋሮች ተመለከተች። ከዚያም፥ «አይዞሽ እማ! ያንን ጥቅስ ታስታውሽ የለ?» አለች። ቀጥላም ቱቦዎቹን ሁሉ ተመለከተች፤ የምላሷን ጫፍ ከአፍዋ ዳርቻ አላወሰች፤ ዓይኖቿንም ራሷን በሰጠችው ሙከራ ላይ በመገረም ገለጠች።

«መሰጠቷ በገሃድ ዓለም ውስጥ ያለው የማንኛውም ነገር ግንዛቤዋ እስከቆየበት ጊዜ ድረስ ቆይቷል። አንድ ጊዜ የኮሌጅ ዲን ሊያያትና ሊጸልይላት የሚገባው ውስን ጉዳይ ካለ ሊጠይቃት መጥቶ ነበር። በዚህ ጊዜ ለመነጋገር እስከማትችልበት ድረስ ተዳክማ ነበር። ይሁንና፥ የበርክሌይን ጥቅስ እንዳብራራለትና እየተጋፈጠች ያለችው ከባድ ጊዜ ወደ ክብር ይለወጥ ዘንድ እንዲጸልይ እንድነግረው በምልክት አሳየችኝ።

«ከመሞቷ ጥቂት ቀደም ብሎ ከአልጋዋ አጠገብ ሳለሁ ታለቅስ ጀመር። ያንን የጎላ፥ መራራና ለቅሶ መቼም ቢሆን አልረሳውም። ነርሶች ከያሉበት ተሯሩጠው በመምጣት በፍቅራቸው ከበቧት። «አይዞሽ ፔጊ፥ ምንም አትሆኚም።»

«ነርሶቹን ሰውነቷን ይዳስሱ ጀመር። በቃላትና በዳሰሳ ለጊዜው ዝም አሰኙዋት (ምንም እንኳ ጊዜው እየገፋ ሲሄድና ጩኸቷም ሲቀጥል ሊረዱት ባይችሉም)። እንዲህ ዓይነት ርኅራኄ ብዙም አጋጥሞኝ አያውቁም። የፔጊ ልዩ ጓደኛ የሆነችው ነርስ ዌንዲ እንደነገረችኝ፤ ከበሽተኞቿ ቢያንስ አንዱን ለማዳን የሚቻል ቢሆን አንድ ሳንባዋን ለመስጠት የማትፈቅድ ነርስ በዚያ ግቢ ውስጥ አትገኝም።

እንግዲህ ከዚህ ሥረ-መሠረት በተቃራኒ ነው የሰው ልጆች የሚያልቁት። ምክንያቱም ነርሶች ከዚህ በላይ ሊረዱ አይችሉም። ሊረዳ የሚችለው እግዚአብሔር ግን ለእርሱ ክብር ለማምጣት ልትሞት የፈቀደችውን ወጣት ሴት ተመልክቶ ሞቷ የ "Cystic fibrosis" በሽተኞቹን የሥጋት ሠንጠረዥ እንዲያንር አድርጓል።

«ፊልፕ፥ ከሥቃይ ስለሚወጣ መልካም ነገር መነጋገሩ ዋጋ የለውም። ወይም ደግሞ እግዚአብሔር ተፈጥሮአዊ የበሽታ ሂደት ፈሩን ተከትሎ እንዲሄድ የሚያደርግ መሆኑን መናገሩ ጠቃሚ አይሆንም። ለዚህም ምክንያቱ ጣልቃ ቢገባም እንኳ በእያንዳንዱ የሰው ልጅ ሥቃይ ውስጥ ጣልቃ መግባት እንዳለበት ወይም እንደሌለበት የሚወስን መሆኑ ነው። በፔጊ ጊዜ ምርጫው በሽታው እንዲረታት መፍቀድ ነበር። ለዚህ ምርጫው የሐዘንና የቁጣ ምላሾቹን ብቻ የምሰጥባቸው ጊዜያት አሉ። ይህንን መግለጹም የልብን ሥቃይ አያጠፋውም።

«ፔጊ ከቶውንም በእግዚአብሔር ላይ አላጉረመረመችም። ይህ የቅድስና እርምጃ አልነበረም፤ የማጉረምረሙ አሳብ ተከስቶላት የሚያውቅ አይመስለኝም። በሞቷ ውስጥ ከነበርን መካከልም በጊዜው ያጉረመረመ ሰው አልነበረም። ሁላችንም የእርሷን ምላሽ እንደግፍ ነበር። የእግዚአብሔር ፍቅር እውነተኛ በመሆኑ፥ ሊጠራጠር የሚችል ሰው አልነበረም።

«ይህን ሁሉ የምነግርህ ለእኔና ለፔጊ ችግር አንድ ዓይነት መፍትሔ ለማግኘት በሚደረግ ጥረት፥ ምናልባትም የእግዚአብሔርን ፍቅር እንዳገኝ ወደሚረዳኝ ነገር እንደገና ትመልሰኝ ይሆናል። ይኸውም «እኔ አለሁልሽ ሜግ!» የሚለው የእግዚአብሔር ዳሰሳ መሆኑ ነው። ነገር ግን እንደዚያ ባለ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ እንዴት ዝም እንደሚል ግሰቤ አልቀረም።

«ይህን ነገር ከዚህ ቀደም ለማንም ትንፍሽ አላልሁም፤ የሰውን እምነት እንዳላናጋ በመፍራት። የእኔን ስሜት ለማሻሻል የሆነ ነገር መናገር እንዳለብህ አታስብ። ይሁንና፥ የልቤን ሥቃይ ስለተካፈልሽኝ አመሰግንሃለሁ። የሰውን ችግር መካፈል ምን ያህል ርዳታ ማበርከት እንደሆነ ብዙዎቹ ሰዎች አይገነዘቡም።»

የሜግን ደብዳቤ ካነበብሁ በኋላ፥ በዚያን ሌሊት ሥራዬን ለመቀጠል አልቻልሁም።

ከዚህ ሲታይ

አሮጌዎቹ ጥያቄዎች እንደገና ተቆሰቆሱ፤ ስለ ማኅበራዊ ፍትሕ-አልባነት፥ ስላልተመለሱ ጸሎቶች፥ ስላልተፈወሱ በሽተኞችና ስለ ሌሎችም ተቆጥረው የማይዘለቁ አድልዎዎች የማስባቸው ጥያቄዎች

ሁሉ ወጥረው ያዙኝ። የሪቻርድም ጥያቄዎች አዲስ ስሜታዊ ጉልበት ተላብሰው እንደገና ተከሰቱ፤ ይህም ሜግ ከልጁ የሆስፒታል አልጋ አጠገብ በኃዘን ታጥራ በምትቀመጥበት ወቅት የተሰማት ስሜት ዓይነት ነበር።

በዚህ ዓለም ጉዳይ ላይ የእግዚአብሔር አቋምና አምላክነት ራሱ ምን ዓይነት ስሜት እንደሚያሳድር ለመረዳት መጽሐፍ ቅዱስን ሳጠና ቆይቻለሁ። ይህንንም ያደረግሁት እንዲህ ዓይነቱን መለኮታዊ ግንዛቤ ለመጨበጥ እንደማንበቃ ሳልረዳ ቀርቼ አይደለም። ይህም ሆኖ፥ የሜግ ደብዳቤ ወደ ሌላ አቅጣጫ ስለገፋኝ ለዚህ መጽሐፍ የመጨረሻ ክፍል የነበረኝም ጠቅላላው አቀራረብ ተለውጧል።

የእግዚአብሔርን የአመለካከት ደረጃ መመልከቱ መልካም ቢሆንም፥ የራሳችንም የአመለካከት እይታ እንዴት ነው? አምላክ መሆን ምን ዓይነት ስሜት እንደሚያሳድር ስመረምር ነበር፤ የሜግ ደብዳቤ ሰው መሆን ምን ስሜት እንደሚያሳድር ወደ ማሰቡ መልሶኛል። የእርሷ ጥያቄዎች የልብ እንጂ የጭንቀት ጥያቄዎች አልነበሩም። እንደ እናትነቷ፥ ልጆቿ አስከፊ ሞት ሲሞቱ ተመልክታለች። ይሁንና፥ እንደ ክርስቲያን ደግሞ አፍቃሪ አምላክ እንዳለ ታምናለች። ሁለቱን እንዴት ታጋጥማቸው?

በዚያን ሌሊት ይህ መጽሐፍ እንዳልተጠናቀቀ ተረዳሁ። እንደ ሜግ በኃዘን በተጠለለው ዓለም ውስጥ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሚፈልጉ ሰዎች ምላሽ ካልሰጡ ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-አሳቦች ብዙም ሊፈይዱ አይችሉም። «ጆን አፕዲክ» በተባለ የልቦለድ መጽሐፍ ውስጥ፥ «አንድ የተበላሸ ነገር አለ። እምነት የለኝም ወይም ደግሞ እምነት ኖሮኝ ከሥራ ላይ አይውልም።» ሲል የተናገረው ግራ የተጋባ አገልጋይ ትዝ ይለኛል። ከሥራ ላይ የሚውለው እንዴት ነው? ከእግዚአብሔር ዘንድ አንድ ነገር ለመጠበቅ ምን መብት አለን?

«እግዚአብሔርም ሰይጣንን፦ በውኑ ባሪያዬን ኢዮብን ተመለከትኸውን? በምድር ላይ እንደ እርሱ ፍጹምና ቅን፥ እግዚአብሔርንም የሚፈራ፥ ከክፉትም የራቀ ሰው የለም አለው»

ኢዮብ 1፡8

ምዕራፍ 22

ብቸኛው ችግር

«እዚህ አንድ ቤተ ክርስቲያን ስላለ ወደዚያው እሄዳለሁ። በየእሑዱ ጠዋት ቤቴን ትቼ በነጭ ዓምዶች ወደተገነባችው ቤተ ክርስቲያን አሽቆለቁላለሁ። በትልቅ ሰንበት ቀን ወደ ሃያ አምስት የምንደርስ ምእመናን እንሰበሰባለን፥ ብዙውን ጊዜ ከስድሳ ዓመት ዕድሜ በታች ያለሁት እኔ ብቻ በመሆኔ፥ የሩሲያን የከርሰ-ምድር ጥናቶች በሚገበኝ ቡድን ውስጥ እንዳለሁ ያህል ይሰማኛል። ምእመናኑ ከተለያዩ የእምነት ክፍሎች (ዲኖሚኔሽናች) የተሰባሰቡ ናቸው። አገልጋያችን የኮንግርጌሽናል ቤተ ክርስቲያን አባል በመሆኑ ነጭ ሸሚዝ ይለብሳል። ሰውዬው እግዚአብሔርን ያውቀዋል። አንድ ጊዜ ለዓለም ሁሉ ግለትም ለመሪዎቿ ጥበብ፥ በሥቃይና በኃዘን ላሉት ተስፋና ምሕረት፥ ለተጨቆኑት መፈታት፥ በአጠቃላይም ለሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ጸጋ እንዲበዛላቸው በመጸለይ እየግለደ እያለ በመከከል አቋርጠ ይጮህ ጀመር፤ ጌታ ሆይ፥ ይህንኑ ልመና በየሳምንቱ በፊትህ እናቀርባለን» ሲል ተናገረ። ለአፍታ ድንግጥ ብሎ ከቆመ በኋላ፥ ጸሎቱን ቀጠለ። ከዚህ የተነሣ፥ ሰውዬውን በጣም እወደዋለሁ።»

–ኢን ዲላርድ፥ Holy the Firm

እስካሁን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዱን መጽሐፍ አግልያለሁ። ይህም በኮንግርጌሽናል አገልጋይ፥ በሪቻርድና ሜግ፥ ከሞላ ጎደል ስለ እግዚአብሔር በሚያስቡ ሰዎች ሁሉ የሚነሡትን ጉዳዮች የሚጋፈጥ መጽሐፍ ነው። የሜግን ደብዳቤ ካነበብሁ በኋላ፥ ራሴን ያገኘሁት የኢዮብን መጽሐፍ ሳነብ ነበር።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙት ሁሉ የበለጠ ዕድሜ ሊኖረው ይችላል የሚባልለት የኢዮብ መጽሐፍ ከፍተኛ ዘመናዊነት ይታይበታል። ጣዕም በሌለው ዓለም ውስጥ አበሳ ስለሚያየው አንድ ሰው ያቀረበው የጠለቀ ገለጻ የዘመኑን ጎብረተሰብ ሥቃይ ያንጸባርቃል። ከመጽሐፍ ቅዱስ የትኛውንም ነገር የማይፈልጉ ሰዎች ለተሐድሶ መጽሐፈ ኢዮብን ያነባሉ። እንግሊዛዊቷ የልቦለድ ደራሲ ሙርዬል ስፓርክ “The Only Problem” ወይም «ብቸኛው ችግር» በሚለው መጽሐፍዋ ውስጥ «ሊያነጋግረን የሚገባው ብቸኛው ችግር መልካም የሆነው አምላክ እንዴት ክፋት እንዲፈጸም ይፈቅዳል? የሚለው ነው» ስትል የኢዮብን ዋነኛ ጭብጥ አንሥታለች። የሥቃይ ችግር የዘመናችን ሥነ-መለኮታዊ አነጋጋሪ ጉዳይ ሲሆን፥ ጥንታዊው ኢዮብ ከማንኛውም ጊዜ በተሻለ ሁኔታ ገልጾታል።

ሪቻርድ እጮኛውንና ሥራውን ስላጣ፥ ብሎም የተረጋጋ ቤተሰባዊ ሕይወት ሊያገኝ ባለመቻሉ አጉረምርሟል። ሜግ ልጆቿን ስላጣች አንብታለች። ይሁንና፥ በየትኛውም መመዘኛ ሲለካ የኢዮብ እጦት ከእነዚህ ወዳጆቼ ይልቃል። 7000 በጎች፥ 3000 ግመሎች፥ 5000 በሬዎች፥ 500 አህዮችና በርካታ አገልጋዮች ወድመዋል። ከዚያም በአንድ ኃይለኛ የነፋስ ማዕበል የኢዮብ ሰባት ወንዶችና ሦስት ሴቶች ልጆቹ አልቀዋል። በመጨረሻም፥ ከእግር ጥፍሩ እስከ ራስ ፀጉሩ ድረስ ሰውነቱ በቁስል በመመታቱ መጽናናው የነበረው ጤንነቱ ከዳው። በአንድ ቀን በምሥራቁ ዓለም እጅግ ታላቅ የነበረው ሰውዬ እጅግ ወደሚታዘንለት ደረጃ ተሻገረ።

ኢዮብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር የመቀያየም ብቸኛው ታሪክ ሲሆን፥ ሪቻርድ፥ ሜግ ወይም ማናችንም ልንጋፈጥ የምንችለውን ማንኛውንም ዓይነት ቅይማት የሚያመለክት ይመስላል። አንድ አሜሪካዊ የሃይማኖት መምህር (ራባይ) "When Bad Things Happen to Good People" ወይም «በጥሩ ሰዎች ላይ ክፉ ነገሮች ሲደርሱ» በሚል ርእስ አንድ ተወዳጅ መጽሐፍ ጽፈዋል። መጽሐፈ ኢዮብ ከዚህ የባሰ ጉዳይ አንሥቷል። ይኸውም እጅግ መልካም በሆኑት ሰዎች ላይ እጅግ የከፉ ነገሮች መድረሳቸው ነው።

የተሳሳተ ግንዛቤ

መጽሐፈ ኢዮብን ማጥናት እንደ ጀመርሁ የሚያስተላልፈው መልእክት ምን እንደሆነ ብትጠይቁኝ ፈጥኜ በመለስሁ ነበር። *መጽሐፈ ኢዮብ ስለ ምን እንደሚያወራ ማን ያጣዋል? ኢዮብ መከራን ስለመቀበል መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተላልፈው ፍጹም የተሟላ አቀራረብ ነው።* ኢዮብ እጅግ ስለ ከፋው ኃዘንና የሚሰቀጥጥ ሥቃይ የሚናገር መጽሐፍ ነው። የመጽሐፉ ግዙፍ ክፍል መከራን በመቀበሉ ጭብጥ ላይ እንደሆነ ጥርጥር የለውም። ከምዕራፍ 3–37 አምስት ብስጩ ሰዎች ስለ መከራ ከሚያነሡት የአሳብ ልውውጥ በቀር የሚታይ ተግባር አይስተዋልበትም። ሰዎቹም ኢዮብ፥ ሦስት ጓደኞቹና የማይጨበጠው ኤሊሁ ነበሩ። ሁሉም ቀደም ሲል ምርጥ የመኖሪያ ቤቱ በነበረው ስፍራ ከአፈር ላይ ብቻውን አዝኖ በተቀመጠው ኢዮብ ላይ ስለደረሰው የከፋ ሁኔታ ምላሽ ለማግኘት በመማር ላይ ነበሩ።

አሁን አሁን መጽሐፉን በትክክል እንዳላነበብሁ፥ ወይም ደግሞ ጠቅላላውን መጽሐፍ እንዳላገናዘብሁ አምናለሁ። የሚበዛው የመጽሐፈ ኢዮብ ክፍል ስለ መከራ ችግር እንደሚናገር ቢታወቅም፥ መጽሐፉ ስለ መከራ እንዳልተጻፈ በመግለጽ ልደመድመው እሻለሁ። መከራ የታሪኩ አካል እንጂ ዐቢይ ጭብጥ አይደለም። አንድ ኪክ

እንቁላል፥ ዱቄት፥ የዱቄት ማጣበቂያና ወተት እንዳልሆነና ኬክን ለመሥራት ግን እነዚህ ነገሮች እንደሚያስፈልጉ ሁሉ፥ መጽሐፈ ኢዮብ ስለ መከራ የሚናገር መጽሐፍ አይደለም። ይልቁንም መጽሐፉ ይበልጥ ጠቃሚ በሆኑትና ዓለም–አቀፋዊ ይዘት ባላቸው ጥያቄዎች ውስጥ እነዚህን ነገሮች የታሪኩ ማበልጸጊያ አድርጎ ይጠቀማል። ሙሉውን ገጽታ ስንመለከተው፤ መጽሐፈ ኢዮብ የሚናገረው እምነትን ለጅግ ግልጽ በሆነ መልኩ ነው።

ወደዚሁ ድምዳሜ ያመራሁበት ቀዳሚ ምክንያት የኢዮብ ምድራዊ የግል ድራማ ሰማያዊ መነሻ እንዳለው ከሚያመለክቱት የምዕራፍ አንድና ሁለት መግቢያዊ «መዋቅሮች» የተነሣ ነው። አንድ ጊዜ ኢዮብን የሰው ልጆች ቅይማት ዋነኛ መገለጫ አድርጌ አቅርቤያለሁ፤ ይህም ረዥም፥ ዝርዝርና ቀጥተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማዕቀብ ያለበት ከመሆኑ በቀር የሜግ ዉድሳን ደብዳቤ ዓይነት ነበር የመሰለኝ። ይሁንና፥ መጽሐፉን ይበልጥ እያጠናሁ ስሄድ ሰብአዊውን የአመለካከት አቅጣጫ እንደማይቀርብ ተረዳሁ። እግዚአብሔር የመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከላዊ ገጸ ባሕርይ መሆኑ ባይታበልም፥ እንደ መጽሐፈ ኢዮብ ግልጽ ሆኖ የታየበት ስፍራ አይገኝም። ሁልጊዜም መጽሐፉን ከምዕራፍ 3 ወዲያ ማለትም ከኢዮብ የእይታ መነጽር ሳነብ መቆየቴን ተገነዘብሁ።

አሳቤን ግልጽ ላድርግ።

መጽሐፈ ኢዮብን ወንጀለኛው እንዳልታወቀበት የምርመራ ድራማ አድርጎ መመልከቱ ጠቃሚ ነው። ድራማው ራሱ ከመጀመሩ በፊት፥ ተመልካቾች የሆንነው ሰዎች አነስተኛ ቅድመ እይታ እናገኛለን፤ ይኸውም የድራማው ዳይሬክተር ስለ ሥራው ለጋዜጠኞች መግለጫ እየሰጠ ሳለ እንደደረሰን ያህል ነው (ምዕራፍ 1–2)። መዋቅሩን ይተርክልንና ዋነኞቹን ገጸ– ባሕርያት ይዘረዝርልናል፤ ከዚያም በድራማው ውስጥ ማን የትኛውን ቦታ እንደሚሸፍን ምክንያቱን ጭምር አስቀድሞ ይነግረናል። እንዲያውም፥ ከአንዱ በቀር በድራማው ውስጥ የሚገኙትን ችግሮች ሁሉ ይፈታል፤ «የዋናው ገጸ– ባሕርይ ምላሽ ምን ይሆን?» ለሚለው ጥያቄ ብቻ መልስ አይሰጠንም። «ኢዮብ እግዚአብሔርን ያምናል? ወይስ ይክዳል?»

በኋላ መጋረጃው ሲከፈት ከመድረኩ ላይ የምንመለከተው ተወንያኑን ብቻ ነው። በድራማው ውስጥ በመዋጣቸው፥ ዳይሬክተሩ አስቀድሞ ስለነገረን ነገር የሚያውቁት የላቸውም። እኛ «ለማይታወቁ» ጥያቄዎች መልስ አለን፤ ዋናው ተዋናይ የሆነው ኢዮብ ግን አያውቀውም። ቀደም ብሎ ለእኛ የተነገረውን ነገር ለማወቅ በመጣር

ከመድረኩ ላይ ጊዜውን ሁሉ ያባክናል። ራሱን በገል እየፈቀፈቀ፥ «ለምን እኔን? ምን አጠፋሁ? እግዚአብሔር ሊለኝ የሚፈልገው ምንድን ነው?» ሲል ይጠይቃል።

ቀደም ብለን መልሱን ከመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች ውስጥ ስለምናውቀው፥ የድራማው ታዳሚዎች ለሆንን ሰዎች የኢዮብ ጥያቄዎች ባዶ የአእምሮ መልመጃዎች ነበሩ። ኢዮብ ምን አጠፋ? ምንም። እርሱ ከሁሉም የተሻለ ሰው ነበር። ራሱ እግዚአብሔር «ፍጹምና ቅን፥ እግዚአብሔርንም የሚፈራ፥ ከክፋትም የራቀ» ሲል አልጠራውምን? እንግዲህ ኢዮብ ለምንድን ነው መከራ የሚቀበለው? ለቅጣት አልነበረም። እርሱ የተመረጠው በሰማያዊ አካላት ታላቅ ውድድር ውስጥ ዋነኛ ተዋናይ እንዲሆን ነበር።

ውርርድ

የራሴን አስተሳሰብ መለስ ብዬ በምገመግምበት ጊዜ፥ አንዳንዴ መጽሐፈ ኢዮብን እንዴት በተሳሳተ መንገድ ልረዳው እችል እንደነበር እገነዘባለሁ። ለዚህም ምክንያት ከሚሆኑት አንዱ የሰውን ልጅ የአጣብቂኝ ሕይወት በብርቱ ጉልበት የሚተነትነው የምዕራፍ 3–37 የገለጻ ኃይል ይመስለኛል። ይህንን ከፍል በምናነብበት ጊዜ በአገላለጹ ኃይል ተረተን የሚነሣውን ጥያቄ ሁሉ ቀደም ሲል በምዕራፍ 1 እና 2 እንደተመለሰ እንዘነጋለን። ሌላም ምክንያት አለ፤ ማንም ሰው የመጀመሪያዎቹን ሁለት ምዕራፎች ሚና አይረዳም። የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት እንኳ ይህንኑ ከፍል በኃፍረት ወደ መመልከቱ ያዘነብላሉ፤ ወይም ደግሞ በኋላ አንድ ሰው ጨምሮት ይሆናል ሲሉ መላ ይመታሉ። ቅደመ–ታሪኩ ሰይጣንና እግዚአብሔር የታሪክ አካላት መሆናቸውን ያሳያል፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ግብረሪያ መጻሕፍት ውስጥ እንደ ውርርድ ዓይነት ቀያይ ምልክቶች ልትመለከት ትችላለህ። የኢዮብ መከራ ሁሉ የመነጨው ሁለት ሰማያዊ አካላት ካነሡት ውርርድ ዓይነት ነገር ነበር።

ችግሩ የተቆሰቆሰው ሰይጣን ኢዮብ ከንቱ ሰው እንደሆነና ለእግዚአብሔርም የታመነው «በዙሪያው ያለው ሁሉ ስለታጠረለት» እንደሆነ በመናገሩ ነበር። ሰይጣን እግዚአብሔር በራሱ ሊወደድ የማይገባው ሆኖ ሳለ እንደ ኢዮብ ላሉት ሰዎች «ጉቦ» በመስጠት ተከታይ እንደሚያደርጋቸው በመግለጫ ይሳለቃል። ጊዜው ትንሽ ቢከፋባቸው እንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች እግዚአብሔርን ከመከተል እንደሚመለሱ ይናገራል። እግዚአብሔር የኢዮብ ምላሽ ለጉዳዩ እልባት እንዲሰጥ በመስማማት በሰይጣን የቀረበውን ንድፈ– አሳብ ሲቀበል፥ ባልጠረጠረው ኢዮብ ላይ አደጋዎች ይዘንቡ ጀመር።

ይህንን ሰማያዊ ውርርድ እንግድነት መቼም ልክደው አልችልም። በሌላ በኩል፥ በኢዮብ ውስጥ የሚገኘው የውርርድ ታሪክ ወደ ዘለዓለሙ መንግሥት የሚያመለክት አነስተኛ ቀዳዳ ስላለው ወደ ዳር ልገፋው አልችልም። ሰዎች በመከራ በሚናጡበት ጊዜ ኢዮብን ያስጨነቁት ጥያቄዎች ይከቡዋቸዋል። ለምን እኔን? እየሆነው ያለው ምንድን ነው? እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ግድ ይሰኛል? ለመሆኑ አምላክ የሚባል አለን? በዚህ የኢዮብ ሥቃይ ትረካ ወቅት ከመጋረጃ በስተጀርባ የመመልከት ዕድል የተሰጠው ለእኛ ለተመልካቾች እንጂ ለኢዮብ አልነበረም። የምንፈልገውን ነገር የመጽሐፈ ኢዮብ ቅድመ-ታሪክ ምዕራፍ (1 እና 2) ይሰጠናል፤ ይኸውም ዓለም ስለምትንቀሳቀስበት ሁኔታ በጨረፍታ የሚያሳየን ክፍል ነው። በየትኛውም ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በማይገኝ መልኩ፥ መጽሐፈ ኢዮብ ብዙውን ጊዜ ከእኛ የተሰወረውን ልዕለ-ተፈጥሮአዊ እንቅስቃሴን ጨምሮ የእግዚአብሔርን የእይታ አቅጣጫ ያሳየናል።

ኢዮብ እግዚአብሔር ንጹሑን ወገን እንደበደለ በመግለጽ ከሶታል። ኢዮብ እግዚአብሔርን ወደ መሳደቡ ጠርዝ እስኪደርስ ድረስ፥ የቁጣና የምፀት መዓት እያወረደ ተቅበዝብዟል። የተጠቀማቸው ቃላት የአዲስነትን ለዛ ስለተላበሱ ለጆሮአችን የሚያስገርም ቤተኛነትን ያስተጋባሉ። በእግዚአብሔር ላይ የሰቀዘ የማጉረምረም ጩኸት ለሚያሰሙ ሰዎቻችን ድምፁን ያሰማላቸዋል። ይሁንና፥ ከኢዮብ አስተሳሰብ በተቃራኒ በዚህ መጽሐፍ እግዚአብሔር ከችሎት ላይ አለመሆኑን ምዕራፍ 1 እና 2 ያረጋግጣሉ። የመጽሐፉ ጭብጥ «በመከራችን ሰዓት እግዚአብሔር ወዴት ነው? የሚል ዓይነት አይደለም። ቅድመ-ታሪኩ ያንን ገልጾታል። ጭብጡ እምነት፤ ይኸውም «በመከራው ጊዜ ኢዮብ ወዴት ነው?» የሚል ነው። ምላሽ የሚሰጠው እንዴት ነው? መጽሐፈ ኢዮብን ለመረዳት ከዚያ መነሣት አለብን።

«በልዕለ-ተፈጥሮአዊ አካል ግመን ግለት አንድ ሰው እዚህ ስኬታማ፥ የበለጸገና መልካም ሕይወት ከኖረ በኋላ የዚህ ዓለም መተኪያ በሆኑት ምርጥ ነገሮች ውስጥ መኖሩን ይቀጥላል ግለት አይደለም፤ ወይም ደግሞ እዚህ እጅግ የተጎሳቆለ ሕይወት ከኖረ በኋላ እዚያ ያጣቸውን ነገሮች ሁሉ ይካሳል ግለትም አይደለም፤ ይልቁን፥ በልዕለ-ተፈጥሮአዊ አካል ግመን ግለት ልዕለ-ተፈጥሮአዊው እዚህ አሁኑኑ ከሁሉም የላቀ እውነታ እንደሆነ ግመን ነው።» (ቲ. ኤስ.ኤሊዮት)

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ፦ ኢዮብ 1-2።

«ሰው ምንድር ነው ታከብረው ዘንድ፥ ልብህንስ ትጥልበት ዘንድ፥
ማለዳ ማለዳስ ትጎበኘው ዘንድ፥ ሁልጊዜስ ትፈታተነው ዘንድ?
የማትተወኝ እስክ መቼ ነው? ምራቄንስ እስክውጥ ድረስ
የማትለቀቀኝ እስክ መቼ ነው?» (ኢዮብ 7፡17-18)

ምዕራፍ 23

በአጽናፈ-ዓለሙ ውስጥ የምንጫወተው ሚና

አንዳንዶች እኛ ለአማልክት በክረምት ጊዜ ልጆች በቀላሉ እንደሚፈጁዋቸው ዝንቦች ነን ይላሉ። ሌሎች ደግሞ የሰማዩ አባታችን ካልፈቀደ የአንዲት ድንቢጥ ላባ እንኳ ወደ ምድር አይወድቅም ይላሉ።

– ቶርንተን ዋይልደር፥ "The Bridge of San Luis Rey"

ስለ ኢዮብ መጽሐፍ ለጻፈው ወዳጄ ሪቻርድ ይኸው ጥንታዊ ሰው ሁሉንም ከሚችል አምላክ ጋር ግብግብ የገጠመን ጀግና መስሎ ታይቶት ነበር። አንድ ጊዜ ሪቻርድ ስለ ኢዮብ ጀግንነት የሚሰጠውን ትንተና ከሰማሁ በኋላ፥ የውርርዱን ታሪክ አነሣሁበት። ቁጣ የፊቱን ላይ ደም ሥሮች ሲገማምድ አስተዋልሁ። «ለማለት የምችለው ነገር ቢኖር ኢዮብ እግዚአብሔርን ለማስደሰት ሲል አንድ የሲኦል ዋጋ እንደከፈለ ነው!» ሲል ጮክ ብሎ ተናገረ።

እኔም ራሴ መጀመሪያ እንዲህ ዓይነቱን ስሜት ለማስወገድ እቸገር ነበር። ሰማያዊ ውድድር በኢዮብ ሕይወት ውስጥ እንደ ዝርፍያና ግድያ፥ የእሳትና የነፋስ ማዕበል፥ ብሎም እንደ ቃል ስለተገለጸ፥ ከችግር መውጣት የሚቻልበት ቀላል መንገድ የለም። እግዚአብሔር አንድን ውድድር ለማሸነፍ እንዲህ ያለ ዋጋ መክፈል ያለበት እንዴት ነው? ሲ. ጂ. ጀንግ በኢዮብ ላይ በጻፈው ኃይለኛ መጽሐፍ እንዳለው፥ «አይጦችን ለማስደንገጥ የአንበሳን ዋጋ ይጠይቃልን?»

መጽሐፈ ኢዮብን ይበልጥ ባጠናሁ ጊዜ ግን የተጻፈውን ነገር የተሳሳተ ምስል እንደያዝሁ ተገነዘብሁ። የጨበጣ ውጊያ መኖሩ እውነት ቢሆንም፥ ውጊያው የተካሄደው በኢዮብና በእግዚአብሔር መካከል አልነበረም። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ለጊዜው ኢዮብን የወከለው ቢሆንም፥ ዋነኞቹ ተጋጣሚዎች ሰይጣንና እግዚአብሔር ነበሩ። የመጀመሪያና የመጨረሻ ምዕራፎች እንደሚገልጹት፥ ኢዮብ በማይታይ ዓለም ውስጥ የሚገኙ አካላት እየተመለከቱት መሆኑን ሳያውቅ ሰማያዊውን ግጥሚያ እየተወጣ ነበር።

የውርርድ አስገራሚ ትእይንት መጽሐፍ ቅዱስ ከመጋረጃ በስተጀርባ ስላለው ድራማ አጭር እይታ የሚሰጥባቸውን ሌሎች ጥቂት ክፍሎች አስታወሰኝ። ለምሳሌ፥ በጣም እንግዳ የሆነ ፉክክር የተገለጸበትን የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 12 ተመልከት፥ ፀሐይን የለበሰችና አሥራ ሁለት ከዋክብትን በአክሊልነት የደፋች እርጉዝ ሴት ከግዙፍነቱ የተነሣ የከዋክብትን ሲሶ በጅራቱ ስቦ ሊጥል የሚችለውን ልጅ ሊውጥ ፈልጎ ይጠባበቃል። ከዚያም ወደ ምድረ በዳ ትሸሻለች፤ ዘንዶው ሴቲቱን ሊያሰጥም ይታገላል፤ በሰማይም ታላቅ ጦርነት ይካሄዳል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ግብራሪያዎች አንደ ቁጥራቸው የተለያዩ አተረጓጎሞችን ለራእይ ምዕራፍ 2 ይሰጣሉ፤ ይሁንና፥ ሁሉም የሚስማሙበት አንድ አሳብ አለ፤ ይኸውም፥ በዚህ ክፍል የተጠቀሰው እንግዳ ምሳሌ ኢየሱስ በቤተልሔም በተወለደ ጊዜ በአጽናፈ-ዓለም ላይ የተከሰተውን የላቀ ረብሻ የሚያሳዩ መሆናቸውን ነው። ራእይ ምዕራፍ 12 ለተለመዱት የግርግም፥ የእረኞችና የተጨፈጨፉት ንጹሐን ትእይንቶች አዲስ ምሳሌዎችን የሚያክል ሌላው የገና ገጽታ እንደሆነ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። የገና «እውነተኛ» ታሪክ ምንድን ነው? የሉቃስ የመጋቢነት ጽሑፍ ወይስ የዮሐንስ ራእይ የጦርነት ታሪክ? በመሠረቱ የእይታ ደረጃቸው ይለያይ እንጂ ሁለቱም አንድ ታሪክ ናቸው። ሉቃስ ከምድራዊ እይታ አንጻር ሲገልጽልን፥ ራእይ ከማይታየው ዓለም ዝርዝር ጉዳዮችን ያቀርብልናል።

ከኢየሱስ ታሪኮች የመጠቀ እውቅናን በተጎናጸፉት ሦስት ምሳሌዎች ግለትም የጠፋው በግ፥ የጠፋው ሣንቲምና የጠፋው ልጅ ታሪኮች ሁለቱ ዓለማት በግልጽ ወደ አንድነት ይመጣሉ። የሦስቱም መልእክት አንድ ነው፤ ይኸውም አንድ ኃጢአተኛ ንስሐ በሚገባበት ጊዜ በሰማይ ታላቅ ደስታ እንደሚሆን ነው። ዛሬ የቢሊግርሃም የቴሌቪዥን ዝግጅት በቀጥታ ስለሚተላለፍ ማንም ሰው ንስሐ የሚገባውን ኃጢአተኛ ሊመለከት ይችላል። ወጣቷ ንስሐ ለሚገቡትና ለሚለወጡት ወደተዘጋጀው ሥራ ስታመራ ካሜራው ይከተላታል። ይሁንና፥ የኢየሱስ ታሪኮች ከዚህ እጅግ የበዙ ሰዎች እንዳሉ ያሳያሉ፤ ከዚያ የስታዲየም ትእይንት በስቲያ ከካሜራ ዓይኖች በተሸሸገ ስፍራ በማይታየው ዓለም ዕፁብ ድንቅ ደስታ ይሆናል።

ዛሬ በማይታየው ዓለም ማመን ዋነኛ የእምነት ክፍፍልን ይፈጥራል። እጅግ በርካታ ሰዎች ስለማይታየው ዓለም ምንም ሳያስቡ ከመኝታቸው ይነሣሉ፤ ቁርሳቸውን ይበላሉ፤ ወደ ሥራ ይሄዳሉ፤ ስልክ

ይደውላሉ፤ ልጆቻቸውን ይንከባከባሉ፤ ከዚያም ወደ መኝታቸው ይሄዳሉ። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው ግን የሰው ልጅ ታሪክ ከሰዎችና መንግሥታት መነሣትና መውደቅ የላቀ ነው። ይህ በአጽናፈ-ዓለም ውስጥ ተራ የሚመስለው ተግባር በማይታየው ዓለም ከተራነት የመጠቀ ውጤት ሊኖረው ይችላል፤ የአጭር ጊዜ የወንጌል አገልግሎት ተልእኮ ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ይጥለዋል (ሉቃስ 15)፤ የአንድ ሕፃን ልጅ መወለድ አጽናፈ-ዓለሙን ሁሉ ይረብሸዋል (ራእይ 12)። እንደ ራእይ 12 እና መጽሐፈ ኢዮብ በመሳሰሉት አንዳንድ ስፍራዎች ጨረፍታውን ከማየታችን በቀር፥ አብዛኛው የዚያ ከስተት ውጤት ከእኛ እይታ ተሰውሮ የሚቀር ነው።

በሚታየው ዓለም ውስጥ ተራ ሰው ሆኖ የኖረው ኢዮብ ሰማያዊ ውጤቶች የሚያስከትሉትን መከራ እንዲታገሥ ተጠርቷል። ይህንን ሰው የሚመራ ብርሃን አልነበረውም፤ የማይታየው ዓለም ስለ እርሱ እንደሚያስብ ወይም እንዳለ እንኳ የተረዳው ነገር አልነበረም። ዳሩ ግን ለቤተ ሙከራ ግልጋሎት እንደሚውል እንስሳ፥ ከሰብአዊነት እጅግ አንገብጋቢ ጉዳዮች ለአንዱ እልባት ለመስጠትና የአጽናፈ-ዓለሙን የታሪክ ቁራሽ ለመወሰን ተመርጦአል።

አንድ ሰው ማለትም በሚጢጢዋ ዓለም ውስጥ የሚኖር ሚጢጢ ነቁጥ በአጽናፈ-ዓለሙ ታሪክ ላይ ለውጥ ያመጣል ብሎ ማመኑ አደናጋሪ ነውን? ነገሩ ለኢዮብ ጓደኞች እንደዚያ ነበረ የመሰለው። ከኢዮብ አጽናኞች የመጨረሻው የነበረው ኤሊሁ የተናገረውን ቀጥሎ አንብብ።

«ኃጢአት ብትሠራ ምን ትጎዳዋለህ?

መተላለፍህስ ቢበዛ ምን ታደርገዋለህ?

ጻድቅስ ብትሆን ምን ትሰጠዋለህ?

ወይስ ከእጅህ ምንን ይቀበላል?

እንደ አንተ ያለውን ሰው ክፋትህ ይጎዳዋል።

ለሰውም ልጅ ጽድቅህ ይጠቅመዋል።»

የኤሊሁ ንግግር ሙሉ ለሙሉ የተሳሳተ መሆኑ ግልጽ ነው። የመጽሐፈ ኢዮብ የመክፈቻና መዝጊያ ምዕራፎች እንደሚገልጹት፥ የአንድ ሰው ምላሽ በእግዚአብሔር ላይ ከፍተኛ ለውጥ የሚያስከትል ሲሆን፥ የሰማይን ጉዳዮች ከአደጋ ላይ ሊጥል ይችል ነበር። (በኋላ ለሕዝቅኤል ባስተላለፈው መልእክት፥ እግዚአብሔር ኢዮብን ከሦስት ወዳጆቹ –ዳንኤልና ኖኅን ጨምሮ አንዱ እንደሆነ ገልጾአል።)

ከሌሎች ለየት ብሎ የቀረበው የኢዮብ ምሳሌ የምድር ላይ ሕይወት እንዴት በአጽናፈ-ዓለሙ ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድር ያሳያል። ጥናቴን በጀመርሁ ጊዜ የምዕራፍ አንድን «አሳሳቢ» ትእይንት ገለል ላደርገው ከጅዬ ነበር፤ ከዚያ በኋላ ግን ነገሩ ድራማ ይሁን ታሪክ የውርርዱ ታሪክ ለሁላችንም ታላቅ የተስፋ መልእክት እንደሚያስተላልፍ ልረዳ ችያለሁ። ለዚያውም ከኢዮብ ሕይወት የሚጨለፍ ኃይለኛ ዘላቂ ትምህርት። በመጨረሻው ውርርድ የአንድ ሰው እምነት ከፍተኛ ዋጋ እንዳለው አመልክቷል። መጽሐፈ ኢዮብ ለፈተና የምንሰጠው ምላሽ ለውጥ እንደሚያመጣ የሚያስረዳውን አሳብ ያጠናክራል። የሰው ልጅ ታሪክ፥ እንዲያውም የራሴ ግላዊ የእምነት ታሪክ በአጽናፈ-ዓለሙ ታሪክ ታላቅ ድራማ ውስጥ ተካቷል።

ፓስካል እንዳለው፥ እግዚአብሔር «የመነሻና ውጤትን» ከብር ሰጥቶናል። አንድ ሰው ትልቅ ለውጥ ስለማምጣቱ እንደ ኤሊሁ ልንጠራጠር እንችላለን። ዳሩ ግን መጽሐፍ ቅዱስ በሌሎች አማኞችም ሕይወት እንደ ውርርድ ዓይነት ነገር እንደተካሄደ ያሳያል። እኛ እግዚአብሔር ለማይታየው ዓለም ለማሳየት የሚጠቀምብን የኤግዝቢሽን ዕቃዎች ነን። ሐዋርያው ጳውሎስ በሮማውያን ዘመን ሕዝቡን ለማዝናናት ከአውሬዎች ጋር የሚጋጠመውን ሰው ታሪክ በማስታወስ በራሱ የሚከተለውን ብሏል፤ «ለዓለም፤ ለመላእክትም፥ ለሰዎችም መጫወቻ ሆነናልና።» በዚያው መልእክቱ ውስጥ የመደነቅ ቅላፄ ያረፈበትን፥ «በመላእክት ላይ እንደምንፈርድ አታውቁምን?» የሚል ቃል አክሏል።

እኛ የሰው ልጆች የምንኖረው ከብዙ የከዋክብት ከምችት ወጣ ብላ በምትገኘው እንደ ነቁጥ ባነሰች ምድር ላይ ነው። ይህ የከዋክብት ከምችት በሚታየው ዓለም ውስጥ ካሉት በሚሊዮን ሚሊዮን የሚቆጠሩ ከዋክብት አንደኛው ነው። አዲስ ኪዳን ግን እዚህ ምድር ላይ የሚፈጸመው ነገር የዚያን አጽናፈ-ዓለም የወደፊት ዕጣ ለመወሰን እንደሚረዳ ይናገራል። ጳውሎስ የሚከተለውን አሳብ በአጽንኦት አስቀምጦታል፤ «የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃልና።» በመቃተት ላይ ያለው «ፍጥረት» ነፃ ሊወጣ የሚችለው በሰው ልጆች መለወጥ ብቻ ነው።

ታላቅ ለውጥ

በክርስቲያን አመለካከት፥ ጠቅላላው የሰው ልጅ ታሪክ ከዘፍጥረት የመጀመሪያ ክፍልና በራእይ የመጨረሻ ክፍል መካከል የሆነ ስፍራ ላይ ይከሰታል። ይህም በተመሳሳይ ብሩሽ ተመሳሳይ ትእይንት የሚሠራ ክፍል ነው። ዔድን ገነት፥ ወንዝ፥ የእግዚአብሔር አንጸባራቂ

ክብርና የሕይወት ዛፍ በሁለቱም ስፍራዎች ተጠቅሰዋል። ታሪክ የሚጀምረውና የሚጨርሰው በአንድ ስፍራ ላይ ነው። በመካከሉ የሚገኘው ሁሉ የጠፋውን መልሶ ለማግኘት የተደረገ ጥረት ነው።*

ሰዎች ከዔድን ገነት ከወደቁ በኋላ ታሪክ ወደ አዲስ ምዕራፍ ተሸጋገረ። ከምን ተነሥቶ ይህንን የሚያህል የሚያስደንቅ አጽናፈ-ዓለም በማፍራት ነበር እግዚአብሔር ፍጥረትን በራሱ የሠራው። አዲሱ ተግባር ዳግም- ፈጠራ በመሆኑ፥ እግዚአብሔር ለዚሁ ሥራ የተጠቀመው መጀመሪያ ሥራውን ያበላሸውን የሰው ልጅ ነበር። የፍጥረት አሠራር ደረጃ በደረጃ ነበር፤ መጀመሪያ ከዋክብት፥ ከዚያ ሰማይና ባሕር፥ ዕፅዋትና እንስሳት፥ በመጨረሻም ወንድና ሴት ነበሩ። ዳግም-ፈጠራ ቅደም-ተከተሉን ይለውጠዋል፤ በወንድና ሴት ተጀምሮ ፍጥረታትን ሁሉ በማደስ ይጠናቀቃል።

የዳግም-ፈጠራ ተግባር በደካማ የሰው ልጆች የሚካሄድ መሆኑ በብዙ መንገዶች ከመጀመሪያው ፈጠራ «የከበደ» ነው። ሥራው እግዚአብሔርን የበለጠ ዋጋ እንዳስከፈለው ደግሞ ግልጽ ነው። ይኸውም የልጁ ሞት ነው። አሁንም እግዚአብሔር ዓለምን ከላይ ወደ ታች ሳይሆን ከታች ወደ ላይ ሊፈውስ ይሻል።

የኢዮብን መጽሐፍ በማጠናበት ጊዜ፥ የውርርድ መሠረታዊ አሳብ በፍጥረት ውስጥ የእግዚአብሔር የመጀመሪያው ጥያቄ በድጋሚ እንደቀረበ ተመለከትሁ፤ ይኸውም«የሰው ልጆች እኔን ለመከተል ይመርጣሉ ወይስ ከእኔ ለመራቅ?» የሚለው ነበር። ከእግዚአብሔር እይታ አንጻር፥ ከአዳም ጀምሮ በኢዮብና በምድር ላይ በኖሩት በእያንዳንዳቸው ወንዶችና ሴቶች በኩል የሚያልፈው የእግዚአብሔር አስኳል ጥያቄ ይኸው ነው። በመጽሐፈ ኢዮብ የቀረበው ውርርድ ጠቅላላውን የሰው ልጅ ሙከራ ወደ መለኮታዊ ጥያቄ ይጋብዛል።

ሰይጣን የሰው ልጆች ነፃ መሆናቸውን ክዶ ነበር። እኛ የመውደቅ ነጻነት እንዳለን አዳምና እርሱን ተከትሎ የመጣው ትውልድ ሁሉ አረጋግጧል።

---

* ጆን ግከኳሪ በዚህ ምንባብ ውስጥ ፍጻሜያችንን ከእግዚአብሔር መዋረድ አንጻር ይተነትናሉ፤ «የመጀመሪያው ኃጢአት የመጨረሻ ጥፋት የሚያስከትል ቢሆን፥ ከመጀመሪያው ጽድቅ ዶክትሪን ጋር ሊጋፈጥ ያሻል። በብሉይ ኪዳን ታሪክ ጽድቅ ከኃጢአት የላቀ ጅማሬ አለው።»

ይሁንና፥ የመነሣት ነጻነት፥ ያለምንም ምክንያት እግዚአብሔርን የማመን ነጻነት. . .? አንድ ሰው እግዚአብሔር እንደ ጠላት ሲገለጽለት ሊያምነው ይችላል? ወይስ እምነት የአካባቢና የሁኔታዎች የምርት ውጤት ይሆን? የመጽሐፈ ኢዮብ የመክፈቻ ምዕራፎች ሰይጣንን የመጀመሪያው ታላቅ የሥነ-ባሕርይ ጠቢብ አድርገው ያቀርቡታል፤ ኢዮብ እግዚአብሔርን እንዲወድ የሚያደርጉ ሽልማቶች ተሰጥተውታል። ሽልማቶቹን አንሡና የኢዮብ እምነት ሲፈራርስ ታያላችሁ ሲል አመክኒዮውን አቀረበ። እግዚአብሔር የሰይጣንን ንድፈ-አሳብ ለፈተና አቀረበ።

የኢዮብ መከራ የሰው ልጅ ነጻነት ወሳኝ ፈተና እንደሆነ ወደ መረዳቱ መጥቻለሁ። ይህም በአሁኑ ዘመናዊ ማኅበረሰብ ውስጥ ሳይቀር በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው። በዓለማችን አንድ ሰው ከውርስ የዘርን ንጥረ ነገር (DNA Programming) ከጂን ገንዳ ተፈጥሮአዊ ገጽታዎች፥ ከባሕላዊ ልማዶችና አካላዊ ካልሆኑት የታሪክ ኃይላት ውህደት እንደሚልቅ ለማመን ትልቅ እምነት ይጠይቃል። ይሁንና፥ በዚህች የሥነ ባሕርይ አሳዳጅ ዓለም እንኳ በተለየ መንገድ ለማመን እንሻለን። በየዕለቱ የምንወስዳቸው ሺህ ቀላልና ከባድ ምርጫዎቹ ዋጋ እንዳላቸው እናስባለን። መጽሐፈ ኢዮብ ግን የአንድ ሰው እምነት ትልቅ ለውጥ እንደሚያመጣ ይናገራል። የሰው ልጆች የሚጫወቱት ሚና አላቸው፤ ያንንም ሚና በተገቢው መንገድ በመጫወት ኢዮብ በጥርጣሬ ወይም በመከራ ለተከበቡ ሰዎች ሁሉ ምሳሌነቱን ያስተላልፋል።

ብዙውን ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር መቀያየም የምንጀምረው የኢዮብን በሚመስሉ ሁኔታዎች ነው። የልጅ ሞት፥ አሳዛኝ አደጋ፥ ወይም ከሥራ ገበታ መነሣት፥ ኢዮብ ወደጠየቃቸው ጥያቄዎች ሊመሩ ይችላሉ። ለምን እኔን? እግዚአብሔር ለምን ይተናከለኛል? እንዲህ የራቀ የሚመስለው ለምንድን ነው? እንደ መጽሐፈ ኢዮብ አንባቢዎች፥ ከመጋረጃው በስተጀርባ ውርርዱ ሲካሄድ ልንመለከት እንችላለን። በራሳችን የመከራ ሰዓት ግን እንዲህ ዓይነቱ እይታ አይኖረንም። አደጋ በሚደርስብን ጊዜ በማይታየው ዓለም ምን እየተፈጸመ እንዳለ ሳናውቅ በጥላ ውስጥ እንኖራለን። እናም ኢዮብ የኖረው ድራማ በእኛ ሕይወት ይደገማል። እግዚአብሔር አሁንም ምስክርነቱ ምን እንደሚወስኑ በማይታወቀው የሰው ልጆች ምላሽ ላይ እንዲደገፍ ይፈቅዳል።

በኢዮብ የውጊያ ሜዳ ውስጥ የህብት፥ የቤተሰብና የእምነት መታጣት ነበር። የእኛ ደግሞ ከዚህ የተለየ ሊሆን ይችላል፤ የሥራ አጥነት፥ የጋብቻ መፈራረስ፥ የፈቃደ-ሥጋ ችግር፥ ሰዎችን የማይስብ የሰውነት አቋም ሊፈትነን ይችላል። በእንዲህ ዓይነት ወቅቶች እንደ

በሽታ፥ የባንክ ሂሳብ፥ የመጥፎ ገጽ ዓይነት ውጫዊ ሁኔታዎች ከፍተኛ ትግል ሊመስሉ ይችላሉ። እግዚአብሔር እነዚያን ሁኔታዎች እንዲለውጥ ልንለምነው እንችላለን። *«ውብ ወይም መልከ መልካም ብሆን ኖሮ ሁሉም ነገር ይለወጥ ነበር። የበለጠ ገንዘብ ቢኖረኝ ኖሮ– ቢያንስ ሥራ አንኳ ቢኖረኝ–በቀላሉ እግዚአብሔርን አምን ነበር።»*

ዳሩ ግን በመጽሐፈ ኢዮብ እንደተመለከትነው፤ የሚበልጠው ጦርነት የሚካሄደው በውስጣችን ነው። እግዚአብሔርን እናምነዋለን? ከኢዮብ እንደምንማረው፥ እምነት እጅግ የሚፈለገው ከባድና የማይቻል በሚመስልበት ወቅት ነው። የእርሱ ትግል መጽሐፍ ቅዱስ በሌላ ስፍራ በግልጽ የሚያስቀምጠውን እውነት ያንጸባርቃል፤ ይኸውም እምነታችን ለእኛና ለፍጻሜያችን ብቻ ሳይሆን፥ ለራሱ ለእግዚአብሔርና እርሱ ለሚያስተዳድረው አጽናፈ–ዓለም ለውጥ የሚያመጣ የመሆኑ አስገራሚ እውነት ነው።

በአጭሩ፥ እግዚአብሔር አጽናፈ–ዓለሙን ወደ ቀደመው ደረጃው በሚመልሰው ታላቅ የለውጥ ተግባር የመካፈሉን ክብር ለተራ ሰዎች እንደሰጣቸው እንመለከታለን። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የጠቃቀስኋቸው ቅይጣቶችም ሆኑ እንደ ካንሰር፥ ሞት፥ የፈራረሱ ግንኙነቶች፥ ባጠቃላይም የጨካኝዋ ምድራችን ግድፈቶች ተጠርገው ይወገዳሉ። አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን ጥበብ ልንጠራጠርና የጊዜ ሰሌዳው እልህ አስጨራሽ ሊሆንብን ይችላል። (ደቀ መዛሙርቱም ኢየሱስ የማይታየውን መንፈሳዊ መንግሥት በመሻት ለአካላዊ መንግሥት ያቀረቡትን ጥያቄ ባገለለ ጊዜ ተቀይመውት ነበር)። ነገር ግን የነቢያቱ ግሩም የተስፋ ቃሎች አንድ ቀን እውን ይሆናሉ፤ ያንንም ከፍጻሜ ለማድረስ የተመረጥነው እኛ –እኔና አንተ ነን።

የዚህን ዓለም ሥቃይና ፍትሕ–አልባነት እንደ መጽሐፈ ኢዮብ ልብን የሚያተራምስ አድርጎ ያቀረበ የለም። የእርሱን ያህል ተነክቶ ከእግዚአብሔር ጋር ያሳለፈውን የቅይጣት ሕይወት የገለጸ ማንም የለም። እናም አሁንም የኢዮብን ማጉረምረምና የእግዚአብሔርን ኃይለኛ ምላሽ ልንከታተል ያሻል። ይህም ሆኖ መጽሐፈ ኢዮብ የሚነግረው የሰው የእይታ መነጽር ከሆነው ማጉረምረም ሳይሆን፥ ከእግዚአብሔር አመለካከት ነው። በቅደመ–ታሪኩ ውስጥ ውርርድ ፈክቶ የሚታየውን እውነት ያቀርባል። ይኸውም ኢዮብ እኔና አንተ በአጽናፈ–ዓለሙ ውስጥ ያለውን ክፋት ወደ በጎነት ለመለወጥ ተባብረን ልንታገል እንደምንችል ነው።

መጽሐፈ ኢዮብ «ለምን?» ለሚለው መጠይቅ አጥጋቢ ምላሽ አይሰጥም። ይልቁንም «ለምን ፍጻሜ?» የሚል ሌላ ጥያቄ ያነሣል።

ባጋጠመው አበሳ የተበሳጨው ሽማግሌው ኢዮብ በመከራዎቹ ሁሉ ለእግዚአብሔር በመታመኑ፥ እጅግ የተቃወመውን የዚህን ዓለም ሥቃይና ፍትሕ-አልበኛነት ለማስወገድ ረድቷል። ሁለት ልጆቿን ከቀበረች በኋላ እንኳ በጥላዎች ውስጥ ከእግዚአብሔር ፍቅር የተጠለለችው ሜግ. . . እነዚያን ከፋቶች ለመለወጥ እየረዳች ነው።

ለምን ይዘገያል? እግዚአብሔር ክፋትና ሥቃይ በዚህ ምድር ላይ በግልጽ እንዲታያትና አሸንፎ እንዲወጣ የሚፈቅደው ለምንድን ነው? እርሱ በቅጽበተ ዓይን ሊሠራ የሚችለውን ነገር እኛ እየተጓተትን እንድናከናውነው የሚያደርገው ለምንድን ነው?

ወደ ኋላ የሚያፈገፍገው ለእኛው ጥቅም ነው። ዳግም-ፈጠራ እኛን ያካትታል፤ እንዲያውም እኛ የዕቅዱ አስኳል ነን። ከሰብአዊ ታሪክ በስተጀርባ ያለው ውርርድ እኛን እንጂ እግዚአብሔርን ለማሳደግ የሚደረግ ጥረት አይደለም። መኖራችን ራሱ በአጽናፈ-ዓለሙ ውስጥ ለሚገኙ ኃይላት የተሐድሶ ሥራ እየተካሄደ እንዳለ ያስረዳል። እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ሰው የሚፈጽመው እያንዳንዱ የእምነት ተግባር እንደ ደወል የሚያቃጭል ሲሆን፥ እንደ ኢዮብ ዓይነቱ በአጽናፈ-ዓለሙ ሁሉ ውስጥ ያስተጋባል።

> «በሙሉ ፍጹማዊነታችንና ታማኝነታችን ልንዋጅ የሚገባው የተበላሸ ነገር በአጽናፈ-ዓለሙ ውስጥ እንዳለ ሁሉ፥ የአሁኑ ዘመን ሕይወታችን እውነተኛ ውጊያን ይመስላል።»
>
> *-ዊልያም ጀምስ፥ "The Will to Believe"*

> «ይህ ሁሉም ተፎካካሪዎች በመጨረሻው እርባና ቢስ ሽልማት እንደሚቀበሉት የሕፃናት ጨዋታ ዓይነት እንደሆነ ከማሰብ፥ በዕለታዊ የዘላለም ሽብር ውስጥ ብረግመድ ይሻለኛል።»
>
> *- ቲ. ኤሰ. ኤልዮት*

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፡-ኢዮብ 35፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 4፥ 6፤ ሮሜ 8።

«በጎነትን በተጠባበቅሁ ጊዜ ክፉ ነገር መጣችብኝ፤
ብርሃንን በትዕግሥት ጠበቅሁ፥ ጨለማም መጣ።
አንጀቴ ፈላች፥ አላረፈችም፤
የመከራም ዘመን መጣችብኝ።»

– ኢዮብ 30፡26–27

ምዕራፍ 24

እግዚአብሔር ፍትሕ–አልባ ነውን?

ኤም. እስኮት ፔክ፥ «ያልተሄደበት መንገድ» *(The Road Less Travelled)* በሚል ርእስ የጻፉት መጽሐፍ የሚጀምረው «ሕይወት አስቸጋሪ ነች» በሚል ባለ ሦስት ቃላት ፈዛዛ ዓረፍተ ነገር ነው። በአንድ ዓረፍተ ነገር አሳጥረን ብንጽፈው መጽሐፉ ኢዮብም ተመሳሳይ አሳብ መግለጹ አይቀርም፤ «ሕይወት ፍትሐዊ አይደለችም!» የሚል ጩኸት ከሁሉም ገጾች ያስተጋባል።

ፍትሕ–አልባነት ለእኛ ከሺዎች ዓመታት በፊት ለኢዮብ ከነበረው ያነሰ ክብደት የለውም። «ያምላክ ያለህ» የሚለውን የተለመደ አባባል ተመልከት። ሰዎች ይህንን ቃል የሚጠቀሙት ከፍተኛ ኃዘን ሲገጥማቸው ብቻ ሳይሆን፥ መኪናቸው አልነሣ ሲል፥ የሚደግፉት የስፖርት ቡድን ሲሸነፍ፥ በመዝናኛ ጊዜያቸው ላይ ዝናብ ሲመጣም ጭምር ነው። ይኸው ሐረግ ሕይወት ፍትሐዊ መሆን እንዳለባትና እግዚአብሔርም በተሻለ ሁኔታ ዓለሙን መምራት እንዳለበት የሚናገር ተፈጥሮአዊ ብያኔ ነው።

አሁን ያለችው ዓለም የሚገባት ተቃራኒ ነች። በመጽሐፈ ኢዮብ ውስጥ በእነዚህ ሁለቱ መካከል የሚገኘው የማያቋርጥ ውጥረት በግልጽ ይታያል። ለሦስት ረዣዥም ዙሮች ኢዮብና ጓደኞቹ በቃላት ቡጢ ሲጨፋጨፉ ቆዩ። ሁሉም በመሠረታዊ አሳብ ላይ ይስማማሉ፤

ይኸውም እግዚአብሔር ሰናይ ምግባር የሚከውኑትን ሊሸልምና ክፉ የሚሠሩትን ሊቀጣ እንደሚገባ ነው።

ይህ ከሆነ፥ መልካምነቱ የተመሰከረለት ኢዮብ በይምሰላዊ ቅጣት የሚሠቃየው ለምንድን ነው? በእግዚአብሔር ፍትሐዊነት ላይ ልበ-ሙሉነት የሚሰማቸው የኢዮብ ጓደኞች የዓለምን የአሁን ገጽታ ትክክለኛነት ለማጽደቅ ተሟገቱ። «በተራ ግንዛቤ እንኳ ብትጠቀም እግዚአብሔር ያለ ምክንያት አይጎዳህም። አንድ ስውር ኃጢአት ሠርተሃል ማለት ነው» ሲሉ ለኢዮብ ነገሩት። ነገር ግን ለዚህ ዓይነቱ ቅጣት የሚዳርግ ምንም በደል እንዳልፈጸመ የሚያውቀው ኢዮብ በአሳባቸው ሊስማማ አልቻለም። እናም ንጹሕ መሆኑን ይገልጽላቸዋል።

ቀስ በቀስ ግን ሥቃዩ የኢዮብን የተወደደ እምነት አዳከመው። ኢዮብ እግዚአብሔር እንዴት ከእርሱ ጎን ሊሆን እንደሚችል ያስባል። ኢዮብ ከዐመድ ዳር ተቀምጦ ነበር። በእግዚአብሔር «ስለተከዳ» ስብራትና ጭንቀት ወረረው። «ወደ እኔ ተመልከቱ፥ ተደነቁም፥ እጃችሁንም በአፋችሁ ላይ አኑሩ።» ሲል ይጮኻል።

ከውስጡ የእምነት ቀውስ ተጠነሰሰ። እግዚአብሔር ፍትሕ-አልባ ነውን? እንዲህ ዓይነቱ አሳብ ኢዮብ የሚያምነውን ነገር ሁሉ በጥያቄ ምልክት ውስጥ ይከተዋል? ነገር ግን የተፈጸመውን ከስተት ከዚህ በተለየ መንገድ ሊያብራራ የሚችለው እንዴት ነው? ሌሎች ምሳሌዎችን ለማግኘት ዙሪያ ገባውን ሲያጤን፥ አንዳንድ ጊዜ ክፉ ሰዎች ለስኬት ሲበቁ አስተዋለ። እርሱ ለማመን እንደሚፈልገው ቅጣት አይደርስባቸውም። ይልቁንም፥ አንዳንድ መንፈሳውያን ሰዎች ሲሠቃዩ ያያል። ሌሎች ብዙ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ምንም ነገር ሳያስቡ ፍሬያማና የደስታ እንክብሎች የበረከቱበትን ሕይወት ይኖራሉ። ለኢዮብ ያገኛቸው መረጃዎች የሚጣጣሙ አልሆኑም። «እኔ ባሰብሁ ቁጥር እጨነቃለሁ፤ ፃርም ሥጋዬን ይይዛል።»

መጽሐፈ ኢዮብ ዘመናዊ የሚመስለው ለእኛም የምናገኛቸው መረጃዎች ስለማይገጥሙልን ነው። ኢዮብ ስለ ሕይወት ፍትሕ-አልባነት የሚያሰማው ሮሮ ለእኛው የሥቃይ ክፍለ ዘመን በተለየ መልኩ የሚስማማ ይመስላል። እስኪ የአሁኑን ዘመን ምሳሌዎች ከኢዮብ ሙግት ውስጥ እንጨምራቸው፤ «ንጹሐን» ሳሉ በሦስተኛው ዓለም በረሃብ የሚያልቁ ሕፃናት በደቡብ አፍሪካ የታሰሩ ታማኝ መጋቢዎች፥ በአገልግሎታቸው የሚሞቱ ክርስቲያን መሪዎች፥ የእግዚአብሔርን ሕግጋት እየተላለፉ በሚፈጽሙዋቸው ጸያፍ ተግባራት

የከበሩ ማፍያዎችና ምግባረ ብልሹ የመዝናኛ ዝግጅት አቅራቢዎች፥ ስለ እግዚአብሔርም ምንም ሳያስቡ በደስታ የሚኖሩ የምዕራብ አውሮፓ ቱጃሮች ሊጠቀሱ ይችላሉ። ኢዮብ ለዚህች ዓለም ፍትሕ-አልባነት ያነሣው ጥያቄ እያንጸባረቀ እንጂ እየደበዘዘ አልሄደም። አሁንም ቢሆን የፍቅርና የኃይል አምላክ በምድር ላይ የተወሰኑ ደንቦችን እንዲከተል እንሻለን። ታዲያ ለምን አያደርገውም?

ፍትሕ-አልበኛነትን መቀበል

በአንድ ወቀት የትኛውም ሰብአዊ ፍጡር ኢዮብን በሽብር ከናጠው ምሥጢራዊ ጉዳይ ጋር ይላተማል። እናም የእግዚአብሔርን ፍትሐዊነት ይጠራጠራል።

ለኢዮብ ሚስት አንድ አሳብ የተገለጻላት ይመስላል፤ «እግዚአብሔርን ስደብና ሙት!» ስትል መክራው ነበር። በሕይወቱ እጅግ ብዙ ነገር የተገላቢጦሽ ሲሆንበት ለምን በአፍቃሪ አምላክ ማመኑን ይቀጥል? በዚህ የኢዮብ ዓይነት ክፍለ ዘመን ከቀድሞው በላይ እጅግ ብዙ ሰዎች ከዚህች ሴት ጋር ወደ መስማማቱ አዘንብለዋል። እንደ ጆርዚ ኮሲንክሲ እና ኤሊ ዊስል የመሳሰሉ አይሁዳውያን ጸሐፍት በእግዚአብሔር ላይ ጠንካራ እምነት መሥርተው ቢጀምሩም፥ እምነታቸው እስራኤላውያን በተጨፈጨፉበት ጥፋት እቶን ተንተክትኮ ሲበን ተመልክተዋል። ከታሪክ ከፍተኛ ፍትሕ-አልበኛነት ጋር ፊት ለፊት በመላተማቸው እግዚአብሔር ሊኖር እንደማይችል ደምድመዋል። አሁንም የሰው ተፈጥሮ ራሱን ደግሟል። ኮሲንስኪና ዊስል የብስጭትን ድምፅት ሊያስወግዱ አይችሉም፤ እነርሱም የመከዳት ስሜት እንደተጫናቸው ሁሉ። ዋነኛው የፍትሐዊነት ስሜታችን ከየት እንደሚመነጭ የሚያመለክተውን መሠረታዊ ጉዳይ ያገላሉ። ዓለም ፍትሐዊ እንድትሆን የምንጠብቀውስ ለምንድን ነው?

በተመሳሳይ ደረጃ የዓለምን ፍትሕ-አልበኛነት የተገነዘቡ ሌሎች ሰዎች ሀልፈተ-እግዚአብሔርን እስከ መካድ ድረስ አይሄዱም። ከዚህ ይልቅ፥ «ምናልባትም እግዚአብሔር በሕይወት ፍትሕ-አልባነት ቢስማማም ምንም ሊያደርግ አይችልም ይሆናል» ሲሉ አማራጭ አሳብ ያቀርባሉ። "*When Bad Things Happen to Good People*" ወይም «ክፉ ነገሮች በመልካም ሰዎች ላይ ሲደርሱ» በሚለው ተወዳጅ መጽሐፋቸው ውስጥ ራባይ ሃሮልድ ኩሽንር ይህንኑ አማራጭ ይከተላሉ። ልጃቸው በበሽታ ተጠቅቶ ሲሞት ከተመለከቱ በኋላ ኩሽንር፥ «እግዚአብሔርም እንኳ ትርምስን ለመከላከል እንደሚቸገር»

እና እግዚአብሔር «የፍትሕ እንጂ የኃይል አምላክ እንዳልሆነ» በመግለጽ ደምድመዋል።

እንደ ራባይ ኩሽንር አገላለጽ፥ እግዚአብሔር እንደማንኛውም ሰው በዚህ ዓለም ፍትሕ–አልበኝነት ይበሳጫል፤ ይሁንና፥ የዓለምን ፍትሕ–አልበኝነት ለመለወጥ የሚያስችል ኃይል የለውም። ኩሽንር ደካማ ቢሆንም እንኳ ለሰው ልጆች ስለሚራራው አምላክ ባቀረቡት ገለጻ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች መጽናናትን አግኝተዋል። ይሁንና፥ እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ራስን የመከላከል እርምጃ የሚያሳዩትን የመጽሐፈ ኢዮብ የመጨረሻ አምስት ምዕራፎች ምን እንደሚያደርጓቸው አስባለሁ። የእነዚህን ምዕራፎች ያህል የእግዚአብሔርን ኃይል በሚያስደንቅ መልኩ የሚያቀርብ ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አይገኝም። እግዚአብሔር ኃያል ካልሆነ፥ ኃይሉ ከጥያቄ ምልክት ውስጥ በገባ ጊዜ ተግባራዊ ለማድረግ እጅግ የሚከብደውን ሁኔታ ለምን መረጠ? (በኩሽንር ስለተገለጸው አምላክ ኤሊ ዊስል ሲናገር፥ «አምላክ የተባለው እርሱ ከሆነ፥ ለምን ሥልጣኑን በገዛ ፈቃዱ ለቅቆ የተሻለ ኃይል ያለው አምላክ አይተካውም?» ብሏል)።

ሦስተኛው ቡድን የሚያስደንቅ ፍትሐዊነት በአጽናፈ–ዓለሙ ውስጥ የሚንሰራፋበትን የወደፊት ዘመን በማገናዘብ፥ የፍትሕ–አልበኝነትን ችግር ያልፈዋል። ለዚህ ቡድን፥ ፍትሕ–አልበኝነት ጊዜያዊ ነገር ነው። ለዚህ እምነት የሒሳብ ቀምር የሚጠቀመው የሒንዱ ካርማ፥ አንዲት ነፍስ ከፍጹም ፍትሕ ለመድረስ 6,800,000 ዳግም ውልደቶችን ማለፍ ሊኖርባት እንደሚችል ያስረዳል። ከእነዚህ ሁሉ ውልደቶች በኋላ፥ ሰውዬው የሚገባውን ሥቃይና ስኬት ያገኛል።

አራተኛው አማራጭ ችግሩን በመካድ የዓለምን ፍትሐዊነት ማወጁ ነው። የኢዮብን ጓደኞች ድምፅ በማስተጋባት፥ እነዚህ ወገኖች ዓለም በተወሰኑላት መደበኛ ሕግጋት እንደምትመራ ይገልጻሉ። ይኸውም ክፉ አድራጊዎች እንደሚወድቁና መልካሞቹ ግን ለስኬት እንደሚበቁ ነው። በኢንዲያና የእምነት –ፈውስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይኸው አመለካከት አጋጥሞኛል። ሃይማኖታዊ ቴሌቪዥኖችን በምከፍትበት ጊዜ ሁሉ፥ አንዳንድ ወንጌላውያን በእውነተኛ እምነት የሚጠይቅ ሰው ሁሉ የተሟላ ጤንነትና የገንዘብ ብልጽግና እንደሚያገኝ ሲናገሩ እሰማለሁ።

እንዲህ ዓይነቶቹ አጓጊ የተስፋ ቃሎች ግልጽ ተቀባይነት እንዳላቸው ይታወቃል፤ ይሁንና፥ እውነታዎችን የማሸነፍ ብቃት የላቸውም። ከእናታቸው ማኅፀን ውስጥ ሳሉ በኤድስ በሽታ የተያዙ

ሕፃናት፥ ወይም "*Foxe's Book of Martyrs*" በተባለው መጽሐፍ ውስጥ የተዘረዘሩት የስደት ገፈት ቀማሾች ሁሉ ሕይወት ፍትሐዊ እንደሆነች ከሚያስረዳው ዶክትሪን ጋር የሚስማሙት እንዴት ነው?* ሕይወት ሙሉ ለሙሉ ፍትሐዊ ነች ብሎ ለመሟገት ከፍተኛ እምነትን ይጠይቃል። ብዙውን ጊዜ ክርስቲያኖች ለሕይወት ፍትሕ-አልባነት ምላሽ የሚሰጡት በቀጥታ በመካድ ሳይሆን በማዳከም ነው።

ይህንኑ ዶክትሪን ብቀበል ለሜግ ውድሳን፥ «ተግተሽ ብትጸልዪ ኖሮ ልጅሽ አትሞትም ነበር» ከማለት በቀር የምለው አይኖረኝም ነበር። ይህን ግን ለማለት አልችልም ነበር፤ ይህን ማለቱ፥ «እዚአብሔር ፔጊን የወሰደው ከጥፋትሽ የተነሣ ነው» ከማለት አይለይም። ሁለቱም አመለካከቶች በመጽሐፈ ኢዮብ ውስጥ ተመልክተዋል። በመጨረሻው ግን እግዚአብሔር ሁለቱንም አመለካከቶች ፉርሽ አድርጓቸዋል።

እንደ ኢዮብ ጓደኞች፥ ከመከራ በስተጀርባ ይኖራል የሚሉትን የተሰወረ ምክንያት ይፈልጋሉ፤

«እግዚአብሔር አንድ ነገር ሊያስተምህር እየሞከረ ነው። በእምነት በእርሱ ላይ የመደገፍ ዕድል ስላገኘህ መደሰት እንጂ የመራራነት ስሜት ማሳየት የለብህም።»

«አሁን ያሉህን በረከቶች አስብ-ቢያንስ በሕይወት አለህ። ይህን ያህል ደካማ አማኝ ነህ እንዴ?»

«አዳዲስ የእምነት ጡንቻዎችን የምትለማመድበት የሥልጠና ደንብ ውስጥ ነው ያለኸው። አትጨነቅ፤ እግዚአብሔር ከጽናትህ በላይ አይፈትንህም።»

---

* በጥንቱ ክርስቲያኖች መካከል የነበረ አንድ የአዋልድ መጽሐፍ በሐዋርያው ጳውሎስ ምስክርነት ስለተለወጠች ተክላ የተባለች ሴት የሚያወጋው ታሪክ ነበረው። የዚህች ሴት እምነት ከማንኛውም ጥቃት ይከላከልላት ነበር፤ የጹር አራዊት ሊበሉዋት ካለመድፈራቸውም በላይ፥ ወንዶች ሊደፍሯት አስበው ሳይሆንላቸው ይቀራል። የሚያሠቃዩዋት ሰዎች ሊያቃጥሉዋት ሲሞክሩ፥ የዝናብና የበረዶ ደመና ወርዶ እሳቱን ያጠፋዋል። ይኸውም መጽሐፍ በስፋት ይሰራጭ ነበር። ይሁንና፥ የተክላ ታሪክ የጓላ ጓላ ለምን የአዋልድ መጻሕፍት ተቀባይነት እንዳጣ ለመረዳት እንደ "Foxe's Book of Martyrs" የሚሉትን ዓይነት ሌሎች የቤተ ክርስቲያን ታሪኮች ማንበቡ ጠቃሚ ነው።

«ያን ያህል አምርረህ አታጉረምርም። ይህን ዕድል ለማያምኑ ሰዎች ታማኝነትህን ለማሳየት ትጠቀምበታለህ።»

«ሁልጊዜም ከአንተ በከፋ ሁኔታ ላይ ላይ የሚገኙ ሰዎች አሉ። እናም ካለህበት ሁኔታ ባሻገር ለእግዚአብሔር ምስጋና አቅርብ።»

የኢዮብ ጓደኞች እንዲህ ዓይነቱን የጥበብ ቃል አቅርበውለታል። በእያንዳንዱ አባባል ውስጥም መጠነኛ እውነት ይስተዋላል። ይሁንና፥ በሥቃይ ውስጥ የሚገኘውን ሰው ጥያቄዎች ለመመለስ እንዲህ ዓይነቱ «ጠቃሚ ምክር» የሚያበረክተው አስተዋጽኦ እንደሌለ መጽሐፈ ኢዮብ በግልጽ ያሳያል። ይህ በተሳሳተ ጊዜ የተቀመመና የተሰራጨ መድኃኒት ዓይነት ነበር።

በመጨረሻም፥ የዓለምን ፍትሕ-አልባነት ለማብራራት አንድ ተጨማሪ መንገድ ያቀርባል። አማራጮችን ሁሉ ከሰማ በኋላ፥ ኢዮብ የመጽሐፉን አሳብ በአንድ ዓረፍተ ነገር ወዳስቀመጥንበት ማጠቃለያ ይመለሳል፤ ይህም፥ ሕይወት ፍትሐዊ አይደለችም የሚለው ነው። ይህ አሳብ ወደ ኢዮብ አእምሮ የሚመጣው እንደ ሕይወት ፍልስፍና ሳይሆን እርሱ ከሚቆጣጠረው በላቀ ሁኔታ ነበር። ለዚህም ነው በሥቃይ ውስጥ የሚያልፈውን ሰው የሚጎዳው «ለምን እኔን?» ስንል እንጠይቃለን። «ምን አጠፋሁ?»

የዘመኑ ኢዮብ

ይህን መጽሐፍ በማዘጋጅበት ጊዜ እግዚአብሔር እንደካዳቸው ከሚያስቡ ሰዎች ጋር በመደበኛነት መገናኘቱን ተያያዝሁ። የቅይማትንና የጥርጣሬን ገጽታና አካላዊ ቋንቋ በገዛ ዓይኖቼ ለማየት ፈለግሁ። ስለ መጽሐፈ ኢዮብ የምጽፍበት ጊዜ ሲደርስ ሕይወቱ እንደ ኢዮብ የሚመስለውን አንድ ሰው ለማነጋገር ወሰንሁ፥ ዳግላስ ብለን እንጥራው።

ለእኔ ዳግላስ የኢዮብን በሚመስል ሁኔታ «ጻድቅ» ነው። ፍጹም ባይሆንም የታማኝነት ሞዴል ነው። ከዓመታት የሥነ-ባሕርይ (ሳይኮቴራፒ) ትምህርት በኋላ ከፍተኛ ጥቅም በሚያስገኝ ሥራ ላይ ተሰማራ። በኋላ ግን የከተማ ውስጥ ድሆችን የሚረዳበት አገልግሎት ለመጀመር ሲል ይህንኑ ሥራ ትቶ ወጣ። የዳግላስ መከራ የጀመረው ከጥቂት ዓመታት በፊት ከባለቤቱ ጡት ውስጥ ጠጣር ነገር በተገኘ ጊዜ ነበር። የቀዶ ሕክምና ባለሙያዎች ያንን ጡት ቢቆርጡም፥ ከሁለት ዓመታት በኋላ ከሳንባዋ ውስጥ ካንሰር እንደተሰራጨ ተገንዘቡ። ባለቤቱ አድካሚ በሆነው «የኬሚዮቴራፒ» ሕክምና እየተሠቃየች ሳለ፥ ዳግላስ በርካታ ቤተሰባዊ ኃላፊነቶችን ሲወጣ

ሰነበተ። አንዳንድ ጊዜ ምንም ምግብ አትመገብም። ጸጉሯ ተሞሸለቀ። ሁልጊዜም ድካም፥ ፍርሃትና ጭንቀት ያሠቃያታል።

በዚህ ሁሉ አጣብቂኝ ውስጥ አንድ ምሽት ዳግላስ፥ ባለቤቱና የአሥራ ሁለት ዓመት ልጃቸው በከተማ ውስጥ በመኪናቸው እየሄዱ ሳለ፥ አንድ የሰከረ አሽከርካሪ ከመስመር ወጥቶ ከመኪናቸው ጋር ተላተመ። የዳግላስ ሚስት ደነገጠች እንጂ አልተጎዳችም። የልጃቸው ፊት ግን በመኪናው መስተዋት ተቆረጠ። እጁም ተሰበረ። ዳግላስ ራሱ ከራሱ ላይ ከፍተኛ ግጭት ደረሰበት።

ከአደጋው በኋላ፥ ዳግላስ በራስ ምታት ይሠቃይ ጀመር። ቀኑን ሙሉ ለመሥራት ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደረሰ። አንዳንድ ጊዜም ዝንጉነት ያጠቃው ጀመር። ከዚህ የሚከፋው ደግሞ አደጋው ከእይታ ብቃቱ ላይ ዘላቂ ችግር ማስከተሉ ነው። አንድ ዓይኑ ቀጥ ብሎ ለመመልከት ሳይችል እንዲሁ ይባዝናል። አንዱ ነገር ሁለት ሆኖ ስለሚታየው፥ ያለረዳት ደረጃ መውረድ አይችልም። ዳግላስ ከችግሮቹ ሁሉ ጋር ተቻችሎ ለመኖር ቢጥርም አንደኛው ግን አማረረው፤ ይኸውም በአንድ ጊዜ ከአንድ ወይም ሁለት ገጽ በላይ ለማንበብ አለመቻሉ ነው። በዘመኑ ሁሉ ከፍተኛ የመጻሕፍት ፍቅር ነበረው። አሁን የዓይን ችግሩ የተወሰኑትን መጻሕፍት በዝግታ እንዲያነብ አስገደደው።

ዳግላስን ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ስደውልለት በቁርስ ላይ እንድንነጋገር አሳብ አቀረበ። የቀጠሮው ሰዓት ሲደርስ፥ ራሴን ለከባዱ የጠዋት ንግግር አዘጋጀሁ። እስከዚህ ጊዜ ድረስ አንድ ደርዘን የሚሆኑትን ሰዎች አነጋግሬአለሁ። ከእግዚአብሔር ጋር የመጣላት መብት ያለው ሰው ቢኖር ያ ሰው ዳግላስ መሆን አለበት። በዚያው ሳምንት ባለቤቱ ከሆስፒታል የአሳዛኝ ውጤት ዘገባ ሰምታ ነበር፤ ይኸውም ከሳንባዋ ውስጥ ሌላ ችግር እንደሚገኝ ነበር።

ቁርስ እየቀረበ ሳለ በሕይወታችን ጉዳዮች ተጠመድን። ዳግላስ ዝም ብሎ በጥንቃቄ ይመገብ ጀመር። ለማቃለል ቢረዳውም፥ በእጁ የያዘውን ወደ አፉ ለማድረስ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልገው ነበር። የሚቅበዘበዘው ዓይኑ የሚፈጥረውን ትርምስ ቸል ለማለት እየሞከርሁ፥ በሚናገርበት ጊዜ ፊት ለፊት ላየው ጣርሁ። በመጨረሻም፥ ቁርሳችንን ጨርሰን ሠራተኛዋ ተጨማሪ ቡና እንድታመጣልን ከነገራት በኋላ፥ ከእግዚአብሔር ጋር ስለመቀያየም እያዘጋጀሁ ያለሁትን መጽሐፍ ገለጽሁለት። «ስለ ራስህ ቅይማት ልትነግረኝ ትችላለህ? እንደ አንተ በመከራ ውስጥ እያለፈ ያለውን ሌላ ሰው የሚረዳ ምን የተማርኸው ነገር አለ?» ስል ጠየቅሁት።

ዳግላስ ለረዥም ጊዜ ዝም አለ። ሽበታም ጺሙን እየነካካ በቀኝ ትከሻዬ አሻግሮ ይመለከት ጀመር። አእምሮውን እያረጋጋው ይሆናል በሚል አሳብ ለአፍታ ጠበቅሁት። በመጨረሻም «እውነቱን ለመናገር፥ ፊሊፕ፥ ምንም ዓይነት ከእግዚአብሔር ጋር የመቀያየም ስሜት አልነበረኝም» ሲል ተናገረ።

በተናገረው አሳብ ተደነቅሁ። ከጠንካራ ታማኝነቱ የተነሣ በሃይማኖታዊ ቴሌቪዥኖች ላይ የሚቀርቡትን «ጠባሳዎችህን ወደ ከዋክብት ለውጥ» ዓይነት ምስክርነቶች አልተቀበለም ነበር። ማብራሪያ እንዲሰጠኝ ጠየቅሁት።

«ምክንያቱ ይኼ ነው። መጀመሪያ በባለቤቴ ሕመም፥ ከዚያም በአደጋው አማካኝነት እግዚአብሔርን ከሕይወት ጋር ማምታታት እንደሌለብኝ ተምሬአለሁ። እኔ የሥቃይ ስሜቴን የምደብቅ ሰው አይደለሁም። እንደ ማንኛውም ሰው በደረሰብኝ ነገር አዝኛለሁ። የሕይወቴን ፍትሕ-አልበኝነት ለመርገምና ኃዘኔን ሁሉ ለመግለጽ ነጻነት ይሰማኛል። ነገር ግን እግዚአብሔርም በዚያ አደጋ ተመሳሳይ ስሜት የሚሰማው ይመስለኛል፤ ያዝናል፤ ይቆጣል። ለሆነው ነገር እርሱን አልወቅሰውም።»

ዳግላስ ቀጠለ፤ «በዚህ ዓለም ካለው ቁሳዊ እውነታ ባሻገር መንፈሳዊውን እውነታ ማየትን ተምሬአለሁ። ብዙዎቻችን እግዚአብሔር ፍትሐዊ ስለሆነ ሕይወት ፍትሐዊ ልትሆን ይገባል ወደሚለው አሳብ እናዘነብላለን። ነገር ግን እግዚአብሔር ሕይወት አይደለም። እግዚአብሔርን ከቁሳዊ የሕይወት እውነታ ጋር ባደነጋገረው (ለምሳሌ የማያቋርጥ ጥሩ ጤንነት በመጠባበቅ)፥ ራሴን ለከፋ ቅይማት አዘጋጅቻለሁ ማለት ነው።

«የእግዚአብሔር መኖርም ሆነ ለእኔ ያለው ፍቅር በጥሩ ጤንነቴ ላይ አይደገፍም። እውነቱን ለመናገር፥ በችግሬ ውስጥ ከበፊቱ የተሻለ ከእግዚአብሔር ጋር ያለኝን ግንኙነት የማጠናክርበትን ጊዜ አግኝቻለሁ።»*

---

* የዳግላስ ምላሽ የዶክተር ፖል ብራንድን ቃል ያስታውሰኛል። «በመከራችን ጊዜ እግዚአብሔር ወዴት ነው?» ተብለው ሲጠየቁ፥ «እርሱ በአንተ ውስጥ ነው፤ እርሱም ጉዳቱን የሚያመጣው ሳይሆን ጉዳቱ የሚደርስበት ነው» ብለው ነበር።

በዚያ ትዕይንት ውስጥ የጠለቀ ቅኔ ነበር። ከእግዚአብሔር ጋር የተቀያየሙትን ሰዎች በማነጋግርባቸው ወቅት እምነታቸው ከድቶአቸው አገኘ ነበር። ዳግላስን እንደ ዘመኑ ኢዮብ የመረጥሁ ሲሆን፥ ከእርሱ የጠበቅሁት ነገር ቢኖር የመረረ የተቃውሞ አሳብ ነበር። ይሁንና፥ ከዚህ ሰው ሕይወት ያልጠበቅሁትን ከፍተኛ የእምነት ትምህርት አገኘሁ።

ዳግላስ፥ «ከሕይወት ሁኔታዎች ጋር በማይገጥም መልኩ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ማድረግን ብንለማመድ፥ ቁሳዊ እውነታ በሚፈራርስበት ጊዜ የምንጠላጠልበት ስፍራ እናገኛለን።» ብሏል። «ከሕይወት ኢ-ፍትሐዊነት ባሻገር በእግዚአብሔር መታመንን እንማራለን። ይኼ እውነታ የመጽሐፈ ኢዮብ ዐቢይ ጭብጥ አይደለምን?»

ምንም እንኳ ዳግላስ «ቁሳዊውን እውነታ» ከ«መንፈሳዊ እውነታ» በግልጽ መለየቱ ቢያሳስበኝም፥ አሳቡ ፈር ሲይዝ ተመለከትሁ። ለቀጣዩ ሰዓት አብረን መጽሐፍ ቅዱስ በማገላበጥ አሳቡን እንመረምር ጀመር። በሲና ተራራ፥ እግዚአብሔር እንደ ጤንነት፥ ብልጽግናና ወታደራዊ ድል የመሳሰሉትን ቁሳዊ ስኬቶች ለማጎናጸፍ ቃል መግባቱ፥ የእስራኤላውያንን መንፈሳዊ ይዘት ለማሻሻል የፈየደው ነገር አልነበረም። እንደ አብርሃም፥ ዮሴፍ፥ ዳዊት፥ ኤልያስ፥ ኤርምያስና ዳንኤል የመሳሰሉት የብሉይ ኪዳን የእምነት ጀግኖችም የኢዮብን በሚያህል አበሳ ውስጥ ተረማምደዋል። ለእነዚህ ሰዎች ለእያንዳንዳቸው ቁሳዊው እውነታ እግዚአብሔር ጠላታቸው እንደሆነ የሚያመለክት ይመስል ነበር። ይሁንና፥ እነዚህ ሰዎች እያንዳንዳቸው ከመከራቸው ባሻገር በእርሱ መታመናቸውን ለመቀበል ችለዋል። ይህንንም በማድረጋቸው እምነታቸው «ደህና አድርጎ ከተንከባከበኝ እግዚአብሔርን እከተላለሁ» ከሚለው «የኮንትራት እምነት» የትኛውንም መከራ ሊቋቋም ወደሚችል ደረጃ ተሸጋግሯል።

ወዲያው ዳግላስ ሰዓቱን ተመልክቶ ሌላ ቀጠሮ እንዳለበት ነገረኝ። በችኮላ ኮቱን ለባበሰና አንድ የመጨረሻ አሳብ ተናግሮ ሊሄድ ተሰናዳ። «ወደ ቤትህ ስትመለስ የኢየሱስን ታሪክ እንደገና እንድታነብ እጠይቅሃለሁ። ሕይወት ለእርሱ ‹ፍትሐዊ› ነበረች? ለእኔ፥ ሕይወት ፍትሐዊ ትሆናለች የሚለውን አስተሳሰብ መስቀሉ ለሁልጊዜም ያወደመው ይመስለኛል» አለኝ።

ዳግላስና እኔ ስለ ኢዮብ በመነጋገር ጀምረን ስለ ኢየሱስ በመወያየት ደመደምን። ይኸው አስተሳሰብ ከልቤ ቀረ፤ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ከሚወዳቸው ሰዎች አንዱ የከፋ የፍትሕ-አልበኛነት

ሥቃይ ተቀብሎ ነበር፤ በአዲስ ኪዳን ደግሞ ራሱ የእግዚአብሔር ልጅ ከዚያ የበለጠ መከራ ተቀብሏል።

ወደ ቤቴ ስመለስ፥ የዳግላስን ምክር ተቀብዬ አሁንም ወንጌላትን አስስ ጀመርሁ፤ ይህንንም ያደረግሁት፥ «ሕይወት ፍትሕ-አልባ ነች ወይ?» ለሚለው ቀጥተኛ ጥያቄ የኢየሱስ ምላሽ ምን እንደሚሆን በማሰብ ነበር። በየትም ስፍራ ፍትሕ-አልበኛነቷን ሲከድ አላየሁትም። ኢየሱስ ከታመመ ሰውዬ ጋር ሲገናኝ፥ በዚህ ምድር ብድራትን ስለ መቀበል አላስተማረውም፤ ወደ እርሱ የመጡትን ሁሉ ይፈውስ ነበር። በዘመኑ በነበሩት ቱጃሮችና ኃያላን ላይ የሚሰነዝራቸው የትችት ቃላት ስለ ማኅበራዊ እኩልነት አለመስፈን ምን እንዳሰበ በግልጽ ያሳያሉ። የእግዚአብሔር ልጅ ለሕይወት ኢ-ፍትሐዊነት የሰጠው ምላሽ እንደ ሌላው ሰው ሁሉ ነበር። በሥቃይ ላይ የሚገኝ ሰው ሲያጋጥመው ከፍተኛ የርኅራኄ ስሜት ያድርበታል። ወዳጁ አልዓዛር በሞተ ጊዜ አንብቷል። ራሱ ከመከራ ጋር ሲጋፈጥ፥ ሌላ አማራጭ እንዳለ ሦስት ጊዜ ደጋግሞ ጠይቋል።

እግዚአብሔር ለኢ-ፍትሐዊነት ችግር ምላሽ የሰጠው በቃላት ሳይሆን በትስእብት የሰውን ልጆች በመጎብኘት ነው። ኢየሱስ እግዚአብሔር ስለ ሕይወት ኢ-ፍትሐዊነት ምን ዓይነት ስሜት እንደሚሰማው የሥጋና የደም ማረጋገጫ ሰጥቷል፤ ምክንያቱም የሕይወትን ቁሳዊ እውነታ ከሁሉም በከፋ ኢ-ፍትሐዊነቱ ተላብሶአልና። በማጠቃለያውም በእግዚአብሔር መልካምነት ላይ ለሚነሡ ስውር ጥያቄዎች ሁሉ የመጨረሻ ምላሽ ሰጥቷል። (ወንጌላትን በማነብበት ጊዜ፥ የአካሉ ክፍሎች የሆንን ሁላችን እርሱ እንዳደረገው ማለትም የታመሙትን በመጠየቅ፥ የተራቡትን በመመገብ፥ የክፋትን ኃይሎች በመቃወም፥ የሚያለቅሱትን በማጽናናት፥ የፍቅርንና የይቅርታን መልካም የምሥራች በማምጣት ሕይወታችንን ብንመራ ኖሮ፥ ምናልባትም «እግዚአብሔር ኢ-ፍትሐዊ ነው?» የሚለው ጥያቄ አሁን በሚሰማበት የጎላ ድምፅት ላያስተገባ እንደሚችል አሰብሁ።)

የከፋ ኢ-ፍትሐዊነት

እግዚአብሔር ኢ-ፍትሐዊ ነውን? ምላሹ የሚወሰነው እግዚአብሔርንና ሕይወትን በምንለይበት ቅርበት ነው። በመሠረቱ ሕይወት በምድር ላይ ፍትሐዊ አይደለም። ዳግላስ መስቀሉ ለዚያ ጉዳይ ለዘላለሙ እልባት እንደሰጠ መናገሩ ትክክል ነበር።

ደራሲው ሄንሪ ኖውን በፓራጓይ የሚያውቋቸውን ቤተሰቦች ታሪክ ጠቅሰው ነበር። ዶክተር የሆነው አባወራ አገሪቱን የሚመራውን

ወታደራዊ መንግሥትና የሰብአዊ መብቶችን ይቃወማል። የአካባቢው ፖሊስ ታዳጊ ወጣት የነበረ ልጁን በማሰር እስከ ሞት ድረስ አሠቃየው። ሁኔታው ያስቆጣቸው የከተማዪቱ ነዋሪዎች የልጁን የቀብር ሥነ-ሥርዓት ወደ ሕዝባዊ የተቃውሞ ሰልፍ ለመለወጥ ፈለጉ። ዶክተሩ ግን ሌላ የተቃውሞ አማራጭ ወሰደ። ቀብሩ በሚፈጸምበት ሰፍራ አባቱ የልጁን አስከሬን ከእስር ቤቱ ባገኘው መልኩ ለሕዝቡ አሳየ፤ አስከሬኑ በኤሌክትሪክና በሲጋራ ከመጠባበሱ በላይ ብዙ ግርፋት እንደደረሰበት ያመለክታል። እዚያ ላይ ልብስ እንኳ ጣል አልተደረገበትም ነበር። የአካባቢው ሰዎች በሣጥን ሳይሆን ከወጎኒ ቤቱ በመጣውና ደም በጠገበ ፍራሽ ላይ የተኛውን አስከሬን በሰልፍ አዩት። ይህ ኢ-ፍትሐዊነትን ቁልጭ አድርጎ ስለሚያሳይ ከፍተኛ የተቃውሞ ምልክት ነበር።

እግዚአብሔርስ በጎልጎታ ይህንኑ አልነበር ያደረገው? ለሕይወት ኢ-ፍትሐዊነት እግዚአብሔርን የሚቀየሙ ሰዎች፥ «ሊሠቃይ የሚገባው እግዚአብሔር እንጂ እኔና አንተ አይደለንም» ይላሉ። «እግዚአብሔር ይኮንን» (God be damned) የሚለው የአሜሪካኖች ርግማን ደህን አድርጎ ይገልጸዋል። በዚያን ዕለት እግዚአብሔር ተኮነነ። የቆሳሰለውንና የተራቆተውን የኢየሱስን ሰውነት የተሸከመው መስቀል የዚህን ዓለም ጭካኔዎችና ፍትሕ-አልባ ተግባራት ገልጦ የሚያሳይ ነበር። መስቀሉ ምን ዓይነት ዓለምና ምን ዓይነት አምላክ እንዳለን በአንድ ጊዜ አሳይቷል። ይኸውም በገዘፈ ፍትሕ-አልባነት የታወቀው ዓለምና የመሥዋዕትነት ፍቅር ያለው አምላክ ከመስቀሉ ላይ መገኘታቸው ነው።

ከጎዘን ወይም ቅይጣት ነፃ የሆነ ማንም የለም። እግዚአብሔርም እንኳ ከዚህ ነፃ አልሆነም። ኢየሱስ ከኢ-ፍትሐዊነት የሚያፈነግጥበትን መንገድ አናገኝም፤ ይልቁንም በዚያው አቋርጦ ወደ ሌላው አቅጣጫ አልፎአል። ስቅለት ይህች ዓለም ፍትሐዊ መሆን እንዳለባት የሚቀርበውን ተለምዶአዊ እምነት እንዳስወገደ ሁሉ፥ ትንሣኤ የአጽናፈ ዓለሙን እንቆቅልሽ የሚያስደምም ፍንጭ አስከትሏል። ከድቅድቅ ጨለማ ውስጥ የሚያስደንቅ ብርሃን ፈንጥቋል።

ቀዳማዊ የፍትሐዊነት ፍላጎት ይለወጣል፤ ሊለወጥም ይገባል። ከመካከላችን በዚህ ዓለም ውስጥ አሁኑኑ የተሻለ ፍትሕ እንዲኖር የማይናፍቅ ማን ነው? በበኩሌ እንከን የሌለበትን ዓለም እንደምናፍቅ አውቃለሁ። የመጽሐት ላይ ጽሑፎቼ ሁልጊዜም ተቀባይነት የሚያገኙበት፥ ሰውነቴ ድካምና እርጅና ሳያውቀው ብርታትን ተጎናጽፎ የሚኖርበት፥ የወንድሜ ሚስት አእምሮው የተበላሸበት ልጅ የማትወልድበትና ፔጊ ውድሳን ረዥም ዕድሜ የምትኖርበት ዓለም

ይናፍቁኛል። ነገር ግን እምነቴን በዚህ ዓይነቷ ዓለም ላይ ብመሠርት፥ እምነቴ እንደሚከዳኝ አውቃለሁ። ታላላቅ ተአምራት እንኳ የዚህችን ምድር ችግሮች አያስወግዱም፥ ሥጋዊ ፈውስ የሚያገኙ ሰዎች የኋላ ኋላ መሞታቸው አይቀርምና።

የሚያስፈልገን ከተአምር የላቀ ነገር ነው። አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ያስፈልገናል፤ እስከዚያ ድረስ ኢ-ፍትሐዊነት አይወገድም።

በብዙ መከራዎችና ኃዘን መካከል በአፍቃሪ አምላክ ለማመን የሚታገል አንድ ወዳጄ፥ «የእግዚአብሔር ብቸኛው ማማኛኛ ትንሣኤ ነው» ሲል ተናግሯል። ምንም እንኳ የዚህ ሰው ቃላት ሥነ-መለኮታዊ ያልሆነና ከባድ ቢሆንም፥ በዚያ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ከባድ እውነት አለ። የክርስቶስ መስቀል ክፋትን ሊያስወግድ ቢችልም፥ ኢ-ፍትሐዊነትን አላስወገደም። ለዚያ ትንሣኤ ያስፈልገን ነበር። አንድ ቀን እግዚአብሔር በራሱ አገዛዝ ሥር ሁሉንም ቁሳዊ እውነታ ከተገቢ ስፍራው ያስቀምጣል። እስከዚያ ድረስ፥ ሕይወታችንን በትንሣኤ አሑድ ማኖር እንዳለብን ማስታወሱ መልካም ነው።

> «እንኳንስ በበረሃ ውስጥ በየትም ስፍራ እግዚአብሔርን ለማፍቀር መታዘዝ በታመምን ጊዜ እንድንድን፥ ጥማት እያቃጠለን ሳለ የደስታ ዝማሬ እንድናቀርብ፥ እግሮቻችን በተሰበሩ ጊዜ እንድንሮጥ የመታዘዝ ያህል ነው። ይሁንና፥ ይህ የመጀመሪያውና ታላቁ ትእዛዝ ነው። በበረሃ ውስጥ እንኳ፥ በተለይም በበረሃ ውስጥ እግዚአብሔርን መውደድ አለብህ።»
>
> – ፍሪድሪክ ቡችነር

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ፡– ኢዮብ 21፥2 ።

«እኔ የማላስተውለውን፥ የማላውቀውንም ድንቅ ነገር ተናግሬአለሁ።» (ኢዮብ 42፡3)

ምዕራፍ 25

እግዚአብሔር ለምን ማብራሪያ አይሰጥም?

ወደ መጽሐፈ ኢዮብ መጨረሻ አካባቢ፥ ልበ-ሙለው ወጣት ኤሊሁ ኢዮብ የእግዚአብሔርን ጉብኝት በመሻቱ ላይ እየተሳለቀ ይናገራል። «እግዚአብሔር እንደ አንተ ስላለው ደካማ ፍጡር የሚጨነቅ ይመስልሃል? የአጽናፈ-ዓለሙ ፈጣሪ የሆነው ሁሉን የሚችል አምላክ ምድርን ለመጎብኘትና ከአንተ ጋር ለመገናኘት የሚፈልግ ይመስልሃል? ለአንተ የሆነ ማብራሪያ የመስጠት ዕዳ አለበትን? ነቅተህ መልስ፥ ኢዮብ።»

ኤሊሁ ረዥም ንግግሩን እየቀጠለ ሳለ፥ ከትከሻው ላይ አንዲት ትንሽ ደመና ታየች። ደመናዋ ወደ ዐውሎ ነፋስነት እየተለወጠች ስትመጣ፥ ከሌሎች ሁሉ የተለየ ድምፅ አስተጋባ። ኤሊሁ ከመቅጽበት ተገታና ኢዮብ መንቀጥቀጥ ጀመረ። እግዚአብሔር ራሱ ከትእይንቱ ላይ ተገኝቶ ነበር። እግዚአብሔር ለኢዮብ የፍትሕ-አልባነት ወቀሳ ምላሽ ለመስጠት ነበር የመጣው።

መጽሐፈ ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር ለሚደረግ ቅይማት እንደ ዋነኛ መረጃ የሚያገለግል ከሆነ፥ ይኸው ከዐውሎ ነፋስ ያስተጋባው ኃይለኛ ድምፅ በሌሎች ጊዜያት ሁሉ ለሚያጋጥም ግራ መጋባትና ጥርጣሬ ጠቃሚ አሳቦችን እንደሚያስተላልፍ እሙን ነው። እንግዲህ እግዚአብሔር ራሱን ለመከላከል ምን ይል ይሆን?

እግዚአብሔር ሊናገራቸው ስለሚችላቸው አያሌ ጠቃሚ ነገሮች ማሰብ ይቻላል። «ኢዮብ፥ በተከሰተው ነገር ከልቤ አዝናለሁ። ለእኔ ስትል ብዙ ፍትሕ-አልባ መከራዎችን ተቀብለሃል፤ እኮራብሃለሁ። ይህ ለእኔም ሆነ ለአጽናፈ-ዓለሙ ምን ማለት እንደሆነ አታውቅም።» እግዚአብሔር መጠነኛ አድናቆት፥ ርኅራኄ ወይም ቢያንስ በማይታየው ዓለም ውስጥ «ከመጋረጃው በስተጀርባ» ስለነበረው ሁኔታ ቢናገር ለኢዮብ መጽናኛ ይሆነው ነበር።

እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነት ነገር አልወጣውም። እንዲያውም «ከምላሹ» ውስጥ የሚገኘው በአብዛኛው ጥያቄ እንጂ መልስ አይደለም። በመከራ ችግር ላይ ሊያነጋግሩ የሚችሉትን ሠላሳ አምስት ምዕራፎች ወደ ጎን በመተው፥ የተፈጥሮአዊውን ዓለም አስደናቂ የቃላት ጉብኝት ወደማካሄዱ ያመራል። ኢዮብን ምርጥ ሥራዎቹ

ወደሚኙበት አዳራሽ በመጋበዝ የኮረብታ ፍየሎችን፥ የሜዳ አህዮችን፥ ሰጎኖችንና ንስሮችን በኩራት የሚያሳየው ይመስላል። ይህንንም የሚያደርገው በራሱ የፍጥረት ሥራ እንደተደነቀ በሚመስል ሁኔታ ነበር። በመጽሐፈ ኢዮብ መጨረሻ የሚገኘው ቅኔ ከዓለም ሥነ-ጽሑፍ ከየትኛውም ጋር አይነጻጸርም። እግዚአብሔር ስለ ተፈጥሮአዊው ዓለም የሚሰጠውን አንጸባራቂ ትንተና እየተከታተልሁ በምደነቅበት ጊዜ እንኳ ግራ የመጋባት ስሜት ይጫነኛል። ከሁሉም ጊዜያት እግዚአብሔር ኢዮብን ለማስተማር ይኸኛውን አቅጣጫ የመረጠው ለምንድን ነው? እነዚህ ቃላት ከኢዮብ ችግር ጋር ተዛምዶ አላቸውን?

ፍሬድርክ ቡችነር "Wishful Thinking" በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ የእግዚአብሔርን ንግግር በማጠቃለያ መልክ ጽፈዋል። «እግዚአብሔር ይናገራል እንጂ ማብራሪያ አይሰጥም። ኢዮብ እርሱን እንደ ማን እንደሚያስብ ይጠይቀዋል። ኢዮብ እንዲብራሩለት የሚፈልጋቸውን ነገሮች ማንሣት ለአንድ ትንሽ እንስሳ ስለ ታዋቂው ሳይንቲስት አልበርት አይነስታይን ለማስረዳት እንደ መሞከር መሆኑን ይናገራል። እግዚአብሔር ዋነኛ ንድፉን አይገልጥም። ራሱን ግን ይገልጻል።» ከዚያ ውብ ቅኔ በስተጀርባ የሚገኘው መልእክት ይህ ነው፤ «ኢዮብ ሆይ፥ ቁሳዊውን ዓለም ስለ ማስተዳደር ትንሽ ግንዛቤ እስኪኖርህ ድረስ ግብረገባዊውን ዓለም ስለ ማስተዳደር አትንገረኝ» የሚል ነው።

«እንዲህ የከፋ ሥቃይ የምታበላኝ ለምንድን ነው፥ እግዚአብሔር ሆይ?» ሲል በመጽሐፉ ሁሉ ውስጥ ኢዮብ ጩኸቱን ሲያስተጋባ ነበር። «ራስህን በእኔ ቦታ አስቀምጥ።»

«አላስቀምጥም!» ሲል እግዚአብሔር ነጎድጓዳዊ ምላሽ ይሰጣል። «አንተ ራስህን በእኔ ቦታ አስቀምጥ!» ፀሐይ በየቀኑ እንድትወጣ፥ ወይም የመብረቅ ብልጭታን የት ስፍራ ለመበተን፥ ወይም አንድን ጉማሬ ለመሥራት ምን ዓይነት ጥበብ መጠቀም እንደሚያሻ ለማስተማር ከመቻልህ በፊት ዓለምን ስለማስተዳድርበት አሠራር አትፍረድብኝ። ዝም ብለህ አድምጠኝ።»

የእግዚአብሔር ንግግር በኢዮብ ላይ ያመጣው ለውጥ የንግግሩን ያህል አስደናቂ ነበር። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ስለ ኢዮብ መከራ አንድም ምላሽ ባይሰጥም፥ ከማዕበሉ የመጣው ብርሃን ኢዮብን ጸጥ አሰኝቶአል። በአዲራና በዐመድ ላይ ተቀምጦ እየተጸጸተ ንስሐ ገባ። ከእግዚአብሔር ጋር የተቀያየመበትም ጉዳይ ሁሉ ተወገደ።

ልናውቀው የማንችለው

ምናልባትም እግዚአብሔር ከዐውሎ ነፋስ ውስጥ ሆኖ ሲናገር የመስማት ዕድል የማይኖረን ሰዎች እግዚአብሔር ለኢዮብ ያስተላለፈውን መልእክት ፈልፍለን ልናወጣ ይገባል። እግዚአብሔር በቀጥታ ለመናገር እንደማይፈልግ ሆኖ የሰጠው ምላሽ የሚፈታውን ያህል ችግር ይፈጥርብኛል። ዝም ብዬ «ለምን?» የሚሉትን ጥያቄዎች ወደ ጎን ልገፋ አልችልም። ሁልጊዜም እንደ ሜግ ውድሳን ካለው ሰው ጋር ስነጋገር ወይም የራሴ ሕይወት መዛባት ሲጀምር እነዚህ ጥያቄዎች ይከሰታሉ።

እግዚአብሔር የኢዮብን ጥያቄ ለመመለስ አለመፈለጉ ለዘመኑ አእምሮ አይመችም። አንድ ነገር ከአእምሮአችን በላይ እንደሆነ ሲነግሩን እንደሰትም። ማብራሪያ ልንሰጥ ስለማንችላቸው የሳይንስ ዘርፎች የሚናገር "The Encyclopedia of Ignorance" የተባለ መጽሐፍ አለኝ። ይሁንና፥ በዓለም ሁሉ የሚገኙ ሳይንቲስቶች በእነዚያ አካባቢዎች በመመራመር የጎደለውን የእውቀት ክፍተት ለመሙላት የሚችሉትን ሁሉ በማድረግ ላይ ናቸው። ምናልባት እግዚአብሔር የሰው ልጅ ለመቼውም የማይረዳው ሥነ-መለኮታዊ (The Encyclopedia of Theological Ignorance) መሐይምነት ዳርቻ ከልሎ ይሆን?

ብዙ ብደራደርም የመጽሐፈ ኢዮብ አሳብ ወደዚሁ ድምዳሜ ይገፋኛል። ሕይወት እንዲህ ኢ-ፍትሐዊ የሆነችው ለምንድን ነው? እግዚአብሔር ሥቃይን ሆን ብሎ የሚጠነስሰውና ሲከሰት እያየ ዝም የሚለው መቼ ነው? በእነዚህ በሁለቱ መካከል ያለውስ ልዩነት ምንድን ነው? እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ የቅርብ፥ በሌላ ጊዜ ደግሞ ዝም ያለ የሚመስለው ለምንድን ነው? እግዚአብሔር እነዚያን ጉዳዮች ወደ በጎነት ለመለወጥ የሚችልባቸው ግሩም ዕድሎች እያሉለት ራሱን ነቅንቆ ዝም ይላል። ለምን ብሎ ሲያብራራ ይኑር? ኢዮብም ሆነ ሌሎች የሰው ልጆች አይረዱትም።

እግዚአብሔር የተናገረው ነገር ባለመኖሩ ለኢዮብ ጥያቄዎች ዝርዝር መልስ ማቅረብ አይቻልም። ልንጠይቅ የምንችለው ነገር ቢኖር እግዚአብሔር ለምን ምላሽ እንደማይሰጥ ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ዝም ብሎ ወደሚቆይበት ወረዳ እየገባሁ ስለሆነ፥ ቀጣዩ መላምታዊ አሠራር ነው። ይህም እግዚአብሔር ለመመለስ የማይፈልጋቸውን ጥያቄዎች ከማንሣት ለማይታቀቡ ወገኖች በማሰብ የቀረበ ነው።

1. እግዚአብሔር እንዳናውቅ የሚፈልገው ምናልባትም ማወቃችን ስለማይረዳን ሊሆን ይችላል።

ተመሳሳይ አሳሳቢ ጥያቄዎች በመከራ ውስጥ የሚገኙትን ግለሰቦች ሁሉ ያስጨንቃሉ፤ ለምን? ለምን እኔን? እግዚአብሔር ሊነግረኝ የሚፈልገው ምንድን ነው? በመጽሐፈ ኢዮብ እግዚአብሔር እነዚህን የምከንያት ጥያቄዎች ገሸሽ በማድረግ በእኛ የእምነት ምላሽ ላይ ያተኩራል። ነገር ግን እግዚአብሔር ጥያቄዎቻችንን ፊት ለፊት ቢመልስ ምን እንደሚከሰት አስብ። ከበስተ ጀርባው ያለውን ምከንያት ብቻ ብናውቅ ሥቃያችንን በተሻለ ሁኔታ እንደምንሸከም እንገምታለን። ግን ይህ እውነት ነው ወይ?

በሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት መካከል አስገራሚ ተመሳሳይነት አይቻለሁ፤ መጽሐፈ ኢዮብና ሰቆቃው ኤርምያስ። ኢዮብ የቤቱንና የንብረቱን መውደም ባለማመን ታሪኩን ይጀምራል፤ የሰቆቃው ኤርምያስም ጸሐፊ የኢየሩሳሌምን ከተማ መፈራረስ ባለማመን ታሪኩን ይጀምራል። ሁለቱም መጻሕፍት ከእግዚአብሔር ጋር የጠለቀ ቅይማት ፈጥረው እንመለከታለን። እንዲያውም በርካታ የመጋልየ መጋልይ ምንባቦች ከእርሱ በላይ ጥንታዊ የነበረው የመጽሐፈ ኢዮብ አገላለጾችን ይመስላሉ። ይሁንና፥ የሰቆቃው ኤርምያስ ጸሐፊ (ምናልባትም የጻፈው ኤርምያስ ሊሆን ይችላል) በጽልመት ውስጥ አልነበረም። ኢየሩሳሌም ለምን እንደተደመሰሰች ያውቅ ነበር። የተደመሰሰችው አይሁዶች ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ቃል ኪዳን ስላፈረሱ ነበር። ይሁንና፥ የምከንያቱ መታወቅ ሥቃዩን ወይም የጭንቀትና የመተው ስሜትን ለማርገብ የፈየደው ነገር አልነበረም። «እግዚአብሔር እንደ ጠላት ሆኗል» ሲል የኢዮብን ዓይነት ቃና ተጠቅሟል። «ለምን ትረሳናለህ? ለረዥም ጊዜ ለምን ትተወናልህ?» ሲል ጠይቋል–ምንም እንኳ መልሱን ሙሉ ለሙሉ ቢያውቀውም፤ ሌሎች የመጽሐፉ ክፍሎች በዝርዝር ገልጸውታል።

ኢዮብን፥ ኤርምያስን፥ ወይም ሜግ ውድሳንን ሊያጽናና የሚችል ማብራሪያ ምን ይሆን? እውቀት ምሑራዊና የራቀ ሲሆን፥ ሥቃይ ግላዊና የቀረበ ነው። የትኛውም ምሑራዊ ምላሽ የሥቃይን ችግር ሊፈታ አይችልም። ምናልባትም እግዚአብሔር የራሱን ልጅ ለሰው ልጆች ሥቃይ እንደ አንድ ምላሽ አድርጎ የላከው ለዚህ ይሆናል፤ ይኸውም የሰውን ልጅ ሥቃይ እንዲጋራና ወደ ራሱም እንዲስብ ነው። ትስእብት የሰውን ልጅ መከራ ባያስወግድም፥ የቀረበና ግላዊ ምላሽ ነበር። ከሁሉም በላቀ እውነተኛ መልኩ የትኞቹም ቃላት ከቃል በበለጠ ድምፀት ሊናገሩ አይችሉም።

«ለምን?» ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት መጽሐፈ ኢዮብን ብትመለከት፥ ማዘንህ አይቀሬ ነው። እግዚአብሔር ምላሽ አልሰጠም፤ ኢዮብም ጥያቄዎቹን ገታ፤ ሦስቱ ጓደኞቹም ለተሳሳተው መላምታቸው ንስሐ ገቡ። ኢየሱስም እንዲሁ የመከራን ቀጥተኛ ምክንያት ለመናገር አልፈለገም። ደቀ መዛሙርቱ ዕውር ሆኖ ስለተወለደ ሰው (ዮሐ. 9) እና በአካባቢያቸው ስለተከሰቱት አደጋዎች (ሉቃስ 13) የተወሰኑ ድምዳሜዎችን ሲያስቀምጡ ኢየሱስ ገሥጾአቸዋል። «ለምን?» ለተሰኙ ጥያቄዎች ፈጣን ምላሽ መስጠት እንደማይቻል ከመጽሐፍ ቅዱስ መረጃ መገንዘብ ይቻላል።

ከእግዚአብሔር ደንቦች አንዱን ብንጥስ ከአደገኛ ሁኔታ ላይ እንወድቃለን። «እግዚአብሔር በጣም ስለወደደው አባትህን ወደ ራሱ ወሰደው» ብሎ አንድን አባት–አልባ ልጅ ለማጽናናት መጣሩ እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ ከማይዘልቅበት ክልል እንደ መግባት ዓይነት ነው። እንደ አውሮፕላን አደጋ፥ መቅሠፍት፥ የሽብርተኞች ቅጣት፥ መድኃኒቶችን ሆን ብሎ መመረዝ፥ በአፍሪካ የብዙዎችን ሕይወት የሚቀጥፈው ረሃብ ዓይነት ችግሮች አንድ ሥልጣናዊ ትርጓሜ ለማግኘት የሚጠብቁ ቢሆንም፥ መጽሐፈ ኢዮብ ጠቃሚ ማስገንዘቢያ ይሰጠናል። ይኸውም እግዚአብሔር ራሱ ማብራሪያ ለመስጠት እንዳልጣረ ነው።

2. *ምናልባትም እግዚአብሔር እንዳናውቅ የሚፈልገው ምላሹን ስለማንረዳው ይሆናል።*

እግዚአብሔር ለኢዮብ ጥያቄዎች ምላሽ ያልሰጠበት ሁኔታ ምሥጢራዊ ራስን የማግለል ጥበብ ላይሆን ይችላል። እግዚአብሔር ይህንን ያደረገው የሕይወትን ግልጽ እውነታ እንደሚያውቅ ለማሳየት ይሆናል። በሚጢጢዋ ምድር ላይ የተቀመጠ አንድ ሚጢጢ ፍጡር የአጽናፈ –ዓለሙን ግዙፍ ንድፍ ሊረዳ አይችልም። ለዓይነ–ስውራን የቀለምን ዓይነት፥ መስማት ለተሳናቸው የሞዛርትን ዜማ፥ ስለ አተሞች ለማያውቅ ሰው የአንጻራዊነትን ንድፈ–ሐሳብ (Theory of relativity) ማስረዳት አይቻልም።

ችግሩን ለመረዳት፥ በማይክሮስኮፕ (አጉሊ –መነጽር) መስተዋት ላይ ከተቀመጠ ነፍሳት ጋር ለመግባባት እንደምትፈልግ አድርገህ አስብ። የዚህ ዓይነቱ ነፍሳት «አጽናፈ–ዓለም» የሚወሰነው በተቀመጠበት የመመልከቻ መነጽር ስፋት ነው። ከመነጽሩ ጠርዞች ውጭ ያለውን ነገር የስሜት ሕዋሳቶች አይገነዘቡም። ለዚህ ዓይነቱ

ፍጥረት የቦታን ወይም የቁመትን ወይም የጥልቀትን ጽንሰ–አሳብ እንዴት አድርገህ ትገልጽለታለህ? «ከላይ» ሆነህ፥ የዚህን ፍጡር ባለ ሁለት አቅጣጫ (two-dimentional) ዓለምና ከአካባቢው የሚገኘውን ባለ ሦስት አቅጣጫ (three-dimentional) ዓለም ልትገነዘብ ትችላለህ። ያ ፍጡር ሊረዳ የሚችለው ግን «ከእርሱ በታች» ያለውን የሁለት አቅጣጫ ዓለም ብቻ ነው።* በተመሳሳይ ሁኔታ፥ የማይታየው ዓለም ከግንዛቤያችን ውጭ ነው፤ ይህም ተአምራት ብለን ከምንጠራቸው አልፎ ከሚከሰቱ ጣልቃ–ገብነቶች ውጭ መሆኑ እሙን ነው። ኢዮብ ወይም እኔና አንተ በአሁኑ አእምሮአችን ጠቅላላውን ምስል ልንረዳው አንችልም።

የፊልም ባለሙያው ዉዲ አለን “Purple Rose of Cairo” በተሰኘው ሥራው ውስጥ ይህንኑ «የሁለት ዓለማት የአመለካከት ደረጃ አንጸባርቋል። መጀመሪያ ዋናው ገጸ–ባሕርይ በፊልሙ ውስጥ ሲጫወት በምትመለከተው በማያ ፋሮ በኩል እናየዋለን። ከዚያም በሚያስደንቅ ሁኔታ ይኸው ዋና ገጸ–ባሕርይ ከባለ ሁለት አቅጣጫ የፊልም መስተዋት ይወጣና ወደ ኒው ጀርሲ ቲያትር ይገባል። ወዲያው በአድናቆት ከተዋጠችው ገጸ–ባሕርይ (ሚስ ፋሮ) ጋር ወደ እውነተኛው ዓለም ይዘልቃል።

ለፊልም ተዋናዩ የውጭው ዓለም አስገራሚ ይሆንበታል። አንድ ሰው በክርን ሲመታው እንደታዘዘው ይወድቃል፤ ነገር ግን በአድናቆት ጥርሱን ያንገጫግጫል፤ እነዚያ ምቶች ሊጎዱት አይገባም ነበር። እርሱና ሚስ ማያ በሚሳሳሙበት ጊዜ፥ ከስመቱን በመጠባበቅ ቆም ይላል። «ሁሉንም ነገር የሚቆጣጠረው እርሱ ነው። ጠቅላላው ዓለም የእርሱ ነው።» እያለ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር በሚያስረዳው ጊዜ ተዋናዋዩ ራሱን በአዎንታ ይነቀንቃል። «አ፥ ሚስተር ማየርን ማለትህ ነው። የፊልም ኩባንያው ባለቤት» ሲል ይመልስለታል። የእርሱ ዓለም በፊልሙ ዓለም ውስጥ ታጥሮአል።

በመጨረሻም፥ ተዋናዩ ወደ ሁለት አቅጣጫ የፊልም መስተዋት በመዝለል ለተቀሩት ተዋንያን ስለ እውነተኛው ዓለም ማብራሪያ ይሰጣቸዋል። ሰውዬው በአእምሮ ሕክምና ሆስፒታል ውስጥ እንዳለ

---

* አንትሮፖሎጂስቶች በሚራራቁ ባሕሎች መካከል እንዲህ ዓይነት የግንዛቤ ክፍተት እንዳለ ይዘግባሉ። ለአንድ የፓፑዋ ኒው ጊኒ የገጠር ሰው የደን ፎቶግራፍ ቢሰጠው፥ ከወረቀቱ ላይ ያረፉትን ነጠብጣቦች ብቻ ይመለከታል። ይህ ሰው ባለ ሁለት አቅጣጫ ምስሎች የሆኑትን ወፎች፥ ፋፋአቴዎች እንደሚወክል ከልምድ ተረድቷል።

ሁሉ በግራሞት ያዩታል። የሚያወራው የማይሆነውን ነበር። ለእነርሱ የፊልሙ ዓላማ እንጂ ሌላ ዓለም እውን አልነበረም።

ዉዲ አለን የባለ ሁለት አቅጣጫውን ፍጥረት ዓይነት መልእክት ያስተላልፋል። አንዱ ዓለም ባለ ሁለት አቅጣጫው ወይም የፊልሙ ዓለም በሌላው ውስጥ የሚኖር ከሆነ፥ ትርጉም ሊሰጥ የሚችለው ከላይኛው ዓለም እይታ አንጻር ብቻ ነው። ምሳሌውን ወደ መጽሐፈ ኢዮብ ብንወስደው፥ አብዛኛዎቹ የኢዮብ ጥያቄዎች «በከፍተኛው» ዓለም ውስጥ የሚገኙትን እንቅስቃሴዎች የሚመለከቱ ናቸው። ይኸው «ከፍተኛው» ዓለም ደግሞ ከእርሱ ግንዛቤ የራቀ ነው።

እግዚአብሔር በሌላው አቅጣጫ «በከፍተኛው» ደረጃ ላይ ይኖራል። እርሱ አጽናፈ-ዓለሙ ይይዘው ዘንድ አይችልም። እኛ በማንረዳው መንገድ፥ እርሱ በጊዜና በቦታ የተገደበ አምላክ አይደለም። ወደ ቁሳዊው ዓለም ዘልቆ ሊገባ ይችላል። ይህንን ባያደርግ ደግሞ የስሜት ሕዋሳቶቻችን ሊረዱት አይችሉም ነበር። ይሁንና፥ ይህ ወደ ቁሳዊ ዓለም የመግባቱ ጉዳይ ለእርሱ ልክ አንዱ ደራሲ በተውኔቱ ውስጥ ራሱን እንደ አንድ ገጸ-ባሕርይ የሚያስተዋውቅበት ዓይነት ነው። በእውነተኛው ዓለም የሚገኝ ሰው በፊልም ውስጥ ዘው ብሎ ገብቶ የሚወጣበት ዓይነት እንደ ማለት ነው።

የጊዜ ጉዳይ

ወጣቷ ሴቲቱ በአንጻራዊው ፈለግ

ከብርሃን በላቀ ፍጥነት ሰትጓዝ

አንድ ቀን ጉዞ ጀምራ

ባለፈው ዕለት ማታ ተመለሰች

የጊዜ ግንዛቤ በእግዚአብሔር (የላይ እይታ) እና በእኛ መካከል ያለውን ግዙፍ ልዩነትን ያመለክታል። ይህም ልዩነት በበኩሉ ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ቅይማት ለብዙዎቹ ያልተመለሱ ጥያቄዎቻችን ምክንያት እንደሚሆን አምናለሁ። ከዚህም የተነሣ እንደማፈንገጥ ዓይነት ሁኔታ ሊያስከትል ይችላል።

ቅዱስ አገስቲን «ኑዛዜዎች» (The Confessions) በተባለው አሥራ አንደኛው መጽሐፋቸው ውስጥ ስለ ጊዜ በሰፊው ጽፈዋል። «ጊዜ ምንድን ነው?» ሲሉ ይጀምራሉ። «አንድ ሰው እንደዚህ ቢጠይቀኝ ይገባኛል። ነገር ግን ለሚጠይቀኝ ሰው ለማብራራት ብፈልግ አይገባኝም።» «ከፍጥረት በፊት እግዚአብሔር ምን ይሠራ ነበር?»

ተብለው ሲጠየቁ አገስቲን፥ እግዚአብሔር ከተፈጠረው ዓለም ጋር ጊዜን ስለፈጠረ እንዲህ ዓይነቱ ጥያቄ ትርጉም እንደሌለውና የጠያቂውን በጊዜ የታሰረ አመለካከት እንደሚያወድም ተናግረዋል።* ከጊዜ «በፊት» የነበረው ዘላለማዊነት ብቻ ነው፤ ዘላለማዊነት ደግሞ ለእግዚአብሔር የማያከትም አሁንነት ነው። ለእግዚአብሔር አንድ ቀን እንደ አንድ ሺህ ዓመታት፥ ሺህ ዓመታት እንደ አንድ ቀን ነው።[2]

አገስቲንና አልበርት አይንስታይን ጊዜንና ቦታን ካዛመዱበት ጊዜ ወዲህ ስላለው ሁኔታ ምን ሊሉ ነው? አሁን ጊዜን እንደ አንጻራዊ እንጂ ፍጹማዊ አድርገን አንመለከተውም። የጊዜ ግንዛቤ በተመልካቹ አንጻራዊ ስፍራ ላይ እንደሚደገፍ ተናግሮአል። ይህንን ምሳሌ ውሰድ፤ የካቲት 23/1987 (እ.ኤ.አ.) ምሽት በቺሊ አንድ የሥነ ጠፈር ባለሙያ በላጤ ዓይኑ የሱፐርኖቫን የርቀት ፍንጣቂ እንደተመለከተ ተገልጾአል። ብርሃኑ እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሣ የእኛዪቱ ፀሐይ በአሥር ቢሊዮን ዓመታት የምትሰጠውን ያህል ኢነርጂ በአንድ ሰኮንድ ይለቅ ነበር። ነገር ግን እውን ያ ነገር በየካቲት 23/1987 ተፈጽሟል? ይህ የተፈጸመው ከፕላኔታችን እይታ አንጻር ብቻ ነው። በመሠረቱ፥ ያ ብርሃን የፈነዳው ከእኛው 1987 በፊት 170, 000 ዓመታት ቀደም ብሎ ነበር። ነገር ግን ከዚያ እጅግ ከላቀ ክስተት የመነጨው ብርሃን በዓመት 6 ትሪሊዮን ማይልስ እየተጓዘ ለመድረስ 170,000 ዓመታት ፈጅቶበታል።

እዚህ ጋ ነው እንግዲህ «ከፍተኛው» የዘላለም እይታ ተለምዶአዊውን የጊዜ ግንዛቤያችንን የሚሸረው። አንድ ከአጽናፈ-ዓለሙ ሁሉ የላቀ ግዙፍ ኑባሬ አለ እንበል። ከግዙፍነቱ የተነሣ ይኸው ኑባሬ በአንድ ጊዜ በምድር ላይና የ 1987 ሀ ሱፐርኖቫ በነበረበት ስፍራ ይገኛል። በ1987 ለዚያ ኑባሬ ሰዓቱ ስንት ይመስልሃል? ይኸው በአመለካከታችን የሚወሰን ነው። ከምድር እይታ አንጻር፥ ኑባሬው የ 1987 ሀ ሱፐርኖቫ ግኝት የሚያካትተውን የ1987 ታሪክ ይመለከት ነበር። ነገር ግን ከ1987 ሀ ሱፐርኖቫ እይታ አንጻር፥ ኑባሬው ምድር ለሚቀጥሉት 170,000 ዓመታት የምታገኘውን

---

* ግርቲን ሉተርም ለዚህ ጥያቄ የሰጠው ምላሽ ከአገስቲን የተሻለ አልነበረም። «እግዚአብሔር ሰማይን ከመፍጠሩ በፊት የት እንደነበር ሲጠየቅ አገስቲን በራሱ ውስጥ እንደነበር ተናግሯል። ሌላው ሰው ተመሳሳይ ጥያቄ ሲጠየቅ፥ እንዳንተ ላለ ደንቆሮ፥ ገብዝ፥ ሽንጋይና ጉጥ መንፈስ ሲአልን እየነነባ ነበር ብያለሁ» ሲል ተናግሯል።

ገጠመኝ ይለማመዳል። ስለሆነም፥ ኑባሬው የቀደመውን፥ (ከመሬት ሆኖ ከ170,000 ዓመታት በፊት የሱፐርኖቫን የብርሃን መረጨት ተመልከቷል)፥ የአሁኑን (በመሬት ላይ የ 1987ቱን ዓመተ ምሕረት ክስተት)፥ እና የወደፊቱን የምድር ላይ ነዋሪዎች ለሚቀጥሉት 170,000 ዓመታት የሚያገኙትን የሱፐርኖቫ 1987 ሀ «የአሁን» ክስተት በአንድ ጊዜ ተካፍሏል።

እንዲህ እንደ አጽናፈ-ዓለሙ የገዘፈው ኑባሬ በየትኛውም ጊዜ በየትኛውም ስፍራ የሚካሄደውን ነገር የመመልከት ብቃት ይኖረዋል። ለምሳሌ፥ በእኛዪቱ ፀሐይ ላይ በአሁኑ ሰዓት ምን እየተፈጸመ እንዳለ ለማወቅ ቢፈልግ፥ ከፀሐይ «እይታ አንጻር» ይመለከታል። ከስምንት ደቂቃዎች በፊት በፀሐይ ላይ ምን እንደተፈጸመ ለማወቅ ቢፈልግ፥ ከምድር «ለሚመለከት» ይችላል። ይህም ብርሃን ከፀሐይ ወደ ምድር 93 ሚሊዮን ማይልስ ከተጓዘ በኋላ የምንመለከተው ነው።

እንዲህ ዓይነቱን ኑባሬ ከጊዜ ነፃ ቢያደርገውም በቦታ ስለሚያስረው ምሳሌው ፍጹም ትክክል አይደለም። ነገር ግን «መጀመሪያ ሀ፥ ከዚያም ለ ይከሰታል» የሚለው የጊዜ ጽንሰ-አሳባችን የፐላኔታችንን ውስን የእይታ አንጻር ይገልጻል። ከጊዜና ቦታ ጽንሰ-አሳብ ውጭ የሆነው እግዚአብሔር በምድር ላይ የሚፈጸመውን ሁሉ እኛ ከመገመት በቀር ሙሉ ለሙሉ በማንረዳበት መንገድ ሊመለከት ይችላል።

እንዲህ ዓይነቶቹ አሳቦች ንድፈ-አሳቦች ብቻ አይደሉም። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የፊዚክስ ተማሪዎች ወደፊት ከብርሃን በሚልቅ ፍጥነት ወደ ሕዋ ከመጠቁ በኋላ ይበልጥ ወጣት ሆነው ስለሚመለሱ ንድፈ-አሳባዊ የሥነ-ጠፈር ባለሙያዎች ይማራሉ። ከአሥር ዓመታት በፊት ባዶ መላምት የነበሩት ንድፈ-አሳቦች የጨረቃን ጨረር በሚጠቀሙና አቶሚክ ሰዓቶችን ወደ ሕዋ በሚልኩ ዘመናዊ ተመራማሪዎች እየተረጋገጡ ናቸው። ሳይንስ የሰዎችን ሕልም እያሟላ ነው፤ በምናባዊ ዓለም ውስጥ ንግሥቲቱ ለአሊስ ኢን ወንደር ላንድ፥ «ወደ ኋላ ብቻ የሚሠራው ማኅደረ ትውስታ እውነትም ደካማ ነው።» ብላለች።

እግዚአብሔርና ጊዜ

አንድ ሌላ ምሳሌ እንጨምር። እኔ እንደ ደራሲ በሁለት የተለያዩ «የጊዜ ዞኖች» ውስጥ እኖራለሁ። መጀመሪያ ዕለታዊ፡- ከመኝታ የመነሣት፥ ቁርስ የመብላት፥ የመልበስና ከዚያ በኋላ ምዕራፎችን፥ ገጾችንና ቃላትን ለማቀድ ወደ ቢሮዬ የመዛወርን ዕለታዊ ተግባር የሚያጠቃልል የእውነተኛው ዓለም ዞን አለ። በዚህ መሀል የምጽፈው

መጽሐፍ ራሱ በራሱ የጊዜ ዞን ውስጥ ሌላ ሰው–ሠራሽ ዓለም ይከሰታል።

የልበ ወለድ መጽሐፍ እየጻፍሁ ብሆን ኖሮ የሚከተሉትን ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ልጠቀም እችላለሁ፤ «ስልኩ አቃጨለ። ወዲያውም ከሶፋዋ ብድግ ብላ አነሣችው።» በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የጊዜው ቅደም ተከተል ይህንን ይመስላል፤ የስልክ ጥሪ፥ ቅጽበታዊ ምላሽ። ነገር ግን ከመጽሐፉ ውጭ ባለው የደራሲው ዓለም ውስጥ በእነዚህ ሁለት ዓይነት ነገሮች መካከል የደቂቃዎች፥ የሰዓታት፥ የቀናትም እንኳ ልዩነት ሊኖር ይችላል። ምናልባትም የአንድ ቀን ሥራዬን «ስልኩ አቃጨለ» በሚል ዓረፍተ ነገር እቋጨውና ለሁለት ሳምንታት ዕረፍት ላይ ልቆይ እችላለሁ። ወደ መጽሐፉ መቼም ብመለስ፥ እዚያ ውስጥ ባለው የጊዜ ዞን መገደቤ አይቀርም። ምንም ቢሆን፥ «ስልኩ አቃጨለ። ከሁለት ሳምንታት በኋላ አነሣችው» ልል አልችልም። ሁለቱን የጊዜ ዞኖች መቀላቀሉ ግራ መጋባትን ይፈጥራል።

መጽሐፉን ከጠረዝሁት በኋላ፤ ከደራሲነቴ ጋር በተያያዘ ልዩ መንገድ ጠቅላላውን መጽሐፍ በጭንቅላቴ እይዛለሁ። «ከላይ» ሆኜ ጠቅላላውን መዋቅር በአንድ ጊዜ ልመለከት እችላለሁ፤ መነሻውን፤ መሀሉንና መደምደሚያውን አውቀዋለሁ። ብዙ ጊዜ ወስዶ ዓረፍተ ነገር በዓረፍተ ነገር በዝግታ ካላጠናው በቀር ማንም ሰው ይህንን ሊያደርግ አይችልም።

የሰውን ልጅ ታሪክ እግዚአብሔር በሚያይበት መንገድ በምናባችን ለመሣል የምንችለው ብቸኛ መሣሪያዎች በመሆናቸው ምሳሌዎችን እጠቀማለሁ። እኛ ታሪክን በተንቀሳቃሽ ፊልም ውስጥ አንዱ ሌላውን እየተከተለ እንደሚሄድ «ፍሬም» (frame) እናያለን። እግዚአብሔር ግን ጠቅላላውን ፊልም በአንድ ጊዜ ያየዋል። እጅግ ከራቀው ኮከብና እኔ ከምጸልይበት ክፍል ውስጥ ሆኖ ያየዋል። ዓረፍተ ነገር በዓረፍተ ነገር ወይም ገጽ በገጽ ሳይሆን እንደ ሙሉ መጽሐፍ ጠቅላላውን አሳብ ይመለከተዋል።

እኛ እንዲህ ዓይነቱን እይታ ልንመለከት የምንችለው በምናባችን በድንግዝግዙ ብቻ ነው። ነገር ግን መፍትሔ የሌለውና በጊዜ የታሰረውን ሕይወታችንን መረዳቱ እግዚአብሔር ለኢዮብ ጥያቄ ለምን ምላሽ እንደነፈገው ሊያስገነዝበን ይችላል። ይልቁንም እግዚአብሔር ኢዮብ ብዙም የማይረዳቸውን መሠረታዊ የአጽናፈ–ዓለም እውነታዎች ካስቀመጠ በኋላ «የቀረውን ለእኔ ተወው» በሚል ማስጠንቀቂያ ምላሽ ሰጥቶታል። እግዚአብሔር ምሥጢሩን

የማይነግረን ምናልባትም ኢዮብ፤ ወይም አልበርት አይንስታይን ወይም እኔና አንተ «የላይኛውን» እይታ ስለማንረዳለት ይሆናል።

እኛ እንደምንገነዘበው፤ ከጊዜ ውጭ ለሚኖርና አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ወደ ጊዜ ጣልቃ በሚገባ አምላክ ምን ዓይነት «ደንቦች» ከሥራ ላይ እንደሚውሉለት ልንረዳ አንችልም። እስኪ «ቅድመ ግንዛቤ» በሚለው ቃል ዙሪያ የሚሸኙትን ውዥንብሮች ተመልከት። እግዚአብሔር ኢዮብ ታማኝ ሆኖ እንደሚጸናና ውርርዱን እንደሚያሸንፍ ቀደም ብሎ ያውቅ ነበር? ይህ ከሆነ፥ ውርርዱ እውነተኛ የሚሆነው እንዴት ነው? በምድር ላይ የሚከሰቱ የተፈጥሮ አደጋዎች ጉዳይ? አስቀድሞ መከሰታቸውን የሚያውቅ ከሆነ ተወቃሹ እርሱ ነውን? በዓለማችን አንድ ሰው በመኪና ውስጥ ቦምብ መጠመዱን እያወቀ ለባለ ሥልጣናት ባያስታውቅ ለሚደርሰው አደጋ ተጠያቂ ነው። እንግዲህ እግዚአብሔር አስቀድሞ እያወቃቸው ለሚፈጸሙት አሳዛኝ ክስተቶች ተጠያቂ ነውን?

ነገር ግን ይህ እግዚአብሔር ለኢዮብ ያደረገው ኃይለኛ ንግግር ዋነኛ መልእክት ሊሆን ቢችልም፥ የእኛውን ደንብ በእግዚአብሔር ላይ ልንጭን አንችልም። ራሱ «ቅድመ-ግንዛቤ» የተሰኘውን ቃል በጊዜ ጽንሰ አሳብ ውስጥ ተቀምጦ ለ ከ ሀ ይቀጥላል የሚለውን ሰው አመለካከት ስለሚያሳይ፥ ችግሩን ያጋልጠዋል። እውነቱን ለመናገር፥ እግዚአብሔር የእኛን ተግባር አስቀድሞ «አይገነዘብም»። ይልቁንም፥ በዘላለማዊ አሁን ውስጥ ሆኖ ተግባራችንን ስናከናውን ያያል። በየትኛውም ክስተት ውስጥ የእግዚአብሔርን ሚና ለመረዳት በምንሞክርበት ጊዜ የግድ ነገሮችን «ከላይኛው» እይታ አንጻር እንመለከታለን። ይህንንም የምናደርገው የእርሱን ባሕርይ ከጊዜ ከተገደበው ደካማ የሥነ-ምግባር መመዘኛችን አኳያ በመፍረድ ነው። ምናልባትም «እግዚአብሔር ያንን አውሮፕላን ገለበጠው?» የሚለውን ዓይነት ችግር እጅግ በተለየ ብርሃን እንመለከት ይሆናል።

ቤተ ክርስቲያን ለረዥም ጊዜ በቅድመ-ግንዛቤና ቅድመ-ውሳኔ ላይ ስትሟገት መቆየቷ በጊዜ ጽንሰ-አሳብ ውስጥ ብቻ ሲገባ የምንገነዘበውን ነገር ለማወቅ መጣራችንን ያመለክታል። በሌላ አቅጣጫ፥ እንዲህ ዓይነቶቹን ጉዳዮች እጅግ በተለየ ሁኔታ እንመለከታለን። መጽሐፍ ቅዱስ በአንዳንድ ምሥጢራዊ ምንባቦቹ ውስጥ ስለ «ላይኛው» እይታ ፍንጭ ይሰጠናል። ክርስቶስ ከዓለም ፍጥረት በፊት እንደተመረጠ ይነግረናል። ይህም ከአዳምና ከውድቀት በፊት፥ ደኅንነት አስፈላጊ ባልሆነበት ወቅት መሆኑ ነው። ከዘመናት በፊት ጸጋና የዘላለም ሕይወት በክርስቶስ ኢየሱስ እንደተሰጠን ይናገራል። እንዴት አንድ ነገር ከጊዜ መፈጠር በፊት ይከሰታል?

እንዲህ ዓይነቱ አገላለጽ ከጊዜ ውጭ የሚኖረውን የእግዚአብሔርን አመለካከት ያሳያል። ጊዜን ከመፍጠሩ በፊት፥ እግዚአብሔር ገና ያልነበረችውንና የወደቀችውን ምድር ለመዋጀት ዐቀደ። ነገር ግን ወደ ጊዜ ሲገባ (እኔ እንደ ደራሲ በመጽሐፌ ውስጥ ራሴን እንደምጽፍ)፥ እግዚአብሔር በጊዜ በታሰረችው ዓለማችን ደንቦች ለመኖርና ለመሞት ተገደደ።*

ዘላለማዊ አሁን

እኛ የሰው ልጆች ጊዜ እንደማያከትም አሁን አድርገን የምንመለከትበት ገጽታ አለ። ነገሮች የሚከሰቱት በቅደም ተከተል መሆኑ እውነት ነው። ጠዋት፥ ከዚያ ከሰዓት፥ ቀጥሎም ምሽት። ነገር ግን የማሰብ ተግባራችን ሁሉ የሚፈጸመው አሁን ነው። በዛሬው ጠዋት ስለበላሁት ቁርስ ባስብ፥ በኃላፊ ጊዜ ስለሆነው ነገር በአሁን ጊዜ እያሰብሁ ነኝ ማለት ነው። በዚህ ምሽት ስለ እራት ባስብ፥ ወደፊት ስለሚሆነው አሁን እያሰብሁ ነኝ ማለት ነው። ያለሁት አሁን ብቻ ስለሆነ፥ ያለፈውንና የወደፊቱን ለማሰብ የምችለው ከአሁን እይታ አንጻር ነው።

ይኸው ግንዛቤ እግዚአብሔር ዓለምን ስለሚያይበት ዘላለማዊ አሁን መጠነኛ ግንዛቤ እንዲኖረን ያደርጋል። ይህም እግዚአብሔርን ለሚጠራጠሩ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስን የማይለዋወጥ አካሄድ ማብራሪያ ሊሰጥ ይችላል። ለእነዚህ ከእግዚአብሔር ጋር ለተቀያየሙና በአሁን ለተጠመዱት ሰዎች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሁለት መፍትሔዎችን ያቀርባል። ይኸውም ያለፈውን እንዲያስታውሱና ወደፊት የሚመጣውን እንዲያስቡ ነው። በመዝሙረ ዳዊት፥ በነቢያት፥

---

* ይህ የግንዛቤ ልዩነት የነቢያትን እጅግ አደናጋሪ ገጽታ ግልጽ ለማድረግ ሊረዳ ይችላል። የተተነበዩት ክስተቶች – ወረራዎች፥ የምድር መናወጥ፥ መጪው መሪ፥ የታደሰችው ምድር– በሚቀጥለው ቀን፥ ወይም የዛሬ ሺህ ዓመት ወይም ከሺህ ዓመታት በኋላ እንደሚፈጸሙ አይገልጹም። እንዲያውም በቅርብ እና በሩቅ የሚፈጸሙ ጉዳዮች በአንድ አንቀጽ ውስጥ ተዳብለው ይገለጻሉ። «ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች» የሚለው የኢሳይያስ የታወቀ ትንቢያ ከዚህ ምድብ የሚገባ ነው። ቀጣዮቹ ሁለት ቁጥሮች ምልክቱ በራሱ በኢሳይያስ ዘመን እንደተፈጸመ ያሳያሉ (አያሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ልጁ የኢሳይያስ ልጅ እንደሆነ ያምናሉ)፤ ነገር ግን ማቴዎስ የትንቢቱን የመጨረሻ ፍጻሜ ከድንግል ማርያም ጋር ያዛምደዋል። የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ለዚሁ የነቢያት የተለመደ አሠራር ሁለት ወይም ሦስት እጅ ፍጻሜ፥ ከፊል ለሙሉው. . .የሚሉትን ዓይነት ስያሜዎች ይሰጣሉ።

ጊዜን ሁሉ ላጠቃለለው አምላክ ቅደም ተከተል ትንሹ ጉዳይ ነው። ስለሆነም ከጊዜ ውጭ የሆነ ኑባሬ ወደ ጊዜ መግባቱ በኢሳይያስ፥ በማርያምና በእኛም ዘመን በተደጋጋሚ የሚሰማ ድምፅ መከሰቱ ያስገርመን ይሆን?

በወንጌላትና በመልእክቶች ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ በተከታታይ የቀድሞውን በማሰብ እግዚአብሔር ያደረጋቸውን ታላላቅ ነገሮች እንድናስብ ይነግረናል። እርሱ ዕብራውያንን ከግብፅ ባርነት ነፃ ያወጣ የአብርሃም፥ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ ነው። እርሱ ከፍቅር የተነሣ ልጁን ለሞት የላከና ከሞትም ያስነሣው አምላክ ነው።

አርቀን ሳንመለከት እግዚአብሔር ለእኛ እንዲያደርግ በምንፈልገው ነገር ላይ ከመጠን በላይ በማተኮር ከዚህ ቀደም ያደረጋቸውን ነገሮች ጠቃሚነት ልንዘነጋ እንችላለን።

በተመሳሳይ ሁኔታ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ወደፊት ያመለክተናል። በባቢሎን ተማርከው ለተወሰዱት አይሁዶች፥ በሮም ወይም በኢራን ወይም በደቡብ አፍሪካ ወይም በአልባኒያ ለተሰደዱት ክርስቲያኖች፥ ባጠቃላይም በየትኛውም ስፍራ የቅይጣት ቁርሾ ለሚንጣቸው ወገኖች ነቢያት ወደፊት የሚመጣውን የሰላም፥ የፍትሕና የደስታ ዘመን ያሳያሉ። እናም በዚያው የወደፊት ተስፋ ውስጥ እንድንኖር ይጠሩናል። የዘመኑ አሳዋሪዎች እይታችንን እያደበዘዙት እንዴት እግዚአብሔር አፍቃሪ፥ ቸር፥ መሐሪና ኃያል «እንደሆነ አድርገን» ልንኖር እንችላለን? ነቢያት ታሪክ የሚወሰነው ባለፈው ወይም በአሁኑ ሳይሆን ወደፊት በሚመጣው እንደሆነ ገልጸዋል።

ለፍትሕ-አልባነት ጥያቄ ሌላ አማራጭ ባለመኖሩ፥ በጊዜ ምሥጢራት ላይ እንዲህ ያለ ሰፊ ምልከታ አካሂጃለሁ። ምንም ዓይነት አመክንዮአዊነትን ብንጠቀም፥ በጊዜ ከታጠረው ሰው እይታ አንጻር እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ኢ-ፍትሐዊ መሆኑ የማይቀር ነው። ፍትሕ የሚነግሠው በዘመን መጨረሻ የእግዚአብሔርን የእይታ ደረጃ ካገኘን፥ ክፋት ሁሉ ከተቀጣ ወይም ይቅር ከተባለ፥ ሕመም ሁሉ ከተፈወሰና ጠቅላላው 'አጽናፈ ዓለም ከታደሰ በኋላ ብቻ ነው። በዚያን ጊዜ የልጅን ሞት በሚመስል «ኢ-ፍትሐዊ» ክስተት ውስጥ የክፋት፥ የውድቀትና የተፈጥሮ ሕግጋት ሚና ምን እንደነበር እንረዳለን። እስከዚያ ድረስ፥ ነገሩን አናውቅም፤ እናም ሊያውቅ በሚችለው አምላክ ላይ እንደገፋለን።

እግዚአብሔር እኛን በጨለማ ውስጥ በማስቀመጡ ስለሚደሰት ሳይሆን፥ ብዙ ብርሃን ለመያዝ የሚችል ዓቅም ስለሌለን ብዙ ነገሮች ሳናውቅ እንኖራለን። እግዚአብሔር በዓይን ቅጽበት ስለ ዓለምም ስለ ታሪክ ፍጻሜም ሁሉንም ያውቃል። ነገር ግን በጊዜ የታሰርነው እኛ የምንረዳው እጅግ በተወሰነ ደረጃ ነው፤ ጊዜው እንዲያልፍ ልናደርግ እንችላለን። ታሪክ ጉዞውን እስኪቋጭ ድረስ እንዴት «ነገር ሁሉ ለበጎ

እንደሚደረግ» አናውቅም። እምነት ማለት በተገላቢጦሹ ጣዕም የሚሰጠውን ነገር ማመን ነው።

በእንዲህ ዓይነቱ የእምነት ብያኔ ላይ ተቃውሞውን የሚገልጽ ወዳጅ አለኝ። «ለክፉው ነገር እግዚአብሔርን ሳትወቅስ፥ ለመልካሞቹ ግን ምስጋና ትሰጠዋለህ?» ሲል ይናገራል። ግልጽ በማይሆን መንገድ ወዳጄ ትክክል ነው። ይሁንና፥ አንዳንድ ጊዜ እምነት የሚጠይቀው ይህንኑ ይመስለኛል። እንደ ኢዮብ፥ ስለ እርሱ ምንም ምልክት ሳያዩ እግዚአብሔርን ማመን። እግዚአብሔርን በፍጹማዊ በጎነቱ ማመን፤ ይህም በጎነት ከጊዜ ውጭ የሚኖርና ጊዜ ገና ያልደረሰበት ነው።

> «ዘለዓለም እንደ ቀን ወይም እንደ ደቂቃ ወይም ሰከንድ ባለው መለኪያችን ሊያገኘን ይችላል። ይሁንና፥ ዘለዓለም በየትኛውም መንገድ አጭር ይሁን ረዥም ከጊዜ ርዝማኔዎች ጋር አይነጻጸርም። ስለሆነም በመጨረሻው ላይ የሚገለጸው ተስፋችን ሙሉ ለሙሉ ከጊዜ ካልሆነ (ያ ከሰብአዊነታችን ጋር ላይስማማ ስለሚችል) ከአስከፊ ሁኔታዎች፥ ከጉስቁልና ከሚጎዳበትና ከማይጎዳበት ጊዜ በየትኛውም ደረጃ ተገኝቶ ተዋረድና ለውጥ ያስከተሉብንን ሁልጊዜም የሚያሳክክ ቁስል የሚፈውስ ይሆናል፤ ይህም ደስተኞች ስንሆንም ሳንሆንም ከሞላ ጎደል በእኩል ደረጃ የሚሠራ ነው። ከጊዜ ጋር ብዙም ስላልታረቅን እንደነቅበታለን። «ከመቼው አደገ! ጊዜው እንዴት ይበራል» ስንል የልምምዳችን አጽናፈ-አቀፋዊ መልስ የተለየ ይመስል እንገረማለን። ይህም ዓሣ በውኃ ርጥብነት በተደጋጋሚ የሚደነቅበት ዓይነት መሆኑ ነው። ያ ደግሞ እንግዳ ነገር ነው፤ ዓሣው አንድ ቀን የየብስ እንስሳ ለመሆን ካልወሰነ በቀር።»
>
> – ሲ. ኤስ. ሉዊስ "Reflections on Psalms"

[1]Frederick Buechner, *Wishful Thinking*, 46.

[2]Saint Augustine, *The Confessions of Saint Augustine*, 286-287.

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፡– ኢዮብ 36–38፤ ሰቆቃወ ኤርምያስ 2፥5፤ 1ኛ ጴጥሮስ 1፤ 2ኛ ጢሞቴዎስ 1፤ ኢሳይያስ 7፥14፤ ሮሜ 8።

«መንገዱ ለተሰወረበት ሰው፥ እግዚአብሔርም
በአጥር ላጠረው ብርሃን ስለ ምን ተሰጠ?
ከእንጀራዬ በፊት ልቅሶዬ መጥቶአልና፥
ጩኸቴም እንደ ውኃ ፈስሶአል።»
ኢዮብ 3፡23-24

ምዕራፍ 26

እግዚአብሔር ዝም ይላል?

አንድ ጊዜ አንድ ወዳጄ ምሽት ላይ ከትልቅ ሐይቅ ውስጥ ገብቶ ይዋኛል። እየተዝናና በዝግታ በሚዋኝበት ጊዜ፥ የምሽት ጭጋግ ከውኃ ላይ አረፈ። ወዲያው ሁሉም ነገር ከእይታው ውጭ ሆነ፤ ምንም ዓይነት አድማስ መሬት ወይም ዕቃም ሆነ ብርሃን ከሐይቅ ዳርቻ አልታይ አለው። ጭጋጉ ብርሃኑን ሁሉ ስላወደመው፥ በመጥለቅ ላይ የምትገኘውን ፀሐይ አቅጣጫ እንኳ ሊመለከት አልቻለም።

ለሠላሳ ደቂቃዎች ከውኃው ውስጥ በስጋት ሲወራጭ ቆየ። ከአንድ አቅጣጫ ይጀምርና ድፍረት አጥቶ በዘጠና ዲግሪ ወደ ሌላ አቅጣጫ ይዞራል። ጥረቱ ለውጥ አላስገኘም። ልቡ በኃይል ሲመታ ይሰማዋል። ጉልበት ለመቆጠብ ሲል ቆም ብሎ ውኃው ላይ ሰፍፎ ይቆያል። አተነፋፈሱን ለመቀነስ ይጥራል። ከዚያም በደመ ነፍስ ትግሉን ይቀጥላል። በመጨረሻም አንድ ደከም ያለ ድምፅ ከሐይቁ ዳር ሲጠራው ሰማ። የድምፁን አቅጣጫ ተከትሎ ወደዚያው አመራ።

ኢዮብ ከፍራስራሽ ላይ ተቀምጦ የሆነውን ሁሉ ለማስታወስ በሚጥርበት ጊዜ እንደዚያ ዓይነት ፍጹም የመጥፋት ስሜት ሳይሰማው አይቀርም። ለእርሱም አቅጣጫው ሁሉ ስውር ሆኖበት ነበር። ወደየት ይጠጋ? በጭጋጉ ውስጥ ሊመራው ይችል የነበረው እግዚአብሔር ዝም ብሎ ተቀመጠ።

የውርርዱ ጠቅላላ አሳብ ኢዮብን በጨለማ ውስጥ ማስቀመጥ ነበር። እግዚአብሔር በሚያነቃቃ ንግግር፥ «ኢዮብ፥ እንደ እምነት ጀግና፥ እንደ ሰማዕት ይህችን አድርግልኝ» ብሎት ቢሆን ኖሮ ኢዮብ መከራውን በደስታ ይቀበል ነበር። ነገር ግን ሰይጣን ኢዮብ እምነት ያለ ውጫዊ እርዳታ ወይም ማብራሪያ ሊጸና ይችል እንደሆነ ጠይቋል።

እግዚአብሔር ይህንኑ አሳብ ሲቀበል፥ ጭጋጉ በኢዮብ ዙሪያ ይሰፍር ጀመር። በመሠረቱ፥ ውርርዱን የጓላ ጓላ ያሸነፈው እግዚአብሔር ነው። ምንም እንኳ ኢዮብ በመራራ ማጉረምረም ውስጥ ቢንከራተትና ሕይወትን ጠልቶ ሞትን ቢመኝም፥ በእግዚአብሔር ላይ ተስፋ ሊቆርጥ አልፈለገም፤ «ቢገድለኝ እንኳ እርሱን እጠብቃለሁ።» ኢዮብ ለማመን የሚያስችል ምክንያት ሳይኖረው አምኗል። በጭጋግ ውስጥ በእግዚአሔር አመነ።

የኢዮብን ታሪክ ስታነብ በውርርዱ ግራ ልትጋባና ከዚያም የእፎይታ አየር ልትተነፍስ ትችላለህ። እፎይ! እግዚአብሔር ለችግሩ እልባት ሰጥቷል። ነጥቡን በሚገባ ካረጋገጠ በኋላ፥ ከተከታዮቹ ጋር በግልጽ ወደሚግባባበት አሠራር ይመለሳል። የተቀረውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እስካላነበብህ ድረስ፥ እንዲህ ብለህ ልታስብ ትችላለህ። እኔ ግን ይህን ለማለት አመነታለሁ፤ ምክንያቱም ይህ ከባድ እውነት በመሆኑ ልቀበለው አልፈልግም። ነገር ግን አጽናፈ-አቀፋዊ የእምነት ሕግ በሚመስለው ነገር ውስጥ እንደ ታላቅ ምሳሌ ሆኖ ይቆማል። እግዚአብሔር የሚያከብረው እምነት ሁሉም ነገር ባከተም ጊዜ እጅግ በተሻለ ሁኔታ የሚያድግ ይመስላል። እግዚአብሔር ዝም ሲል፥ ጭጋግ ሲበረታ ያኔ እምነት ለብ ይላል።

የጭጋጉ አሸናፊዎች

ከዳርቻው ላይ የብርሃን ነጸብራቅ ብልጭ ይልና ከዚያ በኋላ ለረዥም ጊዜ ጽልመት ይነግሣል። ይህ በመጽሐፈ ኢዮብ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያየሁት ሁኔታ ነው። የታላቅ ሕዝብ አባትነቱን አንጸባራቂ ተስፋ አንግቦ ወደ መቶ ዓመት የተቃረበውን ሽማግሌ አብርሃምን አስታውስ። አንድ ልጅ ብቻ እስኪወልድ ድረስ ለሃያ አምስት ዓመታት የቆየው ራእይ እንደ ጠዋት ጤዛ ፈጥኖ የጠፋ ይመስል ነበር። እግዚአብሔር እንደገና ሲናገር፥ አብርሃምን እንደ ኢዮብ በከበደ የእምነት ፈተና አስተናገደው። «የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ሠዋልኝ» አለው፥ የአብርሃምን ልብ ሰቅዞ በሚወጋ የቃላት ቢላዋ።

ከዚያም ከእግዚአብሔር ዘንድ ህልም ያየውንና ዳሩ ግን ራሱን ከጉድጓድ ውስጥ ያገኘውን ዮሴፍን እናገኘዋለን። ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ምሪት በመከተሉ በግብፃውያን እስር ቤት ውስጥ ተጣለ። የዕብራውያን ነፃ አውጪ የነበረው ሙሴም ለአርባ ዓመታት በፈርዖን የደኅንነት ወታደሮች እየታደነ በረሃ ውስጥ ሲደበቅ ኖሯል። በእግዚአብሔር ፈቃድ ከተቀባ በኋላ ቀጣዩን የአሥር ዓመታት ጊዜ ከጦር በማምለጥና በዋሻ ውስጥ በመደበቅ የኖረው ዳዊትም ለዚህ አብነት ይሆናል።

ከረዥም ዝምታ በኋላ ግልጽ መልእክት የሚመጣበት የመለኮታዊ ምሪት የመገናኛ መስመር ኮድ በዜና መዋዕለ ካልዕ ውስጥ በግልጽ ተቀምጧል። በዚህ ክፍል መልካም ስለነበረው ንጉሥ ሕዝቅያስ እናነባለን። ይህ ሰው እግዚአብሔርን እጅግ ደስ በማሰኘቱ እግዚአብሔር የአሥራ አምስት ዓመታት ዕድሜ ጨመረለት። ቀጥሎ ምን ሆነ? «እግዚአብሔር ይፈትነውና በልቡ ያለውን ሁሉ ያውቅ ዘንድ ተወው።»

ከእነዚህ የብሉይ ኪዳን ገጸ ባሕርያት አብዛኞቹ በዕብራውያን ምዕራፍ 11 የክብር ዝርዝር ውስጥ ሰፍረዋል። ይህም ምዕራፍ አንዳንዶች «በዝና የከበረ የእምነት አዳራሽ» ብለው የሚጠሩት ነው። እኔ በበኩሌ ምዕራፉን «ከጭጋጉ የተረፉ ወገኖች ዝርዝር» ብዬ ብጠራው እመርጣለሁ። ለዚህም ምክንያቱ በዚህ ሰፍራ የተጠቀሱት ባለታሪኮች በአብዛኛው አንድ የጋራ ገጠመኝ ስላላቸው ነው፤ እንደ ኢዮብ ጭጋጉ የሚወርድበትና ሁሉንም ነገር የሚያስጨልምበትን የከፋ የፈተና ጊዜ አሳልፈዋል። የዕብራውያን መጽሐፍ በታማኝ ሰዎች ላይ የደረሱትን መከራዎች ይዘረዝራል፤ ሥቃዩ፥ ስድብ፥ ግርፋት፥ እስራት፥ በድንጋይ መወገር፥ በሰይፍ መሰንጠቅ ሁሉ ተፈጽሞባቸዋል።

ቅዱሳን ለዚህ የበቁት ነገሮች ለጊዜው እንደሚታዩት አለመሆናቸውንና የማይታየው ዓለም በዙሪያቸው ያለውን ዓለም ያህል እውነተኛና የሚታመን መሆኑን አጥብቀው ስላመኑ ነው። ዓለም የምትገለበጥ ሲመስል እንኳ እግዚአብሔር ሊታመን ይገባል። ዕብራውያን ምዕራፍ 11 ስለዘረዘራቸው ሰዎች አስደናቂ የእምነት ሕይወት «ዓለም አልተገባቸውምና» ሲል ይደመድማል፤ ከዚያም ይህንን አስገራሚ አስተያየት ያክላል፤ «ስለዚህም እግዚአብሔር አምላካቸው ተብሎ ሊጠራ አያፍርም።» ለእኔ ይኸው ዓረፍተ ነገር ዶርቲ ሰዬር ስለ እግዚአብሔር ሦስት ውርደቶች የሰጡትን አስተያየት ይገለብጠዋል። በተለይ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን የምታሳፍር ሆናለች፤ ነገር ግን የኩራት ጊዜያትንም አምጥለታለች፤ ይህንን ከዕብራውያን ምዕራፍ 11 የእምነት ጀግኖች እንመለከታለን።

የእግዚአብሔር ወዳጆች፥ በተለይም እግዚአብሔር ዝም ያለ በሚመስልበት ጊዜ ግራ መጋባታቸው የማይቀር ነው። ፖል ቶርኒዮር እንዳሉት፥ «የጥርጣሬ አጋጣሚ ከሌለ፥ የእምነትም አጋጣሚ አይኖርም።» እምነት እርግጠኛ አለመሆንንና ግራ መጋባትን ይጠይቃል። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንደሚገደው የሚያሳዩትን ብዙ ማረጋጫዎች ያቀርባል። ከእነዚህ ማረጋጫዎች አንዳንዶቹ ትንፋሽ የሚያሳጥሩ ድንቃ ድንቆች ናቸው። ነገር ግን ዋስትና የላቸውም። ዋስትና እምነትን ያገላልና።

ሁለት ዓይነት እምነቶች

ወዳጄ ሪቻርድ «እምነት» የሚለው ቃል ራሱ መሰናክል እንደሆነ ተናግሯል። ጥርጣሬ ሲገባው ክርስቲያኖች «ብቻ አመን» ይሉታል። ምን ማለታቸው ነው? ለእርሱ እምነት ማለት ጥያቄዎችን የማግለያ እንጂ ምላሽ የመስጫ መንገድ ሆኖ አልታየውም።

አንዳንድ ችግሮች የሚመጡት ቃሉን እየለጠጥን ከምንጠቀምበት መንገድ ይሆናል ባይ ነኝ። መጀመሪያ፥ አንድ ሰው የማይቻለውን የሚውጥበትን የሕፃን ልጅ ዓይነት እምነት ለመግለጽ እንጠቀምበታለን። ዳዊት ጎልያድን ለመግጠም ሲወጣ የዚህ ዓይነቱን የተጋነነ እምነት ከሥራ ላይ አውሎታል፤ (ኢየሱስ ያሞገሰው የሮም የመቶ አለቃም እንዲሁ። ኢየሱስ በሰውዬው የማያፈገፍግ እምነት «ተደንቆ» ነበር)። በዘመናችን፥ «የእምነት ሚሲዮናውያን» ከልጅ ዓይነት እምነት ስለሚወጡ አስገራሚ ተአምራት መጻሕፍት ይጽፋሉ። ይህ ቤቱን የሞሉትን ወላጅ–አልባ ሕፃናት የሚመግብ ወይም ተራራን የሚያንቀሳቅስ «የእምነት ዘር» ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም እንዲህ ዓይነት በርካታ ታሪኮች ተመዝግበዋል።

ነገር ግን ኢዮብ በዕብራውያን ምዕራፍ 11 ከተዘረዘሩት የእምነት ጀግኖች ጋር ሆኖ ሌላ ዓይነት እምነት ያመለክታል። ይህም በዚህ ከእግዚአብሔር ጋር ስለመቀያየም በሚናገረው መጽሐፍ ውስጥ ያጠነጠንሁበት ዓይነት እምነት ተአምራት በማይኖሩበት ጊዜ፥ የተሟሟቀው ጸሎት ምላሽ ሳያገኝ ሲቀር፥ ኃይለኛ ጭጋግ የእግዚአብሔርን የተንከባካቢነት ምልክት ሲንድ አብሮ ሊናድ ይችላል። እንዲህ ዓይነቶቹ ጊዜያት አንድን የላቀ ነገር ይሻሉ፤ እናም ምንም ቢሆን ምንም በእምነት የመኖሩን ገጽታ «ድናት» ብዬ እጠራዋለሁ።

እነዚህን ሁለት ዓይነት እምነቶች ከማደናገር የተነሣ ከእግዚአብሔር ጋር የተቀያየመች አንዲት ነርስ አነጋገሬ ነበር። በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ በማደግዋ የኮሌጅ ተማሪ በነበረችባቸው ጊዜያት እንኳ እግዚአብሔርን አልተጠራጠረችም ነበር። ከግድግዳዋ ላይ ኢየሱስ አንድን ሕፃን የታቀፈበት ሥዕል ተሰቅሏል፤ ይህም «ኩቴዎች» (Footprints) የተሰኘውን በአሜሪካን አገር የሚታወቅ ግጥም ለማብራራት ሲባል የተሠራ ነበር። ይኸውም ሥዕል የሕፃናትን እምነት አጉልቶ የሚያሳይ ነበር፤ በእግዚአብሔር ካመንህ ምንም ዓይነት ሥቃይ አይነካህም የሚል መልእክት ነበረው። በመከራ ጊዜ ወደኋላ ዞር ብለህ ስትመለከት፥ አንዱን የእግር ኮቴ ብቻ ታያለህ፤ ይህም አንተን ኢየሱስ ስለተሸከመህ መሆኑ ነው።

ይህች ነርስ በሃያ አራት ዓመት ዕድሜዋ ከካንሰር በሽተኞች ጋር እንድትሠራ ተመደበች። በዚያ ስፍራ ሆና ስለሠራቻቸው ጉዳዮች በማንሣት የታማሚዎቹን ጉዳይ አንድ በአንድ አጫወተችኝ። ከበሽተኞቿ አንዳንዶቹ እግዚአብሔር እንዲፈውሳቸው፥ እንዲያጽናናቸው፥ ከሥቃይ እንዲገላግላቸው ከጣሪያ በላይ እየጮኹ ይጸልዩ እንደነበር ገለጸችልኝ። ይሁንና፥ ጭካኔ የተሞላበትን ሞት ሞቱ። በእያንዳንዱ ምሽት ይህች ነርስ መፍትሔ የሌላቸውን ሥቃዮች በአእምሮዋ እያውጠነጠነች ከቤቷ ስትደርስ፥ የኮቴዎቹ ሥዕል ብሩኅ ተስፋዋን ይዞ ይጠብቃታል።

አሳቡን በትክክል ለመጨበጥ ሁለት የመዝሙረ ዳዊት ክፍሎችን ጎን ለጎን አንብብ። ከመዝሙር 23 ጀምር፤ «እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም. . . ይመራኛል. . . ክፉውን አልፈራም. . . ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል።» አሁን ደግሞ ወደ ኋላ መለስ ብለህ መዝሙር 22ን አንብብ። «አምላኬ፥ አምላኬ፥ ለምን ተውኸኝ? እኔን ከማዳንና ከጩኸቴ ቃል ሩቅ ነህ. . . በቀን ወደ አንተ እጠራለሁ፥ አልመለስህልኝም. . . አጥንቶቼ ሁሉ ተቆጠሩ፤ እነርሱም አዩኝ ተመለከቱኝም።»

መዝሙር 23 የሕፃን ዓይነት እምነት ሞዴል ሲሆን፥ መዝሙር 22 የጠለቀውንና ይበልጥ ምሥጢራዊ የሆነውን የጽናት እምነት ያሳያል። ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረን ሕይወት ሁለቱንም ሊጨምር ይችላል። ሁሉም ጸሎት በግልጽ ሁኔታ የሚመለስበት፥ እግዚአብሔር የቅርብና ተንከባካቢ የሚመስልበት ልዩ ግንኙነት ሊኖረን ይችላል። እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር ዝም የሚልበት፥ ምንም ነገር በፎርሙላ የማይሠራበትና የመጽሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃሎች ሁሉ ውሸት የሚመስሉበት «የጭጋግ ጊዜም» ያጋጥመናል። ጽናት ከዚያ የጭጋግ ክልል ውጭ እግዚአብሔር አሁንም ንጉሥ እንደሆነና ሁኔታው ምንም ቢመስልም እንዳልተወን ማመንን ያካትታል።

ለእኛ በማይገባን ሁኔታ፥ እንደ ኢዮብ ዓይነት ሁኔታዎች እምነትን «ለማዳበር» እና ከእግዚአብሔር ጋር ይበልጥ ለመቀራረብ እገዛ ሊያደርጉ ይችላሉ።* ጽናት ብዙ የጠራሁት እጅግ የጠለቀ እምነት በድንጋዮች መካከል እንደሚገኝ የሣር ዘለላ በፍጭቶች መካከል

---

* እንደ ኢትዮጵያና ቻይናን በመሳሰሉ አገሮች የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት የጎበኙ የአሜሪካ ክርስቲያኖች ይህንኑ እውነት ሊገነዘቡ ይችላሉ።

ያቆጠቁጣል። የሰው ልጆች የሚያድጉት በመጣርና በመሥራት ነው። በዚህ መልኩ የሰው ልጅ ተፈጥሮ ከመፍትሔዎች ይልቅ ችግሮችን ይሻል። ጸሎቶች ሁሉ ወዲያው በምትሐታዊ ሁኔታ የማይመለሱት ለምንድን ነው? እያንዳንዱ አማኝ ተመሳሳይ የመንፈሳዊ ዲስፕሊን አሰልቺ ፈለግ የሚከተለው ለምንድን ነው? ምክንያቱም የማያቋርጥ ጸሎት፥ ጾምና የቃል ጥናት ብሎም ማሰላሰል በቀዳሚነት የተወጠኑት ለእኛው እንጂ ለእግዚአብሔር ተብለው አይደለም።

ኪርክጋርድ ክርስቲያኖች ጥያቄዎቹን ራሳቸው እንደ መሥራት ከመጽሐፍ ጀርባ የተሰጠውን መልስ እንደሚመለከቱ ተማሪዎች መሆናቸውን ተናግሯል። እኔ እንዲህ ዓይነት ዝንባሌ ያለኝ ሲሆን፥ ይህም የእኔ ችግር ብቻ መሆኑን እጠራጠራለሁ። በአመዛኙ አቋራጭ መንገድ እንሻለን። ነገር ግን አቋራጭ መንገዶች ብዙውን ጊዜ ከዕድገት ይመልሱናል እንጂ ወደዚያ አይመሩንም። እስኪ ይህንን አሳብ በቀጥታ ከኢዮብ ጋር እናዛምደው፤ እርሱ የተጓዘበት ፈተና የመጨረሻ ውጤት ምን ነበር? ራባይ አብርሃም ሄስል እንዳሉት፥ «እንደ ኢዮብ ዓይነት እምነት ሊናወጥ አይችልም፤ የመናወጥ ውጤት ነውና።»

ስለ ጸሎት በጻፉት ወግ ውስጥ ሲ. ኤስ. ሉዊስ ወላጆች ሕፃን ልጆቻቸውን እንደሚንከባከቡ ሁሉ እግዚአብሔር አዳዲስ ክርስቲያኖችን በልዩ ፍቅር እንደሚያስተናግዳቸው ገልጸዋል።[1] እኝህ ሰው የቆየ ክርስቲያን የተናገረውን እንዲህ ሲሉ ጠቅሰዋል፤ «ለጸሎት በርካታ አስገራሚ መልሶችን ያገኘሁ ሲሆን፥ ከአንድ ጊዜ በላይ ተአምራዊ ያልኋቸው ሁኔታዎች አጋጥመውኛል። ነገር ግን እነዚህ ሁኔታዎች የሚከሰቱት ከዳግም ልደት በፊት ወይም ከዳግም ልደት በኋላ ባሉት አጭር ጊዜያት ነው። የክርስትናው ሕይወት እየፈካ ሲሄድ፥ እየቀነሱ ይሄዳሉ። የጸሎት መልሶች ንፍገት በተደጋጋሚ መከሰቱ ብቻ ሳይሆን እያደለ ይሄዳል።»[1]

መጀመሪያ ስንመለከተው፥ እንዲህ ዓይነቱ አሳብ ትክክል ላይመስለን ይችላል። ክርስቲያን እያደገ ሲሄድ እምነት እየቀለለ አይሄድም? ሉዊስ እንደገለጹት፥ አዲስ ኪዳን ምላሽ ስላልተሰጣቸው ጸሎቶች ሁለት ጠንካራ ምሳሌዎች ያቀርባሉ፤

ኢየሱስ «ጽዋው» ከእርሱ እንዲወሰድ ሦስት ጊዜ የጸለየ ሲሆን ጳውሎስም «የሥጋው መውጊያ» እንዲነሣ ሦስት ጊዜያት ለምኗል።

ሉዊስ፥ «እግዚአብሔር እርሱን ለሚያገለግሉት ከሁሉም የተሻለውን ብቻ ያደርግላቸዋል? ከሁሉም በላቀ ሁኔታ ያገለገለው ክርስቶስ የሥቃይ ሞቱ ሲቃረብ፥ «ለምን ተውኸኝ» ብሏል።

እግዚአብሔር ሰው በሆነ ጊዜ፥ ያ ሰው እጅግ በቸገረው ጊዜ ከእግዚአብሔር የቀረበለት ርዳታ እጅግ ትንሽ ነበር። ዓቅም ቢኖረኝ እንኳ ድፍረት የማላገኝለት ምሥጢር እዚህ ጋ አለ። በእዚህ መሀል፥ እንደ እኔና አንተ ያሉ ትናንሽ ሰዎች ከየትኛውም ተስፋና አጋጣሚ ባሻገር አንዳንድ ጊዜ ጸሎታችን ምላሽ ቢያገኝ፥ ለራሳችን ጥቅም የውክቢያ ድምዳሜዎችን ልናበጅ አይገባም። ብርቱዎች ብንሆን ኖሮ የሚቀርብልን የፍቅር መስተንግዶ ያንስ ነበር። ጀግኖች ብንሆን ኖሮ፥ ያለ ምንም ርዳታ ወደ ታላቅ ጦርነት እንላክ ነበር።

የሌለ ጥያቄ

የሲ. ኤስ. ሉዊስ ቃላት የሚያስደምም ድምፅ ያስተጋባሉ። ይሁንና፥ እምነት በፈተና የሚጠነክርበትን የጽናት አሠራር በአንድ ጥሩ ፎርሙላ ላስቀምጠው አልችልም። ይህ መጽሐፍ የተነሣው እምነቱ እስከተፈተነበት ጊዜ ድረስ በአስተማማኝ ሁኔታ ላይ ከነበረው የሪቻርድ ታሪክ ነበር። ፈተናው ሲደርስ እግዚአብሔር እንደከዳው አሰበ። እግዚአብሔር እርሱን ወይም ደግሞ ማንኛውንም የሚወደውን ሰው የሚፈትነው ለምንድን ነው? ሪቻርድ እንዲህ ባለው አምላክ ላይ እምነቱን ጥሎ ሊቀጥል አልቻለም። ጠንካራው የሕፃንነት እምነታቸው በፈተና ጊዜ የከዳቸውን ብዙ ሰዎች አነጋግሬያለሁ።

ከመጽሐፈ ኢዮብ ውስጥ ችላ የማይሉት ጥያቄ አድፍጧል። የፍቅር «ፈተና» ለመስጠት ብሎ አንድ ሰው ሚስቱን ኢዮብ ለተጋፈጠው አደጋ ቢዳርግ፥ እንደታመመ በመቁጠር እናስረዋለን። አንዲት እናት ከባሕሩ ዳርቻ ውስጥ ከሚገኘው ጭጋግ ድምፅዋን አሰምታ አቅጣጫ ባለመጠቆም ከልጆቿ ራሷን ብትደብቅ፥ ለእናትነት የማትበቃ ሴት እንደሆነች እንናገራለን። እንግዲህ እንዲህ ዓይነቱን መለኮታዊ ውርርድ የምንረዳው እንዴት ነው?

ሁለት ምልከታዎችን ከማቅረብ በቀር የምሰጠው ንጹሕ ፎርሙላ የለኝም።

1. *እምነታችን ለእግዚአብሔር ምን ትርጉም እንዳለው ብዙም የምናውቀው ነገር የለም።* በሆነ ምሥጢራዊ መንገድ፥ የኢዮብ አስከፊ ሁኔታ የሰው ልጆች ሁሉ ልምምድ እምብርት ለመሆን በመቻሉ ለእግዚአብሔር «ጠቃሚ» ሆኗል። ከኢዮብ እምነት ባሻገር፥ ከፍጥረት ሁሉ በስተጀርባ ውስጣዊ ዓላማ ከአደጋ ላይ ወድቆ ነበር። እግዚአብሔር ለነፃ የሰው ልጆች ክፍተት የመልቀቅ «አደጋ» ከወሰደበት ጊዜ አንሥቶ፥ ያለ ጉቦ በነፃ የሚቀርብ እውነተኛ እምነት ለእግዚአብሔር እኛ እስከዚህም የማንረዳው ከፍተኛ እሴት ሲያበረክት

እንመለከታለን። ለእግዚአብሔር በእምነት ከመጽናት የበለጠ ፍቅራችንን የምንገልጽበት መንገድ የለም።

እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ፍቅሩን እንደሚፈልግ እየተናገሩ እግዚአብሔር ራሱ ለዚያ ፍቅር ያለን ናፍቆት እንዴት እንደገለጸ መዘንጋቱ ስሕተት ነው፤ ይህም ከዓመፀኛ ልጆች ምላሽ፥ ማንኛውንም ምላሽ እንደሚሻ አባት፤ ከምክንያቶቹ ሁሉ በላይ እምነትን ላጎደለችው ፍቅረኛው አንድ ተጨማሪ ዕድል እንደሚሰጥ የተበደለ አፍቃሪ መሆኑ ግልጽ ነው። እነዚህ እግዚአብሔር በነቢያት ዘመን ሁሉ ደጋግሞ የተጠቀመባቸው ምሳሌዎች ናቸው። እንደ ወላጆች፥ እንደ አፍቃሪዎች በምድር ላይ የሚሰሙን ጥልቅ ስሜቶች እግዚአብሔር ለእኛ የሚሰማው የረሃብ ፍላጎት ነጸብራቆች ብቻ ናቸው። ይህም ፍላጎት እግዚአብሔር ትስእብትንና ስቅለትን እንዲጋፈጥ አድርጎታል።

የሰው ልጆች ማንጻጸሪያዎች ሁሉ እነዚህን ጉዳዮች ማካተት ይሳናቸዋል፤ የሚሳናቸው ግን ማሳነሱ እንጂ ማጋነኑ አይደለም። ኢየሱስ እንደተናገረው፥ በታሪክ መጨረሻ ላይ (ጭጋጉ ለበጎነት ስፍራ ሲለቅ) አሳሳቢው ጥያቄ አንድ ብቻ ይሆናል፤ «የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ በምድር ላይ እምነት ያገኛ ይሆንን?» ሐዋርያው ጳውሎስ ከዘፍጥረት እስከ ኢየሱስ ዘመን የነበረውን የዓለም ሁኔታ ከነደፈ በኋላ፥ እንዲህ ሲል ደምድሟል። «ምናልባትም እየመረመሩ ያገኙት እንደሆነ እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ የሰውን ወገኖች ሁሉ ከአንድ ፈጠረ። ቢሆንም ከእያንዳንዳችን የራቀ አይደለም።» ልጁን መላኩ እግዚአብሔር የከፈለው ዋጋ ነው፤ እንደ ኢዮብ፥ ወይም አንተ ወይም እንደ እኔ ካሉት ሰዎች የሚሰጠው የታማኝነት ምላሽ «ሽልማቱን» ይወክላል።

ውስን እይታ ላለን የሰው ልጆች ከኢዮብ መከራ የተገኘውን «ሽልማት» መገንዘቡ ከባድ እንደሆነ አረዳለሁ። ሲ. ኤስ. ሉዊስ እግዚአብሔር እኛን «ወደ ታላቅ ጦርነት» ስለመላኩ እስከ መግለጽ ሊደርሱ ይችላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ፥ በማይታዩ የመልካምና ክፉ ኃይላት መካከል በሚካሄደው ጦርነት ውስጥ የሰው ልጆች እንደ ዋነኛ የእግረኛ ጦር እንደሚያገለግሉ ይናገራል። በዚህ ውስጥ ዋነኛው መሣሪያችን እምነት ነው። ምናልባትም እግዚአብሔር ወደ አደገኛ የጦርነት ቀጠናዎች የሚልከን ልጁን ወደ ጦር ሜዳ የሚሰድ ማንኛውም ወላጅ ከሚጋፈጠው ዓይነት የኩራት፥ የፍቅር፥ የሥቃይና የጸጸት ስሜት ጋር ሊሆን ይችላል።

የኢዮብ መከራ ለእግዚአብሔር «ጠቅሞታል?» ይህንን ሊመልስ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። መለኮታዊ ሉዓላዊነት ማለት ቢያንስ ይኸው እንደሆነ ወደ መደምደሙ ደርሻለሁ፤ ለእግዚአብሔር

የሚጠቅመው የትኛው እንደሆነ ሊወስን የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። «ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው» ብሏል። ኢየሱስ ዞር ባለ መንገድ የቶማስን ጥርጣሬ በመገሠጽ። ኢዮብ የሕይወትን እጅግ የጨለመ ገጽታ ተመልክቷል፤ የእግዚአብሔርን የጠለቀ ዝምታ ሰምቷል፤ ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ከማመን አልተመለሰም።

2. *እግዚአብሔር ራሱን ከተመሳሳይ የእምነት መመዘኛ ነፃ አላደረገም።* የኢዮብ መከራዎች በኢየሱስ ሕይወት ከተሰሙት የገደል ማሚቶ ማስተጋባት ተለይተው አይችሉም። ኢየሱስ ተፈትኗል። ወዳጆቹንና ጤንነቱን ጨምሮ ሁሉንም ነገር አጥቷል። እንደ ዕብራውያን ጸሐፊ አገላለጽ፥ «ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ።» በመጨረሻም፥ ሕይወቱን አጥቷል።

በመስቀሉ ላይ የተፈጸመውን ነገር ሙሉ ባንረዳም፥ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ ባልታገሠው ፈተና ውስጥ የፈጠራቸውን ሰዎች ለማሳለፍ እንደማይፈቅድ እንመለከታለን። በዓመታት በሥቃይ ውስጥ ከሚገኙ በርካታ ሰዎች ጋር የተነጋገርሁ ስሆን፥ ይህ ሐቅ ለእነርሱ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ መግለጽ ያስቸግረኛል። እንደ ጆኒ ኤሪክሰን ታዳ ካሉት ዝነኞች፥ በገጠር ሆስፒታል ውስጥ ከሚኖሩ፥ የሲያልን ያህል በከፋ የሥ ስተኛው ዓለም እስር ቤቶች ከሚኖሩ ሰዎች የሚከተለውን ዓይነት አሳብ አግኝቻለሁ፤ «ቢያንስ ከኢየሱስ የተነሣ፥ እግዚአብሔር ስሜቴን ይረዳዋል።»

አሁንም የሪቻርድ አሳብ ይታወሰኛል። «ለማለት የምችለው ነገር ቢኖር ኢዮብ እግዚአብሔርን ለማስደሰት አንድ የከፋ ዋጋ እንደከፈለ ነው።» ይህንን ያለው ከዓመድ ላይ ተቀምጦ ቁስሎቹን ስለሚፈገፍገው ኢዮብ እያሰበ ነበር። ነገር ግን ሪቻርድ እነዚህን ቃላት በሚናገርበት ጊዜ ከመስቀሉ ላይ ተንጠልጥሎ ቁስሎቹን ለመንካት ስላልቻለው ኢየሱስ እያሰብሁ ነበር። ኢዮብ የከፋ ዋጋ እንደከፈለ ለመስማማት እገደዳለሁ። በአንድ በኩል፥ እግዚአብሔር ከኢዮብ ላይ በተደረገው ውርርድ የራሱን እጆች አስሯል። እጅግ ቀጥተኛ በሆነው ሁኔታ፥ በስቅለቱ ማታ የራሱ እጆች እንዲታሰሩ ፈቅዶአል። (ኢየሱስ ስለ ስቅለቱ ሲናገር፥ «አሁን ነፍሴ ታውካለች፥ ምንስ እላለሁ? አባት ሆይ፥ ከዚህ ሰዓት አድነኝ። ነገር ግን ስለዚህ ወደዚህ ሰዓት መጣሁ» «አባት ሆይ፥ ስምህን አክብረው» ብሏል።)

መጽሐፍ ቅዱስን በማጠናበት ጊዜ፥ የጸሐፊዎቹ አመለካከት በቀጥታ ወደ መስቀሉ የመቀልበሱ ሁኔታ አስገርሞኛል። የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ስለ ከባባድ ጊዜ ሲናገሩ፥ የኢዮብ፥ የነቢያትና የመዝሙራት

መለያ የነበረውን ቃተታ አይገልጹም። ስለ መከራው ምንም ዓይነት ግልጽ ማብራሪያ አያቀርቡም፤ ይልቁንም ሁለቱን ክስተቶች ማለትም የኢየሱስን ሞትና ትንሣኤ ደጋግመው ይጠቅሳሉ። ጸሐፊዎቹ እነዚህ ክስተቶች የሆነ ሥዕላዊ ማብራሪያ እንደሚያቀርቡ ያሰቡ ይመስላል።

ሐዋርያት በነፃ የገለጹት እምነት ሙሉ ለሙሉ በፋሲካ እሑድ አርፎአል። ይህም እግዚአብሔር በታሪክ ሁሉ እጅግ አሳዛኝ የሆነውን የልጁን ሞት አሁን ስቅለት ብለን ወደምናከብርበት ዕለት የተለወጠበት ነበር። ከጥላ ውስጥ ሆነው መስቀሉን የተመለከቱት እነዚያ ደቀ መዛሙርት ከመሪያቸው ጋር ለሦስት ዓመታት ቆይተው ሳይማሩ የቀሩትን ነገር ወዲያውኑ አስተውለዋል፤ ይኸውም እግዚአብሔር የሌለ በሚመስልበት ጊዜ ከሁሉም በላይ የቀረበ ሊሆን እንደሚችል ነው። እግዚአብሔር ሙት ሲመሰል፥ ምናልባትም ወደ ሕይወት እየመጣ ይሆናል።

የሦስቱ ቀናት ምሳሌ– ኀዘን፥ ጨለማ፥ ድል–ለአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ለሁሉም ፈተናችን የሚሠራ ሞዴል ሆኖ አገልግሏል። ምንም እንኳ «ለምን?» ለተሰኙት ጥያቄዎቻችን ማብራሪያ ባናገኝላቸውም የእግዚአብሔር ፍቅር ማረጋገጫው ወደሆነው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ልንመለከት እንችላለን። ስቅለት እግዚአብሔር ለሥቃያችን እንዳልተወን ያሳያል። ሕይወታችንን የሚጎዱ ክፋቶችና ሥቃዮች ለእግዚአብሔር እውነተኞችና ዋጋ ያላቸው በመሆናቸው፥ እርሱ ራሱ ሊካፈላቸውና ሊታገሣቸው ፈቅዶአል። እርሱም በእግዚአብሔር ዝም ተብሏል፤ ከመስቀሉ ላይ ሆኖ የጠቀሰው፥ መዝሙር 22ን እንጂ መዝሙር 23ን አልነበረም።

የትንሣኤ እሑድ እንደሚያሳየው፥ በመጨረሻው ድሉ የመከራ አይሆንም። ስለሆነም ያዕቆብ፥ «ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት» ብሏል። ጴጥሮስም በበኩሉ፥ «በዚህም እጅግ ደስ ይላችኋል. . . አሁን ለጥቂት ጊዜ ቢያስፈልግ በልዩ ልዩ ፈተና አዝናችኋል» ብሏል። ጳውሎስ፥ «በመከራችን ደግሞ እንደሰታለን» ሲል ጽፎአል። ሐዋርያቱ ከእንዲህ ዓይነት «የተቤዠ መከራ» ምን በጎ ነገር ሊወጣ እንደሚችል ገልጸዋል፤ እነዚህም ብስለት፥ ጥበብ፥ ፍቱን እምነት፥ ጽናት፥ በጎነትና ሌሎችም ሽልማቶች ተካተዋል።

ደስታ ለምን? ይህ ከመከራው ውስጥ በሚፈልቅ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር በትንሣኤ እሑድ በሰፊው ያደረገውን ለእያንዳንዳችን በመጠኑ ሊያደርግልን ስለሚችል ነው። ያዕቆብ፥ ጴጥሮስና ጳውሎስ የጠቀሱዋቸው መከራዎች በብሉይ ኪዳን ከፍተኛ የእምነት ክስረት ሊያስከትሉ ይችሉ ነበር። ነገር ግን የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ጳውሎስ

እንዳለው «ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን» የሚል እምነት ነበራቸው።

ይህ በጣም የታወቀ ጥቅስ በተዛባ መልክ ይተረጎማል። አንዳንድ ሰዎች «እግዚአብሔርን ለሚወዱት መልካም ነገሮች ብቻ ይፈጸማሉ» ብለው ይተረጉማሉ። ጳውሎስ ለማለት የፈለገው ምን ዓይነት ነገሮችን ልንጠብቅ እንደሚገባን ይዘረዝራል፤ እነዚህም መከራ፥ ስደት፥ ጭንቀት፥ ራብ፥ ራቁትነት፥ ፍርሃት፥ ሰይፍ የመሳሰሉትን የሚያካትት ነው። ጳውሎስ እነዚህን ሁሉ ታግሦ አል። ይሁንና፥ «በዚህ ሁሉ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን» ሲል ይናገራል፤ የትኛውም ዓይነት መከራ ከእግዚአብሔር ፍቅር አይለየንም።

ጳውሎስ ነገሩ የጊዜ ጉዳይ እንደሆነ ይናገራል። ትንሽ ጠብቁ፤ በዝምታ የተዋጠውን ጥቁር ዓርብ ወደ ትንሣኤው እሑድ የለወጠው የእግዚአብሔር ተአምር አንድ ቀን አጽናፈ-ዓለሙን ሁሉ ያጥለቀልቃል።

«በደመናት ፊትህን ብትጋርድም፥
እነዚያን ዓይኖች አውቃለሁ፥
ምንም እንኳ አንዳንድ ጊዜ ዘወር ቢሉም፥
ዓይኖችህ ከቶውንም ሰው አይንቁም።»

–ጆን ዶን፥ “A Hymn to Christ”

«አስቸጋሪው ነገር ሁሉ ሰለ ሕይወት ካለን ንድፈ-አሳብ የላቀን ጉዳይ ያመለክታል።»

– ጆርጅ ማክዶናልድ

[1]C.S. Lewis, *The World's Last Night,* 10.

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፦ ኢዮብ 13፤ ዘፍጥረት 22፤ 2ኛ ዜና 32፤ ማቴዎስ 8፤ ማርቆስ 14፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 12፤ ሉቃስ 18፤ የሐዋርያት ሥራ 17፤ ዮሐንስ 20፤ ዕብራውያን 5፤ ዮሐንስ 12፤ ኢሳይያስ 53፤ ያዕቆብ 1፤ 1ኛ ጴጥሮስ 1፤ ፊልጵስዩስ 3፤ ሮሜ 8።

«እነሆ፥ ወደፊት እሄዳለሁ፥ እርሱም የለም፤
ወደ ኋላም እሄዳለሁ፥ እኔም አላስተውለውም፤
ወደሚሠራበት ወደ ግራ ብሄድ አልመለከተውም፤
በቀኜም ይሰወራል፥ አላየውምም።» (ኢዮብ 23፡8-9)

ምዕራፍ 27

እግዚአብሔር ለምን ጣልቃ አይገባም?

ባለፉት ጥቂት ምዕራፎች ውስጥ ስለቀረቡት አሳቦች ወዳጄ ሪቻርድ ምን እንደሚያስብ አውቃለሁ። እንዲያውም፥ ከእርሱ ጋር ሰፊ ውይይት ስላደረግን ምን እንደሚያስብም ሳይቀር አውቃለሁ። እንደምታስታውሰው ሪቻርድ በመጽሐፈ ኢዮብ ላይ መጽሐፍ ስለጻፈ ታሪኩን ለእርሱ መከለስ አላስፈለገኝም። ይልቁንም፥ እግዚአብሔር ለምን ለኢዮብ ምላሽ እንዳልሰጠ በመገመት ከታሪኩ ፍጻሜ ላይ አተኮርሁ። ስለ እእግዚአብሔር አመለካከት ለመረዳት ባለመቻሉና እምነት ለእግዚአብሔር ምን ያህል ዋጋ እንዳለው እገልጽለት ጀመር።

ሪቻርድ በጥንቃቄ አዳመጠኝና አሳቤን ሳጠቃልል፥ ራሱን በመነቅነቅ አዎንታዊ ምላሽ ሰጠኝ። «ያ መልካም ነው፥ ፊሊፕ። ትክክልም ልትሆን ትችላለህ። አንተ በምትለው አሳብ ላይ ችግር የለብኝም። ነገር ግን በእኔና በኢዮብ ታሪክ ውስጥ አንድ ትልቅ ልዩነት አለ። ለመከራዎቹ ሁሉ፥ ኢዮብ በመጨረሻው ከእግዚአብሔር ዘንድ ማብራሪያ ተሰጥቶታል። ከነፋሱ ውስጥ እውነተኛውን ድምፅ የሰማ ይመስላል። ለእኔ ግን እግዚአብሔር በዝምታው ገፍቶአል። ለዚህም ይመስለኛል ኢዮብ ለማመን ሲመርጥ፥ እኔ ላለማመን የመረጥሁት።»

ውይይታችን እየገፋ ሲሄድ፥ ሪቻርድ የሁለት ዓለማትን አሳብ እንደማይቀበል ግልጽ ሆነልኝ። ዛፎች፥ ሕንጻዎች፥ መኪኖችና ሰዎች በሚገኙበት ዓለም ውስጥ እየኖረ ሌላ የማይታይ ዓለም በመኖሩ አሳብ ሊስማማ አልቻለም። «ማረጋገጫ እፈልጋለሁ። ወደ እኔ ዓለም ካልገባ የእግዚአብሔርንስ መኖር እንዴት አውቃለሁ» ሲል ጥርጣሬውን ገለጸ።

ውይይቱ እኔም እራሴ ተጠራጣሪ ወደነበርሁበት ዘመን ወሰደኝ። ሪቻርድ በሚያስገርም ሁኔታ እግዚአብሔርን በቅርበት ስለማውቅ በሚናገሩ አማኞች ተከብቦ በሚገኝበት ክርስቲያናዊ ኮሌጅ ውስጥ

እምነቱን አጥቷል። እኔም ብሆን ይህንኑ በሚመስል የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ውስጥ ነበር እምነት እጅግ አስቸጋሪ ሆኖ ያገኘሁት።

የተጠራጣሪው አመለካከት

እኔም የሪቻርድን ዓይነት የማሰናከያ ዓለት ተጋርጦብኝ ነበር። በኮሌጅ ግቢ ውስጥ አማኞች «መንፈሳዊ» የሚሏቸው ነገሮች ለእኔ ፍጹም ተራ ሆኑብኝ። የማይታየው ዓለም ከሚታየው ጋር የሚገናኝ ከሆነ፥ የልዕለ–ተፈጥሮአዊው ህልውና ምልክቶች ምን ሊሆኑ ኖሯል።

ጸሎትን ለአብነት ውሰድ፤ ሁሉም ነገር የጸሎት መልስ እንዲመስል ክርስቲያኖች የክስተቶችን መልክ የሚያዛቡ ይመስላል። አጎታቸው ለትምህርት ቤት ክፍያ ሃምሳ ዶላር ቢልኩላቸው፥ በደስታ ተፍለቅልቀው የምስጋና ፕሮግራም ያዘጋጃሉ። እግዚአብሔር ከሰማይ ሆኖ እንደሚሰማቸው ለማረጋገጥ እነዚህን «የጸሎት መልሶች» ይቀበላሉ። እኔ ግን ሁልጊዜም ሌላ ማብራሪያ አገኝ ነበር። ምናልባትም የዘመዳቸው ገንዘብ መላክና ጸሎቱ እንዲሁ የግጥምጥሞሽ ጉዳይ ሊሆን ይችላል። እኔ ምንም ሳልጸልይ አልፎ አልፎ ስጦታዎችን የሚልክልኝ አጎት ነበረኝ። ምላሽ ሳያገኙ የሚቀሩ የእነዚህ ተማሪዎች ሌሎች ጉዳዮችስ? እናም ጸሎት ለግድግዳዎች ከመናገር ያላለፈና አንዳንድ ጊዜ ራስን የማርኪያ ትንቢት መስሎ ተሰማኝ።

እንደ ሙከራ፥ በግቢው ውስጥ «መንፈሳዊ» ባሕርያትን እኮርጅ ጀመር። በጸሎት ስብሰባዎች ላይ ተግቼ እጸልይ፥ ስለ መለወጤ የውሸት ምስክርነቶች እሰጥና መንፈሳዊ ቃላት እጠቀም ጀመር። ይህ ደግሞ ጥርጣሬን አጠናከረልኝ። የታዘዘውን ፎርሙላ በመጠቀም ተጠራጣሪ የነበርሁት ሰው ፍጹም ቅዱስ ሆኜ ተገኘሁ። አብዛኛው በሚጠራጠር ሰው ሊከናወን ከቻለ ክርስቲያናዊ ልምምድ እውነት ሊሆን ይችላል?

ይህንን ሙከራ ያደረግሁት የሃይማኖትን ሥነ–ልቦና ስላነበብሁ ነበር። እንደ ዊሊያም ጀምስ ዓይነት ደራሲያን የጻፉዋቸው መጻሕፍት (ለምሳሌ ያህል "The Varieties of Religious Experience") ሃይማኖት ለሕይወት ውጥረቶች ውስብስብ ሥነ–ልቦናዊ ምላሽ እንደሆነ አድርጌ እንድወስድ ገፋፍተውኝ ነበር። ሚስተር ጀምስ እውነተኛው ክርስቲያን ከአዲስ መዋቅር የተሠራ አዲስ ፍጥረት እንደሆነ ገልጸዋል። እኚህ ሰው፥ «የተለወጡት ሰዎች እንደ ምድብ ከተፈጥሮአዊ ሰዎች አይለያዩም፥ እንዲያውም አንዳንድ ዶክትሪናዊ ሥነ–መለኮት የማያውቅ ማንም ሰው የሁለቱን ቡድኖች የዕለት ተዕለት «አደጋዎቹን» በመቆጣጠር ባሕርያቸው መለኮታዊው ከሰብአዊው የሚለይበትን ያህል ለውጥ እንደሚያሳዩ ሊያስረዳ

አይችልም፤ ሲሉ ደምድመዋል። ራሴም ከዙሪያዬ በነበሩት አማኞች ሕይወት አንጸባራቂ ለውጥ ለማየት አልቻልሁም ነበር።

ወደ በኋላ ከምጠቃቅሳቸው ምክንያቶች የተነሣ በተጠራጣሪነቱ አልገፋሁም። ነገር ግን አሁን እንኳ ከሁለት አሥርተ ዓመታት የበለጸገና ጠቃሚ እምነት በኋላ ለሪቻርድ ዓይነቱ ጥርጣሬ ብርቱ ጉልበት እንደሌለኝ እቀበላለሁ። መንፈሳዊ ልምምድ የራስን አሳብ የመመርመሩን ጉዳይ በቀላሉ አይቀበለውም፤ ኃይለኛ ብርሃን ከበራበት ይተናል። ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ያደረግሁባቸውን ጊዜያት ብመረምር፥ ለተፈጸመው ነገር ይበልጥ ተፈጥሮአዊ ማብራሪያ ለማግኘት እችላለሁ። በተፈጥሮአዊውና በመንፈሳዊው ዓለም መካከል የከረረ ልዩነት አይገኝም፤ ሁለቱን የሚለይ ገደል አልተሠራም።

በምጸልይበት ጊዜ «ተፈጥሮአዊ» ሰው መሆኔ አያበቃም፤ እንቅልፍ ይጫጫነኛል፤ አእምሮዬ ይባዝናል፤ ከእግዚአብሔር ጋር እየተነጋገርሁ እያለሁ ከሌሎች ሰው ጋር በምነጋገርበት ጊዜ እንደሚሆነው ስጋቶችና አለመግባባቶች ይከሰታሉ። «በመንፈሳዊ» ጉዳዮች ላይ በምጽፍበት ጊዜ፥ በመለኮታዊ ኃይላት ወደ ሰማይ አላሻቅብም፤ እርሳሶች መቅረጽ፥ ቃላትን መሰረዝ፥ መዝገበ ቃላት ማገላበጥ፥ ጥሩ ያልሆኑትን በርካታ አጀማመሮች ቀዶ መጣል ግዴታዬ ይሆናል። «የእግዚአብሔርን ፈቃድ የማወቅ» አጋጣሚዎች በሕይወቴ በሙሴ ወይም በጌዴዎን ሕይወት ውስጥ እንደማያቸው ምሳሌዎች ቀጥተኞች ሆነው አያውቁም። ከነፍስ ውስጥ የሚያስገመግም ድምፅ ሰምቼ አላውቅም። ብፈልግ አሁን ሪቻርድ ያደረገውን ላደርግ እችል ነበር። ይኸውም መንፈሳዊ ባሕርይን ከአንዳንድ ሥነ-ልቦናዊ ንድፈ -አሳቦች ጋር አጣምሮ ማብራራት መሆኑ ነው።

እንግዲህ በማይታየው ዓለም የማምነው ለምንድን ነው? በዚህ ውስጥ የሲ. ኤስ. ሉዊስ ጽሑፎች ከፍተኛ እገዛ አበርክተውልኛል። በብዙዎች የሲ. ኤስ. ሉዊስ መጻሕፍት ውስጥ የሁለቱ ዓለማት ጭብጥ እንደ ክር ይያያዛል። ይህም "Transposition"[2] በሚል ርእስ አንድ ወጥ የወግ ንድፈ-አሳብ ሆኖ ከመውጣቱ በፊት ለወዳጆቻቸው በጻፉዋቸው ደብዳቤዎችና የልብ ወለድ መጽሐፎቻቸው ውስጥ የተገለጸ አሳብ ነው። ሉዊስ ችግሩ «ተፈጥሯዊና መንፈሳዊ በተባሉት ነገሮች መካከል የሚገኝ ግልጽ ቀጣይነት» እንደሆነ ገልጸዋል። «ይህም የተፈጥሮአዊ ሕይወታችን መሠረት የሆኑት አሮጌ ነገሮች ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ሕይወት ዳግም መገለጽ ነው። «በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የምንመለከተው አሳብ በአብዛኛው ከዚሁ ላይ የሚሰነዘር ነው።

ከጨረሩ አቅጣጫ መመልከት

ሉዊስ የወግ ጽሑፋቸውን የጀመሩት አስገራሚውን በልሳን የመናገር ክስተት በመጥቀስ ነበር። መንፈስ ቅዱስ በዕለተ በዓለ ኀምሳ የመውረዱ ሊካድ የማይችል ክስተት በሰዎች ሌላ ቋንቋ የመናገር ሁኔታ ራሱን መግለጹ ምንኛ እንግዳ ነገር ነው? በወቅቱ ከስፍራው ሆነው ሁኔታውን ለሚመለከቱ ሰዎች የሰካራሞች ትዕይንት ይመስል ነበር። ዛሬ ለብዙ «ሳይንሳዊ» አጥኝዎች በልሳን የመናገሩ ሁኔታ የነርቭ መዛባት ተደርጎ ይተረጎማል። የድምፅ አፈጣጠር እንቅስቃሴ ያህል ተፈጥሮአዊ ተግባራት የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ልዕለ-ተፈጥሮአዊ አካል በሰዎች ማደር እንዴት ሊገለጽ ይችላል?

ሉዊስ በዕቃ ቤት ውስጥ የብርሃን ጨረር የመጠቀምን ምሳሌ ጠቅሰዋል። መጀመሪያ ወደ ክፍሉ ሲገቡ፥ ጨረርና ከአየር ላይ በሚንሳፈፉ አዪራዎች የተሞላ የብርሃን ክምችት ተመለከቱ። ነገር ግን ወደ ጨረሩ ጠጋ ብለው በጨረሩ አቅጣጫ ሲመለከቱ፥ በጣም የተለየ አመለካከት አዳበሩ። ወዲያው ጨረሩን ሳይሆን፥ ከክፍሉ መስኮት በኩል መስመር ሠርተው ከዛፍ ቅርንጫፎች ላይና ከዚያም ባሻገር ከፀሐይ 93 ሚሊዮች ርቀት የሚንቀሳቀሱትን አረንጓዴ ቅጠሎች ተመለከቱ። ጨረሩን መመልከትና በጨረሩ በኩል መመልከት ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው።

ክፍለ ዘመናችን ጨረሩን በመመልከቱ ቴክኒክ ተክኗል። ይህንንም ሂደት ለመግለጽ ብዙውን ጊዜ የሚጠቀሙበት ቃል «የማቃለል ብልሃት» (reductionism) የተባለው ነው። የሰውን ልጅ ባሕርይ ወደ ነርቮችና ኢንዛይሞች ዝቅ አድርገን ልናቃልል እንችላለን። ቢራቢሮዎችን ወደ «ዲኤንኤ» (DNA) ሞሌክዩሎች፥ የፀሐይን ጥልቀት ወደ ብርሃንና ኃይል ሞገዶች (Particle waves of light and energy) ልናቃልል እንችላለን። እጅግ በከረረ መልኩ የሚቃለል ጥበብ ሃይማኖትን እንደ ሥነ-ልቦናዊ ዘይቤ፥ የዓለምን ታሪክ እንደ ዝግመታዊ ለውጥ ትግል አሳብን ራሱ በጭንቅላት ውስጥ የሚገኙትን በቢሊዮን የሚቆጠሩ የኮምፒውተር በሮች እንደሚዘጋና እንደሚከፍት ነገር አድርጎ ያየዋል።

ከሁሉም አቅጣጫ ጨረሩን ለማየት የሠለጠነ ዘመናዊ ዓለም «የእምነት» ፀር ነው። በታሪክ ሁሉ፥ ሁሉም ማኅበረሰቦች የማይታየውን ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ዓለም ህልውና እንደ ዋዛ ይመለከቱታል። እንደ የፀሐይ መውጣት፥ ግርዶሽ፥ ነጎድጓድ የመሳሰሉትን አስደናቂ ነገሮች ከልዕለ-ተፈጥሮአዊ ክስተቶች ውጭ

እንዴት ሊያብራሩት ይችላሉ? አሁን ግን ከዚያ የበለጡትን ነገሮች እንኳ ልናብራራቸው እንችላለን። እጅግ ተፈጥሮአዊ ወይም እጅግ መንፈሳዊ የሆኑትን ከስተቶች ወደሚያካትቷቸው አካላት እናቃልላለን። ሉዊስ በልሳን ስለመናገር እንዳጤኑት፥ እጅግ «ልዕለ-ተፈጥሮአዊ መንገዶች ራሳቸውን ይገልጻሉ።

ከማቃለል ንድፈ-አሳብ በመነሣት በእንዲህ ዓይነቱ ዓለም ውስጥ ስለሚኖር የሚከተሉትን ድምዳሜዎች አውጥቻለሁ።

1. *በመጀመሪያ ደረጃ የማቃለልን ጥበብ ኃይለኛ ጉልበት ልንቀበል ይገባል።* ይህ ኃይል በረከትንም መርገምንም ያመጣል። በረከቱ የመሬት መንቀጥቀጥ፥ ነጎድጓድና ማዕበልን እንድንገነዘብ በማድረግ ከአደጋው ራሳችንን እንድንጠብቅ ማድረጉ ነው። ጨረሩን በመመልከት፥ ወደ ጨረቃ ደርሶ መልስ መብረርን ተምረናል፤ በመኖሪያ ቤታችን ሆነን በቴሌቪዥን የኦርኬስትራን ድምፅ ወደ ጆሮአችን እንድንስብ ረድቶናል። የሰውን ልጅ ባሕርይ ጨረር በመመልከት፥ ኬሚካላዊ ይዘቶችን ልንለይና በመድኃኒቶች አማካኝነት ሰዎችን ከከፋ ሞንቀትና ከአእምሮ መቃወስ እንታደጋለን።

ይሁንና፥ የማቃለል ጥበብ ርግማንንም አስከትሏል። በውስጡ ሳይሆን ቀጥታ ጨረሩን በመመልከት፥ ሕይወትን ከመሠረቷት ንጥረ ነገሮች ወደማይዘል አቅጣጫ እናቃልላታለን። ከእንግዲህ የፀሐይን ወይም የጨረቃን አወጣጥ እንደ «ጥንታውያኑ» አያት-ቅድማያቶቻችን ወይም እንደ አሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ባለ ቅኔዎች አይተን አምልኮት-ቀረሽ አድናቆት ልንቸር አንችልም። ባሕርይንም ወደ ሆርሞኖችና ኬሚስትሪ ካቃለልን፥ የሰብአዊነትን ምሥጢር፥ ነፃ ፈቃድና ፍቅር እናጣለን። ለዓመታት ሁሉ የጥበብ ሰዎችንና አፍቃሪዎችን የቀሰቀሰው የስሜታዊ ፍቅር አምሳል ከመቅጽበት ወደ ሆርሞናዊ የማመንጨት ተግባር ይሸጋገራል።

የማቃለል ጥበብን ምንነት-የአይታ መንገድ-ካልተረዳን፥ የሚያሳድርብን ተጽዕኖ ቀላል አይሆንም። ይህ እውነተኛ ወይም ውሸተኛ ጽንሰ-አሳብ አይደለም። ይህ ስለ ጠቅላላው ሳይሆን የአንድ ነገር አካላት መረጃ የሚሰጠን የአይታ አንጻር ነው።

ለምሳሌ ያህል፥ መንፈሳዊ ተግባራት ከዝቅተኛውና ከከፍተኛው ደረጃ ሊታዩ ይችላሉ። አንዱ ሌላውን አይተካውም፤ (ጨረሩን መመልከት በጨረሩ አቅጣጫ ከመመልከት እንደሚለይ ሁሉ) እያንዳንዳቸው አንዱን ባሕርይ በተለያየ መልኩ ይመለከቱታል። ከዝቅተኛው አመለካከት ሲታይ፥ ጸሎት አንድ ሰው ከራሱ ጋር እንደሚነጋገር ያሳያል (በልሳን መናገርም እንዲሁ)። ከፍተኛው

አመለካከት የሰው ጸሎት በሚታይና በማይታይ ዓለም መካከል እንደ ድልድይ እያገለገለ ልዕለ-ተፈጥሮአዊ እውነታ በመካሄድ ላይ መሆኑን ይገምታል።

እንደ ጉጉ ተመልካች ሆኜ ወደ ቢልግርሃም የወንጌል ስብሰባ ልሄድና ከዚያ ሁሉ እጅግ በርካታ እድምተኛም ውስጥ አንዲት ሴት መርጬ ለቢሊ ግርሃም መልእክት አዎንታዊ ምላሽ እንድትሰጥ ያደረጓትን ማኅበረሰባዊና ሥነ-ልቦናዊ ንድፈ-አሳቦች ልተነትን እችላለሁ። ጋብቻዋ እየፈራረሰ ነበር፤ መረጋጋት ጠምቷት ነበር፤ የአማኝ አያቷን ጥንካሬ ታስታውሳለች፤ መዝሙሩ ወደ ልጅነት የቤተ ክርስቲያን ትውስታ ወሰዳት። ይሁንና፥ እነዚህ «ተፈጥሮአዊ» ምክንያቶች ልዕለ-ተፈጥሮአዊውን አያገልሉትም። በተቃራኒው። እግዚአብሔር ያንን ሰው ወደ ራሱ ለመመለስ የመረጣቸው መንገዶች ሊሆኑ ይችላሉ። ምናልባትም የተፈጥሮአዊውና የመንፈሳዊ መጣጣም ያ ፈጣሪ ያቀደው ሊሆን ይችላል። ያ ቢያንስ የእምነት «ከፍተኛው» አመለካከት ነው። ሁለቱም አንድን ክስተት የመመልከቻ ሁለት መንገዶች በመሆናቸው፤ አንደኛው ደረጃ ሌላኛውን አያስወግደውም።

2. *አንግዳ በሆነ መልኩ፥ ዝቅተኛው አይታ ከከፍተኛው የሚልቅ መሰሎት ሊታይ ይችላል።* ሲ. ኤስ. ሉዊስ በልጅነታቸው ከጥንታዊ ቴፕ የሚመጣውን የማይለይ ዜማ በማድመጥ መጀመሪያ የኦርኬስትራ ሙዚቃ ማድነቃቸውን ያስታውሳሉ። ዜማውን እንጂ ከዚህ ያለፈ ነገር ለመስማት አይችሉም ነበር። በኋላ ለሕዝቡ ወደሚቀርቡበት ኮንሰርቶች ሲሄዱ ግራ ተጋቡ። የተለያዩ ድምፅ ከሚያሰሙ የሙዚቃ መሣሪያዎች እጅግ በርካታ ድምፆች ይጎርፋሉ። «እውነተኛውን ነገር» ናፈቁ፤ ይህም ላልሠለጠነው ጆሮአቸው የጥንቱ ቴፕ የሚያሰማው ጫጫታ ነበር። በዚያን ጊዜ ለሉዊስ መተኪያው ከእውነታው የሚልቅ ይመስል ነበር።

በተመሳሳይ ሁኔታ ቴሌቪዥን ሲመለከት ላደገ ሰው በትንኞች፥ ትንፋሽ በማሳጠርና በሚያበሳጭ የአየር ለውጥ የተሞላው እውነተኛ ተራራ የመውጣት ጉዞ የ «ናሽናል ጆኦግራፊክ» ልዩ ዘገባ ከሚያቀርበው ዝግጅት በላይ ያነሰ መስሎ ሊታይ ይችላል።

ከዚህ በቀረበ ገጽታው፥ ዝቅተኛው አመለካከት በግብረገባዊ ጉዳዮችም ላይ የበለጠ መስሎ ሊታይ ይችላል። የስሜታዊ ፍቅር አምሳል ከፍ ያሉ ሙዚቃዎችን፥ ልቦለዶችና ኦፔራዎችን አነቃንቋል። ነገር ግን እንደ ሑፍ ሄፍነር ዓይነት የማቃለል ጥበብ አራማጆች ወሲብ ከፍቅርና ከመቀራረብ ውጭ ሲሆን የላቀ ስኬታማነት እንደሚኖረው

ይሟገታሉ። ዓለማውያን ደግሞ የሃይማኖትን ድጋፍ ወደ ጎን በመተው፥ ያለ ከፍተኛው ኑባሬው በዚህ ዓለም የመኖርን አሳብ አጉልተው ያቀርባሉ።

3. *የከፍተኛው ዓለም እውነታ በዝቅተኛው ዓለም ግንዛቤዎች ከግልጋሎት ላይ ይውላል።* መዝሙር ከአንድ የሙዚቃ ቅኝት ወደ ሌላው ሊሸጋገር ይችላል። ወይም ለ 10 የኦርኬስትራ መሣሪያዎች የተጻፈው ሙዚቃ ለፒያኖ ሊዘጋጅ ይችላል። በመሠረቱ በሂደት ውስጥ አንድ ነገር እንደሚጠፋ የታወቀ ነው። የፒያኖ ቁልፎችን የሚነካኩ አሥር ጣቶች የኦርኬስትራውን ጠቅላላ ድምፆች ሊያስተጋቡ አይችሉም። ይሁንና፥ በእነዚያ ቁልፎች ድምፅ የመስጠት ዓቅም ላይ የተወሰነው የመሣሪያ ተጫዋች በተቻለ መጠን የሙዚቃውን ይዘት ማስተላለፍ አለበት።

ሲ.ኤስ. ሉዊስ ሳሙኤል ፔፒስ ከመጠን በላይ ስላስደሰተው የሙዚቃ ኮንስተር ከማስታወሻ ደብተሩ ላይ ያሰፈረውን ጽሑፍ ጠቅሰዋል። ፔፒስ የሙዚቃ መሣሪያዎቹ ድምፅ እጅግ ጣፋጭ በመሆኑ አስደሳች ስሜት እንዳሳደረበት ገልጾአል፤ «ስሜቱ ነፍሱን ስላፈናት በፊት ከባለቤቱ ጋር ፍቅር ይዞኝ እንደታመምሁ እንደዚያው ሆንሁ።» ሉዊስ የየትኛውንም ስሜታዊ ምላሽ ሥነ-ሕይወታዊ አሠራር ለመገንዘብ እንድንጥር ይመክሩናል። የውበት፥ የኩራት፥ ወይም የፍቅር ስሜት በሚያድርብን ጊዜ በሰውነታችን ውስጥ ምን ይከሰታል? ለፔፒስ በአንድ ጊዜ አስደሳች ስሜት አሳድሮበታል፤ ይህ ግን ከሕመም ስሜት የተለየ አልነበረም። በሕመም ጊዜ የሚደርሱበት እንደ የሆድ ቁርጠት፥ መዋዠቅ፥ የጅማት መወጣጠር የመሳሰሉት አካላዊ ምላሾች ገጥመውታል።

ከዝቅተኛው የእይታ ደረጃ አንጻር፥ ለደስታና ፍርሃት የሚኖሩን አካላዊ ምላሾቻችን ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ናቸው። በእያንዳንዱ ጊዜ «አድሬናል ዕጢ» ተመሳሳይ ሆርሞን ያመነጫል፤ የምግብ ማድቀቂያ መዋቅር «ኒውሮንስ» (neurons) ተመሳሳይ ኬሚካሎችን ያስወግዳሉ፤ ነገር ግን ጭንቅላት አንዱን መልእክት እንደ ደስታ፥ አንዱን ደግሞ እንደ ፍርሃት ይተረጉማል። የፒያኖ ተጫዋቹ ሙሉውን የኦርኬስትራ ድምፅ ለመግለጽ የተወሰኑት የፒያኖ ቁልፎች እንዳሉት ሁሉ፥ በዝቅተኛ ደረጃው የሰው አካልም የተወሰነ ቃል ብቻ ይኖረዋል።

እዚህ ላይ ነው እንግዲህ የማቃለል ጥበብ ጥበብ ጎድሎት የምንመለከተው፤ የሰውን ስሜቶች (እንደ ኒውሮንስና ሆርሞንስ ወደመሳሰሉ) መሠረታዊ ይዘታቸው በማቃለል «ጨረሩን» ብቻ ብትመለከት፥ አመክኒዮህን ተጠቅመህ ደስታና ፍርሃት አንዱ እንደሆኑ

ልትናገር ትችላለህ፤ ይህም ከሞላ ጎደል ተቃራኒዎች በሚሆኑበት ጊዜ ማለት ነው። የሰው ልጅ አካል የደስታን ስሜት እንዲያስተላልፉ የተወሰነ ሥራ የተሰጣቸው የነርቭ ሴሎች የሉትም። ተፈጥሮ ያን ያህል ለጋሽ አይደለችም። የደስታ ገጠመኞቻችን ሁሉ የሚሰጡት የሕመምን፥ የዳሰሳን፥ የሙቀትንና የቅዝቃዜን ስሜቶች ከሚያስተላልፉ «የብርድ» የነርቭ ሴሎች ነው።

የሕይወት ዘይቤ

የሰው ጭንቅላት ከሞላ ጎደል ፍጹም የሆነ የማሽጋገር ሞዴልነትን ያቀርባል። ምንም እንኳ ጭንቅላት በሰውነት ውስጥ «ከፍተኛውን» እይታ የሚወክል ቢሆንም፥ እንደ እርሱ ምስኪን ወይም ብቸኛ የሆነ የአካል ክፍል የለም። በትልቅ የአጥንት ሣጥን ውስጥ ተጎብሮ መረጃ ለማግኘት በዝቅተኞቹ የአካል ክፍሎች ላይ ይደገፋል። አእምሮ ምንም ነገር አይቶ ወይም ቀምሶ ወይም ዳስሶ አያውቅም። መልእክቶች ሁሉ እዚያ የሚደርሱት በመገናኛ መስመር አማካኝነት ነው፤ ብዙዎቹ የስሜት ልምምዶቻችን እንደ ነጠብጣብ ወይም ቀጥታ መስመር ወደ መሳሰሉ ኤሌክትሪክ መንገዶች ይቀነሣሉ (-.--..-...--)። አእምሮ አንድን ነገር ለመተርጎም የሚችለው ከተለያዩ የአካል ክፍሎች በእነዚህ የመገናኛ መስመሮች የሚመጡለትን መልእክት ከተቀበለ በኋላ ነው።

ይህን ክፍል በምጽፍበት ጊዜ፥ የቤቶቨንን ግሩም ሙዚቃ እየሰማሁ ነኝ። ያ ሙዚቃ በጊዜና በቴክኖሎጂ የተሸጋገረ የተከታታይ መልእክቶች ጥርቅም ብቻ ነው። የጆመረውም ቤቶቨን በአእምሮው «እንዳዳመጠው» ሙዚቃው አሳብ ነበር (የሙዚቃው ቀማሪ በወቅቱ ደንቆሮ በመሆኑ አሳቡን በሙዚቃ መሣሪያዎች ሊሞክር አይችልም ነበር። እናም ሙሉ ለሙሉ የተመራው በራሱ የአእምሮ ትውስታ ነበር። ከመጠን ያለፈ የአእምሮ ብቃት!) ከዚያ በኋላ ቤቶቨን የሙዚቃ ኖታዎች የሚባሉትን ምልክቶች በመጠቀም ሙዚቃውን ከወረቀት ላይ አሰፈረው።

አንድ መቶ ዓመት ያህል የጊዜ ቅጠሎች ከረገፉ በኋላ፥ አንድ ኦርኬስትራ እነዚያን ምልክቶች በማንበብ ተረጎማቸው፤ ከዚያም ቤቶቨን በአእምሮው «የሰማውን» በመገመት ውብ ዜማ አድርጎ አቀነባበረው። የቀረጻ መሐንዲሶች የዚያን ኦርኬስትራ ድምፅ ወደ ቴፕ ሲያስተላልፉ፥ ስቱዲዮው ያንን ምልክት ወደ ሜካኒካል ቅርጽ ይቀይረዋል። በመጨረሻም፥ አነስተኛ ማዕበል እየሠራ ከድምፅ መቅረጫዬ ውስጥ ይዘልቃል።

አሁን ቴፑ እነዚያን ማዕበሎች «እያነበበ» ሲሆን፥ በማጉያዎቹ አማካኝነት የምቱን ለውጥ (vibrations) በእነዚያ ማጉያዎች አማካኝነት

የተፈጠሩት ሞሌኩላዊ ርግብግብታዎች (Molecular) ከጆሮ
ሌሎች ተከታታይ ሜካኒካዊ ተግባራትን ያንቀሳቅሳሉ፤
አጥንቶች የጆሮዬን ታምቡር በመነካካት ርግብግብታዎቹን
ፈሳሽ (viscous fluid) አማካኝነት 25, 000 የድምፅ መቀ
ወደሚጠባበቁበት ክፍል ያስተላልፋሉ። አንድ ጊዜ ከተነ
ተገቢዎቹ ሴሎች ኤሌክትሪካል መልእክታቸውን ያስ
በመጨረሻም፥ እነዚያ የነጠብጣቦችና የቀጥተኛ መስመሮች
የሆኑት መልእክቶች ወደ አእምሮዬ ይደርሳሉ። አእምሮዬ
ሙዚቃ እንደሆነ ወደምረዳበት ድምፅ ይለውጡታል። ያ
የሙዚቃ ሥራ ቆም ብዬ ሳዳምጥ ስሜት ያፍነከንከኛል።
በዝቅተኞቹ የሰውነት ክፍሎች ትብብር የደረሰኝ ነው።

ሽግግር የሕይወት ዘይቤ ነው። እውቀት ሁሉ ወደ እኛ
ወደ ታች ወደ ምልክትነት በሚወርድበት የመለወጥ ሂደት
ወደ ላይ ለትርጉም ፍለጋ በሚኬድ አሠራር ነው። አሁን ስ
ሙዚቃ ሦስት አንቀጾች ጽፌአለሁ። እነዚህ ከአእምሮ
ፈልቀው ወደ ቃላት የለወጥሁዋቸውና ከኮምፒዩ
የተየብሁዋቸው ናቸው። ኮምፒዩተሩም በማግኔታዊ ዲስክ ው
ወደ «ባይኔሪ» ኮድ ይለውጠውና «ሞደም» የተባለው
«ባይኔሪ» ኮዱን ወደ «ዲጂታል» ድምፅ ይቀይረዋል። ከዚያ
በቴሌፎን አማካኝነት ለአሳታሚው ድርጅት ይደርሳል።
አንቀጾች «ሞደም» በሚያስተላልፍበት ጊዜ ለመስማት
ከጫጫታ በቀር ትርጉሙ አይገባኝም። ይሁንና፥ በዚያ ጫጫ
የራሴ አሳቦች ቃላት ይገኛሉ።

ዲጂታል ድምፆችን የሚቀበለው የአሳታሚው ኮምፒዩተር
ወደ ማግኔቲክ ኮዶች ይለውጠዋል። አሳታሚው እነዚያ
በኮምፒዩተሩ መስተዋት ላይ ወደሚታዩ ቃላት ይለውጣቸዋል
ለንባብ ያበቃቸዋል። ለለመደው ዓይንህ፥ ከወረቀት ላይ
እነዚህ ቀለሞች ፊደላትና ቃላትን ይሠራሉ፤ እነዚህም ፊደላ
ወደ ዓይን ሴሎችህ ይተላለፉና በኤሌክትሪካል መስመሮች
ወደ አእምሮህ ይሸጋገራሉ፤ አእምሮህ ደግሞ አንድ ዓይነት
ይሰጣቸዋል።

በዚህች ዓለም ውስጥ ማንኛውም ግንኙነት፥ እውቀት፥
ልምምድ ሁሉ በሽግግር ሂደት ላይ ይደገፋል፤ ይኸውም ትርጉ
ታች» ወደ ኮዶች የሚጓዝና በኋላ ተመልሶ የሚሰባሰብ መ
የታችኞቹ ኮዶች የመጀመሪያውን ትርጉም ይዘው እን
በማመን፥ በተለምዶው በዚሁ ሂደት ላይ እንደገፋለን። የም

ቃላትና የኮምፒዩተር ሞደሙ ሳይቀር ስለ ቤቶቨን የጻፍሁዋቸውን የመጀመሪያ አሳቦች እንደሚያደርሱልኝ አምናለሁ። በአንዲት ትንሽ ወረቀት ላይ የተሠራውን የድንጋያማ ተራሮች ፎቶግራፍ እመለከትና ስፍራውን እንደ ጎበኘሁ ሁሉ አእምሮአዊ ዕረፍት ይሰማኛል። የሽቶን ናሙና ለማሽተት የመጽሔት ላይ ማስታወቂያ እመለከታለሁ። በዚህም ጊዜ ያንን ሽቶ የምትጠቀመው የባለቤቴ ምስል ይከሰትልኛል። ዝቅተኛው የከፍተኛውን አንድ ነገር ይሸከማል።

የመንፈስ ሽግግር

እንግዲህ በመንፈስ ዓለም ውስጥ ተመሳሳይ አጽናፈ-አቀፋዊ መመሪያ በመሥራት ላይ መሆኑን መረዳቱ ሊያስገርመን ይገባ ይሆን?

ከዚህ መጽሐፍ መጀመሪያ ላይ የተነሡትንና ከዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ እንደገና የቀረቡትን የሪቻርድን ጥያቄዎች አስታውስ። እግዚአብሔር ጣልቃ ገብቶ ራሱን በግልጽ የማያሳየው ለምንድን ነው? እንሰማው ዘንድ ለምን ድምፁን ከፍ አድርጎ አይናገርም? ተአምራቱን እንናፍቃለን። ለዚያውም ንጹሕና ያልተነካ ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ክስተት!

«ምንም ያልታከለበት ንጹሕ» የሚለው ሐረግ በዚህ ጉዳይ እምብርት የሆነውን አመለካከት ስለሚያስወግድ ሆን ብዬ የመረጥሁት ነው። እኛ የዘመኑ ሰዎች ተፈጥሮአዊውን ከልዕለ-ተፈጥሮአዊ ለመለየት እንሻለን። ልንዳስሰው፥ ልንመለከተው፥ ልናሽተውና ልንሰማው የምንችለው ተፈጥሮአዊ ዓለም ስለ ራሱ መረጃ የሚሰጥ ይመስለናል፤ ልዕለ-ተፈጥሮአዊው ዓለም ግን ሌላ ጉዳይ እንደሆነ እናስባለን። ስለዚህኛው ዓለም ምንም የተረጋገጠ ነገር የማይታይ ይመስለናል፤ ከራሱ ላይ ቆዳ የለውም፤ ይህ ደግሞ ያሳስበናል። ማረጋገጫ እንሻለን። በደመቀ፥ ምልክትን በሚተውና የጆሮን ታምቡር በሚያርገበግብ መልኩ ልዕለ-ተፈጥሮአዊው ወደ ተፈጥሮአዊው ዓለም እንዲገባ እንፈልጋለን።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጠው እግዚአብሔር ፍላጎታችንን የሚጋራ አይመስለንም። እኛ ተፈጥሮአዊውን ከልዕለ-ተፈጥሮአዊው፥ የሚታየውን ከማይታየው ለመለየት ስንሞክር፥ እግዚአብሔር ግን ሁለቱንም ወደ አንድነት ለማምጣት ይሻል። ዓላማው «የታችኛውን» ዓለም ማዳን፥ የወደቀው ፍጥረት የሚገኝበትን ተፈጥሮአዊ ስፍራ መንፈስና ቁስ አካል በአንድነት ወደሚኖሩበት ወደ ቀደመው ደረጃው መመለስ ነው።

ክርስትናን ተቀብለን ከማይታየው ዓለም ጋር መገናኘት ስንጀምር፥ በምሥጢራዊ መንገድ ወደ ላይ አልተጓዝንም። ከተፈጥሮአዊው ዓለም

የሚያወጡን ለሰማይ የሚስማሙ አካላት አልተጎናጸፍንም። (ከኖስቲኮችና ማኒኪያንስ ጀምሮ፤ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ዓይነቱን አመለካከት እንደ ኑፋቄ ቆጥራዋለች)። ይልቁንም ቁሳዊ አካላችን ከመንፈሳዊ እውነታ ጋር ዳግም ይገናኝና የማይታየው ዓለም ወደሚታየው ዓለም ራሱን የሚያሸጋግርበትን ኮድ መስማት እንጀምራለን። የእኛ ተግባር ከማቃለል ጥበብ እንደሚቃረን መገንዘብ ይቻላል። ዓለም ዳግም «የምትቀደስባቸውን» መንገዶች እንሻለን፤ በተፈጥሮ ውስጥ የምስጋና ሞተር፥ በዳቦና ወይኑ ውስጥ የቅዱስ ቁርባን ጸጋ፥ በሰዎች ፍቅር ውስጥ የፍጹሙን ፍቅር ጥላ ለመመልከት እንፈልጋለን።

ለዚህ ለከፍተኛው ስፍራ ያሉን ቃላት ውስን ናቸው። ለሌላው ሰው እንደምንናገር አድርገን ለእግዚአብሔር እንናገራለን፤ ከዚህ በላይ ተራና «ተፈጥሮአዊ» የሆነ ምን ሊኖር ይችላል? መጸለይ፥ ወንጌሉን መመስከር፥ ማሰላሰል፥ መጾም፥ ለተጠማ አንድ ጽዋ ውኃ ማጠጣት፥ የታሰሩትን መጠየቅ የመሳሰሉት የዕለት ተዕለት ተግባራት የ «ከፍተኛው» ትርጉም እንዳላቸው ተነግሮናል። በተቻለ መጠን እነዚህ ነገሮች የማይታየውን ዓለም ይገልጻሉ።

ዝቅ ካለው የማቃለል ጥበብ አቅጣጫ ሲታዩ መንፈሳዊ ተግባራት ሁሉ ተፈጥሮአዊ «ማብራሪያዎች» አሏቸው። ጸሎት በባዶ ሜዳ ማጉተምተም ነው፤ የኃጢአተኛው በንስሐ መመለስ የስሜታዊነት ተግባር፥ ዕለተ በዓል ጎምሳ የስካር ቀን። ተጠራጣሪ ሰው ያኛውን ዓለም ለመግለጽ የሚጠቀመው ይህንኑ ብቻ ከሆነ፥ ተፈጥሮአዊ ነገሮች የጎሰቆሉ መሆናቸውን ሊናገር ይችላል።

ይሁንና፥ እምነት ከጨረሩ አቅጣጫ በመመልከት ተፈጥሮአዊ እንቅስቃሴዎች የልዕለ–ተፈጥሮአዊው የተቀደሱ ተሸካሚዎች እንደሆኑ ይገነዘባል። ከዚያ እይታ አንጻር፥ ተፈጥሮአዊው ዓለም ጎስቋላ አይደለም፤ በተአምራት የበለጸገ እንጂ። እንዲሁም የእግዚአብሔር መገኘት እንደኛ ባለው «ተፈጥሮአዊ» አካል ውስጥ ሲያድር፥ የተፈጥሮአዊው ዓለም ተአምር «በላቀ ተአምር» ከጡዘቱ ላይ ደረሰ፤ ቃሉ ወደ ሥጋነት ተሻገረ።

ክርስቶስ ሁለቱን ዓለማት በአንድ አካል ውስጥ አንድ አደረገ፤ ከሄድን ገነት ጀምሮ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ መንፈስንና ቁስ አካልን አዋሃደ። የሥነ–መለኮት ምሁር የሆኑት ጀርገን ሞልትማን በአጽንኦት ሊጤን በሚገባው ዓረፍተ ነገር ውስጥ ሁኔታውን እንዲህ ሲሉ ገልጸውታል፤ «የእግዚአብሔር ራሱን በሰዎች መግለጽ የተግባራቱ ሁሉ ፍጻሜ ነው።»[5] ሐዋርያው ጳውሎስም እንዲህ ሲል

ያስቀምጠዋል፤ «እርሱም የአካሉ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው . . . እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር፥ በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአልና።»

ቃሉ ሥጋ ሲሆን፥ በአካሉ ማለትም በቤተ ክርስቲያን መልክ መኖሩን ተወው። የእኛ በጎነት በቀጥተኛ መልኩ የእግዚአብሔር በጎነት ሆነ (ከእነዚህ ከታናናሾች ለአንዱ ያደረጋችሁት ለእኔ እንዳደረጋችሁት ነው)። መከራችን በጳውሎስ አገላለጽ፥ «የመከራው ተካፋይነት» ይሆናል። የእኛ ተግባር የእርሱ ተግባር ይሆናል («እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል»)። በእኛ ላይ የሚደርስ ሁሉ በእርሱ ላይ ይደርሳል። («ሳውል፥ ሳውል፥ ስለ ምን ታሳድደኛለህ?»)። ሁለቱ ዓለማት ማለትም የሚታየውና የማይታየው በክርስቶስ አንድ ሆነዋል፤ ጳውሎስ ደጋግሞ እንደገለጸው፥ እኛ «በክርስቶስ» ነን። የእግዚአብሔር ራሱን በሰዎች አማካኝነት መግለጹ የሥራው ሁሉ ፍጻሜ፥ የፍጥረት ሁሉ ዓላማ ነው።

ከታች ሆነን፥ ተአምር በሚያስደንቅ ኃይል ወደ ተፈጥሮአዊው ዓለም የሚገባ ወረራ እንደሆነ እናስባለን። እንዲህ ዓይነቱንም ምልክት ለማየት እንጓጓለን። ነገር ግን ከላይ ከእግዚአብሔር እይታ አንጻር፥ እውነተኛው ተአምር የሽግግር ተአምር ነው። ይኸውም የሰው ልጅ አካላት በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ዕቃዎች መሆናቸው፥ ተራው የሰው ልጅ የበጎነትና የልግስና ተግባራት ከእግዚአብሔር የምድር ላይ ተሠግዎ የማያንሱ መሆናቸው ነው።

ምሳሌውን ለመፈጸም ከጳውሎስ ቃላት ርቆ መሄድ አያስፈልገኝም። ክርስቶስ ዛሬ በዓለም ያለውን ሚና ለማሳየት የተጠቀመበት ማብራሪያ ስለ ሽግግር ለመግለጽ የተጠቀምሁት ዓይነት ነው። በጳውሎስ አገላለጽ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን የአካሉ ራስ ሆኖ ይሠራል። የሰው ራስ (አእምሮ) ፈቃዱን እንዴት እንደሚፈጽም እናውቃለን። ይኸውም እጆች፥ ዓይኖችና አፍ ይረዱ ዘንድ ትእዛዛትን ወደ ታች በኮድ በማስተላለፍ ነው። ጤነኛ ሰውነት የአእምሮን ትእዛዝ የሚቀበል ነው። ክርስቶስ ፈቃዱን የሚፈጽመው የአካሉ ክፍሎች በሆነው በእኛ አማካኝነት ነው።

እግዚአብሔር ዝም ይላል? ያንን ጥያቄ በሌላ ጥያቄ ብመልሰው ይቀለኛል፤ ቤተ ክርስቲያን ዝም ትላለች? እኛ በዚህች ዓለም የእርሱ አፍ፥ ድምፅ ነን። እንዲህ ያለው ግዙፍ የሽግግር ዕቅድ የእግዚአብሔር መልእክት አንዳንድ ጊዜ ሊደነጋገር ወይም ውል-አልባ ሊሆን እንደሚችል ያረጋግጣል። እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ዝም ያለ

እንዲመስል ዋስትና ይሰጣል። ነገር ግን ራሱን በሰዎች በኩል መግለጹ የእግዚአብሔር ዓላማ ነበር፤ በዚያ ብርሃን ሲታይ፥ ዕለተ በዓለ ኀምሳ ግሩም ዘይቤ ይሆናል። ይኸውም በምድር ላይ የእግዚአብሔር ድምፅ ሊረዱት በማይችሉት መንገድ በሰው ልጆች አንደበት መነገሩ ነው።

ተስፋው

ሲያትል በተባለው የአሜሪካ ግዛት ውስጥ ካሮሊን ማርቲን የምትባል ንቁና ተጫዋች ጓደኛ አለችኝ። ይሁንና፥ ካሮሊን፥ የጡንቻ ችግር አለባት። እናም እንደ ለሃጭ፥ ሥርዓት አልባ የእጆቿ እንቅስቃሴዎች፥ ያልተያያዘ ንግግር፥ ራስን ማወዛወዝ የመሳሰሉት ውጫዊ ሁኔታዎቿ የሚመለከቷት ሰዎች የአእምሮ ዝግመት እንዳለባት እንዲያስቡ አድርገዋል። ለነገሩ ሙሉ ለሙሉ የሚሠራው አካሏ ቢኖር አእምሮዋ ብቻ ነው። የሚቸግራት ሰውነቷን መቆጣጠሩ ብቻ ነው።

መንግሥት ሌላ ቦታ ሊያገኝላት ባለመቻሉ፥ ካሮሊን ለአሥራ አምስት ዓመታት ለአእምሮ ዘገምተኞች በተዘጋጀው ቤት ኖራለች። የቅርብ ጓደኞቿ ልብሶቹን ሁሉ የሚቦጫጭቀውና የድርጅቱን አትክልቶች ሁሉ የሚበላው ሌራ፥ ሦስት ዓረፍተ ነገሮች ብቻ የሚያውቅና ያገኘውን ሰው ሁሉ «እማማ» ብሎ የሚጠራው አርሊን ናቸው። ካሮሊን ከዚያ ቤት ኮብልላ በውጭው ዓለም ተስማሚ ስፍራ ለማግኘት ቆረጠች።

በመጨረሻም እንዳሰበችው ከዚያ ወጥታ የራሷን ቤት መሠረተች። አዲሱን ሕይወት ስትጀምር እጅግ ቀላሉ ተግባር ከፍተኛ ሆነባት። ሻይ ከሻይ ጀበና ወደ ብርጭቆ ራሷን ሳታቃጥል ለመቅዳት የሦስት ወራት ትምህርት አስፈለጋት። ካሮሊን ግን ይህንን ጨምሮ ሌሎችንም ትግሎች ለመወጣት ቻለች። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ጨርሳ ወደ ኮሌጅ ገባች።

በኮሌጁ ውስጥ የሚገኘው ሰው ሁሉ ካሮሊንን የሚያውቃት እንደ አካል ጉዳተኛ ነበር። ከተንቀሳቃሽ ወንበር (Wheelchair) ላይ ስትቀመጥ «ካኖን ኮሚዩኒኬተር» በተባለው መሣሪያ ላይ በዝግታ ስትተይብ፥ ጎብጣ ስትሄድ ያዩዋታል። ከእርሷ ጋር የመነጋገር ድፍረት የሚኖራቸው ጥቂቶቹ ናቸው፤ ወጥነት የሌላቸውን ድምፆችዋን መከተል ይቸግራቸዋል። ካሮሊን ግን በትምህርቷ ተግታ የሁለት ዓመቱን «የአሶሺዬት ኦፍ አርትስ» ፕሮግራም በሰባት ዓመታት አጠናቀቀች። በመቀጠል፥ መጽሐፍ ቅዱስ ለማጥናት በሉተራን ኮሌጅ

ውስጥ ተመዘገበች። እዚያ ሁለት ዓመታት ከቆየች በኋላ፥ በጸሎት ስብሰባ ላይ ለተማሪዎቹ ስብከት እንድታቀርብ ተጠየቀች።

ካሮሊን ብዙ ሰዓታት ፈጅታ መልእክቷን አዘጋጀች። በአማካይ አንድ ገጽ ለመጻፍ አርባ አምስት ደቂቃ በሚወስድ ፍጥነቷ የመጨረሻውን ጽሑፍ ሠርታ አጠናቀቀች። ከዚያም ጓደኛዋ ጆሲ ለእድምተኞቹ እንድታነብላት ጠየቀች። ጆሲ ጠንካራና ግልጽ የድምፅ አወጣጥ ነበራት።

በጸሎት ስብሰባው ዕለት፥ ካሮሊን ከተንቀሳቃሽ ወንበሯ ላይ ከመድረኩ በስተግራ ተቀመጠች። አንዳንድ ጊዜ እጆቿ ከቁጥጥር ውጭ ሆነው ይንቀጠቀጣሉ፤ ጭንቅላቷ ትከሻዋን ለመንካት እስኪቃረብ ድረስ ወደ አንድ አቅጣጫ ያዘነብላል፤ ለሃጭዋም እንዲሁ ይወርዳል። ጆሲ ከአጠገቧ ቆማ ካሮሊን የጻፈችውን በሳልና ሞገስን የተላበሰ ጽሑፍ ታነባለች። የመልእክቱ አሳብ ያተኮረው፥ «ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን» በሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ዙሪያ ነበር።

ለመጀመሪያ ጊዜ አንዳንድ ተማሪዎች ካሮሊን እንደ እነርሱው ጤነኛ ሰው መሆኗን ተመለከቱ። ከዚያ በፊት ብሩሁ ጭንቅላቷ «ከማይታዘዝ» ሰውነት ውስጥ በመኖሩ፥ ለመናገር አለመቻሏ ጉብዝናዋን ሲጋርደው ኖሯል። ነገር ግን እርሷ ከመድረኩ ላይ ተቀምጣ የጻፈችው መልእክት ሲነበብ በመስማታቸው፥ ተማሪዎቹ ከተንቀሳቃሽ ወንበር ላይ ካለው ሰውነቷ አልፈው ጠቅላላ ማንነቷን በምናባቸው ለመመልከት ችለዋል።

ካሮሊን በሚቆራረጥ ድምፅዋ ስለዚያን ዕለቱ ሁኔታ የነገረችኝ ሲሆን፥ ላስታውስ የምችለው ግማሹን ያህል ብቻ ነው። ይሁንና፥ እርሷ የገለጸችልኝ ትእይንት ለእኔ የሽግግር ምሳሌ ሆነልኝ፤ ይኸውም ከማይታዘዝ ሰውነትና የድምፅ ማውጫ አካላት ውስጥ የተቆለፈው ንጹሕ ጭንቅላት ነው። ክርስቶስ እንደ ራስ በነበረው ሚና የተሸከመውን ውርደት የአካሉ ክፍሎች ለሆንነው ለእኛ የሰጠውን ክብር ስረዳ፥ የክርስቶስን ራስነት የሚያስረዳው የአዲስ ኪዳን ምሳሌ አዲስ ትርጉም ሰጠኝ።

ቤተ ክርስቲያን የሆንነው እኛ ወደ ላቀ ደረጃ የተወሰድን የሽግግር ምሳሌዎች ነን። የሚያሳዝነው ለእግዚአብሔር ፍቅርና ክብር የማይነቀፍ ማረጋገጫ ልንሰጥ አንችልም። አንዳንድ ጊዜ እንደ ካሮሊን ሰውነት፥ መልእክቱን እንደ ማስተላለፍ እናደበዝዘዋለን። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ከጠቅላላው የሰው ልጅ ሙከራ በስቲያ የምትገኘው ለዚሁ ነው፤ የሰው ልጆችም የሚኖሩት ለዚህ ነው፤ ይኸውም ፍጥረታት ሁሉ

ከእግዚአብሔር ውጭ የእግዚአብሔርን አምሳል እንዲያዩ ነው። ይህም ከአደጋውና ከውርደቱ ባሻገር ሊከናወን እንደሚገባ አስቦአል።

«ይህ የወረደው ሁሉን ይሞላ ዘንድ ከሰማያት ሁሉ በላይ የወጣው ደግሞ ያው ነው። እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎችም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤ ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ።»

«. . . ሕፃናት መሆን ወደፊት አይገባንም፥ ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፤ ከእርሱም የተነሣ አካሉ ሁሉ እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ፥ በተሰጠለት በጅማት ሁሉ እየተጋጠመና እየተያያዘ፥ ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል።»

[1] William James, *The Varieties of Religious Experience*, 233.

[2]C.S. Lewis, *The Weight of Glory*, 18, 19.

[3]C.S. Lewis, *God in the Dock*, 212.

[4]C.S. Lewis, *Christian Reflections*, 37.

[5]Jurgen Moltman, *God in Creation*, 244.

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፡- ቆላስይስ 1፤ ማቴዎስ 25፤ ፊልጵስዩስ 3፤ ማቴዎስ 10፤ የሐዋርያት ሥራ 9፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 4፤ ኤፌሶን 4።

«ፊትህን ከእኔ የሰወርህ፥

እንደ ጠላትህም የቆጠርኸኝ ስለ ምን ነው?

የረገፈውን ቅጠል ታስጨንቃለህን?

ወይስ የደረቀውን ዕብቅ ታሳድዳለህን?»

ኢዮብ 13፡24–25

ምዕራፍ 28

እግዚአብሔር ስውር ነውን?

የኢዮብን አስጨናቂ ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ ለመረዳት ስል የኢዮብን ቃላት ከሌሎች ንግግሮች ሁሉ ለይቼ አወጣሁ። ስለተጎሳቆለው ጤንነቱ፥ ስለ ልጆቹና የወደፊት ሕይወቱ ሲያጉረመርም ለመመልከት ጠብቄ ነበር። የሚገርመው ግን ኢዮብ ስለ እነዚህ ነገሮች ብዙም የሚለው አልነበረውም። ይልቁንም በእግዚአብሔር መሰወር ንጥል ጭብጥ ላይ ሲያተኩር ተመለከትሁ። ኢዮብን ከሁሉም በላይ የጎዳው ነገር ቢኖር ሰሚ ሳይኖር የሥቃይ ጩኸት ማሰተጋባቱ ነበር። በርካታ የሚሠቃዩ ሰዎች እነዚህኑ ተመሳሳይ ስሜቶች ሲያንጸባርቁ ተመልክቻለሁ። ምናልባትም ባለቤታቸው በካንሰር በሽታ ከሞቱ በኋላ የሚከተለውን አሳብ የጻፉት የሲ.ኤስ. ሉዊስ ሁኔታ ከሁሉም የጠለቀ ሳይሆን አይቀርም።

> «በዚህ መሀል እግዚአብሔር የት ነው? ይህ ከጠለቀ የሥጋት ስሜቶች አንዱ ነው። ከመጠን በላይ ተደስተህ እርሱን ሳትፈለግ ስትቀር. . . እጆቹን ዘርግቶ የሚቀበልህ መስሎ ይሰማሃል። ችግርህ በጠለቀና ሌሎች ርዳታዎች ሁሉ በጨለሙ ጊዜ ወደ እርሱ ስትሄድ ምን ታገኝ ይሆን? ከፊትህ በሩ ይጠረቀማል፤ ከውስጥ በሩ ሲቀረቀር፥ አጥብቆ ሲቀረቀር ትሰማለህ። ከዚያ ወዲያ ዝምታ። ከዚያ ስፍራ ሮጠህ ልትሸሽ ትችላለህ። ብዙ በጠበቅህ ጊዜ ዝምታው ይበልጥ እየጎላ ይሄዳል።»[1]

ከሁሉም በላይ ኢዮብ በእግዚአብሔር ፊት ጉዳዩን ለማስረዳት ይሻ ነበር። የወዳጆቹን ቅድስና ውሸ ቁንጫን እንደሚያባርር አባረረ። እርሱ የፈለገው እውነተኛውን ነገር ነበር። ሁሉን ከሚችል አምላክ ጋር የግል ቀጠሮ ሊይዝ ወደደ። ከሆነው ሁሉ ባሻገር፥ ኢዮብ በእግዚአብሔር ጨካኝነትና ኢ–ፍትሐዊነት ለማመን አይችልም ነበር። ምናልባት አንድ ስፍራ ላይ ቢገናኙ የእግዚአብሔርን አሳብ ለመስማት እንደሚችል ገመተ። ነገር ግን እግዚአብሔርን የትም ሊያገኘው

አልቻለም። ኢዮብ የጓደኞቹን የግብዝነት ጨዋታና ከዚያም በኋላ የሚያስፈራ ባዶ ድምፅ ሰምቷል። በሩ ከፊቱ ላይ ተጠረቀመ።

የእምነት እውነታ

«ጣፋጭ የሆንኸው አምላክ ሆይ፥ ከልቤ ላይህ እሻለሁ፤ ከአንተ ጋር ልሆን እወዳለሁ. . .»

– ጆርጅ ሃሪሰን (መዝሙር)

«እግዚአብሔር ሕያው እንደሆነ አውቃለሁ፤ ዛሬ ጠዋት ከእርሱ ጋር ተነጋግሬአለሁ!»

– ከመኪና ላይ የተለጠፈ ጽሑፍ

«እግዚአብሔር ይወድሃል፤ ለሕይወትህ ግሩም ዕቅድ አለው።»

– የወንጌል ስርጭት ጽሑፍ

«አብሮኝ ይጓዛል፤ ያነጋግረኛል፤ የእርሱ እንደሆንሁ ይነግረኛል።»

– ክርስቲያናዊ መዝሙር

የሰዎች ለእግዚአብሔር እውነተኛ መገኘት ናፍቆት ከሞላ ጎደል በየትኛውም ስፍራ ሊከሰት ይችላል። ይሁንና፥ እግዚአብሔር የሌለ የሚመስሉትን ጊዜያት ከግንዛቤ ውስጥ እስካላስገባን ድረስ ስለ እግዚአብሔር የቅርብ መገኘት አጠቃላይ መርህ ልናስቀምጥ አንችልም። ሲ.ኤስ.ሉዊስ ከዚህ ችግር ጋር ተጋፍጠዋል፤ ኢዮብና ሪቻርድም እንዲሁ። በሆነ ነጥብ ላይ እያንዳንዱ ሰው የእግዚአብሔርን ስውርነት መጋፈጥ አለበት።

አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን መገኘት አጥብቀን እየፈለግን ሳለ ያለ ምንም ማስጠንቀቂያ የደመና ግርዶሽ ሊከበን ይችላል። የደቡብ አፍሪካው አገልጋይ ሬቨሬንድ አለን ቦሳክ ፖለቲካ ተናግረሃል ተብለው ወኅኒ ወርደው ነበር። በዚያም ለብቻቸው በአንድ ክፍል ውስጥ ለሦስት ሳምንታት ታስረው፥ እግዚአብሔር ነፃ ያወጣቸው ዘንድ ሁልጊዜ ተንበርከው ይጸልዩ ነበር። በኋላ ለማኅበረ ምእመናቸው ሲተርኩ፥ «ይህ በሕይወቴ እጅግ አስጨናቂ ጊዜ እንደነበር ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። ለጸሎት ስንበረከክ፥ ቃላት አይመጡልኝም፥ እንባም አልነበረኝም።»[2] ብለዋል። የእኅህ ሰው ገጠመኝ በደቡብ አፍሪካ የብዙዎቹ ጥቁሮች ዕጣ-ፈንታ ነበር፤ ይጸልያሉ፤ ያለቅሳሉ፤ ይጠብቃሉ፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ምላሽ አያገኙም።

አንዳንዶች እግዚአብሔር እንደማይሰወር ሊናገሩ ይችላሉ። አንድ መኪና ላይ የተለጠፈ ሃይማኖታዊ ጽሑፍ፥ «ከእግዚአብሔር የራቅህ መስሎ ከተሰማህ ማን ፈቀቅ እንዳለ ገምት» ይላል። ነገር ግን በዚህ መፈክር ውስጥ የሚገኘው የሰውን ሕሊና የመውቀስ ጥረት እውነትነት

ላይኖረው ይችላል። መጽሐፈ ኢዮብ እግዚአብሔር ራሱ ፈቀቅ ያለበትን ጊዜ ይተርካል። ምንም እንኳ ኢዮብ እግዚአብሔርን ባይበድልና ሁልጊዜም ለርዳታ ቢጮኽም፥ እግዚአብሔር ግን ተደብቆ ሊቆይ መርጧል። ከእግዚአብሔር ስውርነት ጋር መጋፈጡ የእምነት ጉዞ የተለመደ አካል መሆኑን ብትጠራጠር፥ ከሥነ-መለኮት ቤተ መጻሕፍት ውስጥ (ከእግዚአብሔር ጋር ጎብረት ሲያደርጉ የሚኖሩትን ወንዶችና ሴቶች ታሪክ አንብብ። በከበደ ፈተናና «የነፍስ ጽልመት» ውስጥ መኖሩን ያልገለጸ አንድ ሰው ታገኝ እንደሆነ ሞክር።)

መከራ ለሚቀበሉትና ከአጠገባቸው ለሚቆሙት ሰዎች መጽሐፈ ኢዮብ አንድ ጠቃሚ ትምህርት ያስተላልፋል። የሚግ ውድሳን፥ የአለን ቦሳክና የኢዮብ ጥርጣሬዎችና ማጉረምረሞች የደካማ እምነት ምልክቶች ሳይሆኑ ዋጋ ያላቸው ምላሾች ናቸው። እንዲያውም ላቅ ያለ ዋጋ ያላቸው ምላሾች በመሆናቸው፥ እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲካተቱ አድርጓል። የእግዚአብሔር ተቃዋሚዎች የሆኑትን ሰዎች ሙግቶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለማግኘት የሚጠብቅ ሰው አይኖርም። (ከእነዚህ የተቃውሞ ሥራዎች መካከል "Letters from the Earth" የሚለው የማርክ ትዌን እና "Why I Am Not a Christian" የተሰኘው የበርትራንድ ራስል መጻሕፍት ይገኙባቸዋል።) ይሁንና፥ ከሞላ ጎደል እነዚህ አሳቦች ሁሉ በመጽሐፈ ኢዮብ ውስጥም ባይሆን በመዝሙራትና በነቢያት ጽሑፎች ውስጥ ይታያሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቅይማታችን የሚጠበቅ ይመስላል፤ እግዚአብሔር ቀደም ብሎ በእርሱ ላይ የምንጠቀምበትን መሣሪያ ያዘጋጀ ይመስላል፤ እርሱ ራሱ የዘላቂ እምነትን ዋጋ የተረዳው ይመስላል።

ደግሞም ከኢየሱስ የተነሣ ይረዳናል። በጌቴሰማኔና በጎልጎታ እግዚአብሔር ራሱ በማይገለጽ መንገድ የእግዚአብሔርን ስውርነት ለመጋፈጥ ተገዷል። ማርቲን ሉተር አጽናፈ-አቀፋዊውን ትግል ያጠቃለሉት «እግዚአብሔር ከእግዚአብሔር ጋር ሲታገል» በሚል ነበር። በዚያች የጨለማ ሌሊት፥ እግዚአብሔር ራሱ በእግዚአብሔር መተው የሚያስከትለውን ስሜት ጥልቅ ግንዛቤ፥ አግኝቷል።

የኢዮብ ወዳጆች እግዚአብሔር እንዳልተሰወረ ተናግረዋል። ቀደም ሲል እግዚአብሔር እንዴት ራሱን ለእግዚአብሔር እንደገለጸ ለማሳየት እንደ ሕልሞች፥ ራእዮች፥ የቀድሞ በረከቶች የተፈጥሮን ውበቶች ዓይነት አስታዋሾች አቀረቡለት። «በብርሃን ውስጥ የተማርኸውን ወደ ጨለማ ስትገባ አትዘንጋ» ሲሉ ገሰጹት። ከኢዮብ በኋላ የምንኖረው እኛ ደግሞ ከዚያ የበለጠ ብርሃን አለን፤ ይኸውም የተፈጸመ ትንቢት ዘገባና የኢየሱስ ሕይወት ማጣቀሻዎችን መሆኑ ነው። ይሁንና፥

አንዳንድ ጊዜ ሁሉም ግንዛቤዎች ወይም «ማረጋገጫዎች» መንገድ ይለቃሉ። ምንም ያህል አስደሳች ዜና ቢኖረውም፥ ባዶ ትውስታ ሥቃይን ወይም ብቸኝነትን የመግደል ዓቅም አይኖረውም። ምናልባትም ለጊዜው ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችና የማነቃቂያ መፈክሮች የመርዳት ዓቅም ላይኖራቸው ይችላል።

ሦስት ምላሾች

እግዚአብሔር ሊደበቅብኝ የምሰጠውን ተለምዶአዊ ምላሽ ደህና አድርጌ አውቀዋለሁ፤ እኔም እርሱን በመተው እበቀለዋለሁ። በእጁ ፊቱን በመጋረድ ከአዋቂዎች ሊደበቅ እንደሚችል የሚያስበውን ሕፃን ልጅ በሚመስል ሁኔታ፥ እግዚአብሔርን ከሕይወቴ በር ውጭ ላስወጣው እጥራለሁ። ራሱን ካልገለጸልኝ ለምን ስለ እርሱ እጨነቃለሁ።

መጽሐፈ ኢዮብ እንዲህ ላለው ከእግዚአብሔር ጋር ለሚደረግ ቅይማት ሁለት ሌሎች ምላሾችን ይሰጠናል። የመጀመሪያው ምላሽ የታየው እጅግ መሠረታዊ በሆነው የእምነታቸው መመሪያ ላይ በሰነዘረው ጥቃት ኃፍረት በተሰማቸው የኢዮብ ጓደኞች ነበር። የኢዮብ የጠለቀ ቅይማት ከእነርሱ ሥነ-መለኮታዊ ግንዛቤ ጋር አልተዛመደም ነበር። አንድ ራሱን ጻድቅ በሚያደርግና ጻድቅ እንደሆነ በሚያውቁት አምላክ መካከል ግልጽ ልዩነት ተመለከቱ። የኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገር መሻት ራሱ ገረማቸው። እናም ስሜቱን እንዲቆጣጠር ነገሩት። እግዚአብሔር ፍትሕ-አልባ እንዳልሆነ በርግጠኝነት የሚያውቁ መሆናቸውን በመግለጽ እንዲህ ዓይነቱን አሳብ እንዲያስወግድ መከሩት። የሚናገራቸው የመራርነት ቃላት ሊያሳፍሩት እንደሚገባ ገለጹለት።

ሁለተኛው ምላሽ የኢዮብ ነበር። ከጓደኞቼ የማያከትም አመክኒዩ በተቃራኒ፥ ኢዮብ የቁጣ ዶፍ ነበር ያወረደው። «ስለ ምን ከማኅፀን አወጣኸኝ? ዓይን ሳያየኝ ምን ነው በሞትሁ» ሲል ለእግዚአብሔር ተናገረ። ኢዮብ የታሰረች ወፍ እንደምታደርገው መፍጨርጨር ከንቱ የሆነውን የተቃውሞ ትግል ያፋፍም ጀመር። አንዳንድ ጥሩ የመከራከሪያ አሳቦች የነበሩት ሊሆን፥ የጓደኞቹ አመክኒዩ ትክክል እንደሚመስልም ተቀብሏል። ከራሱ ጋር እየተጋጨ በጭንቀት እስከ መዋጥ ደርሶአል። ይህ በጽድቁ የታወቀው ሰውዬ በእግዚአብሔር ላይ ያጉረመርም ጀመር፤ «ወደ ማልመለስበት ስፍራ፥ ወደ ጨለማና ወደ ሞት ጥላ ምድር፥ እንደ ጨለማም ወደ ጨለመች፥ ሥርዓትም ወደ ሌለባት ወደ ሞት ጥላ፥ ብርሃንዋም እንደ ጨለማ ወደ ሆነ ምድር ሳልሄድ፥ ጥቂት እጽናና ዘንድ ተወኝ፥ ልቀቀኝም።»

ከእነዚህ ሁለት ምላሾች የትኛው ተቀባይነት አገኘ? ሁለቱም ወገኖች እርማት የሚያስፈልጋቸው ቢሆንም፥ ከእነዚያ ሁሉ ማለቂያ የሌላቸው ንግግሮች በኋላ እግዚአብሔር ቅዱሳን ጓደኞቹ በንስሐ ወደ ኢዮብ እንዲመጡና እርሱ እንዲጸልይላቸው ያዛል።

በመጽሐፈ ኢዮብ ውስጥ የምንመለከተው አንድ ጠንካራ መልእክት ቢኖር ለእግዚአብሔር የትኛውንም ዓይነት ነገር ልትናገር እንደምትችል ነው፤ ኃዘንህን፥ ቁጣህን፥ ጥርጣሬህን፥ መራርነትህን፥ መከዳትህን፥ ቅይማትህን ሁሉ በእርሱ ላይ ብትወረውር፥ ሁሉንም እንደ ሰፍነግ የመምጠጥ ብቃት አለው። መንፈሳዊ ጀግኖች ብዙውን ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ሊደራደሩ አንመለከትም። በእግዚአብሔር ላይ ከመናገሩ ይልቅ እንደ ያዕቆብ እያነከሱ ሊሄዱ ይመርጣሉ። በዚህ ረገድ፥ መጽሐፍ ቅዱስ የአሁኑን ዘመን-የሥነ-ልቦና መርህ ቀደም ብሎ ያስቀምጣል፤ ይህም ስሜቶችህን ልትክድ ወይም እንዲጠፋ ልታደርግ ስለማትችል፥ ልትገልጻቸው ትችላለህ የሚል ነው። እግዚአብሔር ከአንድ በቀር የሰውን ልጅ ምላሾች ሁሉ ሊያስተናግድ ይችላል። እኔ በልማድ አደርግ የነበረውን ዓይነት እርሱን የማግለል ወይም እንደሌለ ቆጥሮ የመተውን ጥረት አይቀበልም። በኢዮብ ሕይወት ውስጥ ከቶውንም ይኼ ምላሽ አልነበረም።

ትልቁ ምስል

ከመጽሐፈ ኢዮብ የምንጨብጠው ትምህርት ስሜቶቻችንን የመግለጽ ነጻነት ብቻ አይደለም። በማይታየው ዓለም ውስጥ «ከመጋረጃ በስተጀርባ» የሚካሄደው ትእይንት ከእግዚአብሔር ስውርነት ጋር የሚደረገው ተጋፍጦ የተሳሳተ መረዳት ሊያገኝ እንደሚችል ያሳያል። ይህ እግዚአብሔርን እንደ ጠላትና ስውርነቱን ደግሞ ለሰው ልጅ እንዳለማሰብ አድርጎ ወደ መረዳቱ አቅጣጫ ሊነዳ ይችላል።

ኢዮብ የደመደመው በዚህ መልኩ ነው፤ «በቁጣው ቀደደኝ፥ እርሱም ጠላኝ።» ትእይንቱን የምንመለከተው እኛ ኢዮብ እንደተሳሳተ እናውቃለን። ቀድሞ ነገር እግዚአብሔር በራሱ አነሣሽነት የኢዮብን ችግሮች እንዳላስከተለ ቅድመ-ታሪኩ በተዘዋዋሪ መንገድ ያሳየናል። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ፈቃድ የሰጠ ቢሆንም፥ የውርርዱ ታሪክ ለኢዮብ መከራ ጠንሳሽ የሚያደርገው ሰይጣንን እንጂ እግዚአብሔርን አይደለም። በእግዚአብሔር ከመተው በራቀ ሁኔታ፥ ኢዮብ ቀጥተኛና በአጉሊ መነጽር እንደሚደረግ ምርመራ እየታየ ነበር። ኢዮብ በፍርድ ችሎት ቀርቦ ከእግዚአብሔር ጋር ለመደራደር በሚጠይቅበት በዚያ ሰዓት ለአጽናፈ-ዓለሙ በሚበጅ ችሎት ውስጥ የተሳታፊነት ሚና እየተጫወተ ነበር። ይህም በእግዚአብሔር ላይ ጣቱን እንደሚጠቁም

ዐቃቤ ሕግ ሳይሆን፥ የእምነትን ፈተና እንደሚመሰክር ዋንኛ ዋቢ ሆኖ ተቀምጦ ነበር።

ከዚህ ተነሥተን ግን የራሳችንም መከራዎች እንደ ኢዮብ ሁሉ በእግዚአብሔር የተወሰኑትን አንዳንድ የአጽናፈ-ዓለም ጉዳዮች ለማቃለል ሲባል የሚመጡ ናቸው ልንል አንችልም። በተስማሚው መንገድ ግን የራሳችንን ውስን የእይታ ብቃት እውነትን ሊያምታታ እንደሚችል እንገነዘባለን። ሥቃይ እይታን ይቀንሳል። እጅግ ግላዊነት የበዛበት ስሜት፥ ስለ ራሳችን ብቻ እንድናስብ ያስገድደናል።

ከመጽሐፈ ኢዮብ ከምንገምተው የላቀ ነገር በሌላው ስፍራ እየተካሄደ እንዳለ ልንማር እንችላለን። በኢዮብ ላይ የእግዚአብሔር ርቀት ስሜት ተጭኖአል፤ ነገር ግን ከመጋረጃው በስተጀርባ የሚካሄደውን ትእይንት መመልከቱ እግዚአብሔር እንደዚህ የቀረበበት ጊዜ እንደሌለ ያሳያል። በተፈጥሮአዊው ዓለም የሰው ልጆች ከ 30 በመቶ በላይ የብርሃን ቀለሞችን ዳርቻ (light spectrum) ሊመለከቱ አይችሉም። (እንደ ንብ ዓይነቶቹ ነፍሳት ግን ለእኛ የማይታዩትን የአልትራቫዮለት የብርሃን ሞገዶች ለማየት ይችላሉ።) የልዕለ-ተፈጥሮአዊ ዓለም እይታችን ደግሞ ከዚያ ያነሰ በመሆኑ፥ አልፎ አልፎ የዚያን የማይታይ ዓለም ጨረፍታ ከማየት የተሻለ ተግባር ልንከውን አንችልም።

በሌላው ታዋቂ የመጽሐፍ ቅዱስ ገጸ-ባሕርይ ሕይወት የተከሰተው ገጠመኝ ይህንኑ ተመሳሳይ ነጥብ በተለየ መንገድ ያሳየናል። ነቢዩ ዳንኤል ከኢዮብ ጋር ሲነጻጸር፥ የእግዚአብሔርን ስውርነት እጅግ ትሑት በሆነ መንገድ ያስተናግድ ነበር። ዳንኤል በየዕለቱ የሚያቀርባቸው ጸሎቶች ባለመመለሳቸው ግራ ተጋባ፤ እግዚአብሔር ባለማቋረጥ የሚያቀርባቸውን ጥያቄዎች ለምን ችላ እንደሚል ገረመው። ለሃያ አንድ ቀናት ዳንኤል ተግቶ ሊጸልይ ገባ። ከጮማና ወይን ተለይቶ ሰውነቱንም ላይነከባከብ ቆረጠ። በዚህ ጊዜ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ቢጮኽም ምላሽ አላገኘም።

አንድ ቀን ዳንኤል ከጠበቀው የላቀ ምላሽ አገኘ። እንደ መብራት የሚያበሩ ዓይኖችና እንደ መብረቅ የሚያንጸባርቅ ፊት ያለው አንድ ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኑባሬ ከወንዝ ዳር ከች አለለት። ከዳንኤል ጋር የነበሩ ሰዎች ሁሉ በፍርሃት ርደው ከመሬት ላይ ተዘረሩ። ዳንኤልም ስለ ራሱ፥ «ኃይልም አልቀረልኝም፥ ደም ግባቴም ወደ ማሽቀሽቀ ተለወጠብኝ» ብሏል። በብርሃናት ከተንቆጠቆጠው ህላዌ ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ፥ መተንፈስ ተሳነው።

ጎብኚው ለረዥም ጊዜ የዘገየበትን ምክንያት ገለጸለት። የዳንኤልን የመጀመሪያ ጸሎት ከሰማበት ጊዜ አንሥቶ መልስ ለመስጠት

ተዘጋጅቶ ሳለ «የፋርስ መንግሥት አለቃ» እንደ ተቋቋመው አስረዳው። በመጨረሻም ከሦስት ሳምንታት ቆይታ በኋላ፥ ከዋንኞቹ መላእክት አንዱ የሆነው ሚካኤል ተቃውሞውን ጥሶ እንዲያልፍ ሊረዳው ቻለ።

ከመጽሐፈ ኢዮብ ጋር ያለውን ተመሳሳይነት ከመጥቀስ ውጭ፥ አጽናፈ-ዓለሙ በውጊያ ላይ የተሰማራበትን ይህንን አስደናቂ ትእይንት ለመፍታት አልጥርም። ምንም እንኳ አብዛኛው እንቅስቃሴ የተካሄደው ከእይታው በራቀ ሁኔታ ቢሆንም፥ ዳንኤልም እንደ ኢዮብ በመልካምና ክፉ መካከል በሚደረገው አጽናፈ-አቀፋዊ ጦርነት ውስጥ ወሳኝ ሚና ተጫውቷል። ለእርሱ ጸሎት ከንቱ፥ እግዚአብሔርም ግድየለሽ ሊመስለው ይችላል። ነገር ግን «ከመጋረጃው በስተያ» ያለውን ትእይንት መመልከቱ የዚህን ተገላቢጦሽ ያሳያል። እንደ ኢዮብ ሁሉ፥ የዳንኤል ውስን አመለካከት እውነታን አዛብቷል።

በመጽሐፈ ኢዮብ ከሚታየው ውርርድ ባሻገር፥ ድጋፍ ስላስፈለገው የትንቢተ ዳንኤሉ መልአክ ጉዳይ ምን ልንል እንችላለን? ነገሩ ይኸው ነው፤ አጽናፈ-ዓለሙን ሁሉ እንደ መድረክ ጀርባ ያዘለው ትልቁ ምስል ልንመለከት የማንችለውን በርካታ ትእይንት ያካተተ ነው። በመከራ ጊዜ ጸንተን በእግዚአብሔር ላይ ብንደገፍ ወይም ዝም ብለን ብንጸልይ፥ አሁንም አብዝተን ብንጸልይ፥ ከምናልመው በበለጠ ሁኔታ የዚያ ትእይንት ተካፋዮች ልንሆን እንችላለን። ይህንን ለማመን እምነት ያስፈልጋል፤ ፍጹም እንዳልተተውን ለመረዳት እምነት ያስፈልጋል።

ኢዮብ በመጨረሻው ድምፁን በዐውሎ ነፋስ ውስጥ ሲሰማ ያንን እምነት አገኘ። እግዚአብሔር ኢዮብ ሊረዳ የማይችላቸውን እንደ የፀሐይ እንቅስቃሴ፥ ከዋክብት፥ ማዕበሎች፥ የዱር አራዊት የመሳሰሉ ተፈጥሮአዊ ክስተቶችን ያከታትል ጀመር። *«የምትኖርበትን የሚታይ ዓለም ልትረዳ ካልቻልህ፥ የማይታየውን ዓለም እንዴት ለመረዳት ትደፍራለህ!»* በመጨረሻው ትልቁን ምስል በመረዳቱ፥ ኢዮብ በአፈርና በአመድ ላይ ሆኖ ተጸጸተ፤ ንስሐ ገባ።

«እግዚአብሔር ከተደበቀበት ሆኖ ጎሮሮውን በማጽዳት ራሱን እንደሚያጋልጥ ሰው ነው።»

– ሚይስተር ኤክሃርት

[1]C.S.Lewis, *AGrief Observed*, 9.

[2]Allen Boesak *"If You Believe,"*Reformed Journal, (November1985), 11.

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፡– ኢዮብ 10፥ 6፤ ዳንኤል 10።

«እኔ ግን የሚቤዠኝ ሕያው እንደ ሆነ፥
በመጨረሻም ዘመን በምድር ላይ እንዲቆም፥
ይህ ቁርቤቴም ከጠፋ በኋላ፥
በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተለይቼ እግዚአብሔርን
እንዳይ አውቃለሁ፤
እኔ ራሴ አየዋለሁ፥
ዓይኖቼም ይመለከቱታል፥
ከእኔም ሌላ አይደለም።
ልቤ በመናፈቅ ዝሎአል።»

– ኢዮብ 19፡25–27

ምዕራፍ 29

ኢዮብ ለምን ደስተኛ ሆኖ ሞተ?

ኃዘን፥ ዋይታና የመረረ ሙግት ከተመዘገበበት የውርርድ ውጣ ውረድ በኋላ፥ የኢዮብ ታሪክ የልጅ–ልጅ–ልጅ ልጆችን በሰላም በሚያጫውትበት አስደሳች መልኩ ይጠናቀቃል። መጽሐፉ ለኢዮብ የተመለሱለትን በረከቶች በጥንቃቄ ይዘረዝራል፤ 14,000 በጎች፥ 6000 ግመሎች፥ 1000 አህዮች እና 10 አዳዲስ ልጆች።

ይኸው የመጽሐፈ ኢዮብ አስደሳች ፍጻሜ የኖቤል ሽልማት አሸናፊ የሆነውን ደራሲ ኤል ዊስልን ጨምሮ አንዳንድ አንባቢዎችን ያሳስባል። ለዚህ ደራሲ፥ ኢዮብ የእግዚአብሔርን ኢ–ፍትሐዊነት በመቃወም የጀግንነት ሚና ሲጫወት ነበር። ይሁንና፥ በዊስል ግንዛቤ ኢዮብ ይሸነፋል። ኢዮብ እግዚአብሔርን መርዳት አልነበረበትም። የትኛውም ያህል የብልጽግና ስጦታ ኢዮብ የተቀበለውን መከራ ሊያካክስ አይችልም። የሞቱትን አሥር ልጆቹስ ኃዘን ይፍቅለታል ብሎ ለአፍታም አንኳ የሚያምን ሰው አይኖርም።

ይሁንና፥ እስኪ ኢዮብ ስለ ራሱ ይናገር። እግዚአብሔር ከዐውሎ ነፋሱ ውስጥ ሆኖ ግርማ ሞገስን በተላበሰ ድምፅ ከተናገረው በኋላ ኢዮብ እንዲህ ብሏል፦

«እኔ የማላስተውለውን፥ የማላውቀውንም ድንቅ ነገር ተናግሬአለሁ. . .
መስማትንስ በጆሮዬ ሰምቼ ነበር፤ አሁን ግን ዓይኔ አየችህ፤

ስለዚህ ራሴን እንቃለሁ፤ በአፈርና በአመድ ላይ ተቀምጬ እጸጸታለሁ።»

የእግዚአብሔር «ምላሽ– አልባነት» ኢዮብን ሙሉ ለሙሉ እንዳረካው እንመለከታለን።

በሌላ በኩል፥ አንዳንድ አንባቢያን አስደሳቹን ፍጻሜ ከእግዚአብሔር ጋር ለሚደረገው ቅይማት እንደ የመጨረሻው ምላሽ አድርገው ይወስዳሉ። «ተመልከቱ፥ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከአስቸጋሪ ሁኔታ ያድናቸዋል» ሲሉ ይናገራሉ። «እግዚአብሔር የኢዮብን ጤንነትና ሀብት መልሶለታል፤ እኛም እንደ ኢዮብ በእግዚአብሔር ብንታመን ይህንኑ ያደርግልናል።» ይሁንና፥ እነዚህኞቹ አንባቢዎች አንድ ጠቃሚ ጉዳይ ዘልለው አልፈዋል፤ ይህም ካጣቸው ነገሮች የትኞቹም ከመመለሳቸው በፊት ኢዮብ እንደተጸጸተ የሚያሳዩትን ቃላት መናገሩ ነው። ገና በፍርስራሹ ውስጥ ተራቁቶና ቆሳስሉ እያለ ነበር እግዚአብሔርን የሚያመሰግነው። የተለወጠው አንድ ነገር ብቻ ነበር፤ እግዚአብሔር የትልቁን ምስል ጨረፍታ ለኢዮብ አሳይቶታል።

እግዚአብሔር ከኢዮብ ላይ ያስከተለውን ዓይነት የላቀ ውጤት ለማግኘት ሊናገር የሚችለው ነገር የነበረ አይመስለኝም። የተናገራቸው ቃላት የመገኘቱን ያህል አስፈላጊነት አልነበራቸውም። እግዚአብሔር በሚያስደምም ሁኔታ የኢዮብን ጥያቄ መልሶአል፤ ጥያቄውም፥ «እግዚአብሔር አለ ወይ?» የሚል ነበር። ኢዮብ አንድ ጊዜ የማይታየውን ዓለም መኖር ከተመለከተ በኋላ አሳሳቢ ጥያቄዎቹ ሁሉ ደብዝዘው ተሰወሩ።

በእግዚአብሔር አመለካከት በአደጋ ላይ ከወደቁት የአጽናፈ–ዓለም ጉዳዮች አንጻር፥ የኢዮብ መጽናናት ከፍተኛ ስፍራ የሚሰጠው አልነበረም። እውነተኛው ጦርነት ያከተመው ኢዮብ በእግዚአብሔር ላይ ተስፋ ላለመቁረጥ በመወሰን ሰይጣንን ለሽንፈት በዳረገበት ወቅት ነው። ከዚያ ከባድ ድል በኋላ፥ እግዚአብሔር በኢዮብ ላይ መልካም ስጦታዎችን ለማዝነብ ተጣደፈ። ሥቃይ ነው? እኔ በቀላሉ ላስተካክለው እችላለሁ። ተጨማሪ ልጆች? ግመሎችና በሬዎች? ችግር የለም! ደስተኛ፥ የበለጸገና የተትረፈረፈ ሕይወት እንድትኖር እፈልጋለሁ! ይሁንና፥ ኢዮብ፥ ከደስተኛነት የላቀ ነገር ከአደጋ ላይ ወድቆ እንደነበር ልትገነዘብ ይገባል።

የሁለት ዓለማት

መጽሐፈ ኢዮብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሁሉ እጅግ ታማኝ አድርጎ የሚመለከተው ወዳጄ ሪቻርድ አሁንም ለድምዳሜው ሌላ ምላሽ አለው። በእርሱ ግንዛቤ፥ መጽሐፈ ኢዮብ ከሌሎች ሰዎች

ሕይወት ጋር የሚዛመድ ነገር የለውም። «ለኢዮብ እግዚአብሔር በአካል ተገልጾለታል። እናም ስለ እርሱ ደስ ይለኛል። እኔም በእነዚህ ሁሉ ዓመታት ስጠይቅ የኖርሁት ይህንኑ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ሳይገበኘኝ፥ ኢዮብ እንዴት ሊረዳኝ ይችላል?

ሪቻርድ ያተኮረው አስፈላጊ በሆነ የእምነት መለያ መስመር ላይ እንደሆነ አምናለሁ። በአንድ መልኩ፥ የምድር ላይ ሕይወታችን እግዚአብሔር በነፍስ ማዕበል ሳይገለጽለት በፊት ኢዮብ ያሳለፈውን ይመስላል። እኛም ራሳችን የምንኖረው ኃያልና አፍቃሪ ስለሆነው አምላክ መኖር በሚጎተቱ ፍንጮችና ጭምጭምታዎች ውስጥ ነው። እኛም ያለምንም እርግጠኝነት ልናምን ይገባል።

ሪቻርድ እግዚአብሔር ራሱን «ይገልጽ ዘንድ» በመለመን ከቤቱ ወለል ላይ ወድቆ ሲጸልይ ቆይቷል፤ ይህም ለኢዮብ እንዳደረገው እግዚአብሔር ወደሚታየው ዓለም ውስጥ ጣልቃ እንዲገባ በመጠየቅ ነበር። ይህንኑ በማድረግ በእምነቱ ቁማር ተጫወተ። በቁማር ጨዋታው ግን ተሸናፊ ሆነ። እውነቱን ለመናገር፥ እግዚአብሔር በዚህ ዓይነት ሁኔታ ራሱን የማረጋገጥ «ግዴታ» የሚሰማው መሆኑን እጠራጠራለሁ። ብዙ ጊዜ በብሉይ ኪዳን ይህንን አድርጓል፤ በመጨረሻም በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ተገልጾአል። ከዚህ በላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የምንጠይቃቸው መገለጾች ምንድን ናቸው?

ይህንን የምለው በከፍተኛ ጥንቃቄ ነው። ዳሩ ግን ለተአምራት፥ ለሥጋዊ ፈውስ ሳይቀር ከመጠን በላይ መጓጓቱ አንዳንድ ጊዜ የእምነትን መኖር ሳይሆን አለመኖር እንደሚያመለክት አስባለሁ። እነዚህ እንደ ሪቻርድ ዓይነቶቹ ጸሎቶች ለእግዚአብሔር ቅድመ-ሁኔታዎችን ያስቀምጣሉ። ለአንድ ችግር ተአምራዊ መፍትሔ በምንፈልግበት ጊዜ፥ ለእርሱ የሚኖረን ታማኝነት በሚታየው ዓለም ውስጥ ራሱን ይደግፋል?*

ከእግዚአብሔር ዘንድ የግድ የሚታይ ማረጋገጫ የምንፈልግ ከሆነ፥ ለዘለቄታዊ ቅይማት መንገድ እየጠረግን ሊሆን ይችላል። እውነተኛ እምነት እኛ ፈቃዱን እንድናደርግ የሚያነሣሣንን ያህል እግዚአብሔር

---

*ከምሕረቱ የተነሣ፥ እግዚአብሔር ድብልቅ ዓላማ ያለባቸውን ጸሎቶች ሊመልስ ይችላል፤ «ጌታ ሆይ፥ ከዚህ ብቻ ካወጣኸኝ. . .» ተብለው የሚቀርቡለትን የምሽግ ውስጥ ዓይነት ጸሎቶች ሊሰማ ይችላል። ነገር ግን ይህንን መወሰኑ የእርሱ እንጂ የእኛ ድርሻ አይደለም።

የእኛን ፈቃድ እንዲያደርግ ለማስገደድ አይጥርም። የታላቅ እምነት ሞዴሎች የሆኑትን ሰዎች ለማግኘት መጽሐፍ ቅዱሴን በማስስበት ወቅት፥ ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገውን ዓይነት አስደናቂ ገጠመኝ ያሳለፉ ግለሰቦች ምን ያህል ጥቂቶች እንደሆኑ በመመልከት ተደንቄአለሁ። ሌሎች ሰዎች ለእግዚአብሔር ስውርነት ምላሽ የሰጡት ራሱን እንዲገልጽ በመጠየቅ ሳይሆን፥ እርሱ ተደብቆ እያለ ወደፊት በመቀጠልና በእምነታቸው በመጽናት ነበር። ዕብራውያን ምዕራፍ 11 የእምነት ጀግኖች፥ «የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል አላገኙምና፥ ዳሩ ግን ከሩቅ ሆነው አዩትና ተሳለሙት» ይላል።

እኛ የሰው ልጆች በተለምዶ የሚታየውን ዓለም እንደ «እውነተኛው» ዓለም፥ የማይታየውን ደግሞ «እውነተኛ እንዳልሆነ» ዓለም አድርገን እንወስዳለን፤ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስቀምጥልን ግን በተገላቢጦሽ ነው። በእምነት አማካኝነት፥ የማይታየው ዓለም እውነተኛውን ዓለም ቅርጽ ይይዝና በሚታየው ዓለም ውስጥ እንዴት መኖር እንዳለብን መመዘኛውን ያቀርብልናል። ኢየሱስ ክርስቶስ ስለማይታየው ዓለም ወይም «መንግሥተ ሰማይ» ሲናገር፥ ለማይታየው አምላክ እንጂ ለሰዎች እንዳንኖር ገልጾአል።

አንድ ጊዜ ሐዋርያው ጳውሎስ ከእግዚአብሔር ጋር የመቀያየምን ጥያቄ በቀጥታ ገልጾአል። ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲጽፍ፥ ምንም እንኳ ተከታታይ መከራ ቢደርስበትም እንዳልታከተ ገልጾላቸዋል፤ «ነገር ግን የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል። የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና፥ የሚታየው የጊዜው ነውና፥ የማይታየው ግን የዘላለም ነው።»

የወደፊት ቅምሻ

ጳውሎስ መከራዎችን የታገሠ ሲሆን፥ የሞተውም በሰማዕትነት ነው። ሽልማቱ ገና ወደፊት ይጠብቀዋል። ኢዮብ መከራ ተቀብሎ ሲያበቃ በዚህ ምድር ሽልማት አግኝቷል። እኛ ከእግዚአብሔር ልንጠብቅ የምንችለው ነገር ምንድን ነው? ምናልባትም የኢዮብን ታሪክ አጨራረስ ልንመለከት የሚገባን ለእኛ በዚህ ምድር እንደሚሰጠን በረከት ምሳሌ ሳይሆን፥ ወደፊት የሚመጣውን ነገር ምልክት አድርገን ነው። በዚህ መልኩ ከታየ፥ መጽሐፈ ኢዮብ እንደ ጣፋጮ፥ አርኪ ተምሳሌት፥ ለሁላችንም የወደፊቱን ሕይወት ጣዕም የሚያቀርብ የአንድ ሰው የቅይማት መፍትሔ ይሆናል።

በአንድ መልኩ፥ ኤል ዊስል ትክክል ነው፤ ኢዮብ በስተ እርጅናው ያገኛቸው በረከቶች ቀደም ሲል ያጣውን አያካክሉለትም። ዕድሜ ጠግቦ በደስታ የሞተው ኢዮብ እንኳ ያለፈው ኃዘንና ሥቃይን በሕይወት ለነበሩት ትቶ ነው። እናም ከሁሉም የሚከፋው ስሕተት እግዚአብሔር ለዚህች ፍትሕ-አልባና አሳዛኝ ዓለም አንዳንድ አነስተኛ ለውጦችን በማድረግ እንደሚረካ አድርጎ ማሰቡ ይሆናል።

አንድንድ ሰዎች እምነታቸውን ለተአምራት ሲሉ ከአደጋ ላይ ይጥላሉ፥ ተአምራት ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረጉትን ቅይማቶች ሁሉ እንደ ጎርፍ ውኃ ጠራርጎ የሚወስድ ይመስል። ይህ አይሆንም። የዚህን መጽሐፍ ገጾች ከሪቻርድ፥ ሜግ ዉድሰን፥ ዳግላስና ኢዮብ ይልቅ በአካላዊ ፈውስ መቀያየም አያስወግደውም ነበር። አሁንም በዚህች ምድር አንድ ችግር አለ። ሁላችንም መሞታችን አይቀሬ ነው፤ ሞት ለከሀዲውም ለቅዱሱም የማይቀር ነው።

ተአምራት የወደፊቱን ሕይወት እንደሚያመለክቱ ምልክቶች ናቸው። ከዚህ ለበለጠና ዘላለማዊ ለሆነ ነገር የሚቀሰቅሱን ናቸው። የኢዮብ የበስተ እርጅናው ደስተኛነት ከሞት በኋላ የሚደሰትበት ነገር ናሙና ብቻ ነው። ከመጽሐፈ ኢዮብና ከወንጌላት በስተ መጨረሻ የቀረቡት የምሥራቾች በዮሐንስ ራእይ መጨረሻ ላይ የተገለጸው የምሥራች ቅድመ-ምልከታዎች ናቸው። እግዚአብሔር የሚፈልገውን ዓለም ከማየት ልንታቀብ አይገባም።

የመጽሐፈ ኢዮብ ምዕራፍ 42 የተሰፋ ቃል የሚያመለክተው እግዚአብሔር የዘመናችን መለያ የሆነውን ትክክለኛነት የራቀው ነገር ወደ ትክክለኛነት እንደሚለውጥ ነው። ለምሳሌ ያህል፥ የኢዮብ ልጆች ወይም የሜግ ዉድሰን ልጆች ሞትን የመሳሰሉ አንዳንድ ኃዘኖች በዚህ ዓለም ፈውስ ሊገኝላቸው አይችልም። የትኞቹም የማጽናኛ ቃላት በሜግ ዉድሰን ልብ ውስጥ ያጎነቆለውን ኃዘን ሊቀንሱ አይችሉም፤ ያ ኃዘን የተወሰነ ቅርጽ ስላለው -የልጆቿ የፔጊና የጆይ ቅርጽ። በዘመን መጨረሻ ግን ያም ኃዘን ይወገዳል። ሜግ ልጆቿን ዳግም ተሠርተው ታገኛቸዋለች። ፔጊና ጆይ በአሁኑ ጊዜ የደስታ አየር እየተነፈሱ አዲሱን ዓለም በማሰስ ላይ መሆናቸውን ባላምን ኖሮ፥ ምንም ነገር ላምን አልችልም ነበር፤ የክርስትና እምነቴንም ገና ድሮ በተውሁት ነበር። «በዚህች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ፥ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን።»

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ክብር አሸንፎ ሰማይንና ምድርን ወደ ቀደመው የፍጹምነት ደረጃቸው በመመለስ ብቃቱ ላይ

ይወስነዋል። ያ የወደፊት መንግሥት እስኪመጣ ድረስ፥ እግዚአብሔር ኃይል እንደሌለው ወይም አፍቃሪነት እንደሚጎድለው ሊነገር ይችላል።* እስካሁን ነቢያት ስለ ሰላምና ፍትሕ የተናገሩት አልተፈጸሙም። ሰይፎች ወደ ማረሻነት እየተለወጡ አይደለም። በአዲስ አስቀያሚ የኤድስ ጥቃትና ካንሰር እየታገዘ ሞት ሰዎችን ሲውጥ እንጂ ሲዋጥ አንመለከትም። ክፉው እንጂ መልካም ድል ሲነሣ አንታዘብም። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ከሰፊው የታሪክ እውነታ ባሻገር የእግዚአብሔር አገዛዝ ምድርን ወደሚሞላበት ወደ ዘላለሙ መንግሥት እንድንመለከት ያበረታታናል።

ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖረው ቅይማት በሚደረግ በየትኛውም ውይይት፥ መንግሥተ ሰማይ የመጨረሻው ቃል ነው–ከሁሉም በላይ እጅግ አስፈላጊ የሆነ ቃል። የእግዚአብሔርን ድብቅነት በመጨረሻው የሚፈታው መንግሥተ ሰማይ ብቻ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ፥ ሰዎች እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ያዩታል። በሥቃዩ መሐል ኢዮብ፥ «ከሥጋዬ ተለይቼ እግዚአብሔርን እንዳይ አውቃለሁ፤ እኔ ራሴ አየዋለሁ» ሲል ተናግሯል። ያ ትንቢት ለኢዮብ ብቻ ሳይሆን ለሁላችንም እውነት የሚሆንበት ቀን ይመጣል።

ናፍቆት

አንዳንድ ሰዎች እንዲህ ዓይነቱን የወደፊት ሁኔታ እንኳ በምናባቸው ለማየት ይቸገራሉ። ቻርልስ ዊሊያምስ እንዳሉት፥ «አንድን መልካም ነገር ከሆነ ስፍራ ላይ እንከን ሳናወጣለት እንዳንቀር የምድር ላይ ተሞክሮአችን ችግር ይፈጥርብናል።»[2] ሙሉ ለሙሉ የማንረዳውን የወደፊት ሕይወት አሻግሮ ከመመልከት ይልቅ፥ የአሁኖቹን ያልተፈጸሙ ሕልሞች –ቅይማቶች ማየቱን እንመርጣለን።

ለአንድ ስደተኛ፥ መንግሥተ ሰማይ ሰላም ያለበትን፥ ቤተሰብ ደግሞ የተሰባሰበበትን፥ እንደ ምግብና ንጹሕ ውኃ የሚገኙበትን፥ የአዲስ አገር ሕልም ይወክላል። (ብዙዎቹ ነቢያት ለስደተኞች {መጻተኞች} ስለተናገሩ፥ እንዲህ ዓይነቶቹን ምድራዊ ምሳሌዎች ለምን እንደተጠቀሙ ልንረዳ እንችላለን።)

ሁላችንም በተወሰነ ደረጃ እንዲህ ዓይነት ናፍቆቶች አሉን። ይህ ዓለም በብክለት፥ በጦርነት፥ በወንጀልና በስግብግብነት የተሞላ

---

* በአንድ ወቅት ስፔናዊው የተመሰጠ ብሂል አራማጅ ኡናሙኖ ከአንድ ገበሬ ጋር ሲነጋገር፥ ምናልባትም አምላክ እንዳለና መንግሥተ ሰማይ እንደሌለ ገልጾ ነበር። ገበሬውም ጥቂት ካሰበ በኋላ፥ «ታዲያ ይኼ አምላክ ምን ይሠራል?» ሲል መልሶለታል።

ቢሆንም፥ በሁላችንም ውስጥ ዓለም ምን ዓይነት ልትሆን እንደምትችልና እኛም እንዴት ልንሆን እንደምንችል የሚያስታውስ ነገር አለ። እንዲህ ዓይነቱን ናፍቆት ዓለምን በንጹሕ ገጽታ ለመኖር የሚታገሉ ወገኖች ባሉበት የአካባቢያዊነት እንቅስቃሴ ውስጥ ልትመለከት ትችላለህ። ዓለም ከጦርነት ነፃ እንድትሆን በሚጣርበት የሰላም እንቅስቃሴ፥ የፈራረሰውን ጓደኝነትና ፍቅር ለመጠገን በሚሞከርበት የሥነ-ልቦና ተግባራት ሁሉ ውስጥ ናፍቆቱ በጉልሕ ይስተዋላል። በምድር ላይ የምናገኘው ውበትና ደስታ ሁሉ «ያላጋጠመንን መልካም የአበባ ሽታ፥ ያልሰማነውን የገደል ማሚቶ፥ ካልነበኘነው አገር የሚተላለፈውን ዜና»[3] ይወክላል።

ነቢያት እንዲህ ዓይነት ግንዛቤዎች ባዶ ቅዠቶች ሳይሆኑ፥ ወደፊት የሚፈጸመው ነገር ቀዳሚ ማሚቶዎች እንደሆኑ ይናገራሉ። ስለዚያው የወደፊት ዓለም የተሰጠን ዝርዝር መግለጫ በጣም ውስን ነው። ይሁንና፥ እግዚአብሔር የራሱን ታማኝነት የሚያረጋግጥበት የተስፋ ቃል ነው። ወደ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ስንገባ፥ የምንናፍቀውን ሁሉ እናገኛለን። ከመጥፎ ዜናዎች ሁሉ አስደናቂ የምሥራቾች ይወጣሉ፤ ምንም አንከን የሌለበት መልካም ነገር ሰማይና ምድር ደግሞ እግዚአብሔር ባቀደላቸው መንገድ ይንቀሳቀሳሉ። ከሁሉም በኋላ አስደሳች ፍጻሜ ይከሰታል።

ለዚህ የምሥራች የምኞት ዓለም ደራሲ የሆነው ጄ. አር. አር. ቶኪን አዲስ ዓለም ፈጥሯል። ከሦስት ተከታታይ ሥራዎቹ መካከል "The Lord of the Rings" (የቀለበቶች ጌታ) የተባለው ይህንኑ ትእይንት ደህና አድርጎ ይገልጸዋል።

> «አሳዛኙ ነገር ሁሉ ላይሆን ነው ማለት ነው? ዓለም ምን ሆነች?» (ሲል ይጠይቃል ሳም)።
>
> «ታላቅ ጥላ ተነሥቷል» ይልና ጋንዳልፍ ይስቃል። አሁንም ይስቃል። ድምፁ እንደ ሙዚቃ ነበር ወይም ደግሞ በደረቅ ምድር ላይ እንደሚፈስ ውኃ። እያዳመጠ ሳለ ሳቅን ሰምቶ እንደማያውቅ ታሰበው፤ ለማይቆጠሩ ቀናት የሳቅ ድምፅ ሰምቶ አያውቅም። የሚያውቃቸውን ደስታዎች ሁሉ እንደሚያስተጋባ ማሚቶ ያህል ከጆሮዎቹ ላይ ወደቀ። እርሱ ራሱ ግን በእንባ ታጠበ። የዝናቡ ወቅት በፀደይ ነፋስ ተተክቶ ፀሐዩቱ ፍንትው ብላ እንደምትታይ ሁሉ፥ እንባው ቆመ፤ ሳቁ ተከማቸ፤ እየሳቀ ከአልጋው ላይ ተወርውሮ ተነሣ።
>
> «ምን ይሰማኛል?» ሲል ጮኸ። «ምን ብዬ እንደምገልጸው አላውቅም። የሚሰማኝ–የሚሰማኝ» እጆቹን ከአየሩ ላይ አወዛወዛቸው፤ «ከበጋ በኋላ እንዳለ ፀደይ፥ ከቅጠሎቹ ላይ

ፈሰስ እንዳለች ፀሐይ፥ እንደ መለከቶች፥ በገናዎችና እንደ ሰማሁዋቸው መዝሙሮች ሁሉ ይሰማኛል።

በሥቃይ፥ ወይም በፈራረሰ ኑሮ፥ ወይም በኢኮኖሚያዊ ኪሳራ፥ ወይም በፍርሃት ለሚናጡ ሰዎች ሁሉ፥ ለሁላችንም፥ በምድር ላይ ካሳለፍነው የላቀ ጤንነት፥ ሙላት፥ ደስታና ሰላም የሞላበት ነው። ይህንን የማናምን ከሆነ፥ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው እምነት ብሎ ነገር ባይኖረን ይሻላል፤ ያለዚያ ተስፋ፥ ተስፋ የለም።

መጽሐፍ ቅዱስ የሰውን ልጅ ቅይጣት አያሳንሰውም (በመጽሐፈ ኢዮብ ለመከራውና ለተሐድሶው የተሰጠውን የምዕራፎች ክፍፍል አስታውሶ ለአንድ ምዕራፍ ተሐድሶ አርባ አንድ ምዕራፍ ሥቃይ)። ነገር ግን አንድ ቁልፍ ቃል ያህላል፤ ጊዜያዊ። አሁን የሚሰማን ሁልጊዜም አብሮን አይኖርም። ቅይጣታችን ራሱ የአንድ የተሻለ ነገር ምልክት፥ ረሃብ፥ ሕመም ነው። በመጨረሻም፥ እምነት ቤትን የመናፈቅ ዓይነት ነገር ነው፤ ከቶውንም ያልጎበኘነውና ዳሩ ግን ከመናፈቅ ያልታቀብነው ቤት

«የአሰሳችን ሁሉ ፍጻሜ የሚሆነው
ከተነሣንበት ደርሰን
በታውን ለመጀመሪያ ጊዜ ስናውቀው ነው።»

ቲ. ኤስ. ኤልዮት

«አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር አየሁ፥ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛዪቱ ምድር አልፈዋልና፥ ባሕርም ወደፊት የለም። ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ለባልዋ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ። ታላቅም ድምፅ ከሰማይ. . . እነሆ፥ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል፥ እነርሱም ሕዝብ ይሆናሉ፥ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል፤ እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፥ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና ብሎ ሲናገር ሰማሁ።»

[1]Elie Wiesel, *Messengers of God* , 233.

[2]Charles Williams, *The Image of the City*, 136.

[3]C.S. Lewis, *The Weight of Glory*, 5.

[4] J.R.R. Tolkien, *The Return of the King*, 238.

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፦ ኢዮብ 42፤ ዕብራውያን 10፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 4፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 15፤ ኢዮብ 19፤ ራእይ 21።

ምዕራፍ 30

ውርርድ – ሁለት ምሳሌዎች

«ሰዎች ከሚያፍዋጩ ዛፎች ውስጥ ከሚወዱዋቸው ጋር የሚሆኑበት፥ የሚፈልጉትን የሚያገኙበት፥ ቅዝቃዜ በሰፈነበት ጥላ ውስጥ የሚጽናኑበት ሰማያዊ ገነት አለ ወይስ . . . የሁሉም ሰዎች ሕይወት የፈራረሰ፥ ግራ የተጋባ፥ ሥቃይ የነገሠበት፥ ፍቅር የራቀው፥ በጩኸት፥ በአእምሮ ድህነት፥ በሞትና በአበሳ የታጀበ ነው?»

– ፎርድ ማዶክስ ፎርድ፡– “The Good Soldier”

ኢጣሊያዊው ደራሲ አምብርቶ ኤኮ በአሥራ ሦስት ዓመቱ ከአባቱ ጋር ወደ እግር ኳስ መጫወቻ ስፍራ ስለሄደበት ቀን የሚለው አለው። አምበርቶ ስፖርት አያስደስተውም ነበርና ከስቴዲየሙ ውስጥ ተቀምጦ ጨዋታውን ሲመለከት አእምሮው ይዋዥቅ ጀመር። «ከሜዳው ላይ የሚካሄደውን ጣዕም የሌለው እንቅስቃሴ በተፋታ ስሜት ስመለከት ሳለሁ፥ የቀትር ፀሐይ ከዓይኖቼ ፊት ትርጉም የሌለው አጽናፈ–አቀፍዊ ከስተት እየተካሄደ እንዳለ ተሰማኝ. . . ለመጀመሪያ ጊዜ የእግዚአብሔርን መኖር በመጠራጠር ዓለም ዋጋ የሌላት የልብ ወለድ ድርሰት እንደሆነች ወሰንሁ።» [1]

ታዳጊው ወጣት ኤኮ ከስቴዲየሙ ላይ ተቀምጦ የእግዚአብሔርን ዓይነት እይታ በምናቡ ተመለከተ። ይሁንና፥ ከዚያው የወጣቱ እይታ አንጻር የሰው ልጆች ሁሉ እንቅስቃሴዎች ከቆዳ የተሠራችውን ኳስ ከሣር ላይ እያሳደዱ እንደሚሽቀዳደሙት ስፖርተኞች ሁሉ ትርጉም – አልባ መስሎ ታየው። እናም ኤኮ «ከላይ» ሆኖ በዚህች ምድር ላይ እየተካሄደ ያለውን ሁሉ የሚመለከት አካል እንደሌለ ተሰማው። ቢኖርም እንኳ አምበርቶ ኤኮ ለእግር ኳስ ግድ እንደሌለው ሁሉ የዚህ ዓለም ጉዳይ እንደማያሳስበው ተገነዘበ።

የኤኮ የስቴዲየሙ ምሳሌ የእምነትን እጅግ መሠረታዊ ጥያቄ ያስነሣል፤ ይህም ሌሎች ጥያቄዎች ሁሉ የሚደገፉበት ነው፤ ይህም «የዓለምን እንቅስቃሴ የሚመለከት አካል አለ ወይ?» የሚለው ነው። «በአጽናፈ–ዓለሙ ግድ የለሽነት» ተከብበን ትርጉም በሌለው ትርምስ ውስጥ እየተዋከብን ነው ወይስ ለሰው ልጆች ለሚገደው አካል ትእይንት እየከወንን? ኢዮብ ከኃይለኛው የዐውሎ ነፋስ ውስጥ መገለጥ ለዚህ ጥያቄ የራሱን ምላሽ አግኝቷል። እኛስ? ከዚህ የበለጠ ጥያቄ

የለም፤ ይህንን መጽሐፍ ከጠነሰሰው ውይይት አምስት ዓመታት ካለፉ በኋላ፥ ስለዚሁ ጥያቄ ከተጠራጠረው ወዳጄ ከሪቻርድ ጋር ስንነጋገር ራሴን አገኘሁት።

መጀመሪያ ከሪቻርድ ጋር ስገናኝ፥ ወደ መለያየትና ፍች በሚወስድ የመጀመሪያ ደረጃ ላይ ሆኖ ከፍቅረኛው–ከእግዚአብሔር ጋር ያኮረፈ ይመስል ነበር። ከዓይኖቹ ውስጥ የቁጣ ነበልባሎች ይጫወታሉ። ነገር ግን ከአምስት ዓመታት በኋላ ሳገኘው፥ የጊዜው ርዝማኔ እንዳረገበው ተመለከትሁ። ምንም እንኳ በንግግራችን ውስጥ የቁጣ ስሜቱ ከማቆጥቆጥ ባይታቀብም፥ ከኃዘን ወይም ከትዝታ ጋር ሲደባለቅ አየሁ። እግዚአብሔርን ሙሉ ለሙሉ ከአእምሮው ሊያወጣ ያልቻለ ሲሆን፥ የእግዚአብሔር አለመገኘት የመናፍስትን ዓይነት ስሜት አሳደረበት። ስለ እምነት ባላነሣም፥ አሁንም ጉዳቱና መከዳቱ ያልለቀቀው ሪቻርድ ወደዚያው ይመለስ ነበር።

አንድ ጊዜ ግራ በተጋባ ሁኔታ በአርምሞ ተመለከተኝ። «አልገባኝም፥ ፊሊፕ» ሲል መናገር ጀመረ። «በአብዛኛው የምናነባቸው መጻሕፍትና የምንናገራቸው እሴቶች ተመሳሳዮች ናቸው። የእኔን ጥርጣሬና ቅይማት የምትረዳ ይመስላሉ። ይሁንና፥ አንተ ለማመን ቻልህ፥ እኔ ግን አልቻልሁም። ልዩነት ምንድን ነው? እምነትህን ከየት አገኘኸው?»

አእምሮዬ ምላሽ ሊሆኑ ወደሚችሉ አሳቦች ቃበዘ። ስለ እግዚአብሔር መኖር መረጃ ሊሆኑ የሚችሉትን አሳቦች ለመዘርዘር እችል ነበር፤ የፍጥረት ንድፍ፥ የኢየሱስ ከርስቶስ ታሪክ፥ የትንሣኤው ምሳሌዎች፥ የክርስቲያን ቅዱሳን ምሳሌዎች ሀልዎተ–እግዚአብሔርን ሊያጠናክሩልኝ ይችሉ ነበር። ነገር ግን ሪቻርድ እነዚህን ጉዳዮች የእኔን ያህል ያውቃል። ዳሩ ግን አያምንም። በተጨማሪም፥ እኔ እምነቴን ከእነርሱ አላገኘሁም። እምነቴን ያገኘሁት በየካቲት ወር አንድ ማታ ከመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ውስጥ ነበር። እናም ስለዚያ ምሽት ለሪቻርድ አጫውት ጀመር።

የእምነት ማታ

ለእኔ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ የጥርጣሬ መፈልፈያ ስፍራ እንደሆነ ቀደም ሲል ገልጫለሁ። እዚያ የቆየሁት የተኮረጀ «መንፈሳዊ» ባሕርያትን በመማር ነበር፤ እንዲያውም፥ አንድ ተማሪ ጥሩ ውጤት ለማምጣት ይህንኑ ለማድረግ የሚገደድበትም ሁኔታ አለ። ለምሳሌ ያህል፥ «ክርስቲያናዊ አገልግሎት» የሚባል አስደሳች ያልሆነ ነገር አለ። ኮሌጁ እያንዳንዱ ተማሪ የመንገድ ላይ የወንጌል ስርጭት፥ አስረኞችን መጠየቅ፥ ወይም የቤት ጉብኝት በመሳሰሉት አገልግሎቶች

ላይ በመደበኛነት እንዲሳተፉ ይጠይቃል። እኔ ግን «የዩኒቨርሲቲ ሥራ» ለማከናወን ተስማማሁ።

ዘወትር ቅዳሜ ማታ በሳውዝ ካሮላይና ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የሚገኘውን የተማሪዎች ማዕከል እየጎበኘሁ ቴሌቪዥን እመለከት ነበር። «ምስክርነት» የመስጠት ግዴታ ነበረብኝ። በሚቀጥለው ሳምንት ስለ ግል እምነት ያነጋገርኋቸውን ሰዎች አስመልክቼ ዘገባ የማቅረብ ኃላፊነት ነበረብኝ። የፈጠራ ታሪኮቼ እውነተኛ መስለው ሳይታዩ አልቀሩም፤ የተጠራጠራቸው አልነበረም።

በተጨማሪም በዩኒቨርስቲው ሥራ ላይ ከተሰማሩ ሌሎች አራት ተማሪዎች ጋር ሳምንታዊ የጸሎት ስብሰባ ማካሄድ ነበረብኝ። እነዚያ የጸሎት ስብሰባዎች የተወሰነ አካሄድ ነበራቸው፤ ጆ ይጸልያል፤ ክሬይግ፥ ክሪስና ሌላኛው ጆ አራቱም ለአሥር ሰከንዶች ያህል በትሕትና ዝም ብለው ጸሎቱን ይሰማሉ። እኔ ጸልዩ አላውቅም ነበር፤ ከአጭር ጊዜ ዝምታ በኋላ ዓይኖቻችንን ገልጠን ወደ መኝታ ክፍላችን እንመለሳለን።

ነገር ግን በየካቲት ወር ውስጥ አንድ ማታ በመጸለዩ ራሴን ጨምሮ ሁሉም ተደነቁ። ምክንያቱን አላውቅም። ለመጸለይም ዕቅድ አልነበረኝም። ነገር ግን ጆ፥ ክሬይግ፥ ክሪስና ሌላኛው ጆ ከጨረሱ በኋላ፥ ድምፄን ከፍ አድርጌ ስጸልይ ተገኘሁ። «እግዚአብሔር ሆይ፥» ብዬ መጸለይ ስጀምር የውጥረቱ መጠን በክፍሉ ውስጥ ሲጨምር ይሰማኛል።

እንደማስታውሰው ጸሎቴ ይህን ይመስል ነበር፤ «እግዚአብሔር ሆይ፥ ወደ ሲያል ለሚሄዱት አሥር ሺህ የሳውዝ ካሮላይና ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ግድ ይለን ዘንድ እዚህ ተሰባስበናል። ሲያል ካለ ሁላቸውም ወደዚያው ቢሄዱ እኔን እንደሚያሳስበኝ አንተ ታውቃለህ። እኔም እንኳ ወደዚያው ብሄድ ግድ የለኝም።»

በክፍሉ ውስጥ ለሚገኙ ወጣቶች እነዚህ ቃላት ያስከተሉትን ድምፅተ ለመረዳት የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ተማሪ መሆንን ይጠይቃል። ሁኔታው የጥንቆላ ወይም ልጅ የመሠዋት ተግባር እያከናወንሁ ያህል ቢሆንም፥ ማንም ሊያስቆመኝ አልሞከረም፤ እናም ቀጠልሁ።

በሆነ ምክንያት ስለ ደጉ ሳምራዊ እናገር ጀመር። እኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ተማሪዎች ደጉ ሳምራዊ በደም ተጨማልቆ ከመንገድ ዳር ለወደቀው አይሁዳዊ ያሳየውን ዓይነት ርኅራኄ ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች

ልናሳይ ይገባ ነበር። እኔ ግን እንዲህ ዓይነት ስሜት እንደሌለኝ ነገርኋቸው። ለተማሪዎቹ ምንም ስሜት አልነበረኝም።

ከዚያ እንዲህ ሆነ። ለተሰጠን የርኅራኄ ተግባር ምን ያህል ግድ እንደሌለኝ እየተናገርሁ ሳለሁ በጸሎቴ መሀል፥ ያ ታሪክ በአዲስ ብርሃን ይታየኝ ጀመር። እየተናገርሁ ሳለሁ ትእይንቱን በምናቤ እየሣልሁ ነበር፤ አንድ ባላገር የለበሰ ሳምራዊ ደም በደም ሆኖ ወደተኛው ሰውዬ ሊያዘነብል አየሁ። ወዲያውኑ ግን በአእምሮዬ ውስጣዊ መስተዋት እነዚያ ሁለት ምስሎች ተለወጡብኝ። ደጉ ሳምራዊ የኢየሱስ ክርስቶስን መልክ ያዘ። የመንገዱ ላይ ወረበሎች ሰለባ የሆነው አሳዛኝ አይሁዳዊም ሌላ ምስል ያዘ፤ የራሴ ሆኖ ያገኘሁት ምስል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ቁስሎቼን ለማበስና የሚፈሰውን ደም ለማስቆም ርጥብ ጨርቅ ይዞ የሚመጣበት ሁኔታ ከዓይኖቼ ላይ ተንጸባረቀ። የቆሰልሁት የወሮበሎች ሰለባ ሆኜ ጎንበስ ስል፥ ዓይኖቼን ስከፍትና አፌን ሳሞጠሙጥ ተመለከትሁ። ከዚያም በዝግታ እንደሚታይ ፊልም ከፊቱ ላይ ስተፋ አየሁ። ያንን ሁሉ አየሁ። በራእዮች፥ ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌዎች፥ ወይም በኢየሱስ ክርስቶስ ያላመንኩት እኔ። ነገሩ አስደነገጠኝ። ወዲያውኑ ጸሎቴን አቆምሁና ከከፍሉ ወጥቼ ሄድሁ።

በዚያን ማታ ስለሆነው ሁሉ ሳስብ ቆየሁ። ነገሩ ራእይ አልነበረም፤ የሥነ-ምግባር ብልሽት የታከለበት የቀን ቅዠት ይመስላል። አሁንም ቢሆን ልረሳው አልችልም። ምን ትርጉም ነበረው? እውነት ነበር? የማውቀው ነገር ቢኖር የአእምሮ እውቀቴ መናዱን ብቻ ነው። በዚያ ግቢ ውስጥ የእግዚአብሔር መኖር ሊታወቅ እንደማይችል በመናገሬ እታወቅ ነበር። ከዚያን ጊዜ በኋላ ግን ሁኔታው አልቀጠለም። አዲስ የግንዛቤ ነጻብራቅ አገኘሁ። ምናልባትም በራሴ ርግጠኛነት በመደገፌና አስቂኝ ጥርጣሬ አንግቤ በመኖሬ ከሁሉም የባሰሁ ምስኪን ነበርሁ።

በዚያን ሌሊት ለእጮኛዬ የሚከተለውን አጭር ማስታወሻ ጻፍሁላት፤ «ስለ ጉዳዩ ለመነጋገር ጥቂት ቀናት የሚያስፈልጉኝ ቢመስሉኝም፥ በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ እውነተኛ ሃይማኖታዊ ገጠመኝ ያገኘሁ ይመስለኛል።»

ሁለት ውርርዶች

ሪቻርድ ይህንኑ ታሪክ ሳጫውተው ከልቡ ተከታተለኝ። ሁሉም ነገር ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሕይወቴ ውስጥ እንደተለወጠ ገለጽሁለት። ከዚያ ጊዜ በፊት ቀሪ ዘመኔን ስለ ክርስትና እምነት ስጽፍ የምኖር

መሆኔን የነገረኝ ሰው ቢኖር፥ «ዕብድ ነህ» እለው ነበር። ነገር ግን ከዚያን ዕለቱ የየካቲት ማታ ጀምሮ በአንድ ወቅት «ትርጉም–የሌለው የሃይማኖት ጣጣ» አድርጌ የናቅሁትን ሕይወት ቀስ በቀስ እያዘገምሁ አለሁ። በማይታየው ዓለም እንዳምን ዓይኖቼን የከፈቱትን የእምነት ዓይኖች አግኝቻለሁ።

የሪቻርድ ምላሽ ትሕትና የተላበሰ ቢሆንም፥ ለጥያቄው ምላሽ አላገኘም። በሕይወቴ ለተፈጸመው ክስተት አማራጭ ማብራሪያዎች ሊቀርብ እንደሚችሉ ገለጸልኝ። ለበርካታ ዓመታት የአክራሪነትን አመለካከት ስቃወም ነበርና ያለጥርጥር ያ አቋም ከልቤ ውስጥ «በእውቀት ያለማመን» ጥልቅ አሳብ ፈጥሯል። ለረዥም ጊዜያት ስላልጸለይሁ፥ ምንም ያህል እርግጠኝነት ባይኖርበትም የመጀመሪያው ጸሎቴ የደጉን ሳምራዊ «መገለጥ» በሚመስል ጎዳና የሚፈስ የስሜት ጎርፍ ማስከተሉ ሊያስገርመኝ ይገባል?

በሪቻርድ ቃላት ውስጥ ራሴን ስላገኘሁ፥ እርሱ በሚናገርበት ጊዜ ለመፈገግ ተገደድሁ። የተማሪ ጓደኞቼን የግል ምስክርነት ችላ ለማለት አሁን ሪቻርድ የተናገራቸውን ቃላት እጠቀም ነበር። ነገር ግን ከዚያው የየካቲት ማታ በኋላ ነገሮችን የምመለከተው በሌላ አቅጣጫ ነው።

ሪቻርድና እኔ አንዱን ክስተት በሁለት የተለያዩ መንገዶች እየገለጽን ነበር፤ እኔ በጨረሩ አቅጣጫ ስመለከት፥ እርሱ ጨረሩን ያየዋል። እርሱም እኔም የየራሳችን መረጃዎች አሉን። ዋናው የእኔ መረጃ ለሕይወት በነበረኝ አመለካከት ላይ መሠረታዊና ያልተጠበቀ ለውጥ መከሰቱ ነው። መለወጥ ጣዕም የሚሰጠው ከውስጥ ወደ ውጭ ማለትም ለተለወጠው ሰው ብቻ ነው። እናም ከአምስት ዓመታት በፊት ወደጀመርነው ውይይት ተመልሰን ደረስን፤ ይኸውም ሪቻርድ ከሚጠላው የእምነት ምሥጢርነት ላይ መድረሳችን ነው።

ለሪቻርድ እምነትን ፍንትው አድርጌ ባሳየሁት እያልሁ ስመኝ ራሴን አገኘሁት፤ ይህን ለማድረግ ግን ዓቅም አነሰኝ። እግዚአብሔር እስኪፈውሰው ድረስ ከኖርሁት ዕረፍት–የለሽነትና መጻተኛነት ጋር ሪቻርድ ሊታገል አየሁት። ነገር ግን በሪቻርድ ልብ ውስጥ እምነትን ለመትከል አልችልም፤ እርሱ ራሱ ማድረግ አለበት።

እውነትም ሁለት አጽናፈ–አቀፋዊ ውርርድ እየተካሄደ እንዳለ የተረዳሁት በዚህ ውይይት ወቅት ነበር። እኔ ውርርዱን ያየሁት ከእግዚአብሔር እይታ አንጻር ነበር፤

ይህም በመጽሐፈ ኢዮብ ውስጥ እንደተጠቀሰው፥ እግዚአብሔር የወደፊቱን የሰው ልጅ ዕጣ–ፈንታ በአንድ ሰው ምላሽ ላይ የሚጥልበት ነው። ያንን ውርርድ ሙሉ ለሙሉ የሚረዳ ሰው መኖሩን

እጠራጠራለሁ፤ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጅ ታሪክ ወደ አንድ ጉዳይ እንደሚቃለል አስተምሯል፤ «የሰው ልጅ ሲመጣ በምድር ላይ እምነትን ያገኛ ይሆንን?»

የሰውን አመለካከት የሚያሳየው ሁለተኛው ውርርድ ራሱ ኢዮብ የተሳተፈበት ነው፤ ይህም እግዚአብሔርን ያምናል ወይስ ይክዳል? የሚለው ነው። ኢዮብ መረጃዎችን ቢያሰባስብም፥ ብዙዎቹ የእግዚአብሔርን ታማኝነት ሊያሳዩት አልቻሉም። ነገር ግን ወሰነ፤ ይህንንም ያደረገው እምነቱን በእግዚአብሔር ላይ ለመጣል እየጮኸና ራሱን እየዉጪረ ነበር።

እያንዳንዳችን እግዚአብሔር እንዳለ ወይም እንደሌለ አምነን ለመኖር መምረጥ አለብን። አምብርቶ ኤኮ ከቀትር ፀሐይ ሥር ከስቴዲየሙ ውስጥ ተቀምጦ ሳለ የእግር ኳስ ተጫዋቾችን አሽቆልቁሎ በመመልከት፥ የሕይወቱን ወሳኝ ጥያቄ አንሥቷል። ከላይ ሆኖ የሚመለከት አካል አለን? የዚያ ጥያቄ ምላሽ ሙሉ ለሙሉ የሚያርፈው ከእምነት ላይ ነው–ጻድቅ የሚኖረውም በዚሁ እምነት ብቻ ነው።

ሁለት ምሳሌዎች

ይህንን መጽሐፍ በሁለት ታሪኮች እደመድማለሁ። እነዚህን ታሪኮች እውነተኞች ሲሆኑ፥ ለእኔ በአማራጭነት የሚያገለግሉ ናቸው–የእምነትና የእምነት–አልባነት መንገዶች።

የመጀመሪያው ታሪክ ከፍሬድሪክ ቡችነር ስብከት የተወሰደ ነው፡–

«ነገሩ በተለይ የሃያኛው ክፍለ ዘመን ታሪክ ሲሆን፥ ለመናገር በጣም አስቸጋሪ ነው፤ ይህም ከቁጣና ከጭንቀት የተነሣ ጠመንጃ አንሥቶ አባቱን ስለገደለው የአሥራ ሁለት ወይም አሥራ ሦስት ዓመት ልጅ ነው። የግድያ ወንጀሉን ለምን እንደፈጸመ በባለሥልጣናት ሲጠየቅ፥ አባቱን ለመቋቋም ስላልቻለ፥ አባቱ ከዓቅም በላይ ስለጠየቀው፥ ሁልጊዜም ስለሚከታተለውና ስላስጠላው መሆኑን ገልጾአል። ልጁ እስር ቤት ከገባ በኋላ፥ ወታደሩ በዚያን ሌሊት በኮሪደሩ አካባቢ ሲያልፍ ድምፅ ሰምቶ ቆም አለ። ልጁ ክፍል ውስጥ፥ «አባቴን እፈልገዋለሁ፥ አባቴን እፈልገዋለሁ» እያለ ያለቅስ ነበር። [1]

ቡችነር ይህ ታሪክ የሁላችንንም ሕይወት እንደሚያመለክት ይናገራሉ። ዘመናዊው ማኅበረሰብ እስር ቤት እንዳለው ልጅ ነው። አባታችንን ገድለነዋል። በአሁኑ ጊዜ ለእግዚአብሔር ስፍራ የሚሰጡ ፈላስፎች ወይም ደራሲያን ወይም የፊልም ባለሙያዎች ወይም

የቴሌቪዥን ፕሮግራም አዘጋጆች ብዙዎች አይደሉም። እግዚአብሔር ዘመን ያለፈበት ፋሽን ሆኗል። ዘመናዊ ዓለም ከእግዚአብሔር ጋር ውድድር ገብቷል።ያልተመለሱ በርካታ ጥያቄዎች አሉ። ብዙውን ጊዜ አስቀይሞናል።*

ስለየትኛውም ነገር እየተጠራጠሩ መኖሩ አስቸጋሪ ነው። በሥነ-ጽሑፍ፥ (Art) በፊልምና በሁሉም ዘመናዊ ኪነ-ጥበብ ውስጥ የሚንጸባረቁ የግራ መጋባት ልቅሶዎች ይሰማሉ። ከእግዚአብሔር ጋር ለመቀያየም አማራጩ እግዚአብሔር መቀየምን ይመስላል። (በርትራንድ ራስል እንዳለው፥ «የእኔነት እምብርት ሁልጊዜም ለዘላለሙ የከፋ ሥቃይ-ይልቅ የጉጉት ሥቃይ-ዓለም ከያዘችው የላቀ ነገር መፈለግ ነው።)

አሁንም ቢሆን ያንን የአባት-አልባነት ስሜት ከወዳጄ ከሪቻርድ ዓይኖች ውስጥ አነባለሁ። በእግዚአብሔር እንደማያምን ቢናገርም፥ ደግሞ ደጋግሞ ስለ እግዚአብሔር ያነሣል-በተቃውሞ ስሜት። ከህደቱን የሚፈጽም አካል ከሌለ ይህ ሁሉ የቆሰለ የመከዳት ስሜት ከየት ይመጣል?

የፍሬድሪክ ቡችነር ምላሴ አባት -አልባነትን ያመለክታል። ሁለተኛው ደግሞ የአባትን መገኘት ያሳያል። ይህ ደግሞ የራሴ እውነተኛ ታሪክ ነው።

በአንድ የበዓል ቀን ሰባት መቶ ማይሎች ርቃ ወደምትኖረው እናቴ ሄጄ ነበር። በእናትና ልጅ ወግ ስለ ድሮ ትዝታዎች እያነሣን እናወጋ ጀመር። ከሕፃንነት እስከ ታዳጊ ወጣትነት ያሳለፍሁትን ሕይወት የሚያሳዩ ፎቶግራፎች ወጡ፤ የልጅነት የውሸት ጦርነቶች፥ ውሾችና ድመቶች፥ የማያቋርጡ የፒያኖ ልምምዶች፥ የአንደኛ፥ የሁለተኛና የኮሌጅ ትምህርት ምረቃዎች እየተመዘዙ ከፊቴ ቀረቡ። ከእነዚያ ፎቶዎች ውስጥ የእኔ ስም የተጻፈበትን የሕፃን ፎቶ አገኘሁ። ፎቶው ለየት ያለ ነበር። እንደ ማንኛውም ሕፃን አየሁት፤ ወፋፍራም

---

* «ጠዋት ችቦ ለኩሶ ባለግቋረጥ እየጮኸ ወደ ገበያ በመሄድ፥ «እግዚአብሔርን እፈልጋለሁ። እግዚአብሔርን እፈልጋለሁ» ስላለው ሰውዬ አልሰማችሁም? . . . ሰዎቹ ሳቁበት. . . ሰውዬው ከመካከላቸው ዘልሎ በመግባት አፈጠጠባቸው። «እግዚአብሔር የታል?» ሲል ጮኸ። «እኔ ልንገርህ። እኛ-እኔና አንተ-ገድለነዋል።» ሁላችንም የእርሱ ገዳዮች ነን፤ ይህንን ግን እንዴት ልናደርገው ቻልን? ባሕርን እንዴት ልንውጥ እንችላለን? አድማሱን የምንመጥበትን ሰፈነግ ማን ሰጠን? መሬት ከፀሐይዋ ስትፋታ ምን ልናደርግ ነው?» - ፍሬድሪክ ኒቼ- *"The Gay Science"*

ጉንጮች፥ ከፊል ጸጉር – አልባነት የሚታይበት ራስ፥ ከዓይኖቼ ላይ የሚያማትር እይታ ይስተዋልበታል። ነገር ግን ፎቶው ተቀዳዱል– እነዚያ የሕፃንነት ዘመን ወዳጆች የሆኑት ውሾችና ድመቶች የበጫጨቁት ይመስል። እናቴ ሌሎች እጅግ ብዙ ያልተበላሹ ፎቶዎች እያሉዋት ይኼኛውን ለምን እንደጠበቀችው ጠየቅሁዋት።

ስለ ቤተሰቤ አንድ ልታውቁት የሚገባችሁ ነገር አለ፤ የአሥር ወራት ሕፃን ሳለሁ አባቴ በፖሊዮ በሽታ ታመመ። በዚሁ በሽታ ከሦስት ወራት በኋላ ሞተ። አባቴ በሃያ አራት ዓመት ዕድሜው ሙሉ ለሙሉ ለሽባነት ስለተዳረገ፥ ጅማቶቹ እጅግ ተዳክመው ነበር። ስለሆነም ለአተነፋፈስ በሚረዳው ግዙፍ የብረት ሲሊንደር ውስጥ ይተኛ ነበር። አሜሪካኖች ዛሬ ለኤድስ ያላቸውን ዓይነት መሸበር በ 1950 ዎቹ ለፖሊዮ ያሳዩ ነበር። ባለማቋረጥ የምትጠይቀው አንድ ጎብኚው እናቴ ነበረች፤ እርሷም ከሲሊንደሩ ውስጥ ሆኖ ያያት ዘንድ ከብረት ከተሠራው ሳንባ ጋር ወደ ተያያዘው መስተዋት ቀረብ ትልለት ነበር።

እናቴ ይህንኑ ፎቶ እንደ ማስታወሻ ጠብቃ ያቆየችበትን ምክንያት አብራራችልኝ፤ ይኸውም አባቴ በታመመበት ወቅት ከብረት በተሠራው ሳንባ ላይ የተለጠፈ መሆኑ ነው። የእርሷንና የሁለት ልጆቹን ፎቶግራፎች ለማየት በመፈለጉ፥ እናቴ ከብረቶቹ ውስጥ ለማስቀመጥ ተገደደች። ለዚህ ነበር የሕፃንነት ፎቶዬ የተበላሸው።

ሕፃናት የፖሊዮ በሽተኞች ካሉበት አካባቢ እንዲቀርቡ ስለማይፈቀድላቸው፥ አባቴ ወደ ሆስፒታል ከገባ በኋላ አላየሁትም። ብገባም እንኳ በጣም ሕፃን ከመሆኔ የተነሣ የዚያን ጊዜውን ትውስታ ይዤ ልቆይ አልችልም ነበር።

እናቴ ስለተበላሸው ፎቶግራፍ ታሪክ ስታወጋኝ፥ እንግዳና ኃይለኛ ምላሽ ሰጠኋት። አግኝቼ የማላውቀው ሰው ለእኔ ያስብልኝ እንደነበር መገመቱ ግራ የሚያጋባ ይመስል ነበር።

አባቴ በመጨረሻዎቹ የሕይወቱ ዘመናት ከእንቅልፍ ውጭ ያሉትን ጊዜያት ያሳለፈው የቤተሰቡን– የቤተሰቤን–ሦስት ምስሎች እየተመለከተ ነበር። የሚያየው ሌላ ነገር አልነበረውም። ቀኑን ሙሉ ምን ያደርግ ነበር? ይጸልይልን ነበር? ምን ጥርጥር አለው። ይወደን ነበር? ምን ያጠያይቃል። ይሁንና፥ አንድ ሽባ የሆነ ሰው በተለይም ልጆቹ ከክፍሉ እንዳይደርሱ ማዕቀብ ሲጣልበት ፍቅሩን እንዴት ሊገልጽ ይችላል?

ስለዚያ ፎቶግራፍ ብዙ ጊዜ አስቤአለሁ። ይህም አባቴ ከነበረውና አሁን እኔን ካለሁበት የአሥር ዓመታት ታናሽ ሆኖ ከሞተው እንግዳ ሰው ጋር ስለሚያገናኘኝ ነው። እኔ የማላስታውሰውና የማላውቀው አንድ ሰው በተቻለው ዓቅም ሁሉ ስለ እኔ በማሰብ፥ ራሱን ለእኔ ለመስጠትና በማፍቀር ቀኑን ሙሉ ያሳልፍ ነበር። ምናልባትም በሆነ ምሥጢራዊ መንገድ አሁንም በሌላ አቅጣጫ ይህንኑ እያደረገ ይሆናል። ምናልባትም እንደ አጀማመሩ በጭካኔ የተደመደመውን ያንን ግንኙነት የማድስበት ብዙ ጊዜ ይኖረኝ ይሆናል።

ይህንን ታሪክ ያነሣሁት እናቴ የተበላሸውን ፎቶግራፍ ባላየችኝ ጊዜ ያደሩብኝ ስሜቶች በየካቲት ማታ በኮሌጅ የመኝታ ክፍል ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በአፍቃሪ አምላክ ባመንሁ ጊዜ የተሰሙኝ ዓይነት በመሆናቸው ነው። አንድ አካል እንዳለ ተረድቻለሁ። ሕይወት በዚህች ምድር ላይ ስታዘግም የሚታዘባት አካል አለ። ከዚህም በላይ የሚወደኝ አንድ አካል አለ። ነገሩ የላቀ ተስፋ አስደናቂ ስሜት፥ እጅግ አዲስና የሚያርድ በመሆኑ፥ ሕይወቴን ሁሉ ልሰጥበት የሚገባው ሆኖ ተገኘ።

1 አምበርቶ ኤኮ፥ *Travels in Hyper Reality*, 167-168.

2 ፍሬደሪክ ቡችነር፥ *The Magnificent Defeat*, 65.

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ፦ ሉቃስ 18።

ምስጋና

እንደ ኦገስቲን፥ ቡችነር፥ ቼስተርተን፥ ኤሊዩት፥ ሉዊስ፥ ሞልትማን፥ ማክዶናልድ፥ ፓስካል፥ ሴየርስ፥ ቴልክና ዊልያምስ የመሳሰሉ ግለሰቦች በዚህ መጽሐፍ ገጾች ውስጥ በተደጋጋሚ ቀርበዋል። ደራሲው፥ «እውነቱን ለመናገር ‹መጋቢዎች› ናቸው» ሲሉ ያመሰግኗቸዋል። «ከእነርሱ የተነሣ፥ በእምነቴ ልቀጥል ችያለሁ።»

ሪቻርድ ለራሱ ታማኝ የመሆን ቆራጥነት ስለነበረው ደራሲው ሊያመሰግኑት ይሻሉ። «ብዙ ነገር ከእርሱ ተምሬአለሁ። መጠየቁንና መመራመሩን እንደማያቆም ተስፋ አደርጋለሁ» ሲሉ ወደ እግዚአብሔር የሚመጣበትን ዘመን ይናፍቃሉ።

የትርጉም ሥራውን አስመልክቶ፥ ከልቤ ወድጄ የሠራሁት መሆኑን ለመግለጽ እሻለሁ። ሌላው ቢቀር ወደ ዳር የምንገፋቸውን የውስጥ ጩኸቶች አንሥተን መወያየታችን ቀላል ጉዳይ አልነበረም። ከዚህም በላይ ፊሊፕ ያንሲ «የእግዚአብሔርን ሞት» ለዓለም በማወጅ የሚታወቀውን «ዝነኛ» ከሀዲ (athiest) ፍሬድሪክ ኒቼን ጨምሮ፥ የአያሌ ፈላስፋዎችን የአመለካከት አቅጣጫ እየጨረፉ የሳቱበትን ጉድጓድ እንድናይ አድርገውናል።

ከሪቻርድ ጋር እየጠየቅን በተጓዝን መጠን፥ የምናርፍባቸው ኪላዎች የሚተዉልን «በረከት» የመጨረሻውን ነጥብ እስከናጣጥም በተስፋ ያጓጉዙናል። ነጥቡም፥ ከደራሲው አምበርቶ ኤኮ አመለካከት በተቃራኒ፥ «እግዚአብሔር አለ! ሕይወት ከንቱ የዳንኪራ መራገጫ አይደለችም!» የሚል ነው።

ይህንን የትርጉም ሥራ በማከናውንበት ወቅት ከአጠገቤ ሆነው የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ላበረከቱት አገልጋዮች ሁሉ የእግዚአብሔር በረከት እንዲበዛላቸው ጸሎቴ ነው። ሚሲዮናዊያኑ ሚስዝ ዳያንና ቲም ፌሎስ፥ የሥነጽሑፍ ክፍሉ ሥራ አስኪያጅ አቶ ዘነበ ገ/ሐና፥ የኮምፒዩተር ክፍል ሠራተኞች የሆኑት ወ/ሮ ዓለምፀሐይ እውነት፥ ወ/ሮ መስከረም አበበ፥ ጥሩወርቅ በቀለና ንጋቷ ደጴሳ ሊመሰገኑ ይገባል። ከሁሉም በላይ የሕይወታችንና የአገልግሎታችን ራስ የሆነው እግዚአብሔር ሥራውን ማንነቱን ለመግለጽ ይጠቀምበት ዘንድ ጸሎታችን ነው። ሰላምና ጸጋ ይብዛላችሁ።

ግርማዊ

ዋቢ መጻሕፍት (Bibliography)

Augustine, Saint, *The Confessions of Saint Augustine.* Translated by **John K. Ryan. Garden City: Doubleday, 1960.**

Brown, Colin, *Miracles and the Critical Mind.* **Grand Rapids: Eerdmans, 1984.**

Buechner, Frederick. *The Hungering Dark. New York*: **Seabury, 1981.**

_____ . *The Magnificent Defeat.* **New York: Seabury, 1979**

_____. *A Room Called Remember: Uncollected Pieces.* **New York: Harper & Row, 1984.**

_____. *Wishful Thinking: A Theological ABC.* **Harper & Row, 1973.**

Dostoyevsky, Fyodor. ***The Brothers Karamazov.*** **Garden City: Nelson Doubleday (no date).**

Eco, Umberto. *Travels in Hyper Reality: Essays.* **Edited by Helen & Kurt Wolff. Translated from the Italian by William Weaver. New York. Harcourt Brace Jovanovich, 1983.**

Eiseley, Loren. *The Star Thrower.* **Harcourt Brace Jovanovich, 1979.**

Hall, Douglas John. *God and Human Suffering.* **Minneapolis: Augsburg, 1986.**

James, William. *The Varieties of Religious Experience.* **New York: Modern Library, 1936.**

Kierkegaard, Soren. *Philosophical Fragments.* **Translated by David Swenson. Princeton: Princeton University Press ,1962.**

Lewis, C.S. *Christian Reflections.***Grand Rapids**: **Eerdmans, 1974.**

_____. *God in the Dock.* **Edited by Walter Hooper. Grand Rapids: Eerdmans, 1970.**

_____. *A Grief Observed.* **New York: Seabury, 1961.**

_____. *The Weight of Glory and Other Addresses.* **Grand Rapids: Eerdmans, 1975.**

____. *The World's Last Night and Other Essays*. **New York: Harcourt Brace Jovanovich, Inc., 1959.**

MacDonald, George Life Essential: *The Hope of the Gospel*. **Edited by Rolland Hein. Wheaton, Ill.: Harold Shaw, 1978.**

MacDonald, Greville. *George MacDonald and His Wife*. **London: George Allen and Unwin, Ltd., 1924.**

Moltmann, JÜrgen. *God in Creation: A New Theology of Creation and the Spirit of God*. **New York: Harper & Row, 1985.**

Spark, Muriel. *The Only Problem*. **New York: Putnam, 1984.**

Thompson, William I. *The Time Falling Bodies Take to Light*. **New York: St. Martin's Press, 1982.**

Tolkien, J. R.R. *The Return of the King*. **New York: Ballantine, 1976.**

____. **The Tolkien Reader. New York: Ballantine Books, 1966.**

Wiesel, Elie. *Messengers of God: Biblical Portraits and Legends*. **New York: Summit Books, 1985.**

Williams, Charles. *He Came Down From Heaven*. **London: William Heinemann, Ltd., 1938.**

___.*The Image of the City*. **London: Oxford University Press, 1958.**

ጥቂት ስለ ደራሲው

ፊሊፕ ያንሲ እውቅ ደራሲና የ "Christianity Today" ኤዲተር ናቸው። "Where Is God When it Hurts?" የሚል መጽሐፍ የደረሱ ሲሆን፥ "The Student Bible, NIV," "Fearfully and Wonderfully Made" እና "In His Image" የተባሉትን መጻሕፍት ከሌሎች ደራሲያን ጋር በመተባበር ለንባብ አብቅተዋል። እነዚህ አራቱም መጻሕፍት ከወንጌላውያን ክርስቲያን አሳታሚዎች ማኅበር የወርቅ ሜዳሊያ ሽልማት ተቀብለዋል። እንደ "The Saturday Evening Post, Chicago Tribune Magazine, Christianity Today, Eternity, Moody Monthly, እና Reader's Digest" በመሳሰሉት መጽሔቶች ላይ ጽሑፎችን ያቀርባሉ።

ቅይማት

እግዚአብሔር አድሎአዊ ነውን?

እግዚአብሔር ጸሎትን አይመልስምን?

እግዚአብሔር ስውር ነውን?

ከአያንዳንዱ አማኝ ጋር ከፍተኛ ልባዊ ትስስር ባለው በዚህ የፊሊፕ ያንሲ መጽሐፍ ውስጥ እነዚህ ሦስት ጥያቄዎች በግልጽ ተዳስሰዋል። ፊሊፕ ያንሲ እነዚህን ጥያቄዎች የመመለሱን ጥረት የጀመሩት አንድ ወዳጃቸው በእግዚአብሔር ላይ የነበረውን እምነት አሽቀንጥሮ ከጣለበት ገጠመኝ ነው። በሕይወቱ ላይ ተከታትለው የደረሱት ችግሮች ይህ ሰው «እግዚአብሔር ለእኔ የሚገደው አይመለለኝም» ብሎ እንዲደመድም አደረገው። ያንሲ ለዚህ ወዳጃቸው ምላሽ ለመስጠት የጀመሩት ጥረት ከርስቲያኖች በዘመናት ሁሉ ከጠየቋቸው ጥያቄዎች ጋር ፊት ለፊት አላተማቸው። እነዚህም ጥያቄዎች፥ «እግዚአብሔር ፍቅራችንን የሚፈልግ ከሆነ አንዳንድ ጊዜ ለምን መሰናክሎችን ያመጣብናል? በጣም ሩቅ የሚመስለው ለምንድን ነው? ከእግዚአብሔር ልንጠብቅ የምንችለው ነገር ምንድን ነው?. . . » የሚሉ ናቸው።

ፊሊፕ ያንሲ ያካሄዱት ጠቃሚ ጥናት የበለጸጉ፥ ጥረት ብለው የሚታዩና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተማማኝነት ያላቸውን ምላሾች አስገኝቷል። ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ ታትሞ ሲወጣ በምዕራቡ ዓለም ከፍተኛ ተወዳጅነት ያለው የ "Christianity Today" መጽሔት የ1989 ዓ.ም የላቀ መጽሐፍ አድርገው መርጠውታል።

«ሊነጋጋ የደረሰውን እምነት ከመሠረቱ ላይ የሚያጣብቅ ምላሽ በመስጠቱ ረገድ የፊሊፕ ያንሲን ያህል ብቃት ያላቸው ደራሲያን ጥቂት ብቻ ናቸው።» ቻርልስ አር. ስዊንደል

ፊሊፕ ያንሲ ከፍተኛ ተፈላጊነት ያላቸውን መጻሕፍት የጻፉና የ "Christianity Today" መጽሔት ኤዲተር ናቸው። "Wher is God When It Hurts?" የሚል መጽሐፍ የደረሱ ሲሆን፥ "Fearfuly and Wonderfully Made" እና "In His Image" የተባሉትን መጻሕፍት ከሌሎች ደራሲያን ጋር በመተባበር ለንባብ አብቅተዋል። በተጨማሪም "The Student Bible, NIV" ተባባሪ ኤዲተር ሆነው ከመሥራታቸውም በላይ እንደ "Reader Digest" እና "The Saturday Evening Post" በመሳሰሉት መጽሔቶች ላይ ጽሑፎችን ያቀርባሉ።

Printed by SIM Press

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

KAY MAT